# የወንጌል መሰረተ ሐሳቦች



# የወንጌል መሰረተ ሐሳቦች

በኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ታተመ
ሶልት ሌክ፤ ዩታ

© በ2001፣ 1996 by Intellectual reserve Inc.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

በዩ ኤስ ኤ ታተመ

እንግሊዝኛው የጸደቀው 6/96

ትርጉሙ የጸደቀው 6/96
Translation of *Gospel Fundamentals*
Amharic

# ማውጫ


መቅደም . . . . . vii

**ሕይወታችን በሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር** ክፍል አንድ
ምዕራፍ 1 እግዚአብሔር አለ . . . . . 2
ምዕራፍ 2 ሕይወታችን በሰማይ . . . . . 5
ምዕራፍ 3 አዳኛችን . . . . . 9
ምዕራፍ 4 ለመምረጥ ነፃ ነን . . . . . 13

**እግዚአብሔር ካለበት መልቀቅ** ክፍል ሁለት
ምዕራፍ 5 ኢየሱስ ምድርን ፈጠረ . . . . . 19
ምዕራፍ 6 አዳም እና ሔዋን . . . . . 21

**ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት** ክፍል ሶስት
ምዕራፍ 7 መንፈስ ቅዱስ . . . . . 28
ምዕራፍ 8 ከሰማይ አባት ጋር መነጋገር . . . . . 31
ምዕራፍ 9 ነቢያት . . . . . 37
ምዕራፍ 10 ቅዱሳን መፃሕፍት . . . . . 41

**አዳኛችን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ** ክፍል አራት
ምዕራፍ 11 የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት . . . . . 49
ምዕራፍ 12 የኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ክፍያ . . . . . 55

**የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል** ክፍል አምስት
ምዕራፍ 13 እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ . . . . . 63
ምዕራፍ 14 ንስሐ . . . . . 67
ምዕራፍ 15 ጥምቀት . . . . . 73
ምዕራፍ 16 የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ . . . . . 77

**የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን** ክፍል ስድስት
ምዕራፍ 17 የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች . . . . . 89
ምዕራፍ 18 ኢየሱስ ያደራጀው ቤተክርስቲያን . . . . . 97


መምህራን በእነዚህ ምዕራፎች ላይ ከአንድ ክፍል ጊዜ በላይ ሊወያዩበት ይፈልጉ ይሆናል።

ምዕራፍ 19 የዛሬይቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .101
ምዕራፍ 20 የክህነት ሥልጣን ድርጅት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .109
ምዕራፍ 21 ስርዓቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .117

**ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል** ክፍል ሰባት
ምዕራፍ 22 መታዘዝ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .127
ምዕራፍ 23 መስዋዕት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .133
ምዕራፍ 24 የአምልኮ ቀን. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .139
ምዕራፍ 25 የንፅህና ሕግ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .144
ምዕራፍ 26 ታማኝነት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .149
ምዕራፍ 27 የጥበብ ቃል. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .152
ምዕራፍ 28 አስራት እና በኩራት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .157

**ቤተሰባችንን ማዳን** ክፍል ስምንተ
ምዕራፍ 29 ቤተሰብ አስፈላጊ ነው . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .163
ምዕራፍ 30 ተግባራችን የቤተሰብ አባላትን ለመርዳት ነው. . . . . . . . . . . . . . . . . .167
ምዕራፍ 31 ተግባራችን ወንጌልን መስበክ ነው . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .175
ምዕራፍ 32 በቤተሰብ ለዘለዓለም መኖር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .179

**የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት** ክፍል ዘጠኝ
ምዕራፍ 33 የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .187
ምዕራፍ 34 አንድ ሺህ ዓመት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .191

**ከሞት በኋላ ሕይወት** ክፍል አስር
ምዕራፍ 35 ከሞት በኋላ ሕይወት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .197
ምዕራፍ 36 ዘለአለማዊ ሕይወት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .201

**የእምነት አንቀጾች** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .207

አስተማሪው ትምህርቶችን ለመከለስ ወይም ለማስተማር የእምነት አንቀጾችን ሊጠቀም ይችላል፡፡

## መዝሙር እና የሕፃናት መዝሙሮች

(መዝሙሮቹ የተዘረዘሩት ለቀረቡ ሀሳብ ለመጠቀም ነው፣ ነገር ግን ብዙዎቻቸውን ከአንድ በላይ ለሆኑ ዓላማዎች መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ፣ አብዛኛውን የመክፈቻና የመዝጊያ መዝሙሮች ለሁለ ገብ ዓላማዎች ሊጠቀሙ ይችላሉ።)

### መክፈቻ


ባርኮትህን ቁጠር . . . 211
ኑ፤ ኑ፤ እናንተ ቅዱሳን . . . 214
ኑ፤ እናንተ የጌታ ልጆች . . . 216
የእስራኤል እዳኝ . . . 218
እንዴት ጽኑ መሰረት ነው . . . 220
ሁልጊዜ እሻሃለሁ . . . 222
ጣፋጭ ስራ ነው . . . 224
የዮሴፍ ስሚዝ የመጀመሪያ ጸሎት . . . 226
ሁላችንም እንቀጥል . . . 228


### ቅዱስቁርባን


እግዚአብሔር፤ አባታችን፤ ፀሎታችንን ሰማን . . . 231
እነሆ ታላቅ አዳኝ ሞተ . . . 232
ዘላለማዊው አባት፤ እግዚአብሔር ሆይ . . . 233
እንዴት ታላቅ ጥበብና ፍቅር ነው . . . 236
በመደነቅ ቆሚያለሁ . . . 238
በትህትና፤ አዳኛችን . . . 240
ኢየሱስ፤ ትሑቱ ያኔ የተወለደው . . . 242
በርቀት ለምለም ኮረብታ አለ . . . 243
እንዘምር ለኢየሱስ ምስጋና . . . 244


### መዝጊያ


የእግዚአብሔር መንፈስ . . . 245
ከፍ ካለው ተራራ አፋፍ . . . 248
ኦ፤ በል እውነት ምንድን ነው? . . . 250
እግዚአብሔር ሆይ፤ ስለ ነቢይ እናመስግንህ . . . 252
አዳኜ እንዳለ አውቃለሁ . . . 254
አምላክ ከእናንተ ዘንድ ይሁን እስክንገናኝ እንደገና . . . 256
አባቴ ሆይ . . . 258
መልካምን አድርጉ . . . 260
አሁን እንደሰተ . . . 263

## ልዩ አርዕስቶች

እሔዳለሁ እንድሔድ የምትፈልግበት ቦታ (ለተልዕኮ) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .266
ውዳሴ ለስው (ዮሴፍ ስሚዝ) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .269
መጸለይ አስበሃል ወይ? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .272
ፍቅር በቤት (ቤተሰብ፣ ቤት) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .274
ሩቀ፣ ሩቀ ወዲያ በይሁዳ ሜዳ (ገና በዓል) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .276
ብጹዕ ሌሊት (ገና በዓል). . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .278
ክርስቶስ ጌታ ተነስቷል ዛሬ (ፋሲካ) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .280
ተነስቷል! (ፋሲካ) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .282

## የልጆች መዝሙር

የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .286
ያንን ጣፋጭ ታሪክ ሳነብ አስባለሁ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .288
አባቴ እንዳለ አውቃለሁ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .289
አመሰግንሃለሁ፣ ውድ አባት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .290
ደግነት በእኔ ይጀምራል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .291
መልካምን ለማድረግ ድፈር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .292
ጌታ ቤተመቀደስን ሰጠኝ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .294
ወርቃማው ሰሌዳ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .295
በብርሃን መንገዝን አስተምረኝ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .296
የቤተሰብ ጸሎት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .297

**መወቀ የሚገቡ ቃላቶች** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .299

የመጀመሪያ መስመሮች ማውጫና አርዕስቶች (ለሙዚቃ)

ለመዝሙሮችና የሕፃናት መዝሙር በዚህ እትም ውስጥ የተጠቃለሉት በመዝሙሮችና የሕፃናት መዝሙር በሙዚቃ በታጀቡ የድምፅ ካሴቶች (52052) ተቀድቶ በቤተክርስቲያኑ ማከፋፈያ ይገኛል።

# መቅድም

ይህ መጽሐፍ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መሠረታዊ ሃሳቦች ለመማር እና ለማስተማር ይረዳል፡፡ እነዚህን መሠረታዊ ሃሳቦች ማወቀ የህይወትን አላማና እንዴት በእውነት ደስተኛ መሆን እንደምትችሉ ይረዳችኋል፡፡ በዚህ መጽሐፍ የተገለጹት መሠረታዊ ሃሳቦች እውነተኛ ናቸው፡፡ እነዚህን መሠረታዊ ሃሳቦች ሲጥንተው እና ሲገናዝበው ከጸለዩበት፣ ለራስዎ ያውቃሉ፣ እናም መንፈስ ቅዱስ እውነተነቱን ይመሰክርልዎታል፡፡

ይህን መጽሐፍ ለብዙ የተለያዩ አላማዎች መጠቀም ይችላሉ፡፡ ለራስዎ ለመማር እና ለማጥናት መጠቀም ይችላሉ፡፡ ንግግሮችን ለማዘጋጀት ወይም ወንጌልን ለሌሎች ለማስረዳት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

ይህን መፅሐፍ ለቤተሰብ ጥናት እና ለቤተሰብ የቤት ምሽቶች ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ እያንዳንዱ ተምህርት እርስዎ እንደ ወላጅ ወይም እንደ አስተማሪ ሆነው ወጣት ልጆች ምን ያህል እንደተረዱ ለማየት የሚጠየቁ ጥያቄዎች አሉ፡፡

ከዚህ መፅሐፍ ተምርቶችን ስታስተምሩ፣ ለአንድ ምዕራፍ ከአንድ ክፍለ ጊዜ በላይ መጠቀም ይችላሉ፡፡ ወደ ሌላ ርዕስ ከመሄድዎ በፊት ተማሪዎቹ መሰረታዊ ሀሣቡን በደንብ መረዳታቸውን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ የተተረጉሙ ቅዱሳን መፅሐፍት ካልዎት፣ የመጽሐፍ ቅዱሱን ጥቀሶች ይመልከቱና ይወያዩበት፡፡

እንደ አስተማሪነትዎ ለአንድ አመት ከ46 እስከ 50 ገደማ ክፍለ ጊዜዎች ለማስተማር እንደሚያስፈልግዎ በአዕምሮዎ ይያዙ፡፡ ድፍን ዓመቱን ለማጠናቀቀ ለተምህርትዎ ያቀዱ፡፡ ይህም ማለተ በ10 ወይም ከዚያ በላይ ተምህርቶች ላይ አንድ ሳምንተ የበለጠ የጥናት ጊዜ ያስፈልግዎታል ማለተ ነው፡፡ በተለይ ይኽን በእነዚህ ምዕራፎች ማለተ በምዕራፍ 2, 3, 10, 11, 13, 16, 19, 20, 21, 30, 32, እና 36 ላይ መስራተ ተፈልግ ይሆናል፡፡ የተኛው በይበልጥ የክፍልዎን ፍላጎተ እንደሚያሟላ ይወስኑ፡፡

በአመቱ መጨረሻ አቀራቢያ አንድ ወይም ሁለተ ክፍሎችን የዕምነተ አንቀጾች ላይ በመወያየተ ማሳለፍ ይፈልጉ ይሆናል፣ እሱም ደግሞ በዚህ መጽሐፍ ቀርቧል፡፡ እንዲሁም ደግሞ የዕምነተ አንቀጾችን ተምህርቶች ለመከለስ መጠቀም ይችላሉ፡፡

ወላጆች እና መምህራን፣ እነዚህን ተምህርቶች ስታስተምሩና ስታዘጋጁ መመሪያ ለማግኘተ ይፀልዩ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በአስተውሎተ በተምህርትዎ ይምራዎተ፡፡ ምዕራፎችን ማንበብ የሚችል እያንዳንዱ አባል ለክፍል ውይይቶችን ከሌላ አባላቶች ጋር ለማካፈል አዘጋጅቶ ይምጣ፡፡

በዚህ መጽሐፍ ያሉት ስዕሎች ስለምተማሯቸው ጥቂት ትምህርቶችና መሰረታዊ ሀሳቦች እንድትረዱ ግንዛቤ ለመስጠት ይረዳሉ፡፡

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን መዝሙሮች በቤት ውስጥ፣ በቤተክርስቲያን ስብሰባዎች ላይ፣ ወይም በየትኛውም በተገቢው ቦታ መዘመር ይችላሉ፡፡ እግዚአብሔር እንዳለው መዝሙሮችን መዘመር የጸሎት መንገድ ነው፣ እናም እርሱም እነዛን ፀሎቶች ከበረከቶች ጋር ይመልሳል፡፡

*የዚህ ምልክት የተደረገበት ቃል ሲመለከቱ፣ ትርጉሙን ከመጽሐፉ በስተጀርባ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ሌሎች ቃላቶችም ደግሞ ትርጉማቸውን ለመረዳት እንዲረዱህ እዚያው ተጠቅለዋል፡፡

የዚህን መጽሐፍ እውነቶች በሙላተ ጸሎት እግዚአብሔር ይባርክዎ፡፡

# ሕይወታችን በሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር

ክፍል አንድ



# እግዚአብሔር አለ

ምዕራፍ 1

*አንዳንድ ጊዜ ሰዎች፣ እግዚአብሔር አለ? እግዚአብሔር ካለ ምን ይመስላል? እንዴት ስለእርሱ ማወቅ እችላለሁ? ብለው እራሳቸውን ይጠይቃሉ፤*

**እግዚአብሔር እንዳለ ብዙ ነገሮች ያሳዩናል**

ምድር ላይ ያሉትን ብዙ አስደናቂ ነገሮች ስንመለከት፣ አንድ ጥበበኛ ሰው በደንብ እንዳቀደውና እንደሰራው እንገነዘባለን፡፡ በሌሊት ብዙ ከዋክብት እና ፕላኔቶችን በተገቢው ቦታቸው ሲንቀሳቀሱ ስናይ፣ አንድ ታላቅ ኃይል እንደሰራቸው እና እንደሚቆጣጠራቸው እንረዳለን፡፡ ይህን ሁሉ ነገር የሰራው እግዚአብሔር ነው፡፡

እግዚአብሔርን ያዩትና ያነጋገሩት አንዳንድ መልካም ሰዎች አሉ፡፡ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስልና ምን እንድናደርግ እንደሚፈልግ ነግረውናል፡፡ እርሱ የሰማይ አባታችን እንደሆነም ነግረውናል፡፡ ስለእርሱ መማር እንድንችል የተቀደሱ መፅሐፍትን ጽፈዋል፡፡

እያንዳንዳችን እግዚአብሔር እንዳለና እርሱ የሰማይ አባታችን እንደሆነ ማወቅ እንችላለን፡፡ እርሱ ሕያው እነደሆነ እንድናውቀ፣ እናም በይበልጥ ስለ እርሱ ማወቀ እንድንችል ይረዳናል፡፡

***ውይይት***

• እግዚአብሔር መኖሩን የሚያሳዩት አንዳንድ ነገሮች ምንድ ናቸው?

**የሰማይ አባታችን ፍጹም ሰው ነው**

የሰማይ አባታችንን ያዩት መልካም ሰዎች እርሱ እውነተኛ፣ ሕያው እና ሰውን ይመስላል ብለዋል፡፡

የሰማይ አባታችን ጣኦት ወይንም እንስሳ አይደለም፡፡ የስጋና አጥንቶች አካል አሉት፡፡ አካሉ የሰዎችን አካል ይመስላል፣ ነገር ግን የተለየ ነው፡፡ የእርሱ አካል በፍጹም አይሞትም፡፡ የእርሱ አካል ሥቃይ ሊሰማው እና ሊታመም አይችልም፡፡

ስሜቶች አሉት፡፡ ሀዘን ወይም ደስታ ሊሰማው ይችላል፡፡ ሁሉንም ህዝብ ይወዳል እናም ደስተኛ እንዲሆኑ ይፈልጋል፡፡ እርሱ ደግ እና መልካም ነው፡፡ መልካም ነገርን ብቻ ይሰራል፣

እውነትንም ብቻ ይናገራል፡፡ ሁሉንም ነገር ያውቃል፡፡ ሁሉንም ነገር መሰራት ይችላል፡፡ በዙሪያው ሁሉ ብርሃን አለ፡፡ ድምቀቱ እና ውበቱ እስከዛሬ ካየናቸው ከማንኛውም ነገር ይበልጣል።

የሰማዩ አባታችን ልናመልከው የሚገባን ብቸኛ አምላክ ነው፡፡ የሚኖረው ሰማይ ተብሎ በሚጠራ ቦታ ነው፡፡ ይህም ከመሬት የበለጠ የተዋበ ስፍራ ነው፡፡

### *ውይይት*

- እግዚአብሔር ምን ዓይነት ሰው ነው?
- እግዚአብሔር ከእኛ የሚለየው እንዴት ነው?

## የሰማይ አባታችን ፍቅሩን በብዙ መንገድ ያሳየናል

የሰማይ አባታችን እኛን ለመርዳት ሀይሉን ይጠቀማል፡፡ ልጁ ኢየሱስ ሰማይ እና ምድርን እንዲሰራ አድርጎታል፡፡ ፀሀይን፣ ጨረቃን፣ እና ከዋክብትን እንዲሰራም አድርጎታል፡፡ በምድር ላይ ተክሎችንና እንስሳትን እንዲያሰፍር አዞታል፡፡ የሰማይ አባታችን ይህን ሁሉ ነገር ያደረገልን ስለሚወደን ነው፡፡ ጥሩና ደስተኞች እንድንሆን ሊረዳን ይፈልጋል፡፡

የሰማዩ አባታችን እኛን ለመርዳት እውቀቱን ይጠቀማል፡፡ ባለፈው የተከሰተውን ማንኛውንም ነገር ያውቃል፡፡ አሁን እየተከሰተ ያለውን ማንኛውንም ነገር ያውቃል፡፡ እናም ወደፊት ምን እንደሚከሰተም ያውቃል፡፡ የሁላችንንም ሀሳብ ያውቃል፡፡ ሁሉንም ነገሮች ስለሚያውቅ፣ እኛን ለማስደሰት ምን እንደሚያስፈልገን ያውቃል፡፡ በጣም ደስተኛ ለመሆንም ጥሩ መሆን እንዳለብንም ያውቃል፡፡ ስለሚወድን ጥሩ እንድንሆን ሊረዳን ይፈልጋል።

### *ውይይት*

- የሰማዩ አባታችን ፍቅሩን የሚያሳየን እንዴት ነው?

## የሰማዩ አባታችን እንድናውቀው ይፈልጋል

የሰማዩ አባታችን ስለሚወደን፣ ህይወትና የምንኖርበት የተዋበች ምድር ሰጥቶናል፡፡ ማድረግ የሚገባንን ነገሮች እንድናውቅ ይፈልጋል፡፡ እርሱን ማወቀ እንደምንችልም ቃል ገብቶልናል፡፡

እነዚህን ነገሮች መስራት ስለ ሰማይ አባታችን በበለጠ ለመማር ሊረዳን ይችላል

1. የሰራውን ዓለም ተመልክተን ማመስገን እንችላለን፡፡
2. የሰማዩ አባታችን እውነተኛ እንደሆነና እንደሚወደን ማመን እንችላለን፡፡
3. መልካም ሰዎች ስለ ሰማዩ አባታችን የጻፉትን ማንበብ እንችላለን፡፡
4. እሱ እንድንማርና እንድንሰራ የሚፈልገውን ነገሮች መማር እና ማድረግ እንችላለን፡፡
5. የሰማዩ አባታችንን በማነጋገርና እሱን ለማወቀ እንዲረዳን መጠየቀ እንችላለን፡፡

ስለ ሰማዩ አባታችን ማወቀ በህይወታችን ውስጥ ሊረዳን ይችላል፡፡ ስለእርሱ ማወቀ የደስታና የደህንነት ስሜት እንዲኖረን ሊረዳን ይችላል፡፡ እርሱ መልካም በመሆኑ እናም ለእኛ መጥፎ የሆኑ ነገሮችን አያደርግም፡፡ እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገር መማር እንችላለን፡፡ እርዳታውን እንዴት እንደምንጠይቀም መማር እንችላለን፡፡ የተሻልን እና ደስተኛ ህዝቦች መሆን እንችላለን፡፡

## ውይይት

- የሰማዩ አባታችንን ለማወቅና ለመረዳት ምን ማድረግ እንችላለን?
- የሰማዩ አባታችንን ማወቅ እንዴት ይረዳናል?

## ማጣቀሻ

*እግዚአብሔር እንዳለ ብዙ ነገሮች ያሳዩናል*

- የሐዋሪያት ስራ 7፥55–56 (ቅዱሱ ሰው እግዚአብሔርን አይቷል)።

*የሰማይ አባታችን ፍጹም ሰው ነው*

- ኦሪት ዘፍጥረት 1፥26–27 (እግዚአብሔር ሰውን እንደ እርሱ እንዲሆን ፈጠረው)።

*የሰማዩ አባታችን ፍቀሩን በብዙ መንገድ ያሳየናል*

- ኦሪት ዘፍጥረት 1፥1–25 (እግዚአብሔር ሰማይ ምድርንና በውስጣቸው ያሉትን ሁሉንም ነገሮች ሰራ)።
- የሉቃስ ወንጌል 12፥6–7 (እግዚአብሔር ስለ ሰራው ነገሮች ሁሉ ይጠነቀቃል)።

*የሰማይ አባታችን እንድናውቀው ይፈልጋል*

- ኦሪት ዘዳግም 4፥29 (እግዚአብሔርን ማወቅ የሚፈልጉ ያውቁታል)።
- የዮሐንስ ወንጌል 17፥3 (እግዚአብሔርን ማወቅ እንችላለን)።
- 1ኛ የዮሐንስ መልዕክት 2፥3 (እግዚአብሔርን ከታዘዝን፣ ልናውቀው እንችላለን)።
- ሞዛያ 4፥9 (በእግዚአብሔር ማመን ይገባናል)።

# ሕይወታችን በሰማይ

*ምዕራፍ 2*

---

*ወደ እዚህ ምድር ከመምጣታችን በፊት የት እንኖር ነበር? እዚያስ ምን እናደርግ ነበር?*

## እያንዳንዳችን የሰማይ አባታችን ልጆች ነን

ወደ እዚህ ምድር ከመምጣታችን በፊት፣ በሰማይ እንኖር ነበር፡፡ የሰማዩ ቤታችን በምድር ላይ ከምናውቀው ማንኛውም ነገር የበለጠ አስደናቂና የተዋበ ነበር፡፡ ቤተሰብም ነበረን። እርስ በእርስችን የምንዋደድና ደስተኞች ነበርን፡፡ የሰማዩ አባታችን የመንፈሳችን አባት ነበር፣ እናም በዚህ ምክንያት ብዙ ጊዜ የሰማይ አባታችን ብለን እንጠራዋለን፡፡ አባታችን በመሆኑ፣ ይወደናል ስለ እኛም ይጠነቀቃል፡፡

በዚህ ምድር ላይ የሚኖር ማንኛውም ሰው በሰማይ ወንድማችን ወይም እህታችን ነበሩ፡፡ በሰማያዊ ቤተሰባችን ውስጥ ታላቁ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር፡፡ እርሱም ታላቅ ወንድማችን ነው፡፡

በሰማይ ስንኖር አሁን እንዳለን የስጋና አጥንት አካላቶች አልነበረንም። መንፈስ ነበርን፡፡ መንፈስ እንደ ሰው አይነት ቅርጽ አለው፡፡ እንደ መንፈስ፣ እርስ በእርሳችን መነጋገር፣ መንቀሳቀስ፣ መምረጥ፣ በክፉና ደግ መካከል ያለውን ልዩነት ለይተን ማወቅ እንችል ነበር፡፡

በሰማይ ሁላችንም አንመሳሰልም ነበር፡፡ ልክ አሁን እንዳለነው፣ የተለያየን ነበርን። የተለያየ ፍላጐቶችና ችሎታዎች ነበሩን፡፡ ችሎታችንን በተለያዩ መንገዶች መጠቀምን ተምረናል፡፡

### *ውይይት*

- የሰማይ ቤታችን ምን ይመስል ነበር?
- አባታችን ማን ነበር?
- ታላቅ ወንድማችን ማን ነበር?

## የሰማይ አባታችን እንደ እርሱ መሆን እንደምንችል ያውቃል

የሰማይ አባታችን የመንፈሳችን አባት በመሆኑ፣ በሚገባ ያውቀናል፡፡ ይወደናል። እርሱን ለመምሰልና እርሱ የሚያውቀውን ነገሮች ለመማር የሚያስችለንን ችሎታ እንደተቀበልን

---



*የሰማይ አባታችን በምድር ላይ ካለው ማንኛውም ቦታ የበለጠ የከበረና የተዋበ ሰማያዊ ቤት አዘጋጅቶልናል፡፡*

ያውቃል። ያውቀናል። ሁል ጊዜ እንደ እርሱ መልካም እንድንሆን፣ ይፈልጋል። እርሱን ለመምሰል ችሎታችንን እንድናሻሽል ሊረዳን ይፈልጋል።

### *ውይይት*

- የሰማዩ አባታችንን መምሰልንና እርሱ የሚያውቃቸውን ነገሮች መማር እንችላለን?
- በሰማይ አባት እንዳለህ ማወቁ ምን እንዲሰማህ ያደርግሃል?

## የሰማይ አባታችን እኛን ለመርዳት እቅድ አቀዶ ነበር

በሰማይ ብዙ ነገሮችን ተምረናል እናም በምንችለው መጠን እራሳችንን አሻሽለናል፣ ነገር ግን እዚያ ልናደርግ እና ልንማር ያልቻልናቸው ነገሮች ነበሩ፡፡ የሰማዩ አባታችን የበለጠ እንድንማር እቅድ አቀዶልን ነበር።

በሰማይ ጉባኤ ነበርን። ሁላችንም እዚያ ነበርን፡፡ እኛ እንድንማር ለመርዳት ዕቅዱን ገልጾልናል እቅዱን ብንከተልም እንደ እርሱ መሆን እንደምንችል ነግሮናል፡፡

የሰማዩ አባታችን ለተወሰነ ጊዜ የምንኖርበትን ምድር እንደሚሰራ፣ ተናግሯል፡፡ በምድር ላይ ሳለን፣ ከእርሱ ጋር በሰማይ የነበረንን ህይወታችንን አናስታውሰውም፡፡ ጥሩ ነገሮችን ወይም መጥፎ ነገሮችን መመረጥ እንችላለን፡፡ ይህ የሰማዩ አባታችን ከእርሱ ጋር ባልነበርንበት ጊዜ እንደምንታዘዘው ለማየት ፈተና ነበር፡፡

እንደ ሰማዩ አባታችን እቅድ፣ የስጋና አጥንት አካልን እናገኛለን፡፡ የዚህ አይነት አካል የምንፈልገው እርሱ የሚያውቃቸውን ነገሮች ለመማር እና የሚያደርገውን ነገሮች ለማድረግ ነው፡፡ በኋላም፣ እንሞታለን፣ ነፍሳችን ከስጋና አጥንታችን አካል ይለያል፡፡ ነገር ግን ነፍሳችን ከአካላችን ጋር እንደገና ይገናኛል፣ ዳግመኛም በፍጹም አንሞትም፡፡ የሰማዩ አባታችን እንዲያደርጉ የነገራቸውን ነገሮች ካደረጉ ለዘለአለም ከእርሱ ጋር ለመኖር ይመለሳሉ፡፡

እያንዳንዱ ሰው በምድር ላይ እንደ ህመም፣ ስቃይ፣ ሃዘንና ሞት አይነት ችግሮች እንደሚኖርበተ ተምረናል፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ነገሮች እንደምንማር እንረዳለን፡፡ እነዚህ ነገሮች እንድንፋቀርና እርስ በእርሳችን እንድንረዳዳ ሊያስተምሩን ይችላሉ፡፡

የሰማዩ አባታችን ለእያንዳንዳችን በምድር ላይ እንድንወለድ ጊዜንና ቦታን መርጧል። ማወቀ የምንፈልጋቸውን ነገሮች እንድናውቀ እያንዳንዳችንን በምድር ወዴት እንደሚልከን ያውቃል፡፡ ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ለማድረግ ሁላችንም እድሉ ይኖረናል፡፡ የሰማዩ አባታችን መልካም ነገሮችን በማድረግ ከእርሱ ጋር ተመልሰን መኖር እንድንችል ይፈልጋል፡፡ ቢሆንም፣ ማንኛውንም ነገር እንድናደርግ በፍጹም አያስገድደንም፡፡

አንዳንዳችን እርሱን ለመታዘዝ እንመርጣለን፡፡ የምንታዘዘው ከሆነ፣ በበለጠ እንደ እርሱ በመሆን ከእርሱ ጋር ተመልሰን እንኖራለን። አንዳንዶቻችን እርሱን መታዘዝን አንመርጥም፡፡ የማንታዘዘው ከሆነ፣ አንደ እርሱ መሆን አንችልም እናም ተመልሰንም ከእርሱ ጋር መኖር አንችልም፡፡

የሰማዩ አባታችን ለእኛ ያለውን ዕቅድ ስንሰማ፣ በጣም ተደስተን ነበር፡፡ መማርና ማደግ እንድንችል ፈልገን ነበር፡፡ ማንኛውም በምድር ላይ የሚኖር ሰው በእቅዱ ለመኖር ተስማምቷል፡፡

### ውይይት

- የሰማዩ አባታችን ለእኛ ያለው ዕቅድ ምን ነበር?
- የሰማዩ ቤታችንን ለመተው የፈለግነው ለምን ነበር?
- የሰማዩ አባታችን በምድር ላይ እንድናደርግ የሚፈልግብን ምንድነው?

### ማጣቀሻ

*እያንዳንዳችን የሰማይ አባታችን ልጆች ነን*

- የሉቃስ ወንጌል 24፥39 (መንፈስ ስጋና አጥንት የለውም)።
- ወደ ዕብራውያን 12፥9 (እግዚአብሔር የመንፈሳችን አባት ነው)።

*የሰማይ አባታችን እንደ እርሱ መሆን እንደምንችል ያውቃል*

- የማቴዎስ ወንጌል 5፥48 (ኢየሱስ እንደ ሰማዩ አባታችን እንድንሆን ነግሮናል)።
- 3ኛ ኔፊ 12፥48 (ኢየሱስ እንደ እርሱና እንደ እግዚአብሄር አባታችን ፍጹም እንድንሆን ነገሮናል)።
- 3ኛ ኔፊ 27፥27 (የኢሱስ ክርስቶስን አርአያ መከተልና እንደ እርሱ መሆን አለብን)።

*የሰማይ አባታችን እኛን ለመርዳት እቅድ አዘጋጀ*

- የዮሐንስ ወንጌል 14፥2–3 (የሰማዩ አባታችን ወደ እርሱ እንደምንመለስ ተናግሯል)።
- የሐዋርያት ሥራ 17፥26 (የሰማይ አባታችን በእቅዱ መሰረተ ወደ ምድር በተወሰነልን ቦታና ወቀት ላከን)።
- 1ኛ ኔፊ 17፥36 (የሰማዩ አባታችን ምድርን የፈጠረው ለልጆቹ መኖሪያ ነው)።
- 2ኛ ኔፊ 9፥13፤ አልማ 42 (እግዚአብሔር ለእኛ እቅድ አለው)።

# አዳኛችን

*ምዕራፍ 3*

---

*ወደ ሰማዩ አባታችን መርቶ ሊመልሰን የሚችለው ሰው ማን ነው? እርሱን መከተል ያለብን ለምንድን ነው?*

## መሪ ያስፈልገናል

የሰማዩ አባታችን በምድር ላይ በነበርንበት ጊዜ ከእርሱ ጋር የነበረንን ህይወት እንደማናስታውስ ያውቃል፡፡ ወደ እርሱ ለመመለስ ማድረግ የሚያስፈልጉንን ነገሮች አናውቅም፡፡ ደግሞም ኃጢአት እንደምንሰራ ያውቃል፡፡ በኃጢአታችን ምክንያትም ለዘለዓለም ከእርሱ በመለየት እንቀጣለን፡፡ እና ከሞትን በኋላ፣ የስጋና የአጥንት አካል ዳግመኛ ሊኖረን አይችልም።

በእነዚህ ችግሮች የሚረዳን አንድ ሰው ያስፈልገናል፡፡ ይህም ሰው ወደ ሰማዩ አባታችን ለመመለስ ምን ማድረግ እንዳለብን ያስተምረናል፡፡ ከስህተት እንድንቆጠብ ይረዳናል፡፡ ደግሞም ከሞትን በኋላ እንደገና የስጋና አጥንት አካል እንዲኖረን መንገድን ያዘጋጅልናል፡፡ ይህ ሰው አዳኛችን ተብሎ ይጠራል፡፡ ባደረግነው የስህተት ስራዎች የተነሳ ከምንቀጣው ቀጣት እርሱ ብቻ ሊያድነን ይችላል፡፡ እርሱ ብቻ ለሰማዩ አባታችን ታዛዥ መሆንን እንድንማር ሊረዳን ይችላል፡፡ እርሱ ብቻ ከሞት በኋላ ዳግም ሊኖረን የሚችል የስጋና አጥንቶች አካል እንዲኖረን አስችሏል።


### *ውይይት*

- የሰማዩ አባታችን የሚያውቀው በምድር ላይ የሚገጥሙን አንዳንድ ችግሮች ምንድን ናቸው?
- የአዳኙን እርዳታ ለምን እንፈልጋለን?

## የሰማይ አባታችን ኢየሱስ አዳኛችን እንዲሆን መረጠው

የሰማዩ አባታችን ይወደናል፣ እናም እርዳታ እንደምንፈልግ ያውቃል፡፡ የስጋና አጥንቶች አካል የማይኖረን ከሆነና ከእርሱ ጋር ተመልሰን ለዘለዓለም መኖር የማንችል ከሆነ በጣም እንደምንከፋ ያውቃል፡፡ የሚረዳን አንድ ሰው ያስፈልገናል፡፡ የሰማዩ አባታችንም አዳኛችን እንዲሆን አንድ ሰው ፈለገ፡፡ ሁለት ወንድሞቻችን አዳኛችን ለመሆን በፈቃደኝነት ራሳቸውን አቀረቡ፡፡

---



*በሰማዩ አባታችን አመራር ስር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ምድርን ሰራ።*

ታላቅ ወንድማችን፣ ኢየሱስ፣ እርሱን እንዲልከው የሰማዩ አባታችንን ጠየቀ፡፡ እርሱም የሰማዩ አባታችንን እቅድ እከተላለሁ አለ፡፡ ወደ ምድርም መጥቶ ወደ ሰማዩ አባታችን ለመመለስ ማድረግ የሚያስፈልጉንን ነገሮች እንደሚያስተምረን ተናገረ፡፡ ያደረግናቸውን ስህተት ሥራዎችንም ለመክፈል ሞተ፡፡ ደግሞም እኛ ከሞት በኋላ እንደገና ለመኖር እንድንችል አደረገ። የሰማዩ አባታችንን ለመታዘዝ ወይም ላለመታዘዝ ዕራሳችን እንድንመርጥ ይፈቀድልናል፡፡

የምናደርጋቸውን ነገሮች ዕራሳችን መምረጣችን በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ኢየሱስ ያውቃል፡፡ እንድንታዘዝ ሰው የሚያስገድደንም ከሆነ፣ መማርና እንደ የሰማዩ አባታችን መሆን አንችልም፡፡ ኢየሱስ ታላቅ ክብርና ሞገስ ሁሉ ለሰማይ አባታችን እንዲሆን ይፈልጋል፡፡

ሌላኛው ወንድም፣ ሰይጣን፣ የተባለው እርሱ አዳኛችን እንዲሆን እንዲመርጠው የሰማዩ አባታችንን ጠየቀው፡፡ ወደ ምድር መጥቶ ማድረግ የሚገባንን እንድናደርግ እንደሚያስገድደን እና ማናችንም እንደማንጠፋም ተናግሯል፡፡ ለእራሳችን እንድንመርጥም እንደማይፈቀድልንም ተናገረ፡፡ ለሐጢያታችን ክፍያም አይሞትልንም፡፡ የሰማዩ አባታችን ያለውን ታላቅ ክብርና ሞገስ ሁሉ ለመውሰድ ይፈልጋል፡፡ ሰይጣን አምላካችን መሆንም ፈልጎ ነበር፡፡

የሰማዩ አባታችን ስለሚወደን፣ ኢየሱስን አዳኛችን እንዲሆን መረጠው፡፡ በዚህ ምክንያትም፣ ኢየሱስ ብዙን ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ ይጠራል፡፡ ክርስቶስ ማለት አዳኝ እንዲሆን በሰማዩ አባታችን የተመረጠ ማለት ነው፡፡ የሰማዩ አባታችን ከሰይጣን ይልቅ ኢየሱስን መረጠ ምክንያቱም የሰማዩ አባታችን ለራሳችን የመምረጥ መብታችንን እንድናጣ አልፈለገም፡፡ ሌላ ሰው እንድናደርግ ስላስገደደን ሳይሆን፣ ራሳችን ፈልገን ጥሩ ስራዎችን መስራት እንዳለብንም ይውቃል፡፡

## ውይይት

- ኢየሱስ ለእኛ ማድረግ የሚፈልገው ምን ነበር?
- ሰይጣን ማድረግ የፈለገው ምንድን ነበር?
- የሰማዩ አባታችን ኢየሱስ አዳኛችን እንዲሆን የመረጠው ለምንድነው?

## ኢየሱስ አዳኛችንና መሪያችን ነው

የሰማዩ አባታችን ኢየሱስን ሲመርጥ፣ ሰይጣን በጣም ተናደደ፡፡ አንድ ሦስተኛውን በሰማይ ያሉትን መንፈሶች እንዲከተሉት አግባባ፡፡ በአንድነት ሆነው ኢየሱስንና ተከታዮቹን ተዋግተዋል፡፡ የሰማዩ አባታችን የሰይጣንን እቅድ እንዲቀበል ለማስገደድ ፈልገው ነበር፡፡ የሰማዩ አባታችንም ሰይጣንና ተከታዮቹ ሰማይን እንዲለቁ አደረገ፡፡

ሰይጣንና ተከታዮቹ የስጋና የአጥንቶች አካል በፍጹም የላቸውም፡፡ ከሰማዩ አባታችን ጋር ተመልሰው በፍጹም መኖር አይችሉም፡፡ ኢየሱስ አዳኛቸው እንዲሆን የተቀበሉ ብቻ የስጋና አጥንቶች አካል ሊኖራቸው ይችላል፡፡

የስጋና አጥንት አካል ስላለን፣ ኢየሱስን አዳኛችን እንዲሆን እንደተቀበልነው እናውቃለን፡፡ በሰማይ ትክክለኛ የሆኑትን ነገሮች እንመርጣለን፡፡ እዚህ ምድር ላይ ትክክለኛ የሆኑትን ነገሮች መምረጥ አለብን። ኢየሱስን መከተል አለብን፡፡ እርሱ ብቻ ወደ ሰማዩ አባታችን እንዴት እንደምንመለስ ሊያስተምረን ይችላል፡፡ እንደ የሰማዩ አባታችን እስክንሆን ድረስ መልካም ሥራዎችን በመስራትና ስህተት የሆኑ ነገሮችን እንድናሸንፍ ሊረዳን ይችላል፡፡

የሰማዩ አባታችን ኢየሱስን እንድንከተልና እንድንታዘዝ ይፈልጋል፡፡ ኢየሱስ ሁልጊዜ በእሱ መንገድ የሚሰሩ ነገሮችን እንደሚያስተምረን ያውቃል፣ ስለዚህ ኢየሱስን ስንታዘዝ የሰማይ አባታችንንም እንታዘዛለን፡፡ ከኢየሱስ የሆነ ትዕዛዝ ወይም መልዕክት እንዲሁም ከሰማይ አባታችን የሆነ ትዕዛዝ ወይም መልዕክት ነው፡፡

## ***ውይይት***

- ኢየሱስ አዳኛችን እንዲሆን እንደመረጥን እንዴት እናውቃለን?
- ወደ ሰማዩ አባታችን እንዴት እንደምንመለስ ሊያሳየን የሚችለው ብቸኛ ሰው ማን ነው?
- ኢየሱስን ለምን እንከተላለን?

## ***ማጣቀሻ***

*መረ ያስፈልገናል*

- የዮሐንስ ወንጌል 14፥6 (ወደ ሰማዩ አባታችን ለመመለስ ኢየሱስን ነው መከተል ያለብን)።
- 1ኛ ጴጥሮስ 2፥21 (የኢየሱስ ክርስቶስን መንገድ መከተል አለብን)።
- 2ኛ ኔፊ 31፥13፣16 (የአዳኛችንን ምሳሌ ብንከተል፣ እንድናለን)።

*የሰማዩ አባታችን ኢየሱስን አዳኛችን እንዲሆን መረጠው*

- 1ኛ የዮሐንስ ወንጌል 4፥14 (የሰማዩ አባታችን ኢየሱስ የዓለም አዳኝ እንዲሆን መረጠው)።
- 2ኛ ኔፊ 9፥6–26 (ኢየሱስ ለእኛ ሞተ)።
- 3ኛ ኔፊ 27፥13–14 (ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን እንዲሆን ወደ ምድር መጣ)።

*ኢየሱስ አዳኛችንና መሪያችን ነው*

- የማቴዎስ ወንጌል 1፥21 (ኢየሱስ ከኃጢአታችን ሊያነፃን መጣ)።
- 3ኛ ኔፊ 11፥110–11 (ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ኃጢአት ተሰቃይቷል)።
- 3ኛ ኔፊ 18፥16 (ኢየሱስ የምንከተለውን ምሳሌ አሳይቶናል)።
- 3ኛ ኔፊ 27፥21 (ኢየሱስ ምን እንደምናደረግ አሳይቶናል)።

# ለመምረጥ ነፃ ነን

*ምዕራፍ 4*

*ሁላችንም በየዕለቱ ምርጫዎችን እናደርጋለን፡፡ የሰማዩ አባታችን ለራሳችን የመምረጥ መብትን ሰጥቶናል፡፡ ጥሩ ምርጫዎችን ለማድረግ መሞከር የሚገባን ለምንድን ነው?*

## የሰማዩ አባታችን የመምረጥን መብት ሰጥቶናል

በሰማይ ለመምረጥ ነጻ ነበርን፡፡ ኢየሱስን ወይም ሰይጣንን ለመከተል ነጻ ነበርን፡፡ አብዛኛዎቹ የሰማዩ አባታችን ልጆች ኢየሱስን ለመከተል መረጡ፡፡ ሌሎቹ ሰይጣንን ለመከተል መረጡ፡፡ የሰማዩ አባታችን እያንዳንዱ ሰው የራሱን ምርጫ እንዲመርጥ ፈቀዷል፡፡

የሰማዩ አባታችን ደግሞ እዚህ ምድር ላይ ለራሳችን እንድንመርጥ ይፈቀድልናል፡፡ ወደ ምድር ስንመጣ፣ ከእርሱ ጋር የነበረንን ህይወት እንድንረሳ አደረገን፡፡ ከእርሱ ጋር በሌለንበት ጊዜ ለእራሳችን መምረጥን መማር ያስፈልገናል፡፡

### *ውይይት*

- አንድ ነገር እንድታደርጉ ጫና ሲደረግባችሁ ምን ይሰማችኋል?
- አንድ ሰው ማድረግ የምትፈልጉትን ነገር እንድታደርጉ ሲፈቀድላችሁ ምን ይሰማችኋል?

## የሰማዩ አባታችን ዕቅድ የሚሰራው ለመምረጥ ነጻ ከሆንን ብቻ ነው

ከሰማዩ አባታችን የዕቅድ ክፍሉ ጥሩ ነገሮችና መጥፎ ነገሮች ወዳሉበተ ምድር እኛን መላክ ነበር፡፡ መልካም የሆነውን እንድንመርጥ ይፈልጋል፡፡ ሰይጣን መጥፎውን እንድንመርጥ ለማግባ-ባት ይሞክራል፡፡ በመልካም እና በክፉ መሐከል ለመምረጥ ነጻ ነን፡፡

ተክክለኛ ምርጫዎችን ስናደርግ፣ የሰማዩ አባታችን እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገሮች ይበልጥ ማድረግ እንችላለን፡፡ የሰማዩ አባታችን እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገሮች ስናደርግ፣ የበለጠ እንደ እርሱ እንሆናለን፡፡ የተሻለ ምርጫም ለማድረግ ለራሳችን እናውቃለን። በይበልጥ የሚያስደስቱንን እና እንድናዝን የሚያደርጉንን ነገሮች እንረዳለን፡፡

ለራሳችን መምረጥ ካልቻልን፣ ይበልጥ እንደ ሰማዩ አባታችን ለመሆን አንችልም፡፡ ለራሳችን የተሻሉ ነገሮችን ለመምረጥም መማር አንችልም፡፡ የሰማዩ አባታችንን እንደምንወደውና በዕውነተ እርሱን መከተል እንደምንፈልግ ለማሳየትም አንችልም፡፡

## *ውይይት*

- ለመምረጥ መብት ያለን ለምንድነው?

## የሰማዩ አባታችንን ለመታዘዝ መምረጥ ደስተኛ ያደርገናል

ትክክለኛ ምርጫዎች ጥሩ ውጤቶችን ያመጡልናል፤ የተሳሳቱ ምርጫዎች ግን መጥፎ ውጤቶችን ለእኛ ያመጣሉ፡፡ የሰማዩ አባታችንን ለመታዘዝ ከመረጥን፣ ደስተኞችና የተሻሉ ህዝቦች እንሆናለን፡፡ እርሱን ለመታዘዝ ካልመረጥን፣ እናዝናለን እናም የተሻልን መሆን አንችልም፡፡

ትክክለኛ ምርጫዎችን ስናደርግ፣ በእነርሱ ምክንያት ደስተኛ ስንሆን እናያለን፡፡ ጥሩ ነገሮችን ይበልጥ ማድረግ እንዳለብን እንማራለን፡፡ ትክክለኛ ነገርን ለማድረግ መምረጥ ደስተኛ ሲያደርገን ስናይ፣ ትክክለኛ ምርጫዎችን በይበልጥ ማድረግ እንፈልጋለን፡፡ ጥሩ ለመሆን እንመኛለን፡፡ ውጤቱ ለእኛ እንደሆነ ስለምናውቅ፣ ምርጫዎችን በይበልጥ በበለጠ ቀላል ማድረግ እንችላለን፡፡ በይበልጥ እንደ ሰማዩ አባታችን ለመሆን ማወቅ የምንፈልገውን ነገሮች እንማራለን፡፡

የተሳሳቱ ምርጫዎችን ስናደርግ፣ ሀዘንና ሀፍረት ይሰማናል፡፡ የተሳሳቱ ነገሮችን ማድረግ ከቀጠልን፣ ሰይጣን በእኛ ላይ ሀይልን ማግኘት ይጀምራል፡፡ ትክክለኛውን ለማድረግ መምረጥ እያስቸገረንና እየጠነከረብን እና እየጠጠረ ይመጣል፡፡ የሰማዩ አባታችንን ዕቀድ ለመከተል መሞከሩን እናቆማለን፡፡

## *ውይይት*

- ከመረጥካቸው ምርጫዎች ጥቂቶችን አስብ፡፡ የእያንዳንዱ ምርጫ ውጤት ምን ነበር?
- ደስተኛ ለመሆንና ከሰማዩ አባታችን ጋር ተመልሶ መኖርን እንዴት መምረጥ ይችላሉ?
- ትክክለኛ ምርጫን እንዴት የበለጠ ትክክለኛ ምርጫዎችን ለመምረጥ ይረዳዎታል?
- ስህተተ ነገሮችን መምረጥ ማድረግ ወደፊት ጥሩ ምርጫዎችን እንዳይመርጡ እንዴት ያግድዎታል?

## የሰማይ አባታችን ጥሩ ምርጫዎችን እንድንመርጥ ይረዳናል

የሰማዩ አባታችን ጥሩ ምርጫዎችን እንድንመርጥ ይፈልጋል ስለዚህ እርሱ የሚያውቃቸውን ነገሮችን ለማወቅ መማር፣ እርሱ የሚያደርገውን ነገሮች ማድረግ፣ እናም እርሱ ያለውን ነገሮች ሊኖረን ይችላል፡፡ ትክክለኛ የሆኑ ነገሮችን ለማድረግ ከመረጥን ደስተኛ እንደምንሆንና ከእርሱ ጋር ተመልሰን መኖር እንደምንችል ያውቃል፡፡

የሰማዩ አባታችን ጥሩ ምርጫዎችን እንድንመርጥ ሊረዳን ይፈልጋል፡፡ ከእርሱ እርዳታ ጋር፣ ሁሉ እርሱን ከጠየቅነው፣ የሰይጣንን ፈተናዎች እንድንቋቋም ይረዳናል፡፡ ትክክለኛውን ለመምረጥ ብርታት ይሰጠናል፡፡ እቀዱን እንድንከተልና ይበልጥ እርሱን እንድንመስል ይረዳናል፡፡

## ውይይት

- የሰማዩ አባታችን ጥሩ ምርጫዎችን እንድንመርጥ የሚፈልገው ለምንድነው?
- ትክክለኛ የሆነውን እንድናደርግ ያስገድደናል? ለምን?

## ማጣቀሻ

*የሰማዩ አባታችን የመምረጥ መብት ሰጥቶናል*

- የዮሐንስ ወንጌል 14፥15 (ኢየሱስን ከወደድነው፣ ትዕዛዙን እናከብራለን)።
- 2ኛ ኔፊ 2፥21–29 (ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል ለመምረጥ ነጻ ነን)።
- ሔለማን 14፥30–31 (የሰማዩ አባታችን ጥሩውን ወይም መጥፎውን እንድንመርጥ ነጻነት ሰጥቶናል)።

*የሰማዩ አባታችን እቅድ የሚሰራው ለመምረጥ ነጻ ከሆንን ብቻ ነው*

- 2ኛ ኔፊ 2፥11 (ለማንኛውም ጥሩ ነገር ሁሉ ተቃራኒ የሆኑ ክፉ ነገሮች አሉ)።
- አልማ 41፥3–5 (ጥሩ ከሰራን፣ ከሰማዩ አባታችን ጋር ለመኖር እንመሳሰላለን፡፡ መጥፎ ከሰራን፣ እስከመጨረሻው እናዝናለን)።
- 3ኛ ኔፊ 27፥14–15 (ለማድረግ እንደመረጥነው ስራ መዳኘት እንችላለን)።

*የሰማዩ አባታችንን ለመታዘዝ መምረጥ ደስተኛ ያደርገናል*

- 2ኛ ኔፊ 9፥18 (በሰማዩ አባታችን ያመኑ ታላቀ ደስታ ይኖራቸዋል)።
- ሞዛያ 2፥41 (የሰማዩ አባታችንን ትዕዛዛት የሚጠብቁ የተባረኩ ስለሚሆኑ ደስተኞች ናቸው)።


*የሰማዩ አባታችን ጥሩ ምርጫዎችን እንድናደርግ ይረዳናል*

- መዝሙረ ዳዊት 5፥12 (የሰማዩ አባታችን ጥሩ የሆኑትን ይባርካል)።
- መዝሙረ ዳዊት 25፥9 (የሰማዩ አባታችን ጥሩ ለማድረግ የመረጡትን ሰዎች ይረዳል)።
- ወደ ሮሜ ሰዎች 12፥9 (ጥሩ ነገሮችን ማድረግ ይገባናል)።
- 1ኛ ቆሮንቶስ 10፥13 (የሰማዩ አባታችን ፈተናዎችን ለመቋቋም በጣም አስቸጋሪ እንዲሆኑብን አይፈቅድም)።
- ሞሮናይ 7፥28 (በሰማዩ አባታችን የሚያምኑ ሰዎች ጥሩ ማድረግን ይፈልጋሉ)።

# እግዚአብሔር ካለበት መልቀቅ

ክፍል ሁለት





ኢየሱስ ለእኛ የተዋበ ምድርን ፈጥሯል፡፡

# ኢየሱስ ምድርን ፈጠረ

*ምዕራፍ 5*

*ምድርን የሰራው ማነው? ለምንድን ነበር የሰራው?*

## ምድር ያስፈልገናል

የሰማይ አባታችን በሰማይ ካስረዳን የዕቀዱ ክፍል አንዱ ለተወሰነ ጊዜ ሰማይን እንድንለቅ ነበር፡፡ የስጋና አጥንት አካልን ለመቀበልና፣ ትክክለኛ ምርጫዎችን እንደምንመርጥ እና እንደማንመርጥ በመፈተን ለማሳየት ከእርሱ መኖሪያ ርቀን፣ የምንኄድበተ ቦታ ያስፈልገናል፡፡ ይህንን ቦታ አንድ ሰው እንዲሰራልን ፈለገ። እርሱም ኢየሱስ እንዲሰራው መረጠው፡፡

## *ውይይት*

• እግዚአብሔር ምድርን ለእኛ ለመስራት ያቀደው ለምንድነው?

## ኢየሱስ ምድርን ፈጠረ

ኢየሱስ ምድርን ፈጠረ፡፡ እሱም ቀንና ጨለማን ሰራ፡፡ ፀሀይን፣ ጨረቃን ከዋክብቶችን ሰራ፡፡ ውኃውንም ከደረቀ መሬት ለየው እናም ባህሮችን፣ ሀይቆችንና ወንዞችን ሰራ፡፡ ሳሮችን፣ ዛፎችን፣ አበባዎችን እና በምድር ላይ ያሉ ሌሎች ዓይነት ተክሎችን ሁሉ በምድር ላይ ተከለ፡፡ ከዚያም እንስሳትን፣ አሳን፣ ወፎችንና ሌሎች ተናንሽ ነፍሳትን በምድር ላይ አሰፈረ፡፡ ኢየሱስ ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ፣ ምድር ለሰዎች መኖሪያ ዝግጁ ሆነች፡፡

የሰማይ አባታችን ቀጥሎም ወንድና ሴትን ፈጠረ፡፡ ወንዱ ስሙ አዳም እና ሴቷ ስሟ ሔዋን ነበር፡፡ እያንዳንዳቸው የሰማይ አባታችንን አካል የመሰለ የስጋና አጥንት አካል አላቸው፡፡ ይህ ሁሉ ምድርን የመስራቱና ህይወተ ያላቸውን ነገሮች በላዩ ላይ የማስፈሩ ሥራ ፍጥረት ተብሎ ይጠራል፡፡ የሰማይ አባታችን በምድር እና ኢየሱስን በላዩ ላይ እንዲያሰፍር በመራው ነገሮች ሁሉ ተደስቶ ነበር፡፡

## *ውይይት*

• አዳምና ሔዋን እግዚአብሄር ከሰራቸው ከሌሎቹ ነገሮች የሚለዩተ እንዴተ ነው?

## የሰማዩ አባታችን ስለሚወደን ምድርን ሰራልን

አሁን እኛ የምንኖረው የሰማዩ አባታችን ኢየሱስን እንዲሰራ በመራው የተዋበ ዓለም ውስጥ ነው፡፡ ጸሀይ ሙቀትና ብርሀን ተሰጠናለች፡፡ ዝናብ የምንጠጣው ውሀን ፍላጎት ሊያሟላልንና ተክሎች እንዲያድጉ ያደርጋል፡፡ በምድር ላይ ያሉ ተክሎች እና እንስሳትም ለእኛ ምግብና ልብስ ይሆኑናል፡፡

በሰማዩ አባታችን መመሪያ ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ሰራልን፤ እነዚህን ሁሉ ነገሮች እንደሰራልን ስንመለከት፣ የሰማዩ አባታችን እንደሚወደንና እንደሚጠነቀቅልን እንገነዘባለን፡፡

### ውይይት

- የሰማዩ አባታችን ስለ ሰራልን አንዳንድ ነገሮች አስብ፡፡
- የሰማዩ አባታችን እንደሚወደንና እንደሚጠነቀቅልን እንዴት እናውቃለን?

## ስለ ምድር ምስጋናችንን ማሰየት እንችላለን

የሰማዩ አባታችን በምድር ላይ ሁሉንም ነገር ለኛ እንደሰራልን ሁል ጊዜ ማስታወስ ይገባናል፡፡ የማናስታውስ ከሆነ ግን አይደሰተም፡፡ ምስጋናችንን በምድር ላይ ያሉትን ነገሮች በብልሀት በመጠቀም ማሳየት አንችላለን፡፡ በምድር ላይ ማንኛውንም ነገር ማባከን የለብንም፡፡ ለምድር በመጠንቀቅ እናም በንጽህና መጠበቅ ይገባናል፡፡ ወደ ሰማዩ አባታችን ስንጸልይ ስለዚህ የተዋበች ዓለም ማመስገን ይገባናል፡፡ እዚህ እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገሮች በማድረግ ደግሞ ስለ ምድር ያለንን ምስጋና እናሳየዋለን፡፡

### ውይይት

- ለሰማዩ አባታችን ስለ ምድር ያለንን ምስጋና እንዴት ማሳየት እንችላለን?

### ማጠቀሻ

*ምድር ያስፈልገናል*

- ትንቢተ ኢሳይያስ 45፥18 (እግዚአብሔር የሰው ዘር እንዲኖርበተ ምድርን ፈጠረ)።
- 2ኛ ኔፊ 2፥15 (እግዚአብሔር ለእኛ ካለው እቅዱ በአንዱ ክፍል ምድርን ሰራ)።

*ኢየሱስ ምድርን ሰራ*

- ትንቢተ ኢሳይያስ 45፥12 (እግዚአብሔር ምድርን ፈጠረ)።

*የሰማዩ አባታችን ስለሚወደን ምድርን ፈጠረልን*

- ኦሪት ዘፍጥረት 1 (እግዚአብሄር በምድር ላይ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ለእኛ ፈጠረ)።
- ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥38–39 (ከእግዚአብሔር ፍቅር ምንም ሊለየን አይችልም)።

*ስለ ምድር ምስጋናችንን ማሳየት እንችላለን*

- ወደ ኤፌሶን ሰዎች 5፥20 (እግዚአብሔርን ስለ ሁሉም ነገር ማመስገን ይገባናል)።
- ሞዛያ 2፥20–25 (እኛን የሰራንን፣ እግዚአብሔር ማመስገን ይገባናል)።

# አዳም እና ሔዋን

*ምዕራፍ 6*

---

*አዳም እና ሔዋን እነማን ነበሩ? እኛን ለመርዳት ምን አደረጉ?*

## አዳምና ሔዋን ወደ እዚህ ምድር ለመምጣት የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ነበሩ

የሰማዩ አባታችን የመጀመሪያዎቹን የምድር ሰዎች አዳምና ሔዋን ብሎ ሰየማቸው፡፡ የእርሱ ሁለት ምርጥ ልጆቹ ነበሩ፡፡ ለእኛ ለሁላችንም ወደ ምድር እንድንመጣ አመቻችተውልናል፡፡

በሰማይ፣ አዳም ሚካኤል ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ ከመሪዎቻችን አንዱ ነበር፡፡ ከሰይጣን ጋር በተደረገው ጦርነት ላይ መርቶናል፡፡ ሚካኤል ጥሩ ሰው ነበር፡፡ የሰማዩ አባታችን እንዲያደርግ የሚፈልገውን ነገር በማድረጉ፣ በዚህ ምድር ላይ ለመሆን የመጀመሪያው ሰው ሆኗል፡፡

ሔዋን ለሰማዩ አባታችን በጣም ጥሩ ሴት ልጁ ነበረች፡፡ የሰማዩ አባታችን የአዳም ጓደኛ እንድትሆን እና እንድትረዳው ወደ ምድር ከአዳም ጋር ላካት፡፡ የሰማዩ አባታችን አዳም ብቻውን መሆኑ ጥሩ እንዳልሆነ ያውቃል፡፡ አዳም፣ በራሱ፣ እኛ ወደ ምድር እንድንመጣ ሊያመቻችልን አይችልም ነበር፡፡ የሔዋን ድርሻ በእቀዱ ውስጥ እንደ አዳም ድርሻ አስፈላጊ ነበረ፡፡

### *ውይይት*

- የሰማዩ አባታችን አዳምና ሔዋን በምድር ላይ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች እንዲሆኑ የመረጠው ለምንድን ነበር?
- የሰማዩ አባታችን ሔዋን ከአዳም ጋር እንድትሆን የላካት ለምንድን ነበር?

## የኤደን ገነት የአዳም እና የሔዋን የመጀመሪያ ቤታቸው ነበር

የሰማዩ አባታችን አዳምና ሔዋን በምድር ላይ የሚኖሩበትን የተዋበ ስፍራ ፈጠረላቸው፡፡ በታውም የኤደን ገነት ተብሎ ይጠራል፡፡ አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት በነበሩ ጊዜ፣ እያንዳንዳቸው ሊሞት የማይችል የሰጋና አጥንት አካል ነበራቸው፡፡ ልጆች አልነበራቸውም፡፡ ለሚያስፈልጋቸው ነገሮች መስራት ወይም መዝራትና ማጨድ የለባቸውም ነበር፡፡ በሰማይ የነበራቸውን ህይወት አያስታውሱትም፡፡ ክፉ እና ደጉን ለይተው አያውቁም ነበር፡፡

---



ኣዳምና ሔዋን በመሰዊያው ላይ ተንበረከኩ።

በኤደን ገነት ውስጥ፣ አዳምና ሔዋን ከሰማዩ አባታችን ጋር መራመድና መነጋገር ይችሉ ነበር፡፡ ማድረግ የሚገባቸውን ነገሮች ይነግራቸዋል፡፡ ገነትን በማስዋብ እንዲጠብቁትና እንዲጠነቀቁለት፣ ልጆች እንዲኖራቸውም ነገሯቸዋል፡፡ ደግሞም ካንዱ በስተቀር፣ በገነት ካሉት የሁሉም የዛፍ ፍሬ ያለገደብ መብላት እንደሚችሉ ነግሯቸው ነበር፡፡ የሰማዩ አባታችን መልካሙን እና ክፉውን ከሚያሳውቀው ዛፍ ፍሬ ከሆነው እንዳይበሉም ነግሯቸዋል፡፡ ከዚያ የዛፍ ፍሬ ከበሉ እንደሚሞቱም አስጠንቀቀቸዋል፡፡

## *ውይይት*

- የአዳምና ሔዋን ህይወት በኤደን ገነት ውስጥ ከዛሬው ህይወት እንዴት ይለያል?
- የሰማዩ አባታችን አዳምና ሔዋን እንዲያደርጉ የነገራቸው ምንድን ነበር?

## አዳም እና ሔዋን ከሰማዩ አባታችን አብረው ከመሆን ተለዩ

የሰማዩ አባታችንን ዕቅድ ሰይጣን ማፈራረስ እንደሚችል አሰበ፡፡ ወደ ኤደን ገነት መጥቶም ሔዋን መልካሙን እና ክፉውን ከሚያሳውቀው ዛፍ ፍሬ ጥቂት እንድትበላ ሊያግባባትሞከረ፡፡ ፍሬውንም ከበላች እንደማትሞት ነገራት፡፡ እርሱም እንደ የሰማዩ አባታችን መልካሙ እና ክፉውን ለይተሽ ታውቂያለሽ አላት፣ ሔዋንም ሰይጣንን አመነችው፣ እና ፍሬውንም በላች፡፡ ሔዋን ከፍሬው ጥቂት ዕንደበላች ለአዳም ስትነግረው፣ ገነትን መልቀቀ እንደሚኖርባት አወቀ፡፡ እርሱም አብረው መቀየት ይችሉ ዘንድ ከፍሬው ጥቂት ወስዶ በላ፡፡

የሰማዩ አባታችን እንዳይበሉ የነገራቸውን ፍሬ ከበሉ በኋላ የአዳምና የሂዋን ህይወት ተለወጠ፡፡ የሰማዩ አባታችንም ከኤደን ገነት አስወጣቸው፡፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህ ከእርሱ ጋር መራመድ እና መነጋገር አልቻሉም፡፡ ከዚያን በኋላ የሰው ዘር የሰማዩ አባታችን ካለበት ተለዩ። ከሰማዩ አባታችን ጋር ለመሆን ያለመቻል መንፈሳዊ ሞት ይባላል፡፡ አዳምና ሔዋን ከተቀበው ገነት ውጪ በአለም ውስጥ እንዲኖሩ ሆነ፡፡ የሚፈልጉተን ነገሮች ለማግኘትም መስራት ነበረባቸው፡፡

አካላቸውም ተለወጠ፡፡ ከዚያም ልጆች ሊያገኙ ቻሉ። መታመም፣ መሰቃየት እናም ማዘን እናም አንድ ቀን ሊሞቱ እንደሚችሉ ሆነ፡፡ በአዳምና ሔዋን ላይ የመጣው ለውጥ የአዳም ውድቀት ይባላል፡፡

ይህ ለውጥ በሁሉም የአዳምና ሔዋን ተውልድ ላይ ታየ፡፡ እኛም እንደ እነርሱ ልጆች የመውለድ ሃይልና ህመም፣ ስቃይ፣ ሀዘንና ሞት ደግሞ መጣብን፡፡

## *ውይይት*

- የሰማዩ አባታችንን ዕቅድ ለማፍረስ ሰይጣን የሰራው ምን ነበር?
- መልካም እና ክፉን የሚያሳውቀውን ዛፍ ፍሬ ከበሉ በኋላ የአዳምና ሔዋን ህይወት የተለወጠው እንዴት ነበር?
- መንፈሳዊ ሞት ምንድነው?
- የአዳም ውድቀት ምንድነው?

## የአዳም ውድቀት የሰማዩ አባታችን አስፈላጊው የዕቅዱ ክፍል ነበር

የሰማዩ አባታችን ልጆቹ ወደ ምድር መጥተው የስጋና አጥንቶች አካልን እንዲቀበሉ ዕቅድ ነበረው፡፡ አዳምና ሔዋንን ከኤደን ገነት ካስወጣቸው በኋላ ልጆች ማግኘት ጀመሩ፡፡ በኋላም ልጆቻቸው ተጋብተው ልጆችን አፈሩ፡፡ በዚህ መንገድ እንዳቀደው ከሰማያዊ አባታችን ጋር ይኖሩ የነበሩ የመንፈስ ልጆቹ ወደ ምድር መምጣት ጀመሩ፡፡ አዳምና ሔዋን ባደረጉት ምክንያት፣ እያንዳንዳችን ወደ ምድር በመምጣትና የስጋና አጥንቶች አካልን መቀበል ችለናል፡፡

የሰማዩ አባታችን ልጆቹ የሚሹትን እና የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ሰርተው ደግሞ እንዲያገኙ አቀዷል፡፡ አዳምና ሔዋን ከኤደን ገነት ከለቀቁ ጊዜ ጀምሮ የሰማዩ አባታችን ልጆች የሚሹትን እና የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለማግኘት በምድር ላይ እንዲሰሩ አደረገ፡፡

አዳምና ሔዋን የሰማዩ አባታችን እንዳይበሉ ከነገራቸው ፍሬ ከበሉ በኋላ፣ በመልካም እና በክፉ መካከል ያለውን ልዩነት ተማሩ፡፡ አሁንም፣ እያንዳንዳችን በምድር ላይ በመልካም እና ክፉ መካከል ያለውን ልዩነት መማርና መልካም ነገሮችን ወይም መጥፎ ነገሮችን ለማድረግ ለየራስችን መምረጥ እንችላለን፡፡

የሰማዩ አባታችን አዳምና ሔዋንን ከኤደን ገነት ሲያስወጣቸው፣ እርሱ እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ነገሮችን ለማወቀ ሞክረው ነበር፡፡ እነርሱም ታዘዙት እና ልጆቻቸውም እንዲታዘዙት አስተምረዋል፡፡ እኛም እያንዳንዳችን ደግሞ የሰማዩ አባታችን እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገሮች ለማድረግ፣ መማርና እርሱን መታዘዝ እናም ልጆቻችን እርሱን እንዲታዘዙት ማስተማር ይገባናል፡፡

### ውይይት

- የሰማዩ አባታችንን ዕቀድ ሰይጣን አፈራርሶ ነበርን?
- አዳምና ሔዋን ላደረጉት ነገሮች ለምን ማመስገን ይገባናል?

### ማጣቀሻ

*አዳም እና ሔዋን ወደ እዚህ ምድር ለመምጣት የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ነበሩ*

- ኦሪት ዘፍጥረት 1፥26–27 (እግዚአብሔር ወንድና ሴትን ፈጠረ፡፡)
- የዮሐንስ ራዕይ 12፥7–9 (በዚያን ጊዜ ሚካኤል ይባል የነበረው አዳም፣ ሰይጣንን በመቃወም የጻድቃንን መንፈስ መርቷል)
- 1ኛ ኔፊ 5፥11 2ኛ ኔፊ 2፥19–20 (አዳም እና ሔዋን የመጀመሪያዎቹ ወላጆች ነበሩ፡፡)

*የኤደን ገነት የአዳም እና የሔዋን የመጀመሪያ ቤታቸው ነበር*

- ኦሪት ዘፍጥረት 2፥15 (የሰማዩ አባታችን ለአዳም እና ሔዋን ኤደን ገነትን እንዲንከባከቡት ነግሯቸዋል፡፡)

- ኦሪት ዘፍጥረት 2፥16–17 (የሰማዩ አባታችን አዳምና ሔዋን መልካሙን እና ክፉውን የሚያሳውቀውን ዛፍ ፍሬ እንዳይበሉ ነግሯቸዋል፡፡)

*አዳም እና ሔዋን ከሰማዩ አባታችን አብረው ከመሆን ተለዩ*

- ኦሪት ዘፍጥረት 3፥1–5 (ሰይጣን ሔዋንን ፈተናት)።
- ኦሪት ዘፍጥረት 3፥23–24 (እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ከኤደን ገነት አስወጣቸው።)
- ሔለማን 14፥16 (አዳም እና ሔዋን እግዚአብሔር በነበረበት እንዲቆዩ አልተፈቀደላቸውም ነበር)።

*የአዳም ውደቀት የሰማዩ አባታችን አስፈላጊው የዕቅዱ ክፍል ነበር*

- 2ኛ ኔፊ 2፥22–25 (የአዳም ውድቀት ባይኖር ኖሮ ወደ ምድር መምጣት ባልቻልን ነበር)።
- አልማ 12፥26–32 (የአዳም ውድቀት የእግዚአብሔር የዕቅዱ ክፍል ነበር)።

# ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት

ክፍል ሶስት



# መንፈስ ቅዱስ

*ምዕራፍ 7*

---

*የሰማዩ አባታችን እንድናውቅ የሚፈልገውን ነገሮች የሚነግረን አንድ ሰው መርጧል፡፡ ይሄ ሰው ማን ነው፣ እናም የሰማዩ አባታችንን መልዕክት ለመረዳት እንዴት መማር እንችላለን?*

## መንፈስ ቅዱስ እኛን ለመርዳት ከሰማዩ አባታችን እና ከኢየሱስ ጋር ይሰራል

መንፈስ ቅዱስ ከሰማዩ አባታችንና ከኢየሱስ ጋር ይሰራል፡፡ እነርሱ እንዳሉና እንደሚወዱን ይመሰክርልናል፡፡ ማወቅና መስራት የሚያስፈልገንን ነገሮች እንዲያስተምሩንም ይረዳቸዋል እናም ትዕዛዞቻቸውን እንድናከብር ይረዳናል፡፡ የሰማዩ አባታችንና ኢየሱስ እንዳላቸው ዓይነት የስጋና አጥንት አካል የለውም፡፡ እርሱ መንፈስ ነው፡፡ ሰውንም ይመስላል፡፡

የሰማዩ አባታችን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እና መንፈስ ቅዱስ ሦስት የተለያዩ ግለሰቦች ናቸው፡፡ ማወቅና መስራት የሚያስፈልጉንን ነገሮች እንድንማር ለመርዳት ባንድነት ይሰራሉ፡፡ ከሰማዩ አባታችን ወይም ከኢየሱስ መልዕክት ስንቀበል፣ አብዛኛውን ጊዜ መልዕክቶቹን የሚያመጣልን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ደግሞም ትዕዛዛቶቻቸውን እንድናከብር ይረዳናል፡፡

### *ውይይት*

- መንፈስ ቅዱስ ከማን ጋር ይሰራል?
- መንፈስ ቅዱስ ከሰማዩ አባታችንና ከኢየሱስ የሚለየው እንዴት ነው?

## የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

መንፈስ ቅዱስ ስለ ሰማዩ አባታችንና ኢየሱስ ያስተምረናል፡፡ እንደሚወዱንና እንዳሉ ይነግረ-ናል። የሰማዩ አባታችንም የመንፈሳችን አባት እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ደግሞም ኢየሱስ አዳኛችን እንደሆነ ይነግረናል፡፡

መንፈስ ቅዱስ ስለ ሰማዩ አባታችንና ኢየሱስ እናም ወደ ሰማይ ለመመለስ ማድረግ ያለብንን ነገሮች እንድናገናዝብ ይረዳናል፡፡ ደግሞም እውነትን ሁሉ እንድንረዳ እና እንድንማር ይረዳናል፡፡

---

መንፈስ ቅዱስ ደግሞም የሰማዩ አባታችንና የኢየሱስን ትዕዛዛት እንድናከብር ጥንካሬ ይሰጠ-ናል። በሁለት ድርጊቶች መካከል መምረጥ ሲኖርብን ትክክለኛ ውሳኔ እንድንወስን ሊረዳን ይችላል፡፡ በችግር ጊዜም ሰላምን ሊሰጠን ይችላል፡፡

### *ውይይት*

- የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምንድን ነው?
- መንፈስ ቅዱስ ምን እንድናውቅ ሊረዳን ይችላል?
- መንፈስ ቅዱስ ምን እንድናደርግ ሊረዳን ይችላል?

## መንፈስ ቅዱስ ሀይልን በተሞላ መንገድ ያስተምረናል

መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛው ምን እንደሆነና ስህተቱ ምን እንደሆነ ማረጋገጫ ይሰጠናል፡፡ ይህን ማረጋገጫ በፍጹም የማንረሳው እና በጣም ጠንካራ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ አብዛኛውን ጊዜ በጆሮአችን ልንሰማ በምንችለው መንገድ አያነጋግረንም፡፡ በምትኩ፣ ያነበብነው ወይም የሰማነው እውነት እንደሆነ እንድናስብ ወይም እንዲሰማን ያደርጋል፡፡ እነዚህ ስሜቶች በጣም ጠንካራ ናቸው፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተመሳሳይ ጊዜ ለብዙ ሰዎች ሊሰማ ይችላል፡፡ ይህን በይበልጥ ለማገናዘብ፣ ፀሃይን እናስብ፡፡ አንድ ፀሃይ ብቻ አለች፣ ነገር ግን ብርሃኗና ሙቀትዋ በብዙ ቦታዎች ባሉ ህዝቦች በተመሳሳይ ጊዜ ይሰማል፡፡ መንፈስ ቅዱስንም በተመሳሳይ መንገድ ማሰብ ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን እርሱ እራሱ በማንኛውም ጊዜ በአንድ ቦታ ብቻ ቢሆንም ሀይሉ በብዙ ቦታዎች ባሉ ህዝቦች በተመሳሳይ ጊዜ ይሰማል፡፡

### *ውይይት*

- መንፈስ ቅዱስ ማወቅ የሚያስፈልጉንን ነገሮች የሚነገረን እንዴት ነው?
- መንፈስ ቅዱስ በተመሳሳይ ጊዜ ብዙ ሰዎችን እንዴት መርዳት ይችላል?

## መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዳችንን ይረዳናል

የሰማዩ አባታችን አዳምና ሔዋንን ከኤደን ገነት ካስወጣቸው በኋላ፣ ማድረግ የሚገባቸውን ፀለዩና ጠየቁት፡፡ የሰማዩ አባታችንም መንፈስ ቅዱስን ስለእርሱና ኢየሱስ እናም አዳምና ሔዋን ማድረግ ስለሚገባቸው ነገሮች እንዲያስተምራቸው ላከው፡፡ መንፈስ ቅዱስም የሰማዩ አባታችን ትምህርቶች እውነት እንደሆኑ ነገሯቸዋል፡፡ የሰማይ አባታችን እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ነገሮች ለማድረግ ብርታት ሰጣቸው፡፡

ደግሞም የሰማዩ አባታችን ስለአደረገላቸው ነገሮች ተሁተና አመስጋኝ እንዲሆኑ ረድቷቸዋል፡፡

በመንፈስ ቅዱስ አመራር፣ አዳምና ሔዋን ትዕዛዛቱን ከአከበሩ እና ሁል ጊዜ ኢየሱስን ከተከተሉ አንድ ቀን ከሰማዩ አባታችን ጋር ተመልሰው መኖር እንደሚችሉ ተምረዋል፡፡ የመንፈስ ቅዱስ አመራርም በጣም ደስተኛ አድርጓቸዋል፡፡

የሰማዩ አባታችን እያንዳንዳችንን ይወደናል፡፡ እንዲመራንና እውነትን እንዲያስተምረን መንፈስ ቅዱስን ይልክልናል፡፡ ቢሆንም፣ መንፈስ ቅዱስ የሚረዳን ከሰማዩ አባታችንና ከኢየሰስ

የሚመጣልንን ትዕዛዛት እና መመሪያዎች በቁም ነገር ለመከተል ከሞከርን፣ ብቻ ነው። ትዕዛዛቶቻቸውን በቁም ነገር ለማክበር ካልሞከርን ወይንም መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምረን ካልፈለግን፣ ምንም ነገር አይነግረንም። የመንፈስ ቅዱስን ትምህርቶች ከተከተልን፣ የተሻለ ሕይወት ይኖረናል፡፡

## *ውይይት*

- መንፈስ ቅዱስ ለዳምና ሔዋንን የረዳቸው እንዴት ነበር?
- ከመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ለማግኘት ምን ማድረግ አለብን?

## *ማጣቀሻ*

*መንፈስ ቅዱስ እኛን ለመርዳት ከሰማዩ አባታችን እና ከኢየሱስ ጋር ይሰራል*

- የዮሐንስ ወንጌል 14፥26፤ 2ኛ ኔፊ 33፥1 (መንፈስ ቅዱስ የተማርናቸውን ነገሮች እንድናስታውስ ይረዳናል)።
- የዮሐንስ ወንጌል 15፥26 (መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን በተመለከተ ዕውነቱን ያሳየናል)።
- 1ኛ ዮሐንስ 5፥7 (መንፈስ ቅዱስ ከሰማዩ አባታችንና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ይሰራል)።
- 3ኛ ኔፊ 28፥11 (መንፈስ ቅዱስ የሰማዩ አባታችንና ኢየሱስን በተመለከተ ዕውቀት ይሰጣል)።

*የመንፈስ ቅዱስ ሥራ*

- 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥3፤ ወደ ዕብራዊያን ሰዎች 10፥15 (መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ለዳኝ መሆኑን እንድናውቅ ያስተምረናል)።
- 2ኛ ኔፊ 32፥5 (መንፈስ ቅዱስ ማድረግ የሚገባንን እንድናውቅ ይረዳናል)።

መንፈስ ቅዱስ ሀይልን በተሞላ መንገድ ያስተምረናል

- ሞሮናይ 15፥5–7 (መንፈስ ቅዱስ የተኞቹ ነገሮች እውነት እንደሆኑና የተኞቹ ነገሮች እውነት እንዳልሆኑ ይነግረናል)።

*መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዳችንን ይረዳናል*

- የዮሐንስ ወንጌል 16፥13 (መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነቱ ሁሉ ይመራናል)።
- ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥16–17 (መንፈስ ቅዱስ የሰማዩ አባታችን ልጆች እንደሆንን እንድናውቅ ይረዳናል)።

# ከሰማይ አባት ጋር መነጋገር

*ምዕራፍ 8*

*የሰማዩ አባታችን በጣም ይወደናል። በፈለግንበተ ጊዜ ሁሉ ከእሱ ጋር ለመነጋገር ለመቻቸተልናል። ከሰማዩ አባታችን ጋር እንዴት መነጋገር እንችላለን?*

**የሰማዩ አባታችንን ማነጋገር እንችላለን**

የሰማዩ አባታችንን ማነጋገር ፀሎት ይባላል። ምንም እንኳ የሰማዩ አባታችን በሰማይ ቢኖርም፣ እሱን ማነጋገር እንችላለን፣ እናም ይሰማናል። እኛንም ለመርዳት ይፈልጋል። እሱን እንድናነጋግረውም ጠይቆናል። እሱን ስናነጋግር፣ ለእኛ ጥሩ የሆኑትን ነገሮች እንድናደርግ ይረዳናል።

ለሰማዩ አባታችን ስለምናስበው ነገሮች መንገር እንችላለን። እንደምንወደው መንገር እንችላለን። ስለሰጠን ነገሮችም ምስጋናችንን ልንነግረው እንችላለን። እንዲረዳንም ልንጠይቀው እንችላለን።


የሰማዩ አባታችንን ማነጋገር በፈለግንበተ በማንኛውም ጊዜ ማነጋገር እንችላለን። ብቻችንን ስንሆን ማነጋገር አለብን። ብቻችንን ስንሆን ስለግላዊ ስሜቶቻችንና ችግሮቻችን ማነጋገር እንችላለን። ቢያንስ ሁልጊዜ ጠዋተ እና ማታ ከእርሱ ጋር መነጋገር ይገባናል።

ደግሞም ከቤተሰባችን ጋር በአንድነተ ሆነን ልናነጋግረው ይገባናል። ይህንን ሁልጊዜ ጠዋተና ማታ ማድረግ እንችላለን። ደግሞም ይህን ከእያንዳንዱ የማዕድ ሰዓተ በፊተ ስለምግባችን ስናመሰግን ማድረግ እንችላለን።

የሰማዩ አባታችን እኛ ከእሱ ጋር እንድንነጋገር መፈለጉን በፍጹም አይከለክለንም። እርሱ ዘወተር ይወደናል እናም ሊረዳን ይፈልጋል። ስህተተ የሆኑ ነገሮችን ስናደርግ እንኳ፣ ያኔም ይወደናል። ያደምጠናል እናም ይረዳናል።

***ውይይተ***

- የሰማዩ አባታችንን ለምን ማነጋገር ይገባናል?
- እርሱን ማነጋገር የሚገባን መቼ ነው?



በግላችንና በቤተሰብ ጠዋትና ማታ መጸለይ ይገባናል።

## የሰማይ አባታችን እንዴት ከእርሱ ጋር እንደምንነጋገር ነገሮናል

ስንጸልይ፣ ለሰማይ አባታችን በትክክል የሚሰማንና የምንፈልገውን ነገሮች መንገር ይገባናል፡፡ ዘወትር እርሱን ስናነጋገር አንድ ዓይነት ቃላትን መደጋገም አይገባንም፡፡ መጮህ ወይም ማዜም አያስፈልገንም፡፡

እርሱን የምናነጋግርበትን ሁኔታ ነገሮናል፡፡ እርሱን በቀጥታ እንዲህ በማለተ ማነጋገር ይገባናል፣ "የሰማይ አባታችን፣" ወይም ተመሳሳይ ቃላት፡፡ ከእርሱ ጋር በፍቀርና በአክብሮተ መነጋገር ይገባናል፡፡

ቀጥሎ፣ ስለ አደረገልን ነገሮች ማመስገን ይገባናል፡፡

እነዚህ እርሱን ልናመሰግንባቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች ናቸው፣

1. ስለ ተዋበው ምድርና ምግባችን፣ ልብሳችን፣ እና ሌሎች ንብረቶቻችን ልናመሰግነው ይገባል፡፡
2. ስለ ትምህርቶቹና በይበልጥ ስለ እርሱ መማር እና ስለ ችሎታችን ልናመሰግነው ይገባል፡፡
3. ስለቤተሰባችንና ጓደኞቻችን፣ ስለ መልካም ጤንነታችን፣ እና ስለስራችን ልናመሰግነው ይገባል፡፡

ከዚያም ስለምንፈልገው ነገሮች እንጠይቀዋለን፡፡ እነዚህ ልንጠይቀው የምንፈልገው አንዳንድ ነገሮች ናቸው፣

1. የተኞቹ ነገሮች እውነት እንደሆኑና የተኞቹ ነገሮች እውነት እንዳልሆኑ ልንጠይቀው እንችላለን፡፡
2. እኛንና ቤተሰባችንን እናም ጉረቤቶቻችንን እንዲጠብቀን ልንጠይቀው እንችላለን፡፡
3. እርሱ እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገር ለማድረግ እንዲረዳን ልንጠይቀው እንችላለን፡፡
4. ተክክለኛ፣ ነገሮችን ለማድረግ እንድንመርጥ እንዲረዳን ልንጠይቀው እንችላለን፡፡
5. ለሀጢያታችን ንስሀ ለመግባተ እንዲረዳን ልንጠይቀው እንችላለን፡፡
6. ለዕለተ በቂ ምግብ ለማግኘተ እንዲረዳን ልንጠይቀው እንችላለን፡፡
7. ችግራችን እንዲፈታልን እንዲረዳን ልንጠይቀው እንችላለን፡፡
8. ቤተሰባችን ወይም ጓደኞቻችን ያላቸውን ችግሮች እንዲፈታላቸው እንዲረዳቸው ልንጠይቀው እንችላለን፡፡

ፀሎታችንን "በኢያሱስ ክርስቶስ ስም፣ አሜን።" በማለተ፣ መዝጋተ አለብን። ይህም ኢየሱስ አዳኛችን እንደሆነ እንድናስታውስ ይረዳናል፡፡ ኢየሱስ እኛ በምንፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ ሊረዳን በሰማዩ አባታችን አመራር ስር ይሰራል፡፡ የኢየሱስን ስም ከአክብሮተ ጋር መናገር ይገባናል፡፡

### *ውይይት*

- የሰማዩ አባታችንን ስናነጋግረው፣ እንዴት እንጀምራለን?
- እርሱን ልናመሰግንባቸው የምንችለው አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

- ልንጠይቃቸው የምንችለው አንዳንድ ነገሮችስ ምንድን ናቸው?
- የሰማዩ አባታችንን ለነጋግረን ስንጨርስ የምንለው ምንድነው?

## የሰማዩ አባታችን ዘወትር ምላሽ ይሰጠናል

የሰማዩ አባታችን እንደሚሰማን እርግጠኛ መሆን እንችላለን፡፡ ለእኛ ጥሩ የሆኑ ነገሮችን ያውቃል፡፡ እርሱ ዘወትር እኛን ለመርዳት ዝግጁ ነው፡፡

የሰማዩ አባታችን ብዙ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ለማካኝነት መልስን ይልካል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለማወቅና ለማድረግ የምንፈልገውን ነገሮች እንድናገናዝብ ይረዳናል፡፡ አንዳንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሌላ ሰው እንዲረዳን ያነሳሳል፡፡

የሰማዩ አባታችን የሚሰጠንን መልስ ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን ይገባናል፡፡ የጠየቅነውን ነገሮች ላይሰጠን ይችላል፡፡ በጠበቅነው መንገድም ላይመልስልን ይችላል፡፡ ነገር ግን ለእኛ ጥሩ የሆነውን ያውቃል፡፡

### *ውይይት*

- የሰማዩ አባታችን የሚመልስልን እንዴት ነው?
- የጠየቅነውን ነገሮች ዘወትር የማይሰጠን ለምንድነው?

## በመፀለይ የተሻልን ሰዎች እንሆናለን

ትክክለኛ ነገሮችን ማድረግ ላናውቅ እንችላለን፡፡ ልንፈራ እንችላለን፡፡ ችግራችንን እንዴት እንደምናቃልልም ላናውቅ እንችላለን፡፡ የትኞቹ ነገሮች ዕውነት እንደሆኑና የትኞቹ ነገሮች እውነት እንዳልሆኑ ላናውቅ እንችላለን፡፡ ትክክለኛ የሆኑ ነገሮችን ማድረግ ልናውቅ እንችላለን ነገር ግን ለማከናወን ብቁ ብርታት ላይኖረንም፡፡

የሰማዩ አባታችንን በየጊዜው ስናነጋግር፣ በችግሮቻችን ይረዳናል፡፡ ትክክለኛውን ነገሮች እንድንሰራና እንድናውቅ ይረዳናል፡፡ ትክክለኛውን ነገሮች ስናውቅና ስናደርግ፣ የተሻሉ ሰዎች እንሆናለን፡፡ የበለጠ እንደ ሰማይ አባታችን እንሆናለን፡፡

### *ውይይት*

- ከሰማይ አባታችን ጋር በመነጋገር እንዴት የተሻሉ ሰዎች እንሆናለን?

### *ማጣቀሻ*

*የሰማዩ አባታችንን ማነጋገር እንችላለን*

- መዝሙረ ዳዊት፥ 55፥16–17 2ኛ ኔፊ 32፥9 (ከሰማይ አባታችን ጋር በየጊዜው መነጋገር ይገባናል)።
- የሉቃስ ወንጌል 18፥1 (ሁልጊዜ መጸለይ ይገባናል)።
- አልማ 37፥37 (ስለምናደርጋቸው ማናቸውም ነገሮች ከሰማዩ አባታችን ጋር መነጋገር ይገባናል)።

*የሰማይ አባታችን እንዴት ከእርሱ ጋር እንደምንነጋገር ነግሮናል*

- የማቴዎስ ወንጌል 6፥6–13 (እንዴት መጸለይ እንደሚገባን ተነግሮናል)።
- የያዕቆብ መልዕክት 1፥5 (ከሰማዩ አባታችን ጋር ስለ ብዙ ነገሮች መነጋገር እንችላለን)።
- አልማ 34፥17–27 (እነዚህ ለሰማዩ አባታችን ልንጸልይባቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች ናቸው)።
- 3ኛ ኔፊ 19፥6፣ 24 (ኢየሱስ ከሰማዩ አባታችን ጋር እንዴት እንደምንነጋገር አስተምሮናል)።


*የሰማዩ አባታችን ዘወትር ምላሽ ይሰጠናል*


- መጽሐፈ ምሳሌ 15፥29 (የሰማይ አባታችን ጸሎትን ይሰማል)።
- የማቴዎስ ወንጌል 7፥7 (ጠይቁ ታገኙማላችሁ)።
- ሞሮናይ 7፥26፤ 3ኔፊ 18፥20 (የጠየቅነውን መልካም የሆነውን ማንኛውንም ነገር እናገኛለን)።


*በመፀለይ የተሻልን ሰዎች እንሆናለን*

- የሉቃስ ወንጌል 22፥40 (ለመበርታት ፀልዩ ስለዚህም አትፈተኑም)።
- የያዕቆብ መልዕክት 5፥15–16 (የጻድቃኖች ፀሎት ብዙ ጥሩ ነገሮች እንዲከሰቱ ታደርጋለች)።



ጆሴፍ ስሚዝ



ብሪግሀም ያንግ


ጆን ቴይለር


ዊልፎርድ ውድረፍ


ሎሬንዞ ስኖው


ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ


ሂበር ጀ ግራንት


ጆርጅ አልበርት ስሚዝ


ዴቪድ ኦ ማኬይ


ጆሴፍ ፊልዲንግ ስሚዝ


ሀሮልድ ቢ. ሊ


ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል


አዝራ ታፍት ቤንሰን


ሀዋርድ ደብሊው ሃንተር


ጎርደን ቢ ሂንክሊ

የሰማዩ አባታችን በእኛ ጊዜ ነቢያትን ልኳል።

# ነቢያት

*ምዕራፍ 9*

---

*ለሰማዩ አባታችን ዛሬ በምድር ላይ የሚናገረው እናም የሰማዩ አባታችን እንድናውቅ እና እንድናደርግ የሚፈልገውን ሊነግረን የሚችል ማን ነው?*

## ነቢይ ለሰማይ አባታችን የሚናገር ሰው ነው

የሰማዩ አባታችን በምድር ላይ ለእርሱ የሚናገር ሰው ይመርጣል፡፡ ይህም ሰው ነቢይ ይባላል፡፡ ነብዩ የሰማይ አባታችንን ይወዳል እናም የሰማይ አባታችን እንዲያደርግ የሚፈልገውን ነገር ይሰራል፡፡ የሰማዩ አባታችን ነቢዩን ማወቀ እና ማድረግ የምንፈልገውን ነገሮች ያስተምረዋል፡፡ ከዚያም ነቢዩ እነዚያን ነገሮች ለእኛ ይነግረናል፡፡ ነቢዩ ለሰማዩ አባታችን ሲናገር፣ የሰማዩ አባታችን እራሱ ቢያነጋግረን የሚለንን ነገሮች እርሱም ይለናል፡፡

እነዚህ ነቢይ የሚነግረን አንዳንድ ነገሮች ናቸው፤

- ኢየሱስ የሰማዩ አባታችን ልጅ መሆኑን አዳኛችን መሆኑንና፣ ተምህርቶቹም እውነት እንደሆኑ ይነግረናል፡፡
- የሰማዩ አባታችን መስራት አለባችሁ የሚለንን ነገሮች ያስተምረናል፡፡
- መጥፎ ነገሮችን መስራት እንድናቆም ይነግረናል፡፡
- ወደፊት ስለሚከሰቱ ነገሮች ይነግረናል፡፡

የሰማዩ አባታችን ብቻ ነው ነቢይን መምረጥ የሚችለው ሰዎች ነቢይን መምረጥ አይችሉም፡፡ አንድ ሰው ራሱን በእራሱ ነቢይ እንዲሆን መምረጥ አይችልም፡፡ የሰማዩ አባታችን ለነቢይ የእርሱን ሥራ ለመፈጸም እና ለእርሱ እንዲናገር ሥልጣንን ሰጥቷል፡፡ ሰው ይሄን ሥልጣን ከሌለው የሰማዩ አባታችንን መወከል አይችልም፡፡

### *ውይይት*

- ነቢይ የሚናገረው ለማንነው?
- ነቢይ የሚነግረን አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

## የሰማዩ አባታችን ዘወትር እኛን እንዲረዱን ነቢያትን ልኳል

የሰማዩ አባታችን ዘወትር በምድር ላሉ ልጆቹ ይጠነቀቃል፡፡ ከአዳም ጊዜ አንስቶ፣ ልጆቹን ለመርዳት ነቢያትን ልኳል፡፡ ልጆቹን ከአደጋ ለማስጠንቀቀ ነቢያትን ይልካል፡፡ ሰዎችን ከችግር ለማራቀ እንዲመራቸው ልኳቸዋል፡፡ ለታላላቀ ጉዳዮች ሰዎች እንዲዘጋጁ ለመርዳት ልኳቸዋል፡፡ እነዚህ የሰማዩ አባታችን ከላካቸው ነቢያት ጥቂቶቹ ናቸው፣

1. ኖህ፣ መጥፎ ነገሮችን መስራት ካላቆሙ የሰማዩ አባታችን የጥፋት ውሃን እንዲያጠፋቸው እንደሚልክ ለሰዎቹ አስጠንቀቋቸዋል፡፡
2. አብርሃም፣ የሰማዩ አባታችንን ታዟል እናም ልጆቹም የሰማዩ አባታችንን እንዲታዘዙ አስተምሮአቸዋል፡፡ የሰማዩ አባታችን ለአብርሃም እና ለትውልዱ ብዙ ነገሮችን ለመስጠት የተስፋ ቃል ገብቷል፡፡
3. ሙሴ፣ የእስራኤልን ህዝብ ከግብጽ አውጥቶ የሰማዩ አባታችን ወደ አዘጋጀላቸው መሬት መርቶአቸዋል፡፡

በእኛም ጊዜያቶች፣ የሰማዩ አባታችን ነቢያትን ልኳል፡፡ ከብዙ ዘመናት በፊት ያልነበረ ነቢያት አንዱ ዮሴፍ ስሚዝ ይባላል፡፡ እርሱም በአሜሪካ ይኖር ነበር፡፡ በ1820 ዮሴፍ ስሚዝ የ14 ዓመት ልጅ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ፣ ዕውነተኛውን ቤተክርስቲያን ፍለጋ፣ ብዙ ሰዎች የተለያዩ ቤተክርስቲያንን ይቀላቀሉ ነበር፡፡ ዮሴፍ ጥሩ ሰው ለመሆንና የሰማዩ አባታችንን እውነተኛ ቤተክርስቲያን ለማግኘት ፈለገ፡፡

አንድ ቀን ዮሴፍ ቅዱስ የሆነ መፅሐፍን መጽሀፍ ቅዱስ የሚባለውን ያነብ ነበር፡፡ እርሱም ያነበበውም፣ የሆነ ነገር ማወቅ ብትፈልጉ፣ የሰማዩ አባታችንን መጠየቅ አለባችሁ፣ እናም የሰማዩ አባታችን ይነግራችኋል፡፡ እርሱም የሰማዩ አባታችን በእውነት ማድረግ የሚገባውን ነገሮች እንደሚነግረው አመነ፡፡ የተለየ ፀሎት ወደ ሰማዩ አባታችን ለመፀለይም ወሰነ፡፡

አንድ ጠዋት፣ ዮሴፍ ለፀሎት ወደ ተንሽ ደን ሔደ፡፡ እየፀለየ እያለም፣ ከፀሐይ የበለጠ ብሩህ ብርሃን ከሰማይ ወደ ታች መጣ፡፡ በዚህ ብርሃን ውስጥ የሰማዩ አባታችን እና ኢየሱስን አየ፡፡ የሰማዩ አባታችንም ወደ ኢየሱስ እየመለከተ እናም እንዲህ አለ፣ "ይህ የምወደው ልጄ ነው፡፡ እርሱን ስማው!"

ዮሴፍ ኢየሱስ የነገረውን ሁሉ አዳመጠ፣ እናም ኢየሱስ የሰጠውን መመሪያዎች ጠበቀ፡፡

ዮሴፍ እንደ አደገ፣ የሰማዩ አባታችን የእርሱ ነቢይ እንዲሆን መረጠው፡፡ እርሱም ታላቅ ነቢይ ነበረ፡፡ ሰዎችን የሰማዩ አባታችን እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ነገር አስተምሮአቸዋል፡፡

ዮሴፍ ስሚዝ በ1844 ዓ.ም ሞተ፡፡ እርሱ ከሞተ በኋላ፣ የሰማዩ አባታችን ነቢይ የሚሆን ሌላ ሰው መረጠ፡፡ ዛሬም፣ ነቢይ በሚሞትበት ጊዜ፣ የሰማዩ አባታችን ሌላ በምድር ላይ የሚናገርለት ሰው ይመርጣል፡፡

### *ውይይት*

- የሰማዩ አባታችን ከመረጣቸው ጥቂቶቹ ነቢያት እነማን ነበሩ?
- ዮሴፍ ስሚዝ ያደረገው ምን ነበር?

## ዛሬም በምድር ላይ ነቢይ አለ

የሰማዩ አባታችን ዛሬ በምድር ላይ ያሉተን ልጆቹን ይወዳቸዋል፡፡ ብዙ ችግሮች እንዳሉንም ያውቃል፡፡ እኛን ለመርዳት ነቢይን ልኳል፡፡ ልክ ባለፉት ዘመናት ነቢያትን እንዳነጋገረ ሁሉ ዛሬም ነቢይን ያነጋግራል፡፡ የሰማዩ አባታችን ለዚህ ነቢይ ለመላው ዓለም ህዝቦች የሚሆን መመሪያዎችን ይሰጠዋል፡፡ ነቢይ ለመላው ዓለም ህዝብ ከሰማዩ አባታችን መመሪያዎችን ማግኘት የሚችል ብቸኛ ሰው ነው፡፡

ዛሬ በህይወት የሚኖረው ነቢይ ታላቀ ሰው ነው፡፡ የሰማዩ አባታችንን ይወደዋል እናም እሱን መታዘዝ ይፈልጋል፡፡ የሰማዩ አባታችን እኛ እንድናውቀ እና እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገር ለነቢዩ ይነግረዋል፡፡

### *ውይይት*

- የሰማዩ አባታችን ዛሬም ነቢይን የላከው ለምንድ ነው?
- ነቢይ መመሪያዎችን የሚቀበለው ለማንነው?
- ነቢያት የሚነግሩንን ሁሉ ማመን ለምን እንችላለን?

## የሰማዩ አባታችን ለነቢይ የሰጠውን መመሪያዎች ስንታዘዝ ይረዳናል

የሰማዩ አባታችን ነቢይ ለእሱ ሲናገር ነቢዩን እንድንታዘዝ አዞናል፡፡ የሰማዩ አባታችን ለነቢይ የሰጠውን መመሪያዎች ስንታዘዝ፣ በይበልጥ እንደ ሰማዩ አባታችን እንዴት እንደምንሆን እንማራለን፡፡ ማድረግ የሚገባንን ነገሮች እንማራለን፡፡ ችግሮች ሲኖሩብን እንዴት እንደምናቃልላቸው እንማራለን፡፡ የሰማዩ አባታችን ሊረዳን ይችላል፣ እናም በልባችን ውስጥ ሰላምን ያኖርልናል፡፡

### *ውይይት*

- ነቢይ እንድናደርግ የሚነግረንን ነገሮች ማዳመጥ የሚገባን ለምንድነው?
- የሰማዩ አባታችን ነቢይ እንዲነግረን የሚመራውን ነገሮች ስናደርግ የሚረዳን እንዴት ነው?

### *ማጣቀሻ*

*ነቢይ ለሰማይ አባታችን የሚናገር ሰው ነው*

- ኦሪት ዘሁልቁ 12፥6 የሉቃስ ወንጌል 1፥70 (የሰማዩ አባታችን በነቢያት አማካኝነት ይናገራል፡፡)
- ትንቢተ ኤርሚያስ 1፥5–7 (የሰማዩ አባታችን ለነቢያቱ ምን እንደሚሉ ይነግራቸዋል፡፡)

*የሰማዩ አባታችን ዘወትር እኛን እንዲረዱን ነቢያትን ልኳል*

- አሞፅ 3፥7 (የሰማዩ አባታችን ሁል ጊዜ በነቢያቱ አማካኝነት ይናገራል።)
- ወደ ዕብራዊያን ሰዎች 1፥1 (የሰማዩ አባታችን፣ ጥንት በነቢያት አማካኝነት ለሰዎች ተናግሯል።)

*ዛሬም በምድር ላይ ነቢይ አለ*

- 2ኛ ኔፊ 3፥7–24 (የሰማይ አባታችን በኋለኛው ቀን ነቢያትን ለመምረጥ የተስፋ ቃል ገብቷል።)

*የሰማዩ አባታችን ለነቢይ የሰጠውን መመሪያዎች ስንታዘዝ ይረዳናል*

- ኦሪት ዘዳግም 18፥18–19 (ነቢያትን የማያዳምጡ አሁንም ነቢያት በሚያስተምሩት ይፈረድባቸዋል።)
- 3ኛ ኔፊ 28፥34 (የሰማዩ አባታችን የነቢያቱን ቃላት የሚቃወሙትን ከእሱ ጋር እንደገና እንዲኖሩ አይፈቅድም።)

# ቅዱሳን መጻሕፍት

*ምዕራፍ 10*

---

*የሰማይ አባታችን እኛን ለመርዳት አራት ቅዱሳን መጻሕፍትን ሰጥቶናል፡፡ የነዚህን አራት መፅሐፍቶች ስም ያውቃሉን?*

**የሰማዩ አባታችን የተቀደሱ ጽሑፎችን ለእኛ በመስጠት ፍቅሩን ያሳየናል**

የሰማዩ አባታችን እንድናውቀ የሚፈልገውን ነገሮች ነቢያተ እንዲጽፉ ነግሯቸዋል፡፡ እነዚህ ፅሁፎች ቅዱሳን መፃህፍት ይባላሉ፡፡ እነሱም በጣም የተቀደሱ ናቸው ምክንያቱም በእነሱ ውስጥ ያሉተ ነገሮች ከሰማዩ አባታችን የመጡ ናቸውና፡፡ ሰው ያለ ሰማዩ አባታችን ዕርዳታ መጻፍ ከሚችለው ከማንኛውም ነገር የበለጠ አስፈላጊ እና ታላቆች ናቸው፡፡

የሰማዩ አባታችን እኛን ለመርዳተ እነዚህን ፅሁፎች ሰጥቶናል፡፡ እነሱን በማንበብ የሰማዩ አባታችን ለእኛ ያለውን ታላቀ እቀድ መማር እንችላለን፡፡ ከመወለዳችን በፊተ ከእርሱ ጋር ስለ ነበረን ህይወተ መማር እንችላለን፡፡ ስለኢየሱስ ክርስቶስም መማር እንችላለን፡፡ ደስተኞችና እንደ ሰማዩ አባታችን እንድንሆን ማድረግ ያለብንን ነገሮች መማር እንችላለን፡፡

እነዚህ ፅሁፎች የሰማዩ አባታችን እንደሚወደን እና ተክክለኛውን ነገሮች እንድናደርግ እንደሚፈልግ ለመማር ይረዱናል፡፡ ስለ ሰማዩ አባታችን ስለተማሩ ሌሎች ሰዎች ይነግሩናል፡፡ እርሱ ሁሉንም ሰው እንደሚወድም ይነግሩናል፡፡ በእነዚህ ቅዱሳን መፅሃፍት እንደምናነበው ሰዎች የሰማዩ አባታችንን ለመታዘዝ ሲመርጡ፣ ደስተኞች ይሆናሉ፣ እናም ይረዳቸዋል፡፡ እርሱን ሳይታዘዙተ፣ ደስተኞች አይሆኑም፣ እናም የእርሱን እርዳታ አያገኙም፡፡

***ውይይት***

- ቅዱሳን መጽሀፍት ምንድን ናቸው?
- ከቅዱሳን መፅሀፍት ምን መማር እንችላለን?

**አራት ቅዱሳን መጽሐፍት አሉን**

አራቱ ቅዱሳን መጽሐፍት መጽሐፍ ቅዱስ፣ መጽሐፈ ሞርሞን፣ ትምህርትና ቃል ኪዳን፣ እና ታላቁ የክብር ዕንቁ ናቸው፡፡ ሁሉም የሰማዩ አባታችንን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል

ይዘዋል፡፡ ሁሉም የሰማዩ አባታችንን እና የኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛ ተምህርቶችን ያስተምራሉ፡፡

*መጽሐፍ ቅዱስ*

መጽሐፍ ቅዱስ ከአዳም ጊዜ አንስቶ የኢየሱስ ሐዋሪያት ሲኖሩ እስከነበረበት ጊዜ ለነበሩ ሰዎች የተሰጠ የሰማዩ አባታችንን ቃል ይዟል፡፡ እነዚህ ቃላትም ደግሞ ዛሬ እኛ እንድናጠናቸው እና እንድንከተላቸው ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ እነዚህም ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ናቸው፡፡

ብሉይ ኪዳን የሰማዩ አባታችን እንዴት ምድርን እንደፈጠረ እና በምድር ላይ የመጀመሪያዎቹን ወንድና ሴት እንደላከ ታሪኩ ይጀምራል፡፡ ብሉይ ኪዳን የብዙ ነቢያትን፣ እንደ ኖህ፣ አብርሐም፣ እስራኤል፣ ሙሴ፣ ኢሳያስ፣ እና ኤሊያስን ታሪክ ይዟል፡፡ ሰዎች ጥሩ ነገር ሲሰሩ የሰማዩ አባታችን እንዴት ይረዳቸው እንደነበር ታሪኩ ይናገራል፡፡ ሰዎች ነቢያትን ሳይሰሙ እና የሰማዩ አባታችንን ተምህርቶች ሳይታዘዙ ሲቀሩ የእርሱን እርዳታ ማግኘት እንደማይችሉም ይገልጻል፡፡

ሐዲስ ኪዳን የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛው ክፍል ነው፡፡ የኢየሱስን የልደት እና የምድር ላይ ህይወት ታሪኩን ይነግረናል፡፡ የኢየሱስን አንዳንድ መልካም ተምህርቶችና ለሰዎች ያለውን ፍቀር እናም እንዴት እንደረዳቸው የሚነግር ብዙ ታሪኮችን ይዟል፡፡ ከተከታዮቹ መሀከል ሐዋሪያትን እንዴት እንደጠራቸውና እንዳስተማራቸው እናም የእርሱን ሥራ እንዲሠሩ ስልጣን እንዴት እንደሰጣቸውም ይገልፃል፡፡ እርሱ ጌታ እንደነበር ተከታዮቹ አውቀዋል፡፡ በኋላም ጸሐፊዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብለው ጠርተውታል።

ሐዲስ ኪዳን ኢየሱስ ለሰዎች ሁሉ እንዴት እንደተሰቃየና እንደሞተ ይናገራል፡፡ ሐዲስ ኪዳን ሐዋሪያት ስለእርሱ ለሌሎች ሰዎች እንዴት እንዳስተማሩ፣ ኢየሱስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት ስለሚከሰቱ ነገሮች፣ በአለም መጨረሻ ስለሚፈፀሙ ታሪኮች ይናገራል፡፡

የዓለም ህዝቦች ሐዋሪያትን አልተቀበሉዋቸውም ነበር፣ ነገር ግን ሳቁባቸው፣ አሳደዱዋቸው፣ እናም ገደሉዋቸው፡፡ ሁሉም ሐዋሪያትና ነቢያት ሲሞቱ፣ የሰማዩ አባታችንን ቃላት ለመጻፍ የቀረ ማንም አልነበረም፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የተተረጎመ ከሆነ የሰማይ አባታችንን ቃላት ይዟል፡፡

*መጽሐፈ ሞርሞን*

መጽሐፈ ሞርሞን የሰማይ አባታችንን ተምህርቶች በአሚሪካ አህጉር ይኖሩ ለነበሩ ሰዎች የያዘ ነው፡፡ የዚህ መዝገብ ክፍሎች የተጻፉት ኢየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ 2.000 ዓመት በፊት ነበር፡፡ ሌላው ክፍል የተጀመረው ከኢየሱስ ክርስቶስ በፊት 600 አመት ገደማ እና የተፈጸመው 400 ዓመት ከተወለደ በኋላ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ የሰማዩ አባታችንን አስፈላጊ ተምህርቶችን ይዟል፡፡ መፅሐፈ ሞርሞን የተፃፈው በዚያን ጊዜ እና አሁንም ላሉ ሰዎች ኢየሱስ የአለም ሁሉ አዳኝ እንደሆነ እንደያውቁ ለመርዳት ነው፡፡

አብዛኛውን ጊዜ መፅሐፈ ሞርሞን ከኢየሩሳሌም ወደ አሜሪካ አህጉር ስለተጓዙ የሰዎች ስብስብ ይናገራል፡፡ እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ ከ 600 ዓመት በፊት ተጉዘው ነበር፡፡ ሌሂ በተባለ ነቢይና በልጁ ኔፊ ይመሩ ነበር፡፡ የኔፊ ሁለት ወንድሞች ክፉዎች እና አባታቸውን የማይታዘዙ ነበሩ፡፡ እነርሱም ሌማን እና ሌሙዬል ይባላሉ፡፡

ሌሂ ሲሞት፣ የቤተሰቡ አባላት በሁለት ቡድን ተለያዩ፡፡ ኔፊን የተከተሉት ኒፋይቶች ይባላሉ፡፡ ሌማንን የተከተሉት ሌመናይቶች ይባላሉ፡፡ እነዚህ ተንሽ ቡድኖች አድገው ታላቅ ህዝብ ሆኑ ኔፋይቶች እና ሌመናይቶች እርስ በእርሳቸው ብዙ ጦርነቶችን ተዋግተዋል፡፡ ትዕዛዙን የሚያከብሩትን ህዝቦች የሰማዩ አባታችን ይባርክና ይጠብቀ ነበር፡፡

የሰማዩ አባታችን በአሜሪካን አገር ያሉትን ህዝቦቹን እንዲመሩ እና እንዲያስተምሩ ብዙ ነቢያትን መርጦ ነበር፡፡ የአኗኗራቸው እና የትምህርታቸው ታሪክ በመጽሐፈ ሞርሞን ውስጥ ይገኛል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ነቢያት ጥቂቶቹ ኔፊ፣ ያዕቆብ፣ ብንያም፣ አልማ፣ ሞርሞን እና ሞሮናይ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ሁሉ በአሜሪካን ውስጥ ያሉ የሰማዩ አባታችን ህዝቦች ታሪክ ጽፈዋል፡፡ ሞርሞን በነቢያት የተጻፉትን እነዚህን መዝገቦች ወስዶ በአንድ መጽሐፍ ውስጥ በአንድነት አስቀመጠው፡፡

ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ውስጥ ስራውን ከጨረሰ በኋላ መሬታቸውን ሊጎበኝ እንደሚመጣ ለህዝቡ ነቢያት ይነግሯቸው ነበር፡፡ ኢየሱስም በአሜሪካ ላሉ መልካም ሰዎች ተገልጾ ነበር፡፡ *ወንጌሉን እና ከሞቱ በኋላ ወደ ሰማዩ አባታችን ለመመለስ ማድረግ የሚገባቸውን ነገሮችም አስተምሮአቸዋል፡፡

ህዝቦቹ ኢየሱስን አመኑት እናም ለብዙ አመታት ታዘዙት፡፡ መልካም ሰዎች ነበሩ እናም በሰላም ኖረዋል፡፡ ከዚያ በኋላ ስለ ኢየሱስ መርሳት ጀመሩ፡፡ ነቢያቶቻቸውንም ማዳመጥ አቆሙ፡፡ ክፉ ነገሮችን ብቻ ይሰሩ ነበር፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ የመጨረሻው ነቢይ፣ ሞርሞን፣ የህዝቡን፣ የኔፋይቶችን ታሪክ ለልጁ ለሞሮናይ ሰጠው፡፡ ህዝቦቹ ሁሉ ከሌመናይቶች ጋር በተደረገው ታላቅ ጦርነት ከተገደሉ በኋላ፣ ነቢያቱ ስለህዝቦቹ የጻፉትን ታሪክ በኮረብታ ውስጥ ሞሮናይ ቀበረው፡፡

ታሪኩ በኮረብታ ውስጥ ለመቶ ዓመታት ተቀብሮ ቀርቶ ነበር፡፡ በመጨረሻ፣ የሰማዩ አባታችን በ1820፣ ዮሴፍ ስሚዝን የእርሱ ነቢይ እንዲሆን መረጠው እናም ታሪኩ የተ እንደተቀበረ ለዮሴፍ ለማሳየት ሞሮናይን *ከሞት የተነሳን ፍጡር ላከው፡፡ ዮሴፍም ታሪኩን በእንግሊዝኛ ተርጉሞታል፡፡ ይህም መጽሐፈ ሞርሞን በመባል ዛሬ ይታወቃል፡፡

መጽሐፈ ሞርሞን የሰማዩ አባታችን በየተኛው ቦታ በምድር ላይ ያሉትን ህዝቦች እንደሚያውቁና እንደሚወድ ለማሳየት ተፅፏል፡፡ መጽሐፈ ሞርሞን ኢየሱስ በምድር ላይ ላሉ ሰዎች ሁሉ አዳኝ እንደሆነና የሰማዩ አባታችን ልጅ እንደሆነ ያስተምራል፡፡

*ትምህርትና ቃል ኪዳን*

ትምህርት እና ቃል ኪዳን በዚህ ዘመን ላሉ ህዝቦች የሰማዩ አባታችንን ቃላት ይዟል፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን ለማደራጀት መመሪያን ይዟል፡፡ የአባላቱን እና የመሪዎቹንም ተግባር ይገልጻል፡፡ ለአለም ህዝቦች ደግሞ ለረጅም ጊዜ ጠፍቶ የነበረውን ትምህርቶችም ይዟል፡፡ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችንም ይገልጻል፡፡

ትምህርትና ቃል ኪዳን ዛሬ በሕይወት ላለነው መልዕክት አለው፡፡ የሰማዩ አባታችንን የማንታዘዝ ከሆነ የሚመጡትን ነገሮች ያስጠነቀቀናል፡፡ ከታዘዝነው የሰማዩ አባታችን ስለአዘጋጀው አስደናቂ ነገሮችም ይነግረናል፡፡

*ታላቁ የክብር ዕንቁ*

ታላቁ የክብር ዕንቁ መጽሐፈ ሙሴን፣ መጽሐፈ አብርሐምን፣ እና የዮሴፍ ስሚዝን ታሪክ ይዟል፡፡

መጽሐፈ ሙሴ የሰማዩ አባታችን ለሙሴ የሰጠውን ራዕይ ይዟል፡፡ የምድርን አፈጣጠር ይገልጻል፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ የጠፉ ትምህርቶችን ይዟል፡፡

መጽሐፈ አብርሃም ስለምድር አፈጣጠርና ስለሰማዩ አባታችንና ሃይሉ ይናገራል፡፡

የዮሴፍ ስሚዝ ታሪክ የሰማዩ አባታችን ነቢይ እንዲሆን እንዴት እንደጠራው ይናገራል፡፡ ጥቂት የመጽሀፍ ቅዱስ ትርጉሞችንና ንግግሮችን የኋለኛው ቀዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እምነቶችንም ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ መግለጫዎች የዕምነት አንቀፆች ይባላሉ፡፡

በዛሬ ጊዜም በሕይወት ያለው የሰማዩ አባታችን ነቢይ የሰማዩ አባታችን የሚነግረውን ነገሮች ይፅፋል፡፡ የሰማዩ አባታችን ባለፉት ጊዜያት ብዙ ታላቀና አስፈላጊ ነገሮችን ነቢያት እንዲያውቁ አድርጓል፡፡ ዛሬም ለነቢዩ ታላቀና አስፈላጊ ነገሮችን እንዲያውቀ ማድረጉን ቀጥሏል፡፡

## ውይይት

- ዛሬ ያሉን አራቱ ቀዱሳን መጽሐፍት ምንድን ናቸው?
- እነዚህ ጽሑፎች እያንዳንዳቸው ለእኛ የሚያስፈልጉተ ለምንድነው?

## ቀዱሳን መጽሐፍትን ስናጠና የሰማዩ አባታችን ይረዳናል

በቀዱሳን መጽሐፍት፣ የሰማዩ አባታችን ወደ እርሱ እንድንመለስ ያለውን ዕቀድ ያስተምረናል፡፡ ቀዱሳን መጽሐፍትን በማጥናት እንድናውቀና እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገሮች መማር እንችላለን፡፡ ቀዱሳን መጽሐፍትን ካላጠናን፣ በውስጣቸው ምን እንዳለ ማወቀ አንችልም፡፡ የሰማዩ አባታችን ምን ማድረግ እንዳለብን እንደሚፈልግም አናውቀም፡፡

ቀዱሳን መጽሐፍትን በየቀኑ ማጥናት ያስፈልገናል፡፡ ለቤተሰቦቻችንም ደግሞ ከቀዱሳን መጽሐፍት ማንበብ ይገባናል፡፡ ቤተሰቦቻችን ቀዱሳን መጻህፍትን እንዲረዱ መርዳትም

ይገባናል፡፡ ለልጆቻችን እነዚህ የተቀደሱ መጽሐፍት ከሰማዩ አባታችን እንደመጡ ማስተማር ይገባናል፡፡ በእነዚህ መጽሀፍት ምን እንዳለና ስለእነሱ አመስጋኝ እንዲሆኑም እንዲያውቁ መርዳት ይገባናል፡፡

### *ውይይት*

- ቀዱሳን መጽሐፍትን ስናነብ የሰማዩ አባታችን የሚረዳን እንዴት ነው?

### *ማጣቀሻ*

*የሰማዩ አባታችን የተቀደሱ ጽሑፎችን በመስጠት ፍቀሩን ያሳየናል*

- 2ኛ ጢሞቲዎስ 3፥16–17 (የሰማዩ አባታችን እኛን ለመርዳት ቀዱሳን መጽሐፍትን ሰጥቶናል፡፡)
- 2ኛ ኔፊ 29፥3–13 (የሰማይ አባታችን ለሚታዘዙት ሁሉ ቀዱሳን መጽሐፍትን ይሰጣል፡፡)
- 2ኛ ኔፊ 33፥10 (ቀዱሳን መጽሐፍት የኢየሱስ ክርስቶስን ቃላቶች ይሰጡናል፡፡)

*አራት ቀዱሳን መጽሐፍት አሉን*


- 2ኛ ኔፊ 3፥12፣ 2ኛ ኔፊ 29 (የሰማዩ አባታችን ቀዱሳን መጽሐፍትን እንዲጽፉ ብዙ ነቢያትን አዟል፡፡)
- ትምህርትና ቃል ኪዳን 20፥9 (መጽሐፈ ሞርሞን ኢየሱስ ያስተማረውን ወንጌል ይዟል፡፡)


*ቀዱሳን መጽሐፍትን ስናጠና የሰማዩ አባታችን ይረዳናል*

- የዮሐንስ ወንጌል 5፥39 (ቀዱሳን መጽሐፍትን አጥኑ፡፡ ወደ ሰማዩ አባታችን ለመመለስ ይረዱናል፡፡)
- ሞርሞን 7 (ቀዱሳን መጽሐፍት ማወቀ የሚገባንን ነገሮች ያስተምሩናል፡፡)
- ሞሮናይ 10፥3–5 (መንፈስ ቀዱስ ቀዱሳን መጽሐፍት እውነት መሆናቸውን እንድናውቀ ይረዳናል፡፡)

# ለዳኛችን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ

ክፍል አራት





ለዳኛችን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በበረት ውስጥ ተወለደ፡፡

# የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት

## *ምዕራፍ 11*

*የኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማዩ ለባታችን እንድንመለስ ሊረዳን የሚችል ብቸኛ ሰው ነው፣ ስለእርሱ ምን ያውቃሉ?*

**ብዙ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት በታላቅ ጉጉት ይጠባበቁ ነበር**


ኢየሱስ ለዳኛችን ለመሆን ተሰጠ፡፡ ወደ ሰማዩ ለባታችን እንዴት መመለስ እንደምንችል ሊያሳየንም አመጣለሁ አለ፡፡ ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት ይኖሩ የነበሩ ብዙ ሰዎች ለዳኛቸው ለመሆን እንደሚመጣ ያምኑ ነበር፡፡ የእርሱን መምጣት ይጠባበቁ ነበር፡፡ ከኃጢያታቸው ቀጣት ሊያድናቸው እንደሚችልም ያውቁ ነበር፡፡

ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት ይኖሩ የነበሩ ነቢያት ሁሉ ኢየሱስ እንደሚመጣ ለህዝቦች ተናግረው ነበር፡፡ የሰማዩ ለባታችንም ኢየሱስ ወደ ምድር እንደሚመጣ ለለዳም እንዲነገር መላእክ ልኮ ነበር፡፡

ኢየሱስ ከመወለዱ ከብዙ ዓመት በፊት፣ ኢሳይያስ የተባለ ነቢይ ለሀጢያታችን ለመክፈል ኢየሱስ እንደሚሰቃይ በራዕይ ተመልክቶ ነበር፡፡ ኢሳይያስም ሰዎች ኢየሱስን ይጠሉታል አይቀበሉትም እናም ኢየሱስ ታላቅ ሀዘን ይሰማዋል ብሏል፡፡

በመጽሐፈ ሞርሞን ስለእርሱ የምናነበው ነቢይ፣ ኔፊ፣ ኢየሱስ የሚያደርገውን ነገሮች ተመልክቷል፡፡ እነዚህን ነገሮች ኔፊ የተመለከተው ኢየሱስ ከመወለዱ ከብዙ ለመት በፊት ነበር፡፡ ህጻኑን ኢየሱስን በእናቱ ክንድ ውስጥ አይቶታል፡፡ ለኔፊ ህጻኑ የሰማዩ ለባታችን ልጅ እንደሆነ መልዓኩ ነግሮታል፡፡

ብንያም ስለተባለ ነቢይ በመጽሐፈ ሞርሞን እናነባለን፡፡ እርሱም ኢየሱስ ፈጥኖ ወደ ምድር እንደሚመጣ ለህዝቦች ተናግሮ ነበር፡፡ ኢየሱስ ህሙማንን እንደሚፈውስ፣ ሽባ እንዲራመድ እንደሚያደርግ፣ እውር እንዲያይ እና ደንቆሮ እንዲሰማ እንደሚያደርግ ቢኒያም ነግሮአቸዋል፡፡ ርኩስ መንፈስ ያስወጣል እናም የሞቱ ሰዎችንም ወደ ህይወት ይመልሳል፡፡ ቢኒያምም ለህዝቦች የሰማዩ ለባታችንን እንዲወዱና እርስ በእርሳቸው እንዲፋቀሩ ኢየሱስ ያስተምራል ብሏል፡፡



*ኢየሱስ ልጅ እያለ፣ ለዋቂ ሰዎችን በቤተ መቀደስ ለስተምሯቸዋል፡፡*

የመጀመሪያው በካርል ብሎች በፍሬዲሪክስበርግ ህንጻ ጸሎት ቤት ግንብ፣ በዴንማርክ
በፍሬዲሪክስ በርግ ቤተመዘክር ፈቃድ ስራ ላይ ዋለ፡

ኢየሱስ ከተወለደ በኋላ የነበሩት ነቢያት ሁሉ እርሱ እንደሚመጣ ነግረውናል፡፡ ያለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰማዩ አባታችን ዕቀድ ውድቀ ይሆን ነበር፡፡

### ውይይት

• ኢየሱስ ወደ ምድር ለመምጣት የተሰጠው ለምን ነበር?
• እርሱ እንደሚመጣ የመሰከሩት ጥቂት ነቢያቶች እነማን ነበሩ?

## የኢየሱስ መወለድ ለዓለም ታላቅ ደስታን አስገኝቷል

ኢየሱስ የተወለደው ቤተልሄም በተባለች ትንሽ ከተማ ነበር፡፡ እርሱ ሲወለድ መላእክት ዘምረዋል ምክንያቱም በጣም ተደስተው ነበር፡፡ አንድ አዲስ ኮከብ በሰማይ ታይቷል፡፡ እረኞችና የጥበብ ሰዎች እርሱን ለማየትና ለማምለክ ሄደዋል፡፡ በመላው አለም ያሉ ብዙ ህዝቦች እስካሁን የልደቱን በአል ያከብሩታል፡፡

ኢየሱስ እስካሁን ከተወለዱት ሌሎች ህጻናት ሁሉ የተለየ ነበር፡፡ የኢየሱስ አባት የሰማዩ አባታችን ነበር፡፡ የሰማዩ አባታችን የኢየሱስ የመንፈስ አባቱ ብቻ አልነበረም ነገር ግን የስጋና አጥንቶቹ አካልም አባት ነው፡፡ ኢየሱስ ሌሎች ሰዎች የሌላቸውን ሀይል ከሰማዩ አባታችን ተቀብሏል፡፡ ሰዎች እርሱ ካልፈቀደ በስተቀር ህይወቱን መውሰድ አይችሉም፡፡ ከሞተ በኋላም፣ አካሉ ህይወት እንዲኖረው የማድረግ ሀይል አለው፡፡

የኢየሱስ እናት ማሪያም ነበረች፡፡ እሷም ከ 2,000 አመታት በፊት እስራኤል በተባለ ምድር ትኖር የነበረች ንፅሒት ወጣት ሴት ነበረች፡፡ ወጣት ድንግል፣ ልጃገረድ በነበረችበት ጊዜ፣ ሳታገባ፣ ከሰማዩ አባታችን መልአኩም ወደ እርሷ መጣ፡፡ መልአኩም የኢየሱስ ክርስቶስ እናት እንደምትሆን ነገራት፡፡ መልአኩ የሰማዩ አባታችን የኢየሱስ አባት እንደሚሆንም ነገራት፡፡ በምድር ላይ ማንም ሰው የእርሱ አባት አይሆንም አላት፡፡

መልአኩ ማሪያም ልታገባ ወደነበረው ሰውም መጣ፡፡ ሰውየውም ዮሴፍ ይባላል፡፡ መልአኩ ለዮሴፍ የሚወለደው ህጻን የሰማዩ አባታችን ልጅ እንደሚሆን እናም በምድር ላይ የማንኛውም ሰው ልጅ እንደማይሆን ነገረው፡፡ መልአኩ ማሪያምን ማግባት እንደአለበት ለዮሴፍ ነገረው፡፡ ስለዚህ ዮሴፍና ማሪያም ተጋብተው ነበር፡፡ ኢየሱስ ከተወለደ በኋላ፣ ዮሴፍ ኢየሱስን እንደልጁ አድርጎ ይጠነቀቅለት ነበር፡፡

እናቱ ሟች ሰው ስለሆነች፣ ኢየሱስም ረሀብ፣ ጥማት፣ እና ስቃይ ሊሰማው ቻለ፣ እናም ሊሞት ቻለ፡፡

### ውይይት

• የኢየሱስ መወለድ አስፈላጊ ነገር እንደነበር እንዴት እናውቃለን?
• ኢየሱስ ከአባቱ የተቀበለው ምን ሀይል ነበር?
• ኢየሱስ ምድራዊ እናት ስለነበረው ምን ዓይነት ነገሮች ይሰሙታል?

## ኢየሱስ ወንጌሉን ሊያስተምረን መጣ

*ኢየሱስ ኃጢያት የሌለበት ነበር*

ኢየሱስ ሐጢያት የሌለበት ነበር፡፡ የሰማዩ አባታችን እንዲያደርግ የሚፈልገውን ሁሉንም ነገር አድርጓል፡፡ ኢየሱስ ያደገው ሌሎች ህጻናት በሚያድጉበት ዓይነት ነው፡፡ እንዳደገም፣ ጥበብን አገኘ፡፡ የሰማዩ አባታችን ሀይልም ነበረው፡፡

ኢየሱስ የ12 አመት ልጅ በነበረበት ጊዜ፣ የሰማዩ አባታችን እንዲያደርግ የሚፈልገውን ነገሮች ለማድረግ እንደተላከ ያውቅ ነበር፡፡ በምድር ላይ ማከናወን ያለበት ልዩ የሆነ ስራ እንዳለው ያውቅ ነበር፡፡

አንድ ቀን ከማሪያም እና ከዮሴፍ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፡፡ ማሪያምና ዮሴፍ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፣ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር እንዳልነበረ ተመለከቱ፡፡ እርሱን ለመፈለግ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፡፡ ከሶስት ቀን በኋላ በቤተመቀደስ፣ ከጠቢባን ሰዎች ሲነጋገር እና ጥያቄያቸውን እየመለሰላቸው አገኙት፡፡ እርሱን የሰሙት ሁሉ ብዙ ስላወቀና ጥያቄያቸውን መመለስ ስለቻለ ተደንቀው ነበር፡፡ ዮሴፍና ማሪያምም ስላገኙት ተደስተው ነበር፣ ነገር ግን ከእነርሱ በመለየቱ ተከፍተው ነበር፡፡ ኢየሱስ የተለያቸው የሰማይ አባቱን ስራ መስራት ስላለበት እንደሆነ ነገራቸው፡፡

*ኢየሱስ *ተጠምቆ ነበር*

ኢየሱስ 30 አመት ሲሆነው፣ ለመጠመቀ ወደ መጥምቁ ዮሐንስ ሄደ፡፡ ኢየሱስ በፍጹም ሀጢያተኛ ባለመሆኑ ዮሐንስ እርሱን ማጥመቀ እንደማይገባው አስቦ ነበር፣ ነገር ግን ኢየሱስ ዮሐንስ እንዲያጠምቀው ነገረው፡፡ ኢየሱስ የሰማዩ አባታችንን ትዕዛዛት ሁሉ ማክበር ፈልጎ ነበር፡፡ ዮሀንስም ኢየሱስን፣ በውሀ ስር ሙሉ በሙሉ በማስገባት አጠመቀውና እንደገና አስነሳው፡፡ ኢየሱስ ሲጠመቀ፣ የሰማዩ አባታችን ከሰማይ ተናገረ እናም ኢየሱስ የእርሱ ልጅ እንደሆነና፣ የሰማዩ አባታችን፣ በእርሱ በጣም መደሰቱን ገለጸ፡፡ ኢየሱስ ሲጠመቀ መንፈስ ቀዱስም ወደ እርሱ መጥቶ ነበር፡፡

*ሰይጣን ኢየሱስን ፈተኖታል*

ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ፣ ብቻውን በመሆን ለመጾምና ለመጸለይ ወደ ምድረ በዳ ሄደ፡፡ ኢየሱስ ለ40 ቀናት ከጾመ በኋላ፣ ሰይጣን ሊፈትነው መጣ፡፡ ሰይጣን ኢየሱስን አንድ ሀጢያት እንኳ እንዲሰራ ሊያደርገው ቢችል፣ ኢየሱስ እንዲሰራ የተላከውን ነገሮች ለማድረግ እንደማይችል ያውቀ ነበር፡፡ ከዚያም የሰማዩ አባታችን ዕቀድ ይወድቀ ነበር፡፡

ኢየሱስ የሰይጣንን ፈተናዎች ሁሉ ተቋቁሞታል፡፡ በመጨረሻም፣ ሰይጣንን እንዲሄድለት ነገረው፡፡ ሰይጣን ከሄደ በኋላ፣ መላእክት መጡና ኢየሱስን ጉበኙት፡፡

*ኢየሱስ የሰማዩ አባታችንን እንድንወድና እርስ በእርሳችን እንድንዋደድ አስተምሮናል*

ሰይጣንን ከተቋቋመው በኋላ፣ ኢየሱስ ሰዎችን ማስተማር ጀመረ፡፡ ወደ ምድር የመጣበት አንደኛው ምክንያት እንዴት መኖር እንዳለብን ሊያስተምረን ነበር፡፡

የሰማዩ አባታችንን በሙሉ ልባችን፣ አእምሮአችን፣ እና ጥንካሬያችን መውደድ እንዳለብን ኢየሱስ አስተምሮናል፡፡ እራሳችንን እንደምንወድ ሌሎች ሰዎችን ደግሞ መውደድ እንዳለብንም አስተምሮናል፡፡ ሌሎች ሰዎችን ይቀር ማለትና ማገልገልም አለብን፡፡ እነዚህን ነገሮች እንዴት እንደምናደርግ ኢየሱስ አሳይቶናል፡፡ እሱ የሰማዩ አባታችን እንዲያደርግ የጠየቀውን ነገር ሁሉ በማድረግ ለሰማዩ አባታችን ያለውን ፍቀር አሳይቷል፡፡

*ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ይወዳል*

ኢየሱስ ለእያንዳንዱ ሰው ፍቀር ነበረው፡፡ ህሙማንን ፈውሷል፡፡ እውሩ እንዲያይ እና ሽባው እንዲራመድ አድርጓል፡፡ ህጻናት ልጆችን በክንዶቹ አቀፎ እና ባርኮአቸዋል፡፡

ኢየሱስ ኃጢአት ለሚሰሩትም ፍቀሩን አሳይቶአቸዋል፡፡ ለኃጢያቸው እንዲጸጸቱና ከዚያ ወዲህም ኃጢያተ እንዳይሰሩ አስተምሮአቸዋል፡፡ ኢየሱስ የገደሉተን እንኳይወዳቸዋል፡፡ ስለእነሱ ወደ ሰማዩ አባታችን ጸለየላቸው፡፡ ኢየሱስ እሱ እኛን እንደወደደን እርስ በእርሳችን እንድንዋደድ አስተምሮናል፡፡

## ***ውይይት***

- የሰማይ አባታችንን እንደምንወደው ለማሳየተ የምንሰራቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?
- ለሌሎች ያለንን ፍቀር ለማሳየተ ልናደርጋቸው የምንችለው አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?

*ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን አደራጅቷል*

ኢየሱስ ወደ ሰማዩ አባታችን መመለሻውን መንገድ ሰዎች ሁሉ እንዲያውቁተ ፈልጎ ነበር፡፡ መንገዱም ወንጌል ይባላል፡፡ ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን ያደራጀው ሁሉም ሰው ወንጌልን መማር እንዲችሉ ነው፡፡

ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን እንዲመሩ ሐዋሪያተ የተባሉ፣ አስራ ሁለተ ሰዎችን መርጧል፡፡ እሱ ወደ ሰማይ ከተመለሰ በኋላ እነሱ ወንጌልን ለሰዎች እንዲያስተምሩ ነበር፡፡ ኢየሱስ እሱን እንዲወክሉ ለአስራ ሁለቱ ሀዋርያተ ስልጣንን ሰጥቶአቸዋል፡፡ ለሁሉም ሰዎች ወንጌልን ማስተማርና እነሱን ለማጥመቀ ይችላሉ፡፡ ወንጌልን ለማስተማር እንዲረዱና እርሱ እንዲያደረግ የሚፈልገውን ነገሮች ሁሉ ለማድረግ ሌሎችን መምረጥም ይችላሉ፡፡

## ***ውይይት***

- ኢየሱስ አስራ ሁለተ ሀዋሪያተን የመረጠው ለምን ነበር?

## ስለ ኢየሱስ ስንማር፣ ምን ያህል ታላቅ ሰው እንደሆነ እንረዳለን

ኢየሱስ እያንዳንዳችንን እንዴት እንደምንኖር በማሳየት ረድቶናል። እርሱን መምሰልን ስንማር፣ ደስተኛ የሚያደርጉንን ነገሮች መስራት እንማራለን። ከሰማዩ አባታችን ጋር ወደ ሰማይ ተመልሰን ለመኖር የሚረዱንን ነገሮችም መማር እንችላለን።

ኢየሱስ እንደሚወደን ስናውቀ፣ ሰላም ይሰጠናል። ደህንነት እና ያለመፍራት ይሰማናል። መሪያችን በመሆኑ በእርሱ ልንመካ እንችላለን። ችግራችንን እንደሚያውቅ ልንረዳ መገንዘብ እንችላለን። ትምህርቶቹ ችግራችንን እንድናሸንፍ ይረዳናል። ኢየሱስ ለእኛ ያደረገልንን ሁሉ ስንረዳ፣ ለእርሱ ያለን ፍቀር ይጨምራል። ለእርሱ ያለን ፍቀር እርሱን መታዘዝን እንድንፈልግ ያደርገናል። ወደፊት ከእርሱ ጋር የምንሆንበትን ጊዜ በናፍቆት እንጠብቃለን።

### ውይይት

- ስለ ኢየሱስ መማር የሚረዳን እንዴት ነው?
- ስለ ኢየሱስ ሲማሩ ምን ይሰማዎታል?

### ማጣቀሻ

*ብዙ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት በታላቅ ጉጉት ይጠባበቁ ነበር*

- ትንቢተ ኢሳይያስ 53፡3–7 (ኢሳይያስ ስለ ኢየሱስ ተናግሯል።)
- ሞዛያ 3፡5–7 (ብንያም ኢየሱስ የሚያደርጋቸውን ነገሮች ተናግሮአል።)

*የኢየሱስ መወለድ ለዓለም ታላቅ ደስታን አስገኝቷል*

- የሉቃስ ወንጌል 2፣ 3ኛ ኔፊ 1 (የኢየሱስ ልደት።)

*ኢየሱስ ወንጌሉን ሊያስተምረን መጣ*

- የማቴዎስ ወንጌል 3፡15–17 (ኢየሱስ ተጠምቋል።)
- የማቴዎስ ወንጌል 4፡1–11 (ኢየሱስን ሰይጣን ፈተኖታል።)
- የማቴዎስ ወንጌል 25፡35–46፣ የዮሐንስ ወንጌል 15፡12 (ኢየሱስ ሌሎችን እንድንረዳ ይፈልጋል።)
- የማርቆስ ወንጌል 1፡34፣ የማቴዎስ ወንጌል 14፡14 (ኢየሱስ የታመሙ ሰዎችን ፈውሷል።)
- የሉቃስ ወንጌል 2፡40 (ኢየሱስ ሕጻን እያለ እንኳ፣ ብልህ ሆኖ አደገ።)
- የሉቃስ ወንጌል 2፡46–47 (ኢየሱስ የተማሩ ሰዎችን በቤተመቀደስ አስተምሯቸዋል።)
- ዮሐንስ 8፡28–29 (ኢየሱስ የሰማዩ አባታችን እንዲያደርግ የሚፈልገውን ነገሮች አድርጓል።)

*ስለ ኢየሱስ ስንማር፣ ምን ያህል ታላቅ ሰው እንደሆነ እንረዳለን*

- ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ (የኢየሱስ ህይወትና ትምህርቶቹ።)

# የኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ክፍያ

*ምዕራፍ 12*

---

*ኢየሱስ በኃጢአታችን ምክንያት በሀይል ተሰቃይቷል፡፡ ለምን ነበር ለእኛ መሞትን የመረጠው?*

**የሰማይ አባታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛችን እንዲሆን ወደ ምድር ላከው**


የሰማዩ አባታችንን ለመምሰል የስጋና አጥንቶች አካል ሊኖረን ያስፈልጋል፣ ነገር ግን አዳምና ሔዋን የሰማዩ አባታችንን ባለመታዘዛቸው ምክንያት እንደምንሞትና አካላችንን እንደምናጣ የሰማዩ አባታችን ያውቃል፡፡ የሰማዩ አባታችን አትብሉ ያላቸውን ፍሬ በመብላታቸው፣ እነርሱ፣ እና ከእነርሱ በኋላ የሚወለዱት ሰዎች በመጨረሻ ይሞታሉ፡፡ የሰማዩ አባታችን በምድር ላይ እያለን ሁላችንም ሐጢያት እንደምንሰራ ያውቃል፣ እናም በኃጢያታችን ምክንያት ተመልሰን ከእርሱ ጋር ለመኖር አንችልም፡፡ ስለዚህ ለኃጢያታችን ክፍያ መቀጫ እና ታዛዥ ለመሆን ወደ ሰማይ አባታችን መመለስ እንድንችል እርዳታ ያስፈልገናል፡፡ ከሞት በኋላ የሥጋና አጥንቶች አካል እንደገና ለማግኘት እርዳታ ያስፈልገናል፡፡ ኢየሱስም እንደሚረዳን ተናግሯል፡፡ እርሱ አዳኛችን ይሆናል፡፡

ለኃጢአታችን መስዋዕት ለመክፈል ኃጢአት የሌለበትን ሰው እንፈልግ ነበር፡፡ ኢየሱስ ይህን ለማድረግ የሚችል ብቸኛ ሰው ነበር፡፡ ኃጢአትን አልሰራም፡፡ እርሱ በሞት ላይ ሀይል አለው፣ ስለዚህም ከሞት በኋላ ዳግመኛ አካል እንዲኖረን ሊረዳን ይችላል፡፡ እርሱ እኛን በጣም ይወደናል፡፡ ለኃጢያታችን ለመሰቃየት ፈቃደኛ ነበር፣ ስለዚህም ከኃጢያታችን ንጹህ መሆን ችለናል፡፡ ለእኛ ለመሞትም ፈቃደኛ ነበር ሰለዚህም ከሞት በኋላ ወደ ህይወት ለመመለስ ችለናል፡፡ የኢየሱስ መስዋዕት ለእኛ የኃጢአት ክፍያ ይባላል፡፡

### *ውይይት*

- የሰማዩ አባታችን ኢየሱስን ወደዚህ ምድር መላኩ አስፈላጊነቱ ለምንድን ነበር?

---



*በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ ኢየሱስ፣ የሰው ዘርን ሁሉ ሐጢያት በላዩ ላይ ተሸከመ።*

## የኢየሱስ ስቃይ እርሱና የሰማዩ አባታችን ምን ያህል እንደሚወዱን ያሳየናል

የሰማዩ አባታችን በጣም ስለሚወደን ልጁን፣ ኢየሱስን፣ ወደ ምድር ላከው፣ እናም ለእኛ እንዲሰቃይና እንዲሞት ፈቀዶለታል፡፡ ኢየሱስም በጣም ስለሚወደን ለእኛ በታላቀ የህመም ስቃይ ሞቶልናል፡፡ ኢየሱስ ስቃዩ ታላቀ እንደሚሆን ያውቀ ነበር፡፡ መሸከም ከሚችለው በላይም ነበር፡፡ ነገር ግን እኛ እንደ የሰማዩ አባታችን መሆን እንድንችል ይፈልግ ነበር፡፡

ኢየሱስ ጌተሰማኒ ወደሚባል የአተክልተ ስፍራ ሄደ፡፡ እዚያም የሰማዩ አባታችን እንዲረዳው ተንበረከከና ጸለየ፡፡ የሚቻል ከሆነ፣ ከስቃይ እንዲያድነው የሰማዩ አባታችንን ጠየቀው፡፡ ነገር ግን የሰማዩ አባታችን እንዲያደርግ የሚፈልገውን አደርጋለሁ አለ፡፡ ኢየሱስ እንዲሰቃይ አልተገደደም፡፡ ምክንያቱም ይሄ የሰማዩ አባታችን የእቅዱ ክፍል ስለነበር፣ በዚህም ከኃጢያታችን መንጻት እንድንችል እርሱ ለመሰቃየተ መርጧል፡፡

በጌተሰማኒ፣ የእርሱ የራሱ እንደሆኑ በመቁጠር ኢየሱስ ለሰው ዘር ሁሉ ኃጢያተ ተሰቃይቷል፣ ለዚህ ሁሉ ኃጢያተ የእርሱ ስቃይ ማናችንም ልንረዳው ከምንችለው በላይ ነበር፡፡ ህመሙ ታላቀ ስለነበር ተንቀጠቀጠ፡፡ ከሰውነቱ ቀዳዳ ሁሉ ደም ይወጣም ነበር፡፡

በኋላም፣ ክፉ ሰዎች መጥተው ወደ ኢየሩሳሌም ገዢዎች ወሰዱት፡፡ እዚያም ተፋበት እናም መቱት፡፡ የእሾህ አክሊል ሰሩና በራሱ ላይ ደፋበት፡፡ በእርሱ ላይ ተሳለቁበተ እናም ቀለዱበት፡፡

ገዢዎቹም ኢየሱስን እንዲሰቀሉተ ለወታደሮቹ ነገሯቸው፡፡ ወደሚሞተበተ ቦታ ከባድ የእንጨተ መስቀል እንዲሸከም አደረጉተ፡፡ በእጆቹና በእግሮቹ ሚስማር በመቸንከር በመስቀል ላይ ሰቀሉተ፡፡ የአዳምን አለመታዘዝና የእኛን የሀጢያተ ቀጣተ ስቃይ በመስቀል ላይ ጨረሰው፡፡

ስለዚህ በመስቀል ላይ ለብዙ ሰዕታተ ተሰቅሎ ተተወ፡፡ ምንም እንኳ እየተሰቃየ ቢሆንም፣ ምንም እንኳ አንዳንድ ሰዎች ቢቀልዱበተም፣ ዝምተኛና ተዕግስተኛ ነበር፡፡ በመጨረሻም ለሰማዩ አባታችን ነፍሱን ወደ እርሱ እንዲመልሳተ ነገረው፣ እናም ሞተ፡፡


ኢየሱስ እራሱን ከሞተ ለማዳን ሀይል ነበረው፡፡ በህይወተ ለመኖር ይችል ነበር፣ ነገር ግን መሞተን መረጠ፣ በዚህም ከሰማዩ አባታችን ጋር ተመልሰን መኖር እንችል ዘንድ፡፡

ኢየሱስ ሲሞተ፣ ነፍሱ ከስጋው ተለየች፡፡ ከሞተ በኋላ በሶስተኛው ቀን፣ ነፍሱ ወደስጋው ተመለሰች፣ እናም እንደገና ሕያው ሆነ፡፡ የነፍስ ወደ ስጋ መመለስ ትንሳኤ ይባላል፡፡

ኢየሱስ ከትንሳኤ በኋላ ለሐዋሪያቶቹና ለሌሎች ሰዎች ታይቶ ነበር፡፡ ለሐዋሪያቶቹ በእጆቹና በእግሮቹ የቀሩተን የሚስማሮቹን አሻራ አሳይቶአቸዋል፡፡ እነርሱም ዳሰሱተ እናም ወደ ህይወተ የተመለሰው፣ መሪያቸው፣ ኢየሱስ፣ እንደነበረ አውቀውታል፡፡ ከእነርሱ ጋር ተነጋግረዋል እናም ከነሱ ጋር ተመግቧል፡፡

### ውይይት

- የሰማዩ አባታችን ለእኛ ያለውን ፍቀር ያሳየን እንዴተ ነው?
- ኢየሱስ ለእኛ ያለውን ፍቀር ያሳየን እንዴተ ነው?



ኢየሱስ ለህዝቦች ሁሉ ኃጢአት በመስቀል ላይ ሞተ፡፡

## ኢየሱስ ከኃጢአታችን መንጻት እንድንችል አመቻችቶልናል

ኢየሱስ ብቻ ለኃጢአታችን ዋጋን መክፈል ችሎአል። እርሱ እንደሚኖር በማመንና ትዕዛዛቱን በመጠበቅ የእርሱን ስቃይ ለእኛ ጠቃሚ አድርጎታል። ለኃጢያታችን ማዘን ይገባናል። ከዚያም ወዲህ ተመልሰን መስራት የለብንም። የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቶች መከተል አለብን። ከዚያም የሰማዩ አባታችን ኃጢያታችንን ይቀር ይለናል።

### *ውይይት*

- ኃጢአተዎን ለማሸነፍ ኢየሱስን ለምን ፈለጉ?
- የኢየሱስ የኃጢአት ክፍያ ለእርስዎ መከፈል እንዲችል ለማድረግ የሚያስፈልግዎ ምንድነው?

## ኢየሱስ ሁላችንም ዳግም አካላችንን ማግኘት እንድንችል አመቻችቶልናል

ኢየሱስ በፈቃደኝነት ሞተ እናም ለትንሳኤም የመጀመሪያ ሰው ነበረ። እራሱን ለማስነሳት ሀይል የነበረው ብቸኛ ሰው ነበረ። እኛም ትንሳኤን እንድናገኝ አመቻችቶልናል።

ምንም እንኳ ብንሞት፣ ዳግም እንኖራለን። ስንሞት ነፍሳችን ከአካላችን ተለያለች። ነገር ግን ኢየሱስ ሞትን ካሸነፈበተ ጀምሮ፣ ነፍሳችን እና አካላችን ዳግም ባንድነት ይገጣጠማሉ። ለዘለአለም ይኖራሉ። ዳግመኛ በፍጹም አንሞትም። ይሄ ኢየሱስ ለእያንዳንዱ በምድር ላይ ለተወለደው የሰጠው ነፃ ስጦታ ነው።

### *ውይይት*

- ኢየሱስ እኛ አካላችን ዳግም ማግኘት እንድንችል ያመቻቸው እንዴት አድርጎ ነው?
- የሚነሳው ማነነው?

### *ማጣቀሻ*

*የሰማዩ አባታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን እንዲሆን ወደ ምድር ላከው*

- ማቴዎስ ወንጌል 16፥21 (ኢየሱስ ለሐዋሪያቶቹ እንደሚሞት እና እንደሚነሳ ነግሯቸዋል።)
- አልማ 34፥9–16 (ለኃጢያታችን መክፈል የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው)

*የኢየሱስ ስቃይ እርሱና የሰማዩ አባታችን ምን ያህል እንደሚወዱን ያሳየናል*

- የሉቃስ ወንጌል 22፥39–46 (የኢየሱስ ታሪክ በጌተሰማኒ የአተክልተ ሥፍራ።)
- የዮሐንስ ወንጌል 3፥16 (የሰማዩ አባታችን በጣም ስለሚወደን እንዲያድነን ኢየሱስን ላከው።)

*ኢየሱስ ከሐጢአታችን መንጻት እንድንችል ለመቻቸቶልናል*

- ወደ ሮሜ ሰዎቾ 5፥12–17 (ኢየሱስ ባደረጋቸው ነገሮች አማካኝነት የትንሳኤን ስጦታ እናገኛለን።)
- 1ኛ ቆሮንቶስ 15፥21–22 (ሞት በአዳም ምክንያት መጣ፣ ትንሳኤ በኢየሱስ ምክንያት መጣ።)

- 1ኛ ጴጥሮስ 1፥18–20 (በኢየሱስ ደም መፍሰስ ድነናል፡፡)
- 1ኛ ዮሐንስ 1፥2 (ኢየሱስ ከሐጢአታችን ሁሉ መንጻት እንድንችል ለመቻቻቷል፡፡)
- 2ኛ ኔፊ 2፥21–22 (ትዕዛዛቶቹን የምናከብር ከሆነ፣ የኢየሱስ ስቃይ ያድነናል፡፡)
- ሔለማን 14፥15–18 (ኢየሱስ ሞቶልናል ስለዚህም ዳግም መኖር እንችላለን፡፡)
- ሞርሞን 9፥12–14 (ትንሳዔ ሞትን እንድናሸንፍ ፈቀዶልናል፡፡)

*ኢየሱስ ሁላችንም ዳግም አካላችንን ማግኘት እንድንችል ለመቻቻቶልናል*

- ዮሐንስ 5፥28–29 (ሁላችንም በትንሳኤ እንነሳለን፡፡)
- አልማ 11፥40–45 (አካል ወደ ራሱ ትክክለኛ ቀርጽ ሊመለስ ይችላል፡፡

# የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል

ክፍል አምስተ





*ወደ ሰማዩ አባታችን ለመመለስ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ዕምነት ሊኖረን ይገባል።*

# እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ

*ምዕራፍ 13*

---

*ምንም እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስን ባናየውም በእርሱ እንዴት ማመን እንችላለን?*

**በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንና በእርሱ መታመን እንችላለን**

እምነት ማለት በማናየው ሰው ወይም ነገር ማመን ማለት ነው፣ እናም በዚያ እምነት መሰረት በድርጊቱ መጠን እናደርጋለን፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ገበሬ ዘር ዘርቶ ለዘሩ እንክብካቤ ካደረገ ተክሎቹ እንደሚያድጉ እምነት አለው፡፡ ስለዚህ ዘሮችን ይዘራል እናም ውሃ ያጠጣቸዋል እናም ይንከባከባቸዋል፡፡ ይህን ሲያደርግ፣ ተክሎቹ ያድጋሉ እናም ምግብን ይሰጡታል፡፡

በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ማለት፣ እርሱ እንደሚኖር እናምናለን ባናየውም እንኳ እንታዘዘዋለን። እነዚህ በኢየሱስ እምነት ሲኖረን የምናምናቸው ጥቂት ነገሮች ናቸው፣

1. የሰማዩ አባታችንን እቅድ ለመከተል እንዲረዳን የሰማዩ አባታችን ኢየሱስን እንደመረጠው እናምናለን፡፡
2. ኢየሱስ አዳኛችን እንደሆነ እናምናለን፡፡
3. የሰማዩ አባታችን ልጅ በመሆን በዚህ ዓለም ላይ ተወልዶ እንደነበር እናምናለን፡፡
4. ወደ ሰማዩ አባታችን እንዴት እንደምንመለስ ሊያስተምረን ወደ ምድር እንደመጣ እናምናለን፡፡
5. እንደሚወደን እናምናለን፡፡
6. ለኃጢአታችን እንደተሰቃየ እናምናለን ስለዚህ ንስሀ መግባት እንችላለን እናም ስለእርነሱ መቀጣት አይኖርብንም፡፡
7. በሞቱ እና በትንሳኤው እናምናለን፡፡
8. ተምህርቶቹ እውነት እንደሆኑ እናምናለን፡፡
9. ኢየሱስን ከታዘዝን ከሰማዩ አባታችን ጋር ተመልሰን መኖር እንደምንችል እናምናለን፡፡

በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ወደ ሰማዩ አባታችን መመለስ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በእርሱ እምነት ሲኖረን፣ እናምነዋለን እናም ስለ እርሱ ለመማር እንፈልጋለን፡፡ ወደ ሰማዩ

---

አባታችን መርቶ ሊመልሰን የሚችለው አንድ ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡ በኢየሱስ ያመኑትና የሚታዘዙት ብቻ ተመልሰው ከሰማዩ አባታችን ጋር መኖር ይችላሉ፡፡

### ***ውይይት***

- እምነት ምንድነው?
- እምነት በኢየሱስ ማለት ምን ማለት ነው?
- ስለ ኢየሱስ የምናምናቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?
- በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ሊኖረን የሚያስፈልገው ለምንድነው?

## ኢየሱስ በእርሱ ያለንን እምነት የምናሳድግበት መንገድ ሰጥቶናል

ኢየሱስ ስለ እርሱ እንዴት መማር እንደምንችልና በእርሱ እንዴት እምነት ሊኖረን እንደሚችል ነግሮናል፡፡ ቅዱሳን መጻሕፍትን እንድናነብና ነቢያት ስለ እርሱ የጻፉትን እንድንማር ነግሮናል፡፡ በአሁኑ ወቀት በህይወት ያሉትን ነቢይ እንድናዳምጣቸው ጠይቆናል፡፡ እነዚህን ነገሮች ስናደርግ፣ ስለ ኢየሱስ ይበልጥ እንማራለን፡፡

ስለ ኢየሱስ ስንማር፣ መጸለይ ይገባናል፡፡ የሰማዩ አባታችንን ስለ ኢየሱስ ያነበብነውን እና የሰማነውን እንዲረዳን መጠየቅ ይገባናል፡፡ የሰማዩ አባታችን ስለተማርናቸው ነገሮች እንዲረዳን መንፈስ ቅዱስን ይልካል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ የሰማዩ አባታችን ልጅ እና፣ አዳኛችን እንደሆነ፣ ትምህርቶቹ እውነት እንደሆኑ ይነግረናል፡፡

አልማ የተባለው ነቢይ የሆነ ነገር እውነት እንደሆነ ማወቀ ከፈለግን፣ ልንፈትነው ይገባል ብሏል፡፡ ይህንንም ዘርን ከመዝራት ጋር ያወዳድረዋል፡፡ ጥሩ ዘርን ከዘራንና ከተንከባከብነው፣ ያድጋል፣ እናም ጥሩ ዘር እንደነበርም እናውቃለን፡፡ ዘሩ ካላደገ፣ መጥፎ ዘር እንደነበር እናውቃለን፡፡ የኢየሱስ ትምህርቶች እውነት መሆናቸውን ማወቀ ከፈልግን፣ ልናጠናቸውና ልንታዘዛቸው ይገባል፡፡

እምነት በኢየሱስ ማለት በእርሱ እናምናለን ከማለት የበለጠ ነው፡፡ ማለትም በእርሱ በሀይል በመታመን እንድናደርግ የሚያዘንን ሁሉ ለመታዘዝ እንፈልጋለን፣ ማለት ነው፡፡ ኢየሱስን በእውነት የሚታዘዙት ብቻ በእርሱ እምነት አላቸው፡፡ እና እርሱን ስንታዘዘው፣ በእርሱ ያለን እምነት ጠንካራ ይሆናል፡፡ የእርሱ ትምህርቶችም ከሰው ሳይሆን፣ ከሰማዩ አባታችን እንደመጡ እንማራለን፡፡

ኢየሱስን የማንታዘዝ ከሆነ፣ እምነታችን ደካማ ይሆናል፡፡ እንድናደርግ ያዘዘንን ነገሮች ስናደርግ፣ እምነታችን በጥንካሬ ያድጋል፡፡ እርሱ እንዳለ እርግጠኛ እውቀት እስኪኖረን ድረስ እምነታችን ልክ እርሱን በእርግጥ ማየት እንደምንችል፣ በጥንካሬ ሊቀጥል ይችላል፡፡

### ***ውይይት***

- ኢየሱስን ባናየውም እንኳ በእርሱ እምነት እንዴት ሊኖረን ይችላል?
- በኢየሱስ እምነት እንዲኖረን እርሱን መታዘዝ ያለብን ለምንድነው?

## በኢየሱስ እምነት ሲኖረን ታላቅ እውቀትና ሀይልን ማግኘት እንችላለን

በቅዱሳን መጻሕፍት ስለ ነቢያቶች እንደምናነበው በኢየሱስ ጠንካራ እምነት እንደ ነበራቸው ነው። ይህ እምነት ሕዝቦቻቸውን እንዲረዱ ሀይል ሰጥቶአቸዋል። በኢየሱስ እምነት ስለነበራቸው፣ በራሳቸው ለማድረግ የሚችሉትን ነገሮች ማድረግ ሀይል ነበራቸው።

ኢየሱስ በምድር ላይ ከመወለዱ በፊት፣ የሰማዩ አባታችን ኖህ ለተባለው ነቢይ መርከብ እንዲሰራ እንዲመራው አዘዘው፣ ምክንያቱም በኖህ ጊዜ የነበሩት ክፉ ሰዎች ንስሀ የማይገቡ ከሆነ የሰማዩ አባታችን ታላቅ ጎርፍ እንደሚልክ ነገረው። ሰዎቹ ንስሀ አልገቡም ነበር። ኖህ ኢየሱስን አመነው እና መርከብንም ሠራ። ጎርፍ ሲመጣ ንስሀ ያልገቡት ሰዎች ሁሉ ሞቱ፤ ነገር ግን ኖህና ቤተሰቡ በመርከብ ውስጥ በደንብ ተጠብቀው ዳኑ፣ ምክንያቱም ኢየሱስን አምነውት እናም እርሱ ያላቸውን ሰርተው ነበርና።

ሙሴ ሕዝቦቹን ከባርነት አውጥቶ የመራ ነቢይ ነው። የሰማዩ አባታችን ሙሴን እንዲረዳው ኢየሱስን ላከው ምክንያቱም ሙሴ በኢየሱስ ያምን ነበር እና ኢየሱስ እንዲያደርግ የነገረውን ነግሮች ሁሉ አድርጓል።

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበርበት ጊዜ፣ በእርሱ ታላቅ እምነት ያላት ሴት ነበረች። ለረጅም ጊዜ ታማ ነበር፣ እና የኢየሱስን ልብስ ብቻ መንካት ብትችል፣ እንደምትፈወስ ታምን ነበር። ኢየሱስ ሰዎች በተሰበሰቡበት ይሄድ ነበር። ከተሰበሰቡት መኸከል ወደ እርሱ ተጋፋች እና ልብሱን ነካቸው። ወዲያውኑም ተፈወሰች። ኢየሱስም እምነቷ እንዳዳናት ነገራት።

ነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ነበረው። በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ የሰማዩ አባታችን ጸሎታችንን ካመንን እንደሚመልስልን እንደሚመልስልን አነበበ። ዮሴፍ ወደ ሰማዩ አባታችን ጸለየ። የሰማዩ አባታችንና ኢየሱስ ለዮሴፍ ተገለጹለት። የሰማዩ አባታችን ለዮሴፍ ኢየሱስን እንዲሰማው ኢየሱስ የነገረውን እንዲታዘዝ ነገረው። ዮሴፍም ኢየሱስን ታዞታል፣ እናም ስለዚህ መጽሀፈ ሞርሞንን ለማግኘትና የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን እንዲመለስ ለመርዳት ችሏል።

እኛ ደግሞ በኢየሱስ እምነት ካለን ይረዳናል። በችግሮቻችንም ይረዳናል። ተስፋ ስንቆርጥም እንዲሁ ይረዳናል። ሐጢያተንም እንድናሸንፍ ይረዳናል። ቤተሰቦቻችንና ሌሎች ሰዎችን ለመርዳት እንችላለን።

በኢየሱስ እምነት ሲኖረን፣ የሰማዩ አባታችንን ዕቅድ መከተል መጀመራችን ነው። ወደ ሰማዩ አባታችን መርቶ የሚመልሰንን ነገር በማድረግ መኖር እንጀምራለን። ከቀጠልንበተም፣ አንድ ቀን ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም ለመኖር እንችላለን።

### *ውይይት*

- በኢየሱስ እምነት ሲኖረን ምን አይነት እውቀትና ሀይል ሊኖረን ይችላል?

## *ማጣቀሻ*

*በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንና በእርሱ መታመን እንችላለን*

- የዮሐንስ ወንጌል 14፥6 (ወደ ሰማዩ አባታችን የምንመለስበትን መንገድ ሊያሳየን የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው።)
- የሐዋሪያት ስራ 4፥12 2ኛ ኔፊ 2፥9 9፥23 ሞዛያ 3፥12 (ከሀጢያታቸው ሊድኑ የሚችሉት በኢየሱስ እምነት ያላቸው ብቻ ናቸው።)
- ዕብራዊያን 11፥1፣ አልማ 32፥21 (እምነት መኖር ማለት በማናየው ነገር ማመን ማለት ነው።)
- ዕብራዊያን 11፥6 (ያለ እምነት፣ የሰማዩ አባታችንን ማገልገል አንችልም።)
- ሞዛያ 4፥10–11 (በኢየሱስ እምነት ሊኖረን ይገባል።)

*ኢየሱስ በእርሱ ያለንን ዕምነት የምናሳድግበት መንገድ ሰጥቶናል*

- የዮሐንስ ወንጌል 5፥39 (ቅዱሳን መጻህፍት ስለኢየሱስ ይመሰክራሉ፣ ስለዚህ እነሱን ማጥናት አለብን።)
- የዮሐንስ ወንጌል 7፥16–17 (ኢየሱስ እንድናደርግ የነገረንን ነገሮች ካደረግን፣ የእሱ ትምህርቶች እውነት እንደሆኑ እናውቃለን።)
- 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥3 (በኢየሱስ እምነት እንዲኖረን መንፈስ ቅዱስ ይረዳናል።)
- የያዕቆብ መልዕክት 2፥17 (ኢየሱስ እንድናደርግ የነገረንን ነገሮች በማድረግ በእሱ እንደምናምን እናሳያለን።)
- አልማ 32፥27–39 (ኢየሱስን ለመታዘዝ ከሞከርን፣ ትምህርቶቹ መልካም እንደሆኑ እናውቃለን።)

*በኢየሱስ እምነት ሲኖረን ታላቅ እውቀትና ሀይልን ማግኘት እንችላለን*

- የሉቃስ ወንጌል 8፥43–48 (ኢየሱስ በሱ ላይ ባላት እምነት ምክንያት አንዲት ሴትን ፈውሷል።)
- ዕብራዊያን 11 (ኢየሱስ በእምነታቸው ምክንያት ብዙ ሰዎችን አረድቷቸዋል።)

# ንስሐ

*ምዕራፍ 14*

*ስህተትን ስናደርግ እንድናዝን ያደርገናል፡፡ ስህተት የሆነ ነገርን ካደረግን በኋላ እንዴት እንደገና ደስተኛ መሆን እንችላለን?*

**የሰማይ አባታችን ኃጢአትን የምናሸንፍበትን መንገድ አቀዶልናል**

የሰማዩ አባታችን በምድር ላይ ሁላችንም ስህተተን እንደምናደርግ ያውቃል፡፡ የምናደርጋቸው ስህተቶች ሀጢያቶች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር እንዳናደርግ የነገርንን ነገሮች ስናደርግ ሀጢያት እንሰራለን፡፡ እግዚአብሔር እንድናደርግ የነገረንን ነገሮችም ሳናደርግ ስንቀር ሀጢያቶችን እንሰራለን፡፡

የሰማዩ አባታችን ኃጢአተን አያደርግም፣ እናም ኃጢአተ የሚሰሩ ሰዎች ከእርሱ ጋር እንዲኖሩም አይፈቀድም፡፡ ከእርሱ ጋር ለመኖር ለሀጢያታችን ንስሃ መግባት አለብን፡፡ ንስሃ መግባት ማለተ ስለሀጢያታችን ማዘንና ሀጢያተ ማድረግን ማቆም ማለተ ነው፡፡

የሰማዩ አባታችን ይወደናል፡፡ ሀጢያታችን ወደ እርሱ ከመመለስ እንዲከለክለን አይፈልግም፡፡ ስለዚህም እኛን የሚረዳበተን መንገድ አቀዷል፡፡

የሰማዩ አባታችን ኢየሱስን ለሀጢያታችን ንስሃ እንድንገባ እንዲረዳን ላከው፡፡ ኢየሱስ ሀጢያተን ለማስወገድ ማድረግ ያለብንን ነገሮች አስተምሮናል፡፡ እነዚህን ነገሮች እንድናደርግም ብርታተ ይሰጠናል፡፡ በእርሱ ስናምንና ስንከተለው፣ ልቦቻችንን ይለውጠዋል ስለዚህም ሀጢያተ ለማድርግ እንኳ አንፈልግም፣ ነገር ግን መልካም ነገር ብቻ ማድረግ እንፈልጋለን፡፡ ለሀጢያታችን መሰቃየተ የማንፈልግ ከሆነ፣ በኢየሱስ ማመን አለብን፡፡ በኢየሱስ በዕውነተ የሚያምኑ ለሀጢያታቸው ንስሃ ይገባሉ፡፡

በኢየሱስ ስናምንና ንስሃ ስንገባ፣ የኢየሱስ መሰቃየተ ለሀጢያታችን ይከፍልልናል እናም ንጹህ እንሆናለን፡፡ ንጹህ በመሆናችን የተነሳ ከሰማዩ አባታችን ጋር ተመልሰን ለመኖር እንችላለን፡፡

## *ውይይት*

- ንስሐ መግባት ማለት ምን ማለት ነው?
- የሰማዩ አባታችን ለሀጢያታችን ንስሀ እንድንገባ የሚፈልገው ለምንድነው?
- በኢየሱስ በእውነት ዕምነት ያላቸው ለኃጢአታቸው ንስዛ የሚገቡት ለምንድነው?

## የሰማዩ አባታችን ንስሐ ለመግባት ማድረግ የሚያስፈልገንን ነግሮናል

ንስሐ ለመግባት፣ በኢየሱስና ባስተማራቸው ነገሮች ማመን አለብን፡፡ ለኃጢአታችን እንደተሰቃየ ማመን አለብን፡፡ እርሱ ብቻ ለኃጢአታችን ክፍያ መክፈል እንደሚችል ማመን አለብን፡፡ ኃጢአታችንን እንድናሸንፍ እንደሚፈልግ እና ይህን እንድናደርግ እንደሚረዳን ማመን አለብን፡፡ እርሱ ያዘዘንን ለማድረግ ጠንክረን መስራት አለብን፡፡

ንስሐ ስንገባ፣ ኢየሱስ እኛ እንድንሆን በሚፈልገው መንገድ እንዲለውጠን እንፈቅድለታለን፡፡ ስህተተ ነገሮችን ማድረግ እናቆምና ተክክለኛ ነገሮችን መስራት እንጀምራለን። እውነተ ያልሆኑ ነገሮችን የምንናገር ከሆነ፣ እናቆምና እውነተ የሆኑ ነገሮችን ብቻ እንናገራለን፡፡ የሆነ ነገር ከሰረቀን፣ ለባለቤቱ እንመልሳለን እናም ዳግመኛ በፍጹም ማንኛውንም ነገር አንሰርቀም፡፡ ለሌሎች ሩህሩህ ካልሆንን፣ እናቆምና ደግ ነገሮችን ለእነርሱ እናደርጋለን፡፡

ንስሐ ስንገባ የሚከተሉተን ነገሮች እናደርጋለን፣

*ኃጢአተ መስራታችንን ለራሳችን እንቀበላለን፣* የሰማዩ አባታችንን ሳንታዘዝ ስንቀር ኃጢአተ እየሰራን እንደሆነ እናውቃለን፡፡ ንስዛ ስንገባ፣ ስህተተ ነገሮችን ለማድረግ ማመካኘታችን አይደለም ስህተተ እንደሰራን አምነን እናም መለወጣችን ነው።

ለሰራናቸው ስህተተ ነገሮች ስናዝን፣ ንስዛ ስንገባ፣ ስህተተ ነገሮችን ለመስራታችን ልባዊ መከፋት ይሰማናል፡፡ ስለሀጢያታችን እናዝናለን ብቻ አንልም፡፡ ስለሰራናቸው እውነተኛ ዛዘን ይሰማንና እናም ባልሰራናቸው ኖሮ ብለን እንፀፀታለን፡፡ የሰማዩ አባታችንም የሚያዘንን ደግሞ ለመስራት እንፈልጋለን፡፡

*ስህተተ ነገሮችን መስራት እናቆማለን።* ኃጢአተ እንደሰራን ለራሳችን ብቻ የምናምን ከሆነና፣ ዛዘን ተሰምቶናል ብቻ የምንል ከሆነ፣ እውነተኛ ንስዛ አልገባንም፡፡ እውነተኛ ንስዛ ለመግባት፣ ደግሞ ስህተተ ነገሮችን መስራት ማቆም አለብን፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለማቆም ቀላል አይደለም፣ ነገር ግን ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው የሚያስፈልገንን እርዳታ ሊሰጠን ነው፡፡ የሰማዩ አባታችን ኢየሱስ እንዲረዳን እንድንፈቅድለተ ይፈልጋል ምክንያቱም ያ ፍጹም የምንሆንበተ እና ከእግዚአብሔር ጋር ተመልሰን መኖር የምንችልበተ ብቸኛው መንገድ በመሆኑ ነው፡፡

*ኃጢአታችንን እንናዘዛለን።* በኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ መናዘዝ ማለተ ያደረግነውን ስህተተ ስራ ለሰማዩ አባታችንና ለቤተክርስቲያን መሪ መናገር ማለተ ነው፡፡ አንዳንድ የምንፈጽማቸው ሀጢያዎቶች እኛን ብቻ ይጎዱናል፡፡ ወደ ሰማዩ አባታችን ስንጸልይ፣ ስለዚህ ሀጢያተ መንገርና ይቅር እንዲለን እናም እንድናሸንፋቸው እንዲረዳን መጠየቅ ይገባናል፡፡ የእኛ ሀጢያተ ሌላ ሰውን የሚጎዳ ከሆነ ለዚያ ሰው እና ለእግዚአብሔር

እንናዘዛለን፡፡ በጣም መጥፎ ሀጢያቶችን ልንናዘዝ ይገባናል፣ ይህ ማለት እንደዝሙት፣ ያሉትን ለቤተክርስቲያናችን መሪዎች፣ *ጳጳሳችን ወይም * የቀርንጫፍ ፕሬዚዳንታችን ለሆኑት መንገር ማለት ነው፡፡

*የሰራነውን ስህተት ለማስተካከል የምንችለውን እንሰራለን።* ንስሃ ስንገባ፣ የሰራነውን መጥፎ ነገሮች እናርማለን፡፡ ለምሳሌ፣ ከጎረቤት ሰርቀን ከሆነ፣ የወሰድነውን ነገር እንመልሳለን፡፡ የወሰድነው ነገር የሌለ ከሆነ፣ እንተካለን ወይም እንከፍላለን፡፡

*የሌሎችን ኃጢአት ይቀር እንላለን፣ የሰማዩ ለባታችን ሌሎችን ይቀር እንድንል ለዞናል፡፡* እርሱ ይቀር እንዲለን ከፈለግን፣ እኛም ሌሎችን ይቀር ማለት አለብን፡፡ በሰሩት ስህተት ነገሮች የተነሳ ሌሎችን የምንጠላቸው ከሆነና ይቀር የማንላቸው ከሆነ፣ የሰማዩ አባታችንም ሃጢያታችንን ይቀር አይለንም፡፡

*በህይወታችን ሙሉ የኢየሱስን ትእዛዛት ሁሉ ከልብ ለመታዘዝ እንሞክራለን፣* ትክክለኛ የሆነውን እስከምንሰራ ድረስ የምናደርጋቸውን የስህተት ስራዎች መለወጣችንን እንቀጥላለን፡፡ የምናደርጋቸውን መጥፎ ነገሮች ለማረም በየቀኑ የምንችለውን እናደርጋለን፡፡

*ስህተት የሆነ ነገር ባደረግን በማንኛውም ጊዜ ንስሃ መግባት አለብን፡፡* አሁኑኑ ንስሃ መግባት አስቸጋሪነቱን እናስብ ይሆናል፡፡ በኋላ ንስሃ መግባት ይቀላል ብለንም እናስብ ይሆናል፡፡ ነገር ግን አይቀልም፡፡ ንስሃ ለመግባት ስንገዘብ ለማድረግ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ንስሃ ለመግባት መቆየት በመንፈሳዊም ወደ ኋላ ይጎትተናል፣ ምክንያቱም ስለሰማዩ አባታችን ይበልጥ እንድንማር ለምናደርጋቸው ስህተት ነገሮች ንስሃ ካልገባን ከሰማዩ አባታችን ጋር ለመኖር እንድንዘጋጅ ሊረዳን አይችልም፡፡ ስህተት በምናደርግበት በማንኛውም ጊዜ፣ ወዲያውኑ ንስሃ መግባት ይገባናል፡፡

## *ውይይት*

- ንስሐ ለመግባት ማድረግ የሚያስፈልገን ምንድነው?

## እያንዳንዳችን ንስሐ መግባት እንችላለን

እያንዳንዳችን ንስሃ መግባት እንችላለን፡፡ አንዳንዴ ንስሃ በጣም አስቸጋሪ መስሎ ሊታየን ይችላል፡፡ ድክመታችንን በፍጹም ማሸነፍ እንዳማንችል ሆኖ ሊሰማን ይችላል፡፡ ሰይጣን ያንን እንድናምን ይፈልጋል በመሆኑም ስህተት መስራቱን እንቀጥላለን፡፡ ንስሃ መግባት እንደምንችል ማስታወስ አለብን፡፡ በራሳችን ልናደርገው አንችልም፡፡ እርዳታ እንፈልጋለን፡፡ እያንዳንዳችን የሰማዩ አባታችን ልጆች ነን፣ እናም ኢየሱስን እንዲረዳን ልኮታል፡፡ ከኢየሱስ እርዳታ ጋር የሰማዩ አባታችን እንድንሰራ ያዘዘንን ነገሮች ሁሉ መስራት እንችላለን፡፡

ወደ ሰማዩ አባታችን የኢየሱስን እርዳታ ፈልገን ከጸለይን ኢየሱስ ይረዳናል፡፡ እርሱ እና የሰማዩ አባታችን ትክክለኛ ነገሮችን እንድናደርግ ይፈልጋሉ፡፡ የምናደርጋቸውን ስህተት ነገሮች አይወዱትም፡፡ ነገር ግን ስህተት ነገሮችን ስንሰራ እንኳ፣ አይጠሉንም፡፡ ንስሃ እንድንገባ ይፈልጋሉ፣ ስለዚህም የሰማዩ አባታችን ይቀር ሊለን ይችላል እናም ደስተኛ መሆን እንችላለን፡፡

### ውይይት

- ንስሐ መግባት አስቸጋሪ ሲመስለን እንኳ ለምን ንስሃ መግባት ይኖርብናል?
- ንስሐ ለመግባት የሚረዳን ማን ነው?

## የሰማዩ አባታችን ንስሃ ስንገባ ይሸልመናል

እምነታችንን በኢየሱስ ላይ በመጣል እና ንስሃ ብንገባ የሰማዩ አባታችን ሙሉ በሙሉ ይቀር ይለናል፡፡ ስለነዚያ ቀጣተም መጨነቀ አይኖርብንም፡፡ ይቅርታ ማድረግ ብቻም አይደለም ደግሞ ኃጢያትን ዳግም እንዳንሰራ እርዳታ ስለሚሰጠን እኛ ግን ዘወትር ጥሩ ነገሮች ብቻ እናድርግ፡፡ ስለዚህም ኢየሱስም ይህንን እርዳታ ይሰጠናል።

በአንድ ጊዜ እንደ ሰማዩ አባታችን መሆን እንደማንችል ማስታወስ ይገባናል፡፡ ነገር ግን በኢየሱስ እምነታችንን ስንቀጥል እና ለሃጢያታችን ንስሃ ስንገባ እናም ኢየሱስን ለመታዘዝ ስንሰራ፣ የሰማዩ አባታችን ሃጢያታችንን ይቀር ማለቱን ይቀጥላል፡፡ ኢየሱስ እኛን መርዳቱን ይቀጥላል፡፡ በይበልጥ እና የበለጠ እንደ ሰማዩ አባታችን እንሆናለን፡፡ በመጨረሻም፣ ከሰማዩ አባታችን ጋር ለመኖር መመለስ እንችላለን፡፡

ንስሐ ስንገባ፣ ደስታ ይሰማናል፡፡ ስለሰራናቸው ስህተተ ነገሮች አንከፋም፣ ነገር ግን በኢየሱስ እርዳታ ድክመታችንን ስላሸነፍን ደስታ ይሰማናል፡፡ ከዚያም ፈተናዎችን ለመቋቋም ሀይል እንዳለን እናውቃለን እናም ተክክለኛ ነገሮችን እናደርጋለን፡፡

### ውይይት

- ንስሐ ስንገባ የምንቀበለው ሽልማተ ምንድነው?

### ማጣቀሻ

*የሰማዩ አባታችን ኃጢአተን የምናሸንፍበተን መንገድ አቀዶልናል*

- የያዕቆብ መልዕክተ 4፥17 (ኃጢአተን መፈጸም ማለተ እግዚአብሔር እንዳናደርግ የነገረንን ማድረግ ነው)።
- 1ኛ ዮሐንስ 1፥8 (ሐጢአተ አልሰራንም የምንል ከሆነ፣ እውነተ እየተናገርን አይደለም)።
- 1ኛ ዮሐንስ 5፥17 (ጽድቀ ያልሆነ ማንኛውም ነገር ማድረግ ኃጢአተ ነው)።

*የሰማዩ አባታችን ንስሃ ለመግባተ ማድረግ የሚያስፈልገንን ነግሮናል*


- የማቴዎስ ወንጌል 6፥14–15፣ 3ኛ ኔፊ 13፥14–15 (ሌሎችን ይቀር ማለተ አለብን)።
- አልማ 32፥13–16 (ተሁተ እንድንሆን ከመገደድ ይልቀ በራሳችን ተሁተ መሆን የተሻለ ነው)።
- አልማ 34፥32–36 (ንስሃ ለመግባተ ጊዜው አሁን ነው፡፡)

*አያንዳንዳችን ንስሐ መግባት እንችላለን*

- 1ኛ ኔፊ 3፥7 (የሰማዩ አባታችን እኛ ልናደርግ የማንችለውን ነገሮች እንድናደርግ በፍጹም አይጠይቀንም)።
- አልማ 42፥29–30 (ለኃጢአቶቻችን ምክንያት ማቀረብ አይገባንም)።

*የሰማዩ አባታችን ንስሃ ስንገባ ይሸልመናል*

- ሞዛያ 5፥5–9 (ኢየሱስ ንስሐ የሚገቡትንና እሱን የሚታዘዙትን ይረዳቸዋል)።
- ሞሮናይ 8፥24–26 (ንስሐ የገቡ መጠመቀ ይችላሉ)።



አልማ በሞርሞን ውሃ ውስጥ ተጠመቀ።

# ጥምቀት

*ምዕራፍ 15*

---

*መጠመቅ በዚህ ምድር ማድረግ ከምንችለው በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ነው፡፡ ጥምቀት በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? ለመጠመቅ ትክክለኛው መንገድ ምንድነው?*

**የሰማዩ አባታችን እንድንጠመቅ አዞናል**

መጠመቅ ማለት ሙሉ በሙሉ ለአፍታ በውሀ ስር መግባትና ለማጥመቅ ሥልጣን ባለው ሰው እንደገና መነሳት ማለት ነው፡፡ ጥምቀት የሰማዩ አባታችን ለእኛ ካለው የእቅዱ ክፍል አንዱ ነው፡፡ የሰማዩ አባታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንደምናምን፣ እንደምንወደው እና እርሱን መታዘዝ እንደምንፈልግ እናም ለኃጢያታችን ንስሃ እንድንገባ ለማሳየት እንድንጠመቅ አዞን ነበር፡፡

ኢየሱስ የሰማዩ አባታችን ልጆቹን ሁሉ እንዲጠመቁ እንዳዘዛቸው ያውቅ ነበር፡፡ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፣ ተጠምቆ ነበር፡፡ ይህን ያደረገበት ምክንያት የሰማዩ አባታችንን መታዘዝ ስለሚፈልግ ነበር፡፡ የሰማዩ አባታችንን መታዘዝ እና መጠመቅ ደግሞ እንዳለብንም ሊያሳየን ፈልጎ ነበር፡፡

እድሚው ስምንት ዓመት የደረሰ ማንኛውም ሰው፣ ትክክለኛው ምን እንደሆነና ስህተቱ ምን እንደሆ የሚረዳ፣ በኢየሱስ እምነት ያለው እና ንስሃ የገባ መጠመቅ ይገባዋል፡፡ እድሚያቸው ከስምንት ለመት በታች የሆኑ ልጆች መጠመቅ ለያስፈልጋቸውም፡፡ የሰማዩ አባታችን በሚያደርጉት አይፈርድባቸውም፡፡ ትክክለኛው ምን እንደሆነና ስህተቱ ምን እንደሆነ በለአምሮ ስንኩልነት መረዳት የማይችሉ መጠመቅ አያስፈልጋቸውም፡፡ ሌሎች ህዝቦች ሁሉ ከሰማዩ አባታችን ጋር ተመልሰው ለመኖር የሚፈልጉ መጠመቅ አለባቸው፡፡

ኢየሱስ መቼ መጠመቅ እንደሚገባን ነግሮናል፡፡ እርሰ ለተከታዮቹ እንደነገራቸው ሕዝቦቹ ስለእርሱ ካወቁ በኋላ፣ በእርሱ ካመኑ እና ንስሃ ከገቡ መጠመቅ አለባቸው፡፡ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ላሉት ለአንዳንድ ወንዶች የማጥመቅ ስልጣን ሰጥቶአቸዋል፡፡



ለኃጢያታችን ይቅር ለመባል በመጥለቅ መጠመቅ አለብን፡፡

## ውይይት

• የሰማይ አባታችን እንድንጠመቅ የሚፈልገው ለምንድነው?
• ኢየሱስ የተጠመቀው ለምን ነበር?
• መጠመቅ የሚያስፈልገው ማን ነው?

## መጠመቅ ማከናወን ከምንችለው በጣም አስፈላጊ ነገሮች አንዱ ነው

በመጠመቅ፣ የሰማዩ አባታችን ለእኛ ያለውን እቅድ መከተል እንደምንፈልግ እናሳየዋለን፡፡ ኢየሱስን እንደመሪያችን ለመቀበል ቃል እንገባለን፣ እናም እንድናደርግ የነገረንን ሁሉ እንታዘዛለን፡፡ ዘወትር እርሱን እና ለእኛ የሰራውን ነገሮች ለማስታወስ ቃል እንገባለን፡፡

እምነታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ስናደርግ፣ ለሃጢያታችን ንስሃ ስንገባ፣ እና ስንጠመቅ፣ የሰማዩ አባታችን ሀጢያታችንን ይቀር ይለናል፡፡ ከእርሱ ጋር ተመልሰን ለመኖር እንደምንችል ቃል ይገባልናል፡፡ እንደ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን አባላት ይቀበለናል፡፡ ስለ እርሱ የበለጠ እንድንማርና፣ ተክክለኛውን ነገሮች እንድናደርግ እንዲረዳን መንፈስ ቅዱስን ይልክልናል፡፡ ስንጠመቅ ለመፈጸም ቃል የገባነውን ነገሮች ማድረግ ከቀጠልን እነዚህን በረከቶች ሁሉ እንቀበላለን፡፡

እነዚህን በረከቶች መቀበል የምንችለው ከተጠመቅን ብቻ ነው፡፡ ይህ ከሰማዩ አባታችን ጋር ተመልሰን ለመኖር የሚያስችለን ብቸኛው መንገድ ነው፡፡ ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት ለመሆን የሚያስችለን ብቸኛ መንገድ ነው ይህ መንፈስ ቅዱስን ስጦታ የምንቀበልበት ብቸኛው መንገድ ነው፣ መንፈስ ቅዱስ ሊኖረን የሚገባ መብት ነው በህይወታችን እንዲረዳን ነው፡፡ ይህ ስጦታ የሚሰጠን ከተጠመቅን በኋላ ነው፡፡ ከሰማዩ አባታችን ጋር ተመልሰን ለመኖር እነዚህ ነገሮች ሁሉ በየተራ አስፈላጊዎች ናቸው፡፡

## ውይይት

• ስንጠመቅ ለሰማዩ አባታችን የምንገባው የተስፋ ቃል ምንድነው?
• ስንጠመቅ የሰማዩ አባታችን ለእኛ የገባው ቃል ኪዳን ምንድነው?
• ጥምቀት በጣም ያስፈለገው ለምንድነው?

## ለመጠመቅ እራሳችንን ማዘጋጀት ይገባናል

ከመጠመቅ በፊት አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ አለብን፡፡ ስለኢየሱስ ክርስቶስ መማርና በእርሱ ማመን፣ ለሀጢያታችን ንስሃ መግባት፣ ኢየሱስ እንድናደርግ ያዘዘንን ነገሮች ማድረግ አለብን፡፡

## ውይይት

• ለጥምቀት ለመዘጋጀት ምን ማድረግ አለብን?

## ጥምቀት አዲስ ጅማሬን ይሰጠናል

ጥምቀት ከኃጢያት የነጻናል፣ አዲስ ህይወት እንድንጀምር ያደርገናል፡፡ ኢየሱስ በአንድ ወቀት ዳግም እንደመወለዳችን ነው ብሏል፡፡ ሰው በመንፈስ ካልተወለደ በቀር፣ ከሰማዩ አባታችን ጋር ተመልሶ ለመኖር አይችልም ብሏል፡፡

ከኢየሱስ ተከታዮች አንዱ፣ ጳውሎስ እንዳለው፣ ከተጠመቅን በኋላ አዲስ ህይወት መጀመር አለብን። እሱም እንዳለው ለመጠመቅ ከውሃ ስር ስንገባ ሃጢያታችንን ሁሉ የመቀበር ያህል ነው። ከውሃ ውስጥ ስንወጣ፣ ንጹህ አዲስ ሰው፣ አዲስ ህይወት ለመጀመር ዝግጁ መሆንን ዓይነት ነው ብሏል። ጥምቀት ወደ ሰማዩ አባታችን የምንመለስበትን መንገድ ያስጀምረናል።

## *ማጣቀሻ*

*የሰማዩ አባታችን እንድንጠመቅ አዘናል*

- 2ኛ ኔፊ 31፥4–7 (ኢየሱስ መጠመቅ እንደሚያስፈልገን አሳይቶናል።)
- 3ኛ ኔፊ 11፥21–27 (ሰው እንዴት መጠመቅ እንደሚገባው ኢየሱስ አስተምሯል።)
- ሞሮናይ 8፥9–22 (ትንንሽ ልጆች መጠመቅ አይገባቸውም።)

*መጠመቅ ማከናወን ከምንችለው በጣም አስፈላጊ ነገሮች አንዱ ነው*

- ወደ ሮሚ ሰዎች 6፥3–7 (በጥምቀት አማካኝነት ነጽተናል።)
- 3ኛ ኔፊ 27፥16 (የሰማዩ አባታችን የሚጠመቁትን ይባርካል።)

# የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ

*ምዕራፍ 16*

*መንፈስ ቅዱስ እውነት የሆኑ ነገሮችን እንድናውቅና እንድንረዳው ይረዳናል፡፡ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንዴት ማግኘት እንችላለን?*

## መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሊመራን ይችላል

መንፈስ ቅዱስ ሰው ከመጠመቁ በፊት ሊረዳው ይችላል፡፡ የኢየሱስ ትምህርቶች እውነት እንደሆኑ ለሰውየው ሊነግረው ይችላል፡፡ ለአንዳንድ ጊዜ እውነተኛውን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የት እንደምናገኝ ይነግረናል፡፡ ነገር ግን እስክንጠመቅ እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እስኪሰጠን ድረስ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር አይኖርም፡፡

በሉዊስ ኪዳን ቆርኔሌዎስ ስለተባለ ሰው እናነባለን፡፡ እርሱም ያልተጠመቀ ሰው ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ ትምህርቶች እውነት እንደሆኑ ነገረው፡፡ በኋላ ቆርኔሌዎስ ተጠመቀና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተቀበለ፡፡

## የሰማዩ አባታችን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የምንቀበልበትን መንገድ ሰጥቶናል

የሰማዩ አባታችን ለኛ ስላለው እቀድ እንደለወቀን፣ ለሐጢያታችን ንስዛ ለመግባትና ኢየሱስ እንድናደርግ የነገረንን ነገር ሁሉ ለመታዘዝ እንፈልጋለን፡፡ ነገር ግን ይህንን ያለ እርዳታ ማድረግ አንችልም፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሁሉም ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ እርዳታ የማግኘት መብት ነው፡፡ ይህንን ስጦታ ከተጠመቀን በኋላ ወዲያውኑ እናገኛለን፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለመቀበል መዘጋጀት አለብን፡፡ በኢየሱስ ማመንና ያዘዘንን በጥንካሬ ለማድረግ መሞከር አለብን፡፡ ለሀጢያታችን ንስዛ መግባትና መጠመቅ አለብን፡፡

ከተጠመቀን በኋላ፣ ከሰማዩ አባታችን የተሰጠ ስልጣን ያላቸው ሰዎች እጃቸውን በራሳችን ላይ ይጭኑና፣ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ይሰጡናል፣ እናም በይፋ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት ያደርጉናል፡፡ ደግሞም ይባርኩናል፡፡

### *ውይይት*

• የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የምንቀበለው እንዴት ነው?



*ራስ ላይ እጅን በመጫን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ መቀበል አለብን።*

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሊረዳን የሚችልበት ብዙ መንገዶች አሉ፡፡ ከኢየሱስ መልዕክት ሊያመጣልን ይችላል፡፡ ስለኢየሱስና የሰማዩ አባታችን ብዙ ነገሮችን ሊያስተምረን ይችላል፡፡

ችግራችንን እንዴት እንደምናቃልል እንድናውቅ ሊረዳን ይችላል፡፡ ሊያጽናናን ይችላል፡፡ ሃጢያታችንን እንድናሸንፍ ሊረዳን ይችላል፡፡ ተክክለኛ ነገሮችን እንድናደርግ ሊረዳን ይችላል፡፡

መንፈስ ቅዱስ እንድናስተውል እና ሌሎችን እንድንወድ ሊረዳን ይችላል፡፡ እንዴት እንደምንረዳቸው እንድናውቅ ሊረዳን ይችላል፡፡ የኢየሱስን ትምህርቶች እንድናግዝ ሊረዳን ይችላል፡፡ ስለሰማይ አባታችንና ኢየሱስ ሌሎች ሰዎችን ስናስተምር ምን ማለት እንዳለብን እንድናውቅ ሊያስተምረን ይችላል፡፡

## *ውይይት*

• መንፈስ ቅዱስ ህይወታችንን መለወጥ የሚችልበት አንዳንድ መንገዶች ምን ምንድናቸው?

## ይህ ስጦታ እንዲኖረን ለኃጢያታችን ንስሐ መግባት አለብን


በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተሻልን ሰዎች መሆን እና ጥሩ ነገሮችን ማድረግ እንችላለን፡፡ በይበልጥ እንደ ሰማዩ አባታችን መሆን እንችላለን፡፡ ነገር ግን ሁል ጊዜ ጥሩ ነገሮችን ለማድረግ መሞከር አለብን፣ አለበለዚያ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር አይቀይም፡፡ ጥሩ ሃሳብ ለማሰብ መሞከር አለብን። የኢየሱስን ትምህርቶች ለመከተል መሞከር አለብን። ስህተት የሆነ ነገር ስናደርግ፣ ንስሃ መግባት አለብን፡፡ ይህን ሁሉ ነገሮች ለመስራት ስንሞክር፣ መንፈስ ቅዱስ ይረዳናል፡፡

አንዳንድ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በልባችን የሞቀ ሰላማዊ ስሜት እንዲኖረን በማድረግ ይመራናል፡፡ ስህተት የሆነ ነገር ስናደርግ ይህ የደስታ ስሜት ከእኛ ይለያል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ድምጽ በአእምሮአችን፣ በመስማት፣ ማድረግ ያለብንን ወይም ማድረግ የሌለብንን ይነግረናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ የሚነግረንን ለማዳመጥና ለመታዘዝ ሁልጊዜ ዝግጁ መሆን አለብን፣ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜ የሚነግረን ኢየሱስ እንድናደርግ የሚፈልገውን ነው፣ እናም ኢየሱስን በመታዘዝ ብቻ ወደ ሰማዩ አባታችን መመለስ እንችላለን፡፡

መንፈስ ቅዱስን የማንታዘዝ ከሆነና ስህተተ ነገሮችን ማድረግ ከጀመርን፣ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ይለያል፡፡ ከእኛ ጋር አይኖርም ወይም ትክክለኛ ነገር የማናደርግ ከሆነ አይረዳንም፡፡ ነገር ግን የእርሱን አመራር የምንከተል ከሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ ምን ጊዜም በቋሚነተ ከእኛ ጋር ይሆናል፡፡ የተሻልን ሰዎች እንድንሆንና ከሰማይ አባታችን ጋር ስለሚኖረን ህይወተ እንድንዘጋጅ ይረዳናል፡፡

## *ውይይት*

• መንፈስ ቅዱስ ሊረዳን እንዲችል ምን ማድረግ አለብን?



ዮሴፍ ስሚዝ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መጽሐፈ ሞርሞንን ተርጉሟል፡፡

## በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሌሎች ልዩ የሆኑ በረከቶችን እንቀበላለን

በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የምንቀበለው አንዳንድ ልዩ በረከቶች መንፈሳዊ ስጦታዎች ይባላሉ፡፡ ኢየሱስ እነዚህን ስጦታዎች ለእራሱ እውነተኛ ቤተክርስቲያን አባሎች ቤተክርስቲያኑ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ሁሉ ይሰጣል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ሀይል አማካኝነት እነዚህን ስጦታዎች ይሰጠናል፡፡ እነዚህን ስጦታዎች ልንረዳቸው ያስፈልጋል ስለዚህም በብልሀት ልንጠቀምባቸው እንችላለን፡፡

*በሌላ ቋንቋ የመናገር ስጦታ*

አንዱ ስጦታ ሰዎች ሌላ ቋንቋ እንዲናገሩ ይረዳል፡፡ ኢየሱስ ይህን ስጦታ ለሰዎች የሰጠበት አንዱ ምክንያት ቋንቋዎቹን ለሚናገሩት ሰዎች ወንጌልን ለማስተማር እንዲረዳቸው ነው፡፡

*ሌላ ቋንቋን የመተርጎም ስጦታ*

ሌላው ስጦታ ስለወንጌል የሚነገሩቸውን ሰዎች ይረዳል፡፡ ሌላ ቋንቋዎችን የመተርጎም ስጦታ የማያውቁትን ቋንቋ ከኢየሱስ የተነገረ መልዕክትን እንዲያገናዝቡ ይረዳቸዋል፡፡

*ኢየሱስ የሰማዩ አባታችን ልጅ እንደሆነ የማወቅ ችሎታ*

ሌላው ስጦታ ሰዎች ኢየሱስ የሰማዩ አባታችን ልጅ እንደሆነ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡ ቅዱሳን መጻህፍት ኢየሱስ አዳኝ እንደሆነ ሰው ማወቅ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ እንዲያውቅ ከረዳው ብቻ ነው ይላሉ፡፡ ይህ የተሰጠው ኢየሱስ እውነተኛ የሰማዩ አባታችን ልጅ እንደሆነ፣ እና የአለም አዳኝ እንደሆነ፣ የሚታወቀው በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ነው፡፡

*የሌሎችን ምስክርነት የማመን ስጦታ*


የሌሎችን ምስክርነት የማመን ስጦታ አንድ ሰው ስለኢየሱስ የሚላቸው ነገሮች እውነት እንደሆነ እንዲያውቁ ይረዳል፡፡ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ምስክርነትን እንድናውቀና እንድናምን ይረዳናል፡፡

*የእምነት ስጦታ*

የእምነት ስጦታ የኢየሱስን ትእዛዛት እንድናከብር ይረዳናል፡፡ ያለ እምነት አንዳች ሌላ መንፈሳዊ ስጦታዎችን መቀበል አንችልም፡፡ ያለ እምነት ወደ ሰማዩ አባታችን መመለስ አንችልም፡፡ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ጠንካራ እምነት አላቸው፡፡ የዚህን ዓይነት በመጽሐፈ ሞርሞን ውስጥ ነቢይ የሆነው አንዱ በኢየሱስ ታላቀ እምነት ነበረው፣ ኢየሱስም ታይቶት ነበር፡፡ ነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝም እንደዚሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ታላቀ እምነት ነበረው፣ የሰማይ አባታችንና ኢየሱስ ታይተውት ነበር፡፡

*የትርጉም ስጦታ*

የትርጉም ስጦታ ሰዎች የሰማዩ አባታችን እና የኢየሱስን እናም የተከታዮቹን የተጻፉ ቃሎች ከአንዱ ቋንቋ ወደ ሌላው ቋንቋ እንዲተረጎሙ ይረዳቸዋል፡፡ ነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ መጽሐፈ



የያሬድ ወንድም ኢየሱስ በምድር ላይ ከመወለዱ በፊት የኢየሱስን ጣት ስለተመለከተ ታላቅ እምነት ነበረው፡፡

ሞርሞንን ሲተረጉም ይህ ስጦታ ነበረው፡፡ ይህ ስጦታ ተርጓሚው የመልዕክቱን ትክክለኛነትን እንዲረዳ ይረዳዋል፣ ከዚያም በትክክል ይተረጉመዋል፡፡

*የዕውቀት ስጦታ*

የእውቀት ስጦታ ሰዎች የሰማይ አባታችን እና የኢየሱስን ስራ እንዲረዱ ይረዳቸዋል የሰማዩ አባታችን እንዳለው እኛ ማድረግ ያሌለብንን ካላወቅን ወይም ካልተረዳን እርሱ የሚፈልገውን ነገሮች ካላደረግን ወደ እርሱ መመለስ አንችልም፡፡ የሰማዩ አባታችን ወደ እርሱ መመለስ እንድንችል የሰጠንን ዕቀድ ማወቀ ይገባናል።

በዚህ ህይወተ ያገኘነው እውቀት ከሞተን በኋላ በመንፈስ ዓለም ውስጥ ሊረዳን ይችላል፡፡ ስለ እርሱ ተምህርቶች እና ተዕዛዛቶች ስለሰማይ እና ምድር፣ በራሳችን ሀገር እና በሌሎች ሀገሮች ስለተከሰቱ ነገሮች እንድናውቀ ይፈልጋል። ይህንን እውቀት በጥበብ መጠቀም ይገባናል። እውቀትን ለመሻት መንፈስ ቀዱስ እንዲረዳን መጠየቀ ይገባናል።

*የጥበብ ስጦታ*

ይህ ስጦታ የሰማዩ አባታችን እውቀትን ህዝቡ በተገቢው መንገድ እንዲጠቀምበት የሰጠውን ለመርዳት ነው። እኛ ይህንን ስጦታ ሕይወታችንን ለማሻሻል እና በማስተማር እና ለሌሎች ብልሃዊ ምክር በመስጠት መጠቀም ይገባናል፡፡

*የማስተማር ስጦታ*

ወንጌልን የማስተማር ስጦታ ለሌሎች ሰዎች በሚረዱበት መንገድ በማስተማር መርዳት ነው፡፡ ይህ ስጦታ ሊኖረን የሚችለው በኢየሱስ እምነት ሲኖረንና በጥናት እና በጸሎት አማካኝነት ብቻ ነው፡፡

*የትንቢት ስጦታ*

የትንቢት ስጦታ ሰዎች ባለፉት ጊዜያት የተከሰቱትን ነገሮች፣ አሁን እየሆኑ ያሉትን ነገሮች፣ እና ወደፊት የሚሆኑትን ነገሮች እንዲያውቁና እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል፡፡ ነቢያት ይህ ስጦታ የተሰጣቸው ናቸው፣ ነገር ግን እኛም በህይወታችን እንዲመራን ሊኖረን ይችላል፡፡

** የራዕይ ስጦታ*

መንፈስ ቀዱስ ለሰዎች የሚረዳቸውን ነገሮች ይገልጽላቸዋል፡፡ እያንዳንዳችን ለራሳችን ጥቀም ራዕዮችን መቀበል እንችላለን፡፡ ነገር ግን ለመላው ቤተክርስቲያን የሆነ ራዕይ የሚሰጠው ለነቢይ ብቻ ነው፡፡ በቤተክርስቲያን መሪያችን ለሆነ ሰው ራዕይ መቀበል አንችልም፡፡ መንፈስ ቀዱስ የሚሰጠን ማንኛውም ነገር ከሌሎች ተዕዛዛትና በሰማዩ አባታችን እና ከኢየሱስ ተምህርቶች ጋር ይስማማል፡፡

*የፈውስ ስጦታ*

የፈውስ ስጦታ የታመሙ ሰዎች እንዲሻላቸው ይረዳቸዋል፡፡ አንዳንዶቹ የመፈወስ እምነት አላቸው እናም ሌሎቹ ሌሎች ሰዎችን የመፈወስ እምነት አላቸው፡፡

*ተአምራትን የማድረግ ስጦታ*

ተአምራት የመስራት ስጦታ የተሰጠው ሰዎችን ለመርዳት ነው፡፡ ተአምር የሰማዩ አባታችን ለእኛ የሚያደርግልን ነገር ነው እኛ በራሳችን ሀይል ልናደርገው ከምንችለው የበለጠ ነው፡፡ ኢየሱስ በአዲስ ኪዳንና በመጽሐፈ ሞርሞን በእርሱ በሚያምኑት መሀከል ተአምር ይኖራል ብሏል፡፡

*ሰይጣን እነዚህን መንፈሳዊ ሀይሎች ማስመሰል ይችላል*

ሰይጣን እውነተኛ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለማስመሰል ነገሮች እንዲሆኑ ማድረግ ይችላል፡፡ እራሱን መልአክ እንዲመስል ማድረግ ይችላል። ክፋ ነግሮች ጥሩ እና ተክክለኛ ሆነው እንዲገለጹ ማድረግ ይችላል፡፡ ሀሰተኛ ነቢይ እውነተኛ ነቢይ ሆኖ እንዲታይ ማድረግ ይችላል፡፡ ሰዎችን ለማታለል ተአምራትን መስራት ይችላል፡፡ አስማተኛ (ጠንቋይ)፣ የሙት መንፈስ ጠሪዎች፣ እድል ነጋሪዎች፣ እናም ሌሎች እነርሱን የመሰሉ ያላቸውን ሀይል የሚቀበሉት ከሰይጣን ነው፣ እናም የኢየሱስ ተከታዮች አይደሉም፡፡ ከእነርሱ መራቀ ይገባናል፡፡

ሰይጣን ነገሮች በጣም እውነት ሆነው እንዲታዩ ማድረግ ይችላል፣ ውሸት መሆናቸውን የምናውቅበተ ብቸኛው መንገድ የሰማዩ አባታችንን በመጠየቀ ነው፡፡ ሠይጣን ወይም ተከታዮቹ መንፈሳዊ ስጦታዎችን አስመስለው ሊሰሩ እርግጠኛ ያልሆነ ስሜት፣ ሰላማዊ ያልሆነ ስሜት ይኖረናል፡፡ የመንፈሳዊ ሥጦታን እውነተኛነት እና የሰይጣን ማስመሰል መሆኑን የምናውቅበተ የማወቀ ስጦታ የማስተዋል ስጦታ ይባላል፡፡

## ውይይት

- መንፈሳዊ ስጦታዎች ምን ምንድን ናቸው?
- እውነተኛ መንፈሳዊ ስጦታዎችንና በሰይጣን ማስመሰያዎች መካከል ያለውን ልዩነው እንዴት ለይተን ማወቀ እንችላለን?

## ያለንን ስጦታዎች ለማሳደግ እና ለመጠቀም መስራት ይገባናል

ከፆምን እና ከፀለይን እናም ከአጠናን የትኞቹ ስጦታዎች እንዳሉን መማር እንችላለን፡፡ ስጦታዎቻችንን መጠቀም የምንችለው የኢየሱስን ተዕዛዛት ስናከብር ብቻ ነው፡፡ ከዚያም ሌሎችን ለመርዳትና የኋለኛው ቀዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንዲገነባ ለመርዳት መጠቀም እንፈልጋለን፡፡ የማናሳድጋቸው ከሆነና ስጦታዎቻችንን የማንጠቀምበት ከሆነ፣ እናጣቸዋለን፡፡

ኢየሱስ በምንባረክበት መንፈሳዊ ስጦታዎች መኩራት አይገባንም ብሏል፡፡ እንደ ቅዱስ ከማያስቧቸው ሰዎች ጋር ስለእነርሱ መነጋገር አይገባንም፡፡ እነዚህ ስጦታዎች የተሰጡን ለእኛ እንዲውሉ ሌሎች ሰዎችን ለመባረክ ነው፡፡ እነዚህ ስጦታዎች የተቀደሱ እንደሆኑ ማስታወስ አለብን፡፡ እነዚህን ስጦታዎች ኢየሱስ የሰጠን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው፡፡ እርሱ የሚጠይቀን እንድናመሰግነውና እነዚህን ስጦታዎች እንድንጠቀምባቸው እንደሚፈልገው እንድንጠቀም ብቻ ነው፡፡

### ውይይት

- የትኞቹ ስጦታዎች እንዳሉን እንዴት ማረጋገጥ እንችላለን?
- መንፈሳዊ ስጦታዎችን በተቀደሰ ሁኔታ እንዴት እንጠብቃቸዋለን?

## የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለእኛ ዋጋ ያለው ሊሆን ይችላል

ዘወትር ጥሩ ነገሮችን ለማድረግ እና ኢየሱስን ለመታዘዝ መሞከር አለብን፣ አለበለዚያ የመንፈስ ቅዱስ ሀይል ከእኛ ጋር አይቀይም፡፡ መልካም ሃሳቦችን ለማሰብ መሞከር አለብን፡፡ ስህተት የሆነ ነገር ስናደርግ ንስሃ መግባት አለብን፡፡ መንፈስ ቅዱስ የሚነግረንን ነገሮች ለመረዳት መሞከር አለብን፡፡ የሚሰጠንን ምክር መከተል አለብን፡፡

ኢየሱስን ከልባችን ከታዘዝን፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ህይወታችንን ይባርከዋል፡፡ አሁን ደስተኛ ህይወት እንዲኖረን እና ከሰማይ አባታችንም ጋር ለሚኖረን ህይወት እንድንዘጋጅ ይረዳናል፡፡

### ውይይት

- መንፈስ ቅዱስ ሊረዳን እንዲችል ምን ማድረግ አለብን?

### ማጣቀሻ

*መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሊመራን ይችላል*

- 2ኛ ኔፊ 32፥5፣ ሞሮናይ 10፥5–7 (መንፈስ ቅዱስ አንድ ነገር እውነት እንደሆነ ይነግረናል፡፡)

*የሰማዩ አባታችን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የምንቀበልበትን መንገድ ሰጥቶናል*

- የሐዋሪያት ሥራ 10፥44–48፣ 2 ኔፊ 31፥17–18 (የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሚሰጠው ከጥምቀት በኋላ ነው፡፡)
- ሞሮናይ 8፥25–26 (መንፈስ ቅዱስ መቀበል እንችላለን፡፡)

*ይህ ስጦታ እንዲኖረን ለኃጢያታችን ንስሃ መግባት አለብን*

- ሞዛያ 2፥36 (የሰማዩ አባታችንን ትእዛዛቶችን ሳናከብር ስንቀር፣ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች እናጣለን፡፡)
- ሞሮናይ 8፥28 (ንስሃ ካልገባን፣ መንፈስ ቅዱስ እኛን መርዳት መሞከሩን ያቆማል፡፡)

*በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሌሎች ልዩ የሆኑ በረከቶችን እንቀበላለን*

- 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥1–11 ሞሮናይ 10፥8–19፣ ትምህርትና ቃልኪዳን 46፥10–33 (መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ሊሰጠን ይችላል፡፡)
- የማርቆስ ወንጌል 16፥17–18፣ ሞርሞን 9፥7–24 (መንፈሳዊ ስጦታዎች የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ክፍሎች ናቸው)፡፡

*ያሉንን ስጦታዎች ለማሳደግና ለመጠቀም መስራት ይገባናል*


- የማቴዎስ ወንጌል 25፥14–30 (የሰማይ አባታችን ለሱ ስራ እንድንጠቀምባቸው ስጦታዎችን ይሰጠናል፣ እናም የማንጠቀምባቸው ከሆነ ልናጣቸው እንችላለን)፡፡


*የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለእኛ ዋጋ ያለው ሊሆን ይችላል*

- አልማ 34፥37–38 (መንፈስ ቅዱስ እንድናደርግ የሚነግረንን ነገሮች ለማድረግ መሞከር ይገባናል)፡፡

# የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን

ክፍል ስድስተ





አብርሃም ከጌታ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ።

# የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች

*ምዕራፍ 17*

*የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ከሌሎች ሰዎች የተለዩ ናቸው፡፡ ተከታዮቹ እነማን ናቸው? እንዴተስ ነው የሚለዩተ?*

**የኢየሱስ ተከታዮች የሰማዩ አባታችንን ይወዱታል**


የኢየሱስ ተከታዮች በእርሱ የሚያምኑና የሚታዘዙተ ሰዎች ናቸው፡፡ በኢየሱስ አማካይነት የሰማዩ አባታችንን እቀድ ተምረዋል እናም ሊከተሉተ ፈልገዋል፡፡ የሰማዩ አባታችንን ይወዱታል እናም ለሁሉም ቢቻል የተሻለ ህይወተ እንደሚፈልግ ያምናሉ፡፡ ኢየሱስ የሰማይ አባታችን ልጅ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ኢየሱስ የእነርሱ አዳኝ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ የእነርሱ ከሰማዩ አባታችን ጋር ተመልሶ መኖር ኢየሱስ እንዳመቻቸላቸው ያምናሉ፡፡ ኢየሱስን በመከተልና ትዕዛዛቶችን በማክበር ብቻ ለሃጢያታቸው ይቀርታ ማግኘተና ወደ ሰማዩ አባታችን መመለስ እንደሚችሉ ያምናሉ፡፡

ኢየሱስን የሚከተሉተ እግዚአብሔር እና ኢየሱስ ስላደረጉላቸው ሁሉ አመስጋኞች ናቸው፡፡ ኢየሱስን መታዘዝ ይፈልጋሉ፡፡ ለሀጢያታቸው ንስሃ ይገባሉ፡፡ ተጠምቀዋል፣ እናም የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ተቀብለዋል፡፡ ሰዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር አስፈላጊዎች እንደሆኑ ይረዳሉ፡፡ በማንኛውም በተቻለው መንገድ ሌሎች ሰዎችን ለመርዳተ ይሞክራሉ፡፡

እውነተኛ የኢየሱስ ተከተዮች የተቀደሱ የተስፋ ቃል ይገባሉ፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለመጠራተ ለሰማዩ አባታችን ቃል ይገባሉ። ይህ ማለተም እንደ እርሱ ቤተክርስቲያን አባል ለመታወቀ፣ የእርሱን ተምህርቶች ሁሉ ለመቀበልና ለመከተል፣ እናም ዘወተር እርሱን ለማስታወስ ነው፡፡ ደግሞም ሌሎች ሰዎችን ለመውደድና ለመርዳተም ቃል ይገባሉ፡፡

የሰማዩ አባታችን ለኢየሱስ ተከታዮች የተቀደሰ የተስፋ ቃል ኪዳኖችን ገብቷል፡፡ ቃል ከገባቸው ነገሮች ጥቂቶቹ፣

1. እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላተ ይቀበላቸዋል፡፡
2. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ይሰጣቸዋል፡፡



*ሙሴ እጁን በመጫን ለአሮን የክህነት ስልጣንን ሰጥቶታል፡፡*

3. የሚፈልጉትን ነገሮች እንዲያገኙ ይረዳቸዋል፡፡
4. የእርሱን ስራ እንዲሰሩ ሀይሉን ይሰጣቸዋል፡፡
5. ታላቅ በረከቶችን አሁንና ለዘለአለም ይሰጣቸዋል፡፡
6. ኢየሱስን መታዘዝ ከቀጠሉ ከእርሱ ጋር ተመልሰው እንዲኖሩ ይፈቅድላቸዋል፡፡

## *ውይይት*

• የኢየሱስ ተከታዮች ከሌሎች ሰዎች የሚለዩት እንዴት ነው?
• የኢየሱስ ተከታዮች ለማድረግ ቃል የሚገቡት ምንድነው?
• ኢየሱስ እና የሰማዩ አባታችን ለኢየሱስ ተከታዮች የገቡት የተስፋ ቃል ምንድነው?

## ኢየሱስ የሰማዩ አባታችንን ኃይል ለተከታዮቹ ይሰጣል

ኢየሱስ ለተከታዮቹ የእርሱን ስራ ለማከናወን እንዲረዱት ስልጣን ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ስልጣን የክህነት ሥልጣን ይባላል፡፡ ይህንን ሥልጣን የሰማዩ አባታችን ለኢየሱስ ሰጥቶታል፡፡

የክህነት ሥልጣን መኖር ታላቅ በረከት ነው፡፡ የክህነት ሥልጣን የተቀደሰ ሥልጣን ነው፡፡ እውነተኛ የኢየሱስ ተከታዮችና ትዕዛዛቱን ለመታዘዝ ከልባቸው የሚሰሩት ብቻ የክህነት ሥልጣን እንዲኖራቸው ተፈቅዶላቸዋል፡፡

አንድ ሰው የክህነት ስልጣን ሲኖረው፣ ኢየሱስ እንዲያደርግ የሚፈልገውን አንዳንድ ነገሮችን ማድረግ ይችላል፡፡ ሌሎች ሰዎችን ስለሰማይ አባታችን እና ስለ ኢየሱስ በማስተማር፣ ሊያጠምቃቸው፣ እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ የክህነት ሥልጣን ያለው ሰው ቤተሰቦቹ ሲታመሙና ሌሎች ችግሮች ሲኖሩባቸው ሊባርካቸው ይችላል፡፡ ሰዎች በኢየሱስ ባመኑበትና ትዕዛዛቱን በታዘዙበት በማንኛውም ጊዜ፣ ኢየሱስ የክህነት ስልጣንን እና ሌሎች በረከቶችን ሰጥቷቸዋል።

## *ውይይት*

• የክህነት ሥልጣን ምንድነው?
• ኢየሱስ ለተከታዮቹ የክህነት ስልጣንን የሰጠው ለምንድነው?

## ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ብዙ ሰዎች በእርሱ አምነው ትዕዛዛቱን ይከተሉ ነበር

*አዳምና ሔዋን እናም አንዳንዶቹ የአነርሱ ልጆች ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት በሱና በትዕዛዛቶቹም አምነው በማክበር ተከተለውታል፡፡*

የሰማዩ አባታችን ለአዳምና ሔዋን በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑና ትዕዛዛቱን እንዲያከብሩ ነግሯቸዋል፡፡ አንድ ቀን ወደ ምድር እንደሚመጣ ተናግሯል፡፡ አዳምና ሔዋን እንደሚታዘዙ ቃል ገብተዋል፡፡ ቃላቸውንም ጠብቀዋል፡፡ ተጠምቀዋል፣ እናም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታንም ተቀብለዋል።

ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት፣ የክህነት ስልጣንን ለአዳም ሰጥቶት ነበር፡፡ ኢየሱስን ለሚታዘዙት ወንዶች ልጆቹ የክህነት ስልጣን እንዲሰጣቸው ፈቅዶለት ነበር፡፡ አዳምም በእያንዳንዳቸው ታዛዥ ወንዶች ልጆቹ ላይ እጁን ጫነ እና የክህነት ሥልጣኑን ሰጣቸው፡፡ በኋላም፣ የአዳም ልጆች ለወንዶች ልጆቻቸው በተመሳሳይ መንገድ የክህነት ስልጣንን ሰጧቸው፡፡

### *ውይይት*

• አዳምና ሔዋን የኢየሱስ ተከታዮች ለመሆን ያደረጉት ምን ነበር?
• የኢየሱስ ተከታዮች የክህነት ሥልጣንን የተቀበሉት እንዴት ነበር?

*አብርሃም ኢየሱስን አመሰገነ እናም ትዕዛዛቶቹን ተከተሏል*

አብርሃምና ቤተሰቡ በኢየሱስ ያምኑ ነበር፡፡ አንድ ቀን ወደ ምድር እንደሚመጣም ያምኑ ነበር፡፡ አብርሃም ኢየሱስን እንደሚታዘዝና የእርሱን ስራ እንደሚሰራ ለሰማዩ አባታችን ቃል ገብቶ ነበር፡፡ የሰማዩ አባታችንም ለአብርሃም፣ የሚታዘዝ ከሆነ፣ እርሱንና የእርሱን ተውልዶች እንደሚባርክ ቃል ገብቶለት ነበር፡፡ እነዚህ የሰማዩ አባታችን ከገባቸው ቃሎች ጥቂቶቹ ናቸው፣

1. ለአብርሃምና ተውልዶቹ የክህነት ስልጣን ይሰጣቸዋል፡፡
2. ለአብርሃምና ተውልዶቹ የሚኖሩበት ምድር ይሰጣቸዋል፡፡
3. ለአብርሃም ብዙ ትውልድን ይሰጠዋል፡፡
4. አብዛኛዎቹ የአብርሃም ተውልዶች የኢየሱስ ተከታዮች ይሆናሉ፡፡
5. አብዛኛዎቹ የአብርሃም ተውልዶች የኢየሱስን ስራ ለመፈጸም እና ስለሰማይ አባታችንና ኢየሱስ ለሌሎች ሰዎች ማስተማርን ይመርጣሉ፡፡

አብርሃም ልጆቹ በኢየሱስ እንዲያምኑና ትዕዛዛቶቹን እንዲጠብቁ አስተምሯቸዋል፡፡ አብርሃም ይስሃቀ ለተባለው ልጁ የክህነት ሥልጣንን ሰጥቶታል፡፡ ይስሃቀ ያዕቆብ ለተባለው ልጁ የክህነት ሥልጣንን ሰጥቶታል፡፡ በኋላም፣ የሰማዩ አባታችን የያዕቆብን ስም ወደ እስራኤል ለውጦታል፡፡ እስራኤል አስራ ሁለት ወንድ ልጆች ነበሩት፡፡ እርሱም በኢየሱስ እንዲያምኑና ትዕዛዛቱን እንዲያከብሩ አስተምሯቸዋል፡፡ የክህነት ስልጣን ነበራቸው፡፡ የእስራኤል ልጆች ተውልድ አስራ ሁለት የእስራኤል ነገዶች ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡

### *ውይይት*

• የሰማዩ አባታችን ለአብርሃም የገባው ቃል ምን ነበር?
• እስራኤል ማን ነበር?

*የእስራኤል ህዝቦች በኢየሱስ አምነው ትዕዛዛቱንም ያከብሩ ነበር*

በምድራቸው ላይ በቂ ምግብ ባለመኖሩ ምክንያት፣ እስራኤልና ወንዶች ልጆቹ ግብጽ ወደምትባል ምድር ለመኖር ሄዱ፡፡ በግብጽ ይኖሩ የነበሩት ህዝቦች በሃይል እንዲሰሩ አደረጓቸው፡፡ የእነርሱ አገልጋዮች ሆነው በግብጽ እንዲኖሩ አስገደዷቸው፡፡ ኢየሱስ ሊሰጣቸው ቃል ወደገባላቸው ምድር እንዲመለሱም አልፈቀዱላቸውም፡፡

ከብዙ አመታት በኋላ፣ የሰማዩ አባታችን የእስራኤልን ተውልድ ከግብጽ አውጥቶ እንዲመሬቸው ሙሴ የተባለውን ሰው መረጠው፡፡ ሙሴ ከግብጽ ህዝብ እንዲያመልጡ ለመርዳት የክህነት ሥልጣኑን ተጠቀሞ ነበር፡፡ ኢየሱስ ሊሰጣቸው ቃል ወደገባላቸው ምድር መርቷቸዋል፡፡ ይህ ምድር ከነአን ይባል ነበር፡፡ ዛሬ ይህ ምድር እስራኤል ተብሎ ይጠራል፡፡

## *ውይይት*

• ሙሴ የኢየሱስን ህዝቦች ከግብጽ እንዲያመልጡ ለመርዳት የተጠቀመው ሀይል ምን ነበር?

*የእስራኤል ህዝቦች በኢየሱስ ማመናቸውን አቁመው ነበር*

የእስራኤል ህዝቦች በከንዓን ምድር ለብዙ አመታት ከኖሩ በኋላ፣ በኢየሱስ ማመናቸውንና ትዕዛዛቱን ማክበር አቆሙ፡፡ ኢየሱስ ንስሃ እንዲገቡና ትዕዛዛቱን እንዲጠብቁ እንዲነግሯቸው ነቢያተን ልኮ ነበር፡፡ ኢየሱስ ከላካቸው ነቢያተ ኢሳይያስ፣ ኤሊያስ፣ እና ኤርሚያስ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ሌሎችም ብዙ ነቢያቶች ነበሩ፡፡

ነገር ግን የእስራኤል ህዝቦች ንስሃ አልገቡም ነበር፡፡ ስለዚህም የሰማዩ አባታችን ሌሎች ህዝቦች እንዲመጡና እንዲገዟቸው ፈቀደላቸው እና ምድራቸውንም ወሰዱባቸው እናም አብዛኞዎቹ ወደ ሌሎች ምድሮች ተበታተኑ፡፡ ይህ ህዝቦቹን ታዛዥ አደረጋቸው እናም ኢየሱስን እንዲያስታውሱተና እንዲታዘዙተ አድርጓቸዋል፡፡ነገር ግን ኢየሱስ በቤተልሄም ከመወለዱ ከብዙ አመታት በፊተ፣ የእስራኤል ህዝቦች እንደገና ሀጢያታኞች ሆኑ፣ እናም የሰማዩ አባታችን ሮማዊያን የተባሉተ ህዝቦች የእስራኤልን ህዝቦች እንዲማርኩ ፈቀደላቸው፡፡ ምድራቸውንና የተቀደሱ ህንጻዎቻቸውንም ተቆጣጥረውተ ነበር፡፡

## *ውይይት*

• ህዝቦቹ ለሰማይ አባታችን የገቡተን ቃል ሲረሱና መታዘዛቸውን ሲያቆሙ ምን ሆኑ?

*ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ ተከታዮቹን አደራጅቶ ነበር*

ኢየሱስ በምድር ላይ በመጣበተ ጊዜ፣ ለሰዎች የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አስተምሯል፡፡ የእርሱን ትምህርቶች የሚያከብሩ ከሆነ፣ ለዘለዓለም በኃጢያታቸው መሰቃየተ እንደሌለባቸው አስተምሮ ነበር፡፡ በእርሱ እንዲያምኑና ንስሃ እንዲገቡ ነግሯቸዋል፡፡ መጠመቅ አለባቸው ብሏል፡፡ እነርሱን ለመርዳት መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ ቃል ገብቷል፡፡ እግዚአብሔርን እንዲወዱና እንዲታዘዙተ አስተምሯቸዋል፡፡ ሌሎች ሰዎችን እንዲወዱና እንዲረዱዋቸውም አስተምሯቸዋል፡፡

በኢየሱስ ያመኑተና የታዘዙ ሰዎች ተከታዮቹ ሆነዋል፡፡ የእርሱን ህዝቦች የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በሚባል ቡድን ውስጥ አደራጅቷቸዋል፡፡ በእርሱ ቤተክርስቲያን አስተማሪና መሪ ለነበሩ ሰዎችም የክህነተ ሥልጣንን ሰጥቷቸዋል፡፡

### *ውይይት*

- ኢየሱስ ሰዎች እንዲከተሉት የረዳቸው እንዴት ነበር?
- የኢየሱስ ተከታዮች ለመሆን ሰዎች ማድረግ የሚያስፈልጋቸው ምን ነበር?

## ከኢየሱስ ተከታዮች አንዱ መሆን ታላቅ ክብር ነው

ኢየሱስን የሚከተሉ ደስተኞች ናቸው፡፡ የሰማዩ አባታችን ለነሱ ያለውን እቅድ ያውቃሉ፡፡ የሰማዩ አባታችን እንደሚወዳቸው ያውቃሉ። እሱ ኢየሱስን እንዲከተሉ እንደሚፈልግ ያውቃሉ፣ ስለዚያም ኢየሱስ ወደ እሱ እንዲመለሱ ሊረዳቸው ይችላል፡፡ ደስተኛ እንዲሆኑ ማድረግ የሚገባቸውን ነገሮች ያውቃሉ፡፡ የሚረዳቸውና የሚያጽናናቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አላቸው፡፡ ችግሮች ሲኖሩባቸው፣ ኢየሱስ እንደሚረዳቸው ያውቃሉ፡፡ ኢየሱስን ለመከተል እምነት ስላላቸው እግዚአብሔር እንደሚባርካቸው ያውቃሉ፡፡

ኢየሱስን የሚከተሉ የሰማዩ አባታችን ስለሰጣቸው ብዙ በረከቶች አመስጋኞች ናቸው፡፡ ስለዚህ በረከተ ሲጸልዩ የሰማዩ አባታችንን ያመሰግናሉ፡፡

የኢየሱስ ተከታዮች ያልሆኑ ሰዎች የኢየሱስ ተካታዮች መሆን ይችላሉ፡፡ ቅዱሳን መጻህፍትን በማንበብና የቤተክርስቲያኑን መሪዎችን በማዳመጥ ስለእሱ መማር ይችላሉ፡፡ በሱ ማመን፣ ንስሃ መግባትና፣ መጠመቅ ይችላሉ፡፡ ኢየሱስን ከታዘዙ፣ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ተከታዮች ቃል የገባውን ነገሮች ዘወተር ያገኛሉ።

### *ውይይት*

- ከኢየሱስ ተከታዮች አንዱ መሆን ታላቅ ልዩ ክብር የሆነው ለምንድነው?

### *ማጣቀሻ*

*የኢየሱስ ተከታዮች የሰማዩ አባታችንን ይወዱታል*

- የዮሐንስ ወንጌል 8፥12 (ኢየሱስ እንድንከተለው ይፈልጋል)፡፡
- 2ኛ ኔፊ 31፥12 (ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንከተልና እሱ ያደረገውን እንድናደርግ ታዘናል)፡፡
- ሞዛያ 2፥41 (የኢየሱስን ትዕዛዛት የሚያከብሩ በማንኛውም መንገድ ተባርከዋል)፡፡
- 3ኛ ኔፊ 18፥37 (ኢየሱስ ለደቀ ሙዛሙርቱ ለሌሎች የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንዲሰጡ ሀይልን ሰጥቶአቸዋል)፡፡

*ኢየሱስ የሰማዩ አባታችንን ሀይል ለተከታዮቹ ይሰጣል*


- ኦሪት ዘጸዓት 3 (ሙሴ ከሰማዩ አባታችን ስልጣን ተቀብሏል)፡፡
- ኦሪት ዘሁልቁ 27፥18–23 (ሙሴ እጁን በኢያሱ ራስ ላይ ጫነ እናም ከሰማዩ አባታችን ሥልጣንን ሰጠው)፡፡

*ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ብዙ ሰዎች በእርሱ ለምነው ትዕዛዛቱን ይከተሉ ነበር*

- ኦሪት ዘፍጥረት 12፥1–2፤ 17፥1–8 (ለኢየሱስ ተከታይ፣ አብርሃም ቃል ኪዳን ተሰጥቶታል)።
- ኦሪት ዘዳግም 28፥9–10 (እግዚአብሔር ከእስራኤል ህዝብ ጋር ቃል ኪዳን አድርጓል)።
- ትንቢተ ኤርሚያስ 23፥3–4 (እግዚአብሔር የእስራኤልን ህዝቦች ንስሃ ከገቡ በኋላ አንድ ላይ ይሰበስባቸዋል)።
- ትንቢተ ሕዝቅኤል 20፥33–36 (የእስራኤል ህዝብ ይሰበሰባል)።
- የሉቃስ ወንጌል 6፥13 (ኢየሱስ አስራ ሁለቱን ሀዋሪያቶች መረጠ)።
- የዮሐንስ ወንጌል 15፥16 (ኢየሱስ ለሀዋሪያቶቹ ሥልጣንና ሀይል ሰጥቶአቸዋል)።
- 3ኛ ኔፊ 21፥26–29 (የኢየሱስ ተከታዮች ከሁሉም ህዝቦች ይሰበሰባሉ)።

*ከኢየሱስ ተከታዮች አንዱ መሆን ታላቅ ክብር ነው*

- 2ኛ ኔፊ 31፥13 (ኢየሱስን የሚከተሉና ያስተማረውን የሚያደርጉ ልዩ በረከቶች ይጠብቃቸዋል)።
- አልማ 5፥57 (ኢየሱስን የሚከተሉ ከጻድቃን ጋር ይቆጠራሉ)።
- ሞሮናይ 7፥48 (የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች እንደ እግዚአብሔር ይሆናሉ)።



ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋሪያትን ሾሟል፡፡

# ኢየሱስ ያደራጀው ቤተክርስቲያን

*ምዕራፍ 18*

*ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ቤተክርስቲያንን አደራጅቶ ነበር፡፡ ያ ቤተክርስቲያን ምን ተብሎ ይጠራ ነበር? የእርሱን ቤተክርስቲያን የመራው ማን ነበር?*

## ኢየሱስ ላደራጀው ቤተክርስቲያን መሪ ነበር

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ቤተክርስቲያን አደራጅቶ ነበር፡፡ ይህ ቤተክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ የኢየሱስ ቤተክርስቲያን አባሎች ቅዱሳን ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ ኢየሱስ ራሱ የቤተክርስቲያኑ ራስ ነበር፡፡ እራሱ መርቶቷል፡፡ ቤተክርስቲያኑን በመምራት እንዲረዱት አስራ ሁለት ሰዎችን መርጦ ነበር፡፡ እነርሱም ሐዋሪያት ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ እነዚህ ሀዋሪያት ደግሞ ነቢያትም ነበሩ፡፡ ኢየሱስ እጁን በራሳቸው ላይ በመጫን ለእያንዳንዳቸው የክህነት ሥልጣንን ሰጥቷቸዋል፡፡ የእርሱን ስራ እንዲሰሩ አዟቸዋል። እነዚህ ሐዋሪያትና ነቢያት በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ መሪዎች ነበሩ፡፡

በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ የክህነት ሥልጣንን የተቀበሉ ወንዶች እጃቸውን በሌሎች መልካም ወንዶች ራስ ላይ ይጭኑና የክህነት ሥልጣንን ይሰጧቸዋል፡፡ ይህ የክህነት ሥልጣን ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሰው የሚተላለፍበት ብቸኛው መንገድ ነው፡፡ የክህነት ሥልጣን አይገዛም፡፡

### *ውይይት*

• የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን መሪ ማን ነበር?
• ኢየሱስን ይረዱት የነበሩ ሰዎች ምን ተብለው ይጠሩ ነበር?

## ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገ በኋላ ቤተክርስቲያኑ በምድር ላይ ቀጥሏል

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ፣ ቤተክርስቲያኑ በምድር ላይ ቀጥሏል፡፡ በአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ይመራ ነበር፡፡ አንድ ሐዋሪያ ሲሞት፣ እርሱን ለመተካት ኢየሱስ ሌሎች ሰዎችን ይመርጣል። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት፣ ኢየሱስ ለሌሎች ሐዋሪያት አዲሶቹ ሐዋሪያት ማን

መሆን እንደሚገባ አሳውቀአቸዋል፡፡ አስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ሌሎች መልካም ሰዎችን መርጠዋል እናም የኢየሱስ ቤተክርስቲያንን ስራ እንዲሰሩ ለመርዳት የክህነት ሥልጣንን ሰጥተዋቸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ሰባዎቹ፣ ሊቀ ካህናት፣ ቄሶች፣ ጳጳሶች፣ ካህናት፣ አስተማሪዎች፣ እና ዲያቆኖች ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ ተግባራቸውም በምዕራፍ 20 ተገልጿል፡፡

*ኢየሱስ በራዕይ አማካኝነት ቤተክርስቲያኑን መርቷል*

በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ኢየሱስ በምድር ላይ ላሉ ሰዎች የሚሰጠው መልዕክት ራዕይ ይባላል፡፡ ኢየሱስ የእርሱን ቤተክርስቲያን የሚመራው ለነቢያት እና ለሌሎች መሪዎች ሊያደርጉ የሚገባቸውን ነገሮች ይገልጽላቸዋል፡፡

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት፣ ዘወትር ከሐዋሪያቱ ጋር እንደሚሆን ነግሮአቸዋል። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እነርሱን ለመምራት መገናኘቱን እንደሚቀጥል ነበር።

## ውይይት

• ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ቤተክርስቲያኑን እንዴት ይመራ ነበር?

*የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እውነተኛ ተምህርቶችን ይዟል*

የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን መሪዎች በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ራዕይ ከኢየሱስ ይቀበላሉ። ለምሳሌ፣ ኢየሱስ ለሐዋሪያው ጴጥሮስ ወንጌልን ለእስራኤል ህዝብ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ህዝብ ማስተማር እንደሚገባ ነግሮታል። ኢየሱስ ለሐዋሪያው ጳውሎስ ለህዝቡ ማስተማር የሚገባውን ብዙነገሮች ነግሮታል፡፡ ኢየሱስ ለሐዋሪያው ዮሐንስ ስለወደፊቱ ብዙ ነገሮችን ነግሮታል፡፡

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፣ ሰዎችን በእርሱ እንዲያምኑ፣ ንስሐ እንዲገቡና እንዲጠመቁ አስተምሯቸዋል፡፡ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ሰጥቷቸዋል፡፡ የሰማዩ አባታችንን እንዲወዱና እንዲታዘዙት አስተምሯቸዋል፡፡ ሌሎች ሰዎችን እንዲወዱና እንዲረዱዋቸው አስተምሯቸዋል፡፡

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ፣ ሐዋሪያቶች ኢየሱስ ያስተማረውን ተመሳሳይ ነገሮች አስተምረዋል፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት መሆን የሚፈልጉ ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት እንዲኖራቸው፣ ለኃጢያታቸው ንስሐ እንዲገቡ፣ መጠመቅ እንደሚገባቸው አስተምረዋል። የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ አግኝተዋል፡፡ የሰማዩ አባታችንን መውደድና መታዘዝን ተምረዋል፡፡ ሌሎች ሰዎችን መውደድና ማገልገልን ተምረዋል፡፡

## ውይይት

• ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ምን ማድረግ አለባቸው?

የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሆኑት መንፈሳዊ ስጦታዎችን ተቀብለዋል።

ከስጦታዎቹ አንዳንዶቹ በሽተኞችን የመፈወስ ዕምነት፣ ስለወደፊቱ ክስተቶች የመናገር ችሎታ፣ እና ራዕይ የመቀበል ሀይል ናቸው፡፡

### ውይይት

• አንዳንድ መንፈሳዊ ስጦታዎች ምን ምንድን ናቸው?

## የኢየሱስ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ አልቆየም

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከተመለሰ በኋላ፣ ሐዋሪያቶቹ ቤተክርስቲያንን ይመሩ ነበር፡፡ ብዙ ሰዎች የቤተክርስቲያኑ አባላት ሆኑ፡፡ ነገር ግን አንዳንድ አባላቶች ኢየሱስና ሀዋሪያት በስተማሯቸው ነገሮች ፋንታ፣ ስህተተ ነገሮችን ማመንና ማስተማር ጀመሩ፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች የሰማዩ አባታችን የስጋና አጥንቶች አካል የለውም ብለው አስተምረዋል፡፡

ኃጢያተኞች የቤተክርስቲያኑን መሪዎችና ሌሎች የቤተክርስቲያን አባላትን ማሳደድ ጀመሩ፡፡ ሀጢያተኞቹ ሰዎች ሀዋሪያትንና ሌሎች የክህነት ሥልጣን ያላቸውን መሪዎች ገድለዋል፡፡ ብዙ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላትንም ገድለዋል፡፡

የኢየሱስን እውነተኛ ትምህርቶች የሚያምን እስኪጠፋ ድረስ ሰዎች በብዛተ ስህተተ ትምህርቶችን ያስተምሩ ነበር፡፡ ማንም የክህነተ ሥልጣን አልነበረውም፣ ስለዚህ ማንም የኢየሱስን ስራ በምድር ላይ መስራት ወይም ለሰማዩ አባታችን ልጆች ሁሉ ከኢየሱስ መመሪያዎችን መቀበል የሚችል አልነበረም። የኢየሱስን እውነተኛ ትምህርቶች የሚያምን በጠፋበትና ማንም የእርሱን ሥልጣን ያልያዘበት ጊዜ የክህደተ ዘመን ይባላል፡፡

በክህደተ ዘመን ጊዜ፣ ሰዎች ኢየሱስ ካደራጀው ቤተክርስቲያን የተለየ ቤተክርስቲያኖችን አደራጅተው ነበር፡፡ ኢየሱስ ያላስተማረውን ነገሮች ያስተምሩ ነበር፡፡ የክህነተ ሥልጣን አልነበራቸውም፡፡ በኢየሱስ ቤተክርስቲያን ከሚደረገው ስርዓተ የተለየ ያደርጉ ነበር፡፡ ከኢየሱስ ምንም ራዕይ አልነበራቸውም፡፡ ኢየሱስና ሀዋሪያቶች እነርሱን እንዳስተማሯቸው ማንኛውንም የወንጌል ትዕዛዛተ አያስተምሩም፡፡ ነቢያተ ይህ ሁሉ እንደሚሆን ተናግረዋል፡፡

### ውይይት

• ክህደተ የተከሰተው እንዴተ ነበር?

## ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን ወደ ምድር እንደሚልክ ቃል ገብቷል

ኢየሱስ ሰዎች የእርሱን ሀይልና እውነተኛ ትምህርቶችን እንደሚያጡ ያውቀ ነበር፡፡ ስለዚህ እውነተኛው ቤተክርስቲያን በምድር ላይ እንደገና የሚደራጅበትን መንገድ አዘጋጅቷል፡፡

ሀዋሪያው ዮሀንስ ወንጌል መቼ ተመልሶ እንደሚመጣ በራዕይ ተመልክቶ ነበር፡፡ ኢየሱስ ለሰዎች ስለሰማዩ አባታችን እውነቱን እንዲያስተምራቸው መላዕክቱን እንደሚልክ ተመልክቷል፡፡ ኢየሱስ ሁሉም የሰማዩ አባታችን ልጆች ወንጌልን፣ የክህነተ ሥልጣንን፣ እና ወደ ሰማዩ አባታችን መመለስ እንዲችሉ ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ሁሉ መቀበል እንደሚችሉ ያረጋግጣል፡፡

### ውይይት

• ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን እንደገና በምድር ላይ የሚደራጅበትን መንገድ ያዘጋጀው ለምን ነበር?

## *ማጣቀሻ*

*ኢየሱስ ላደራጀው ቤተክርስቲያን ራስ ነበር*

- ሉቃስ ወንጌል 9፥1 (ኢየሱስ ለሐዋሪያቶቹ ኃይል ሰጥቷቸዋል።)
- 3ኛ ኔፊ 27፥8 (የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሚጠራው በስሙ ነው።)

*ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገ በኋላ ቤተክርስቲያኑ በምድር ላይ ቀጥሏል*

- የማቴዎስ ወንጌል 16፥16–18 (ከኢየሱስ ሞት በኋላ ቤተክርስቲያንን እንዲመራ ጴጥሮስ ተመረጠ።)
- ማቴዎስ 28፥20 (ኢየሱስ ሁልጊዜ ከሐዋሪያት ጋር ሊሆን ቃል ኪዳን ገብቷል።)
- የማርቆስ ወንጌል 3፥14 (ኢየሱስ ሐዋሪያት እንዲሆኑ አስራ ሁለት ሰዎችን መረጧል።)
- የማርቆስ ወንጌል 16፥17–18፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥4–11 (የኢየሱስ ተከታዮች መንፈሳዊ ስጦታዎች ይኖራቸዋል።)
- ሉቃስ ወንጌል 10፥1 (ኢየሱስ ወንጌልን እንዲሰብኩ ሰባ ሰዎችን መረጧል።)
- የዮሐንስ ወንጌል 14፥26 (በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት ኢየሱስ ዘወትር ከሀዋሪያት ጋር ይሆናል።)
- የሐዋሪያት ሥራ 1፥23–26 (የሞተውን ሐዋሪያ ለመተካት አዲስ ሐዋሪያ ተመርጧል።)
- የሐዋሪያት ሥራ 8፥18–20 (ጴጥሮስ የክህነት ሥልጣን እንደማይገዛ ለአንድ ሰው ነገሮታል።)
- የሐዋሪያት ሥራ 10 (በራዕይ አማካኝነት፣ ጴጥሮስ ወንጌል ለማናቸውም ሰው እንደሆነ ተምሯል።)
- የሐዋሪያት ሥራ 14፥23 (ቄሶች በስብሰባዎች ውስጥ *ይሾማሉ።)
- ኤፌሶን 2፥19–20 (ኢየሱስ በሀዋሪያትና ነቢያት የሚመራው፣ ቤተክርስቲያኑ ዋና የማዕዘን ድንጋይ ነው።)
- ኤፌሶን 4፥11–13 (የተሾሙ ባለስልጣናት የማዕረግ ሥም የተሰጣቸው በኢየሱስ ነው።)
- የያዕቆብ መልዕክት 5፥14–15 (በሽተኛ የክህነት ሥልጣን ባለው ሰው ሊባረኩ ይችላል።)

*የኢየሱስ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ አልቀየም*

- ትንቢተ አሞጽ 8፥11–12 (ሰዎች እውነትን ይፈልጋሉ፣ የት እንደሚያገኙት አያውቁም።)
- የማቴዎስ ወንጌል 24፥9–12 (ሀዋሪያቶች ይገደላሉ።)
- 2ኛ ተሰሎንቄ 2፥3–4 (የክህደት ዘመን አስቀድሞ ተነግሯል።)
- 2ኛ ጴጥሮስም 2፥1 (ሃሰተኛ ነቢያት ውሸት አስተምረዋል።)

*ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን በምድር ላይ እንደሚመልስ ቃል ገብቷል*

- የሐዋሪያት ሥራ 3፥20–21 (ኢየሱስ ወንጌሉን በምድር ላይ ለመመለስ ይመለሳል።)
- የዮሐንስ ራዕይ 14፥6 (ወንጌሉን ለመመለስ መልአክ ይረዳል።)
- ዳንኤል 2፥44–45 (የሰማዩ አባታችን መንግስት በመጨረሻዎቹ ዘመናት ይመሰረታል።)

# የዛሬይቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን

*ምዕራፍ 19*

---

*እውነተኛውን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ዛሬ ከየት ልናገኝ እንችላለን?*

**ለብዙ ዓመታት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ አልነበረም**

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑን አደራጀ። ቤተ ክርስቲያኑ እርሱ ወደ ሰማይ ከተመለሰ በኋላ ለተወሰነ ጊዜ በምድር ላይ ቆይቷል። ህዝቡ እውነተኛ ትምህርቱን ማስተማርና ማመን ሲያቆም፣ በኋላ ኢየሱስ የክህነት ስልጣን እና ቤተ ክርስቲያኑን ከምድር ወሰደ፡፡


ለብዙ ዓመታት፣ ህዝቦች ያለ እውነተኛ ወንጌልና የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ኖረዋል፡፡ ህዝቦች በራሳቸው ዛሳብ ላይ ተመርኩዘው እና ከመጽዛፍ ቅዱስ ጥቂት ትምህርት በመያዝ ብዙ ቤተ ክርስቲያኖችን አደራጁ። ነገር ግን እነዚህ ቤተክርስቲያኖች የሰማዩ አባታችን የክህነት ስልጣን የላቸውም። ሁሉም የኢየሱስ ትምህርቶች አልነበራቸውም፡፡ ከኢየሱስ የማያቋርጥ ራዕይ አልነበራቸውም። ሁሉም መንፈሳዊ ስጦታዎች የላቸውም፡፡

ከጊዜ በኋላ ሰዎች ስለ ሰማያዊ አባታችን እውነት ለማወቀ መሻት ጀመሩ፡፡ ስለ የሰማይ አባታችን ትምህርት እና እውነት መፈለግ ጀመሩ፡፡ አንዳንዶቹ እውነተኛው ወንጌልና የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ እንዳልነበረ ተረዱ። የሰማይ አባታችን እውነተኛውን ወንጌልንና የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ወደ ምድር ለመመለስ ጊዜው የደረሰ መሆኑን ያውቁ ነበር፡፡

### *ውይይት*

- ኢየሱስ ለምን የክህነት ስልጣንን ከምድር ላይ ወሰደ?
- እነዚያ ሕዝቦች ያደራጇቸው ቤተክርስቲያናት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ለምን አልሆኑም?

---



የሰማይ አባታችንና ኢየሱስ ዮሴፍ ስሚዝን ጎበኙተዋል፡፡

## የሰማይ አባታችን እውነተኛይቱን ቤተክርስቲያን ለመመለስ የገባልንን ቃልኪዳን ጠብቋል

የሰማዩ አባታችን ሁሉንም ልጆቹን ይወዳል፡፡ እነርሱም ከሞቱና ከተነሱ በኋላ ከእርሱ ጋር ለመኖር ማድረግ የሚገባቸውን እንዲያውቁ ይፈልጋል፡፡ እውነተኛይቱን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከምድረ ገጽ ከመውሰዱ በፊት፣ ይህ ነገር እንደሚሆን ኢየሱስ ለነቢያቶችና ለሐዋሪያቶች ገልፆላቸዋል፡፡ በአንድ ወቀት ደግሞ ቤተክርስቲያኑን ወደ ምድር እንደሚመልስ ቃል ገብቷል፡፡ ይህንን የሚያደርገው እውነተኛውን ወንጌሉን ለመቀበል ዝግጁ የሆኑ ሰዎች እንደገና ሲኖሩ ነው፡፡

*ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን ወደ ምድር መልሷል*

ኢየሱስ በምድር ላይ በኖረበት ወቀት ቤተክርስቲያኑን እንደ አደራጀው ዓይነት ሥልጣንና በረከተ ያለውን ቤተክርስቲያን ወደ ምድር መልሷል። ትዕዛዛቱን ለመጠበቀ ፍቃደኛ የሆነ እያንዳንዱ ሰው የቤተክርስቲያኑ አባል መሆን ይችላሉ።

*የሰማዩ አባታችን ዮሴፍ ስሚዝ ቤተክርስቲያኑን በመመለስ እንዲረዳው መረጠው*

በ1820፣ ኢየሱስ እውነተኛውን ወንጌልና ቤተክርስቲያን ወደ ምድር መመለስ ጀመረ፡፡ ዮሴፍ ስሚዝ የተባለው ወጣት ልጅ የትኛው ቤተክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንደሆነ ለማወቀ ፈለገ፡፡ እርሱም አንድ ሰው አንድን ነገር ለማወቀ ከፈለገ፣ ሰማያዊ አባታችንን መጠየቀ እንዳለበት ከመፅሐፍ ቀዱስ አነበበ። እርሱም የትኛውን ቤተክርስቲያን መከተል እንደሚገባው የሰማይ አባታችንን ለመጠየቀ ወሰነ፡፡ እርሱም በቤቱ አቀራቢያ ወደሚገኘው ጫካ ውስጥ ገብቶ የትኛውን ቤተክርስቲያን መከተል እንዳለበት የሰማዩ አባታችንን በፀሎት ጠየቀ። ለዮሴፍ ስሚዝ የሰማዩ አባታችንና ኢየሱስ ተገለጡለት፡፡ የሰማዩ አባታችን ዮሴፍ ኢየሱስን እንዲሰማና እንዲታዘዘው ነገረው፡፡ ከዚያም ኢየሱስ ዮሴፍን ማናቸውንም ቤተክርስቲያን እንዳይከተል ነገረው፡፡ እውነተኛ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ እንደሌለ ነገረው።

እውነተኛ ወንጌልና የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከምድር ላይ ከተወሰደበተ ጊዜ ጀምሮ የዚህን ዓይነት ራዕይ ከሰማዩ አባታችን የተቀበለ ማንም የለም። ከዚያን ራዕይ ወዲህ ብዙ ሌሎች ራዕዮች ታይተዋል። የሰማዩ አባታችን ዮሴፍ ስሚዝን በምድር ላይ እንዲወክለው መረጠው፡፡ ኢየሱስ በእርሱ አማካኝነት እውነተኛውን ወንጌልና የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን መለስ፡፡

### ውይይት

• ዮሴፍ ስሚዝ ራዕይ ያየው ለምንድን ነው?

*የክህነት ሥልጣን ተመልሷል*

የክህነት ሥልጣን በ1829 ወደ ምድር ተመለሰ፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ ከሰማይ መጥቶ እጁን በዮሴፍ ራስ ላይ በመጫን የተወሰነ ክህነት ስልጣንን ሰጦትታል። ይህ የክህነት ሥልጣን አሮናዊ

የክህነት ስልጣን ይባላል። መጥምቁ ዮሐንስ፣ ይህንን የክህነት ሥልጣን የመለሰው፣ ኢየሱስንም ያጠመቀው ሰው ነበር፡፡ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ፣ ሶስቱ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ሐዋሪያት፣ ደግሞ መጥተው ለዮሴፍ ስሚዝ ተጨማሪ የክህነት ሥልጣን ሰጡት፡፡ ይህም የክህነት ሥልጣን መልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ተብሎ ይጠራል።

ሌሎች ነቢያቶች፣ ሙሴና ኤልያስን ጨምሮ፣ መጥተው ለዮሴፍ ስሚዝ ሌሎች የተቀደሱ ሥራዎችን እንዲሰራ ሥልጣንን ሰጥተውታል፡፡ ከሰማይ አባታችን የተሰጠው ሥልጣን ወንጌልን እንዲያስተምር፣ የተቀደሱ ሥራዎችን እንዲሰራ፣ እና ቤተክርስቲያኒቱን በምድር ላይ እንደገና እንዲመራ ነው፡፡

## *ውይይት*

• ዮሴፍ ስሚዝ መጀመሪያ የክህነት ሥልጣንን እንዴት ተቀበለ?

*ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን እንደገና አደራጅቷል*

በሚያዝያ 6 ቀን 1830 ዓ.ም፣ ኢየሱስ በራዕይ አማካኝነት፣ ዮሴፍ ስሚዝ ቤተክርስቲያኒቱን እንደገና እንዲያድራጅ መራው፡፡ ኢየሱስ በምድር ላይ ሲኖር የቤተክርስቲያኑ እራስ ነበር፡፡ አሁንም የቤተ ክርስቲያኑ እራስ እርሱ ነው፡፡ የእርሱ ቤተ ክርስቲያን አባላት አሁንም ቀዱሳን ተብለው ይጠራሉ።

ዛሬ ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን የኋለኛው ቀን ቀዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ብሎ ሰይሞታል፡፡ የኋለኛው ቀን የሚለው ቃል በምድር ላይ በኋለኛው ጊዜ ያለውን ይህንን ቤተክርስቲያን መሆኑን ያሳያል። ኢየሱስ በአለም ላይ የምደሰተበት ብቸኛው እውነተኛ ቤተክርስቲያን ይህ ነው ብሏል።

ኢየሱስ በምድር ላይ ቤተክርስቲያኑን የሚመራ ነቢይ ይመርጣል። ኢየሱስ ይህንን ነቢይ ይመራዋል፡፡ ለዚህ ነብይ ቤተክርስቲያኑን እንዲመራ ሥልጣን ይሰጠዋል፡፡ ዮሴፍ ስሚዝ የመጀመሪያው የኋለኛው ቀን ቀዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነብይ ነበረ። የቤተክርስቲያኑ ነቢይ የቤተክርስቲያን ፕሬዚዳንትም ተብሎ ይጠራል፡፡ ፕሬዚዳንቱ የሚረዱት ሰዎች ይኖሩታል። እነርሱም አማካሪዎች ይባላሉ፡፡ ነቢዩ ሲሞት፣ ኢየሱስም አዲስ ነቢይ ይመርጣል፡፡

ኢየሱስ በተጨማሪ ቤተክርስቲያኑን ለመምራት እንዲረዱ አስራሁለት ሐዋሪያትን መረጠ፣ ሌሎች ጥሩ ሰዎች እና ወንዶች ልጆችም የክህነት ሥልጣንን ይቀበላሉ። እነርሱም ሐዋሪያትንና ነብያትን ይረዳሉ፡፡ እነርሱም ሊቀካህናት፣ ሽማግሌዎች፣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ቄሶች፣ አስተማሪዎች፣ እና ዲያቆናች ይባላሉ፣ ልክ እንደጥንቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አጠራር ይጠሩ ነበር፡፡

ኢየሱስ ለዮሴፍ ስሚዝ ቤተክርስቲያኑ እንዴት መዋቀር እንዳለበት ነግሮታል፡፡ በአንድ ክልል ውስጥ ቤተክርስቲያኑ ተሟልቶ ሲደራጅ፣ ያ ክልል *ስቴክ በመባል ይታወቃል፡፡ ፕሬዚዳንቱ ስቴኩን ይመራል። እርሱን የሚረዱ ሁለት አማካሪዎች ይኖሩታል፡፡

ስቴክ በአነስተኛ ክልሎች ይከፈላል፡፡ እነዚህ ክልሎች *ዋርድ በመባል ይታወቃሉ፡፡ የክህነት መሪው ዋርዱን የሚመራ፣ ኢጲስ ቆጶስን ይጠራል እሱን ለመርዳት ሁለት አማካሪዎች ይኖሩታል፡፡

ገና ስቴክ ባልተደራጀበት ክልሎች፣ በቀርንጫፎች የተገነቡ *ዲስትሪክቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ቀርንጫፎች በፕሬዚዳንትና በሁለት አማካሪዎች ይመራሉ። ወንጌልን የሚያስተምሩ ብዙ ሚሲዮናዊያን ያሉበት ክልሎች *ሚሲዮን ተብለው ይጠራሉ።

*የክህነት ሥልጣን ያላቸው ወንዶች በቡድን ይደራጃሉ*

የክህነት ሥልጣን ያላቸው የተደራጁ ወንዶች ቡድን ተብለው ይጠራሉ። የክህነት ስልጣን ቡድን በክህነት ስልጣን ውስጥ ተመሳሳይ የክህነት ሥልጣን ያላቸው ወንዶች ስብስብ ነው፡፡ እርስበርስ እና ሌሎች ሰዎችን ለመርዳት ይተባበራሉ።

## *ውይይት*

- የአሁኑ ወቀት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እራስ ማን ነው?
- ቤተክርስቲያንን በመምራት እንዲረዱ የተጠሩት ሰዎች ምን ተብለው ይጠራሉ?

## የአሁኑ ወቀት ቤተክርስቲያን የተደራጀው ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ እንዳደራጀው ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ነው

*አሁንም ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን በራዕይ ይመራል፡፡*

በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት፣ ኢየሱስ እንዴት ቤተክርስቲያኑን መምራት እንዳለበት ለነቢዩ ይነግራል። ለሐዋሪያት እና ሌሎች የቤተክርስቲያኑ መሪዎችም እንዲሰሩ የሚፈልገውን ይገልጽላቸዋል፡፡ በራዕይ አማካኝነት፣ ኢየሱስ የቤተክርስቲያኑን አባላት ያለማቋረጥ ይመራቸዋል፡፡

*ማንኛውም ሰው የቤተክርስቲያኑ አባል መሆን ይችላል*

ማንኛውም ሰው ኢየሱስ በምድር ላይ እያለ ሰዎች ቤተክርስቲያኑን በተከተሉበት ተመሳሳይ ሁኔታ አሁንም የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን ይችላል፡፡ እሱ ወይም እሷ በኢየሱስ ማመንና ንስሃ መግባት አለባቸው። ግለሰቡ መጠመቅ ይገባዋል። ግለሰቡ ከተጠመቀ በኋላ፣ እሱ ወይም እሷ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ይቀበላሉ፡፡

## *ውይይት*

- በአሁኑ ወቀት የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን ለመከተል ምን ማድረግ ይገባናል?

*የአሁኑ ወቀት የቤተክርስቲያኑ አባላት መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይቀበላሉ*

ኢየሱስ ሁልጊዜ ለቤተክርስቲያኑ አባላት መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይሰጣል፡፡ እነዚህ ሁሉ መንፈሳዊ ሃይሎች ዛሬ በቤተክርስቲያን ውስጥ ይገኛሉ፡፡

### ውይይት

• ከመንፈሳዊ ስጦታዎች ጥቂቶቹ ምን ምንድን ናቸው? (ምዕራፍ 16ን ይመልከቱ)

*ኢየሱስ እውነተኛ ትምህርቶቹን መልሷል*

ኢየሱስ እርሱና ሐዋሪያቱ ያስተማሩትን ትምህርቶች መልሷል፡፡ መሰረታዊ ትምህርቶቹ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን፣ ንሥሐ መግባት፣ ጥምቀት እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ናቸው፡፡ ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያኑ የሠጠው አንዳንድ አስፈላጊ እውነቶች፣

1. የሰማይ አባታችን የሥጋና የአጥንት አካል አለው።
2. እኛ በሰማይ የሚገኝ አባታችን የመንፈስ ልጆች ነን። በዚህ ምድር ላይ ከመወለዳችን በፊት ከእርሱ ጋር በመንፈስ በሰማይ ኖረናል።
3. አዳም ላደረገው ሳይሆን የምንቀጣው ለራሳችን ሃጢያት ብቻ ይሆናል፡፡ ብዙ ሰዎች አዳምና ሔዋን የተከለከለውን ፍሬ በመብላታቸው ምክንያት፣ እኛ፣ ልጆቻቸው ስንወለድ ኃጢያተኞች ነን ብለው ያምናሉ። ይህ እውነት አይደለም፡፡ ህፃናት ሲወለዱ ሐጢአተኞች አይደሉም። የዋሆች ናቸው። ስለዚህ፣ እስከ ስምንት ዓመት ዕድሜ ድረስ መጠመቀ አያስፈልጋቸውም፡፡
4. አንድ ሰው *ሥርዓቶችን ለማከናወን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ የክህነት ሥልጣን ሊኖረው ይገባል (ምዕራፍ 21 ይመልከቱ)።

### ውይይት

• ኢየሱስ ለሕዝቦች እንደገና የሰጠው ትምህርቶች አንዳንዶቹ ምን ምንድን ናቸው?

### የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በፍጸፁም እንደገና ከምድር አይወሰድም

እውነተኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አሁን ያለው፣ የክህነት ሥልጣን፣ እና ወደ ምድር የተመለሰው እውነት ነው፣ ዳግም በፍፁም ከምድር አይወሰዱም። የሰማይ አባታችን በምንም ዓይነት ሊጠፋ የማይችል መንግሥት አቋቁማለሁ ብሏል። ይህም መንግሥት የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነው፡፡ እርሱም ለዘለዓለም ይዘልቃል፡፡

ብዙ ሰዎች የኋለኛውን ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ተከታይ ሆነዋል። በዓለም በብዙ ሀገሮች የቤተክርስቲያኑ አባላት ይገኛሉ። የበለጠ ብዙ ሰዎች የቤተክርስቲያኑ አባል መሆንን ይቀጥላሉ፣ የሰማዩ አባታችን ልጆች ሁሉ ወንጌሉን ሰምተውና ለመቀበል ዕድል ያገኛሉ፡፡

### ውይይት

• ሌሎችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሠምተው ለመከተል እንዲችሉ ለመርዳት እርስዎ ምን ማድረግ ይችላሉ?

## ማጣቀሻ

*ለብዙ ዓመታት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ አልነበረም*

- ትንቢተ ኢሳይያስ 24፥5 (ሕዝቡ እውነተኛውን ትምህርቶች ይለውጣል።)
- ትንቢተ አሞፅ 8፥11–12 (ነቢዩ ህዝቡ የሰማይ አባታችንን እውነተኛውን ቃል እንዴት ማግኘት እንዳለበት አያውቅም አለ።)
- 4ኛ ኔፊ. 1፥26–29 (ሕዝቦች የራሳቸውን ቤተክርስቲያን ሰሩ፡፡)

*የሰማይ አባታችን እውነተኛይቱን ቤተክርስቲያን ለመመለስ የገባልንን ቃል ኪዳን ጠብቋል*


- ትንቢተ ኢሳይያስ 2፥2–4 (የሰማይ አባታችን መንግስቱን በኋለኛው ቀናት ይመሰርታል።)
- 2ኛ. ኔፊ 3፥6–15 (ዮሴፍ የተባለው ነቢይ እውነትን ወደ ምድር ለመመለስ ረድቷል፡፡)

*የአሁኑ ወቀት ቤተክርስቲያን የተደራጀው ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበርበት ጊዜ እንዳደራጀው ዓይነት ቤተክርስቲያን ነው*

- የሐዋርያት ሥራ 3፥20–21 (ነቢያት ሁሉ ነገር ይመለሳል ብለዋል፡፡)
- 2ኛ ኔፊ 29፥9 (ኢየሱስ ትናንትም፣ ዛሬም እና ለዘለዓለም አንድ ነው፡፡)
- ሞሮናይ 10፥7–19 (ኢየሱስ ትናንትም፣ ዛሬም፣ ለዘለዓለም፣ የሚሰጣቸው መንፈሳዊ ስጦታዎች አንድ ዓይነት ናቸው።)

*የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በፍፁም እንደገና ከምድር አይወሰድም*

- ትንቢተ ዳንኤል 2፥44–45፤ የማቴዎስ ወንጌል 21፥43 (የሰማይ አባታችን የማይጠፋ ዘልዓለማዊ መንግሥት ለመመስረት ቃል ገብቷል፡፡)




*የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን ክርስቶስን እንደ ሊብይ የማዕዘን ድንጋይ እናም ሐዋርያቶችና ነቢያቶችን እንደ መሰረተ አድርጎ ማነፃፀር ይቻላል።*

# የክህነት ሥልጣን ድርጅት

*ምዕራፍ 20*

*የሰማይ አባታችንን ስራ ለማከናወን አንድ ሰው ሥልጣንን እንዴት ማግኘት ይችላል?*

**አንድ ሰው የክህነት ሥልጣን ሲኖረው የሰማይ አባታችንን ወክሎ መስራት ይችላል**

የሰማይ አባታችን የክህነት ሥልጣንን ብቃት ላላቸው አዋቂ ወንዶች እና ወንድ ልጆች የእርሱን ሥራ በምድር ላይ እንዲያከናውኑ የሚሰጣቸው ስልጣን ነው። እርሱም ይህንን ሥልጣን ለኢየሱስ ሰጠ። ኢየሱስም ይህን ሥልጣን በምድር ላይ ላሉ ወንዶች ሰጠ፡፡ የክህነት ሥልጣን ያላቸው አዋቂ ወንዶችና ወንድ ልጆች የሰማዩ አባታችንን እና ኢየሱስን ይወክላሉ፡፡ ሌሎች አዋቂ ወንዶች እና ወንድ ልጆች መሥራት የማይችሉትን ነገሮች እነርሱ መስራት ይችላሉ። ሚሲዮናዊ በመሆንም እውነተኛውን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ማስተማር ይችላሉ፡፡ የታመሙትንም ሰዎች መባረክ ይችላሉ፡፡ የተቀደሱ ሥራዎችንም በቤተክርስቲያን ውስጥ ማከናወን ይችላሉ።

ኢየሱስ አንድ ሰው የክህነት ሥልጣንን ለሌላ አዋቂ ወንድ ወይም ወንድ ልጅ የሚሰጥበትን መንገድ ነግሮናል። አንድ የክህነት ሥልጣን ያለው ሰው እጁን በአዋቂ ወንድ ወይም በወንድ ልጅ እራስ ላይ ይጭናል። ከዚያም እርሱ ባለው የቀስና ሥልጣን እና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለእርሱ የክህነት ሥልጣንን ይሰጠዋል፡፡

የኢየሱስን ትዕዛዛት የሚታዘዝ አዋቂ ወንድ ወይም ወንድ ልጅ ብቻ የክህነት ስልጣንን ማግኘት ይችላል፡፡ ኢየሱስ አዋቂ ወንዶችና ወንዶች ልጆች የእርሱን ትዕዛዛት የሚታዘዙ ከሆነ ብቻ ሥራውን እንዲያከናውኑ ይፈቅድላቸዋል፡፡

የክህነት ሥልጣንን በትክክለኛ መንገድ ከሚጠቀም አዋቂ ወንድ ወይም ወንድ ልጅ በስተቀር ታላቅ ሰው በምድር ላይ የለም፡፡

### *ውይይት*

- የክህነት ሥልጣን ምንድነው?
- የክህነት ሥልጣንን መቀበል የሚችለው ማን ነው?

## የክህነት ሥልጣን በሁለት ክፍሎች ይከፈላል

ሁለቱ የክህነት ሥልጣን ክፍሎች አሮናዊ የክህነት ሥልጣንና የመልከ ዔዴቀ የክህነት ሥልጣን ናቸው። አንዳንድ ጊዜ አሮናዊ የክህነት ሥልጣን አነስተኛ የክህነት ሥልጣን ተብሎ ይጠራል። የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን አንዳንድ ጊዜ ትልቁ የክህነት ሥልጣን ተብሎ ይጠራል።

*አሮናዊ የክህነት ሥልጣን*

አሮናዊ የክህነት ሥልጣን፣ የነቢዩ ሙሴ ወንድም፣ በአሮን ስም የሚጠራ ነው፡፡ አሮን በሙሴ ጊዜ የነበረ መሪ ነው።

አንድ ወንድ ወይም አንድ ወንድ ልጅ ቢያንስ ዕድሜው 12 ዓመት ከሞላው አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን መቀበል ይችላል፡፡ አዋቂ ወንዶች እና ወንዶች ልጆች አሮናዊ የክህነት ሥልጣን ያላቸው ሰዎችን ማስተማር ይችላሉ፡፡ አንዳንድ አሮናዊ የክህነት ሥልጣን ያላቸው ሰዎችን ማጥመቀ ይችላሉ። እነርሱም ሰዎች ኢየሱስን እንዲያስታውሱት ይረዷቸዋል። በብዙ መንገድም ሰዎችን መርዳት ይችላሉ፡፡

*የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን*

የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን መልከ ጼዴቀ በሚባል ሰው ሥም የተሰየመ ነው፡፡ መልከ ጼዴቀ የክህነት ሥልጣን የነበረው በጣም ፃድቀ ሰው ነበር። እሱም የኖረው በአብረሃም ጊዜ ነበር። ሊቀካህን ነበር። የክህነት ሥልጣን በስሙ ከመጠራቱ አስቀድሞ፣ በእግዚአብሄር ልጅ ትዕዛዝ መሰረት፣ ቀዱስ የክህነት ሥልጣን ተብሎ ይጠራ ነበር ሰዎች የሰማዩን አባታችንን ሥም ብዙ ጊዜ እንዳይጠቀሙ ለማገድ የክህነት ሥልጣኑ ሥም ወደ መልከ ጼዴቀ ተለውጧል።

አንድ ሰው የመልከጼዴቀ ሥልጣንን ለመያዝ ቢያንስ ዕድሜው 18 ዓመት መሙላት አለበት፡፡ የመልከጼዴቀ ክህነት ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ለቤተክርስቲያኑ አባላት ቡራኬ ለመስጠት ሃይል አላቸው፡፡ እነዚህን ቡራኬዎች በሚሰጡበት ጊዜ ኢየሱስ ማወቀ የፈለጉትን እና መናገር ያለባቸውን ነገሮች ይገልጽላቸዋል።

### *ውይይት*

• በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉት ሁለት የክህነት ስልጣኖች ምንድን ናቸው?

## የእያንዳንዱ የክህነት ሥልጣን እና ሃላፊነቶች

አሮናዊ የክህነት ሥልጣን ያላቸው አዋቂ ወንዶች እና ወንዶች ልጆች በዚህ የክህነት ሥልጣን ውስጥ በክህነት ኃላፊነት የተሾሙ የሚከተሉትን ነገሮች ለማድረግ ሃይል አላቸው፡፡

1. ወንጌልን ማስተማር።
2. ማጥመቀ።
3. *ቀዱስ ቁርባንን ማዘጋጀት፣ መባረክ፣ እና ማሳለፍ።

4. የመልከጼዴቀ ክህነት ሥልጣን ያላቸውን የቤተክርስቲያን አባላትን በጉብኝት እና በመርዳት ማገዝ፡፡
5. አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን ለሌሎች መስጠት።

የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ያላቸው ወንዶች እነዚህን ነገሮች ለማድረግ ሥልጣን አላቸው፡፡

1. ቤተክርስቲያንን መምራት።
2. ወንጌልን መስበክ።
3. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን መስጠት።
4. ልዩ ቡራኬን መስጠት።
5. ህፃናትን መባረክና መሰየም።
6. ህሙማንን መፈወስ፣
7. ለሌሎች የክህነት ስልጣንን መስጠት።
8. አሮናዊ የክህነት ሥልጣን ያላቸው ሰዎች እና ወንዶች ልጆች ማድረግ የሚችሉትን ነገሮች ሁሉ ማድረግ፡፡

አንድ ሰው የክህነት ሥልጣንን ሲቀበል፣ በክህነት ሥልጣን ሹመት ውስጥ ለኃላፊነት ተመደበ ማለት ነው። ሁለቱም አሮናዊ የክህነት ሥልጣንና የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን በርካታ ሃላፊነቶች አሏቸው። እያንዳንዳቸውም ልዩ ተግባሮች አሉዋቸው፡፡

## ውይይት

• የመልከጼዴቀ የክህነት ስልጣን ያላቸው ምን ለመስራት ሥልጣን ይኖራቸዋል?
• የአሮናዊ የክህነት ሥልጣን ያላቸው ምን ለመስራት ሥልጣን ይኖራቸዋል?

*የአሮናዊ የክህነት ሥልጣን ኃላፊነቶችና ተግባሮቻቸው*

የአሮናዊ የክህነት ሥልጣን ኃላፊነቶች ዲያቆን፣ አስተማሪ፣ ካህን፣ ኤጲስ ቆጶስ ናቸው፡፡

ዲያቆን

የቤተክርስቲያኑ ወንድ አባል ዕድሜው ቢያንስ 12 ዓመት የሞላው የክህነት ሥልጣን ሊሰጠው እናም በድቁና ሊሾም ይችላል። እርሱም የኢየሱስን ትዕዛዛት እና የቤተክርስቲያኑን ህግ መታዘዝ ይኖርበታል፡፡

እነዚህ የዲያቆን ተግባራት ናቸው፤

1. ቅዱስ ቁርባንን ማሳለፍ።
2. መሪዎችን መርዳት።
3. በአሮናዊ የክህነት ሥልጣን ውስጥ ያሉትን አስተማሪዎች ሲታዘዙ ተግባሮቻቸውን ለማከናወን መርዳት፣

አንድ ዲያቆን ለሌላ ሰው የክህነት ሥልጣን መስጠት አይችልም፡፡ ማንንም ሰው ማጥመቅ አይችልም። ቅዱስ ቁርባንንም መባረክ አይችልም፡፡

አስተማሪ

የቤተክርስቲያን ወንድ አባል ቢያንስ ዕድሜው 14 ዓመት የሆነው የክህነት ሥልጣን መቀበልና በአስተማሪነት ሊሾም ይችላል፡፡ የኢየሱስን ትዕዛዛት እና የቤተክርስቲያንን ሕጎች መታዘዝ አለበት፡፡

እነዚህ የአስተማሪ ተግባራት ናቸው፣

1. የቤተክርስቲያንን አባላት አካላዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች እንዲያገኙ በመርዳት መጠበቅ።
2. አባላት የኢየሱስን ትዕዛዛት እንዲጠበቁ መርዳት፡፡
3. የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ያላቸውን በመርዳት ከእነርሱ ጋር ቤተሰቦችን በመጎብኘትና እነዚህን ቤተሰቦች ከእነርሱ ጋር አብሮ በመጎብኘትና የኢየሱስን ትዕዛዛት እንዲያከብሩ በማስተማር መርዳት ነው፡፡
4. ቅዱስ ቁርባንን ማዘጋጀት፡፡
5. አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ ዲያቆን የሚያከናውናቸውን ነገሮች ሁሉ ይሰራል፡፡

አንድ አስተማሪ የክህነት ሥልጣንን ለሌላ ሰው መስጠት አይችልም፣ ማንንም ማጥመቅም አይችልም። ቅዱስ ቁርባንንም መባረክ አይችልም።

ካህን

የቤተክርስቲያኑ ወንድ አባል ዕድሜው ቢያንስ 16 ዓመት የሆነው የክህነት ሥልጣንን ለመቀበልና በቀስና ሊሾም ይችላል። እርሱም የኢየሱስን ትዕዛዛት እና የቤተክርስቲያንን ሕጎች ማክበር ይገባዋል።

እነዚህ የካህን ተግባራት ናቸው፣

1. ወንጌልን ማስተማር።
2. አባላትን የኢየሱስን ትዕዛዛት እንዲጠብቁ ማበረታታት።
3. ማጥመቅ።
4. ቅዱስ ቁርባንን መባረክ።
5. ሌሎች ዲያቆናትን፣ አስተማሪዎችን፣ እና ቄሶችን መሾም።
6. ማንም የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ያለው በስብስባ ውስጥ ከሌለ ስብሰባዎችን መምራት፡፡

አስተማሪና ዲያቆን የሚያከናውኑትን ሁሉንም ነገሮች አንድ ቄስ መሥራት ይችላል። ማንንም ለኤጲስ ቆጶሳት ኃላፊነት ወይም ለየትኛውም የመልከጼዴቀ የክህነት ስልጣን መሾም አይችልም፡፡

ሊጺስ ቆጶስ

ሊጺስ ቆጶስ የዋርድ መሪ ነው፡፡

እነዚህ የሊጺስ ቆጶስ ተግባራት ናቸው፣

1. በእርሱ ዋርድ ውስጥ አሮናዊ የክህነት ሥልጣን ያላቸውን ይመራል፡፡
2. በእርሱ ዋርድ ውስጥ የቄሶችን ቡድን ይመራል፡፡
3. የቤተክርስቲያን አባላት ምግብ፣ ልብሶች እና ሌሎች ነገሮችን በአደጋ ጊዜ እንዲያገኙ ይረዳል፡፡
4. የቤተክርስቲያኑን አባላት ለተወሰኑ በረከቶችና ዕድሎች ብቁ መሆናቸውን ይወስናል።
5. ሰዎች ለቤተክርስቲያኑ የሚሰጡትን ገንዘብና ሌሎች ነገሮች ይቀበልና በጥንቃቄ ይጠብቃል፡፡
6. በእርሱ ዋርድ የሚገኙ አባላት መንፈሳዊ መመሪያን ሲጠይቁ ወይም ምክር የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ሲረዳ ይመክራቸዋል፡፡

የቤተክርስቲያን ፕሬዚዳንት የስቴክ ፕሬዚዳንቶች ወንዶችን በሊጺስ ቆጶስነት እንዲሾሙ ያዛሉ።

## *ውይይት*

• የዲያቆን፣ የአስተማሪ፣ የቄስ፣ እና የሊጺስ ቆጶስ ተግባራት ምን ምንድን ናቸው?

*የመልከጼዴቀ ክህነት ሥልጣን ኃላፊነትና ተግባራቸው*

የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ሹመቶች ቄስ፣ ሊቀካህን፣ ፓትሪያርክ፣ ሰባዎቹ እና ሐዋሪያት ናቸው፡፡ እነዚህ እያንዳንዳቸው ኃላፊነቶች ልዩ ተግባሮች አሏቸው፡፡

ቄስ

1. ማጥመቀ።
2. የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ መስጠት።
3. ሥብሰባዎችን መምራት።
4. ሊቀ ካህን ባልተገኙበት ሥብሰባዎችን ይመራል፡፡
5. ወንገልን ይሰብካል፡፡
6. ሐሙማንን ይባርካል፡፡
7. ሕፃናትን ይባርካል፡፡
8. የክህነት ስልጣንን ለሌሎች መስጠት እናም በሽማግሌነት፣ በቀስና፣ በአስተማሪነት፣ በድቁና፣ ሥልጣን መሾም።
9. አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉንም የቄስ፣ የአስተማሪ፣ ወይም የዲያቆን ተግባራትን ማከናወን፡፡

ሊቀ ካህን

የሊቀ ካህን አብይ ተግባር በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ መሪ መሆን እና ለመንፈሳዊ ነገሮች ዛላፊ መሆን ነው። አንድ ሊቀ ካህን አስፈላጊነቱ ማንኛውንም ሽማግሌ፣ ቄስ፣ አስተማሪ፣ ወይም ዲያቆን የሚፈጽሙትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

ፓትሪያርክ

ፓትሪያርክ ለቤተክርስቲያኑ አባላት ልዩ ቡራኬዎችን የሚሰጥ ሊቀ ካህን ነው። እነዚህ ቡራኬዎች *የፓትሪያርክ ቡራኬዎች ይባላሉ። የፓትሪያርክ ቡራኬ አባላት ኢየሱስ እንዲያድርጉ የሚፈልገውን ነገሮች እንዲረዱ ይረዳቸዋል።

ሰባዎቹ

የሰባዎቹ አብይ ተግባር ወንጌልን የቤተክርስቲያን አባል ላልሆኑ ሕዝቦች መስበክ ነው፡፡ ሰባዎቹም በተጨማሪም ሐዋሪያትንም ቤተክርስቲያኑን እንዲመሩ ይረዷቸዋል፡፡

ሐዋሪያ

ሐዋሪያ በመላው ዓለም የኢየሱስ ክርስቶስ ልዩ ምስክር ነው፡፡ ሐዋሪያት በመላው ዓለም የቤተክርስቲያኑን ጉዳይ ይመራሉ፡፡ እያንዳንዱ ሐዋሪያ ሁሉንም የቀስና ሥልጣን አላቸው፡፡ ነገር ግን የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት፣ ሀዋሪያም የሆነው፣ ብቻ ሁሉንም የቀስና ሥልጣኖችን መጠቀም ይችላል። ሌሎች ሐዋርያቶች ሥልጣናቸውን የሚጠቀሙት የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት በሚስጣቸው አመራር ብቻ ነው።

*የክህነት ስልጣን ቁልፎች*

የክህነት ሥልጣን በኢየሱስ ስም የመሥራት እና ወደ ሰማዩ አባታችን የመመለስ ስልጣን ነው። የክህነት ሥልጣን ቁልፎች ያንን ሥልጣን ለመጠቀም ፈቃድ የመስጠት ስልጣን ናቸው፡፡ ይህ ማለት ምንም እንኳን ብዙ ሰዎች የክህነት ሥልጣን ያላቸው ቢሆንም፣ አንድ ሰው የክህነት ሥልጣኑን እንዲጠቀም ፈቃድ ለመስጠተ ስልጣን ሊኖረው ይገባል። ለምሳሌ ያህል፥ አንድ ቄስ የማጥመቀ ሥልጣን አለው። ነገር ግን ኤጲስ ቆጶሱ እንዲያጠምቀ እስኪፈቀድለተ ድረስ ማንንም ማጥመቀ አይችልም። ኤጲስ ቆጶሱ በዋርዱ ውስጥ የአሮናዊ ክህነት ሥልጣን ቁልፎች ይኖረዋል። ሌላ ምሳሌ፥ አንድ የክህነት ሥልጣን ያለው ሰው የክህነት ሥልጣንን ለሌላ ሰው ሊሰጥ የሚችለው በዚያ ሥፍራ የክህነት ሥልጣን ቁልፎች ካለው ሰው ፍቃዱን ሲቀበል ብቻ ነው። ይህም ከኤጲስ ቆጶሱ፣ ከስቴክ ፕሬዚዳንቱ ወይንም ከሚሲዮን ፕሬዚዳንቱ ሊሆን ይችላል፡፡

## ***ውይይት***

• የክህነት ሥልጣን ቁልፎች ምን ምንድን ናቸው?

*የክህነት ሥልጣን ያላቸው ለዋቂ ወንዶች እና ወንዶች ልጆች ቡድን*

አንድ ዓይነት የክህነት ሥልጣን ኃላፊነት ያላቸው ለዋቂ ወንዶች እና ወንዶች ልጆች በቡድኖች ውስጥ የተደራጁ ናቸው፡፡ እነዚህ ስብስቦች ቡድን ተብለው ይጠራሉ። በመልከ ጼዴቀ ክህነት ሥልጣን ውስጥ ቄሶች ቡድኖችና የሊቀካህናት ቡድኖች አሉ፡፡

በአሮናዊ የክህነት ሥልጣን ውስጥ የዲያቆን ቡድኖች፣ የአስተማሪ ቡድኖች፣ እና የቄሶች ቡድኖች አሉ።

አንድ ለዋቂ ወንድ ወይም ወንድ ልጅ በክህነት ሥልጣን ኃላፊነት ሲሾም፣ በክህነት ስልጣን ውስጥ ተመሳሳይ ኃላፊነት ያላቸው ሰዎች ቡድን አባል ይሆናል። ወደ ሌላ ስልጣን እስኪሾም በዚያው ቡድን ውስጥ ይቆያል። የቡድኑ መሪዎች እያንዳንዱን የቡድን አባል ያስተምራሉ እናም ይረዳሉ።

*የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ቡድን*

የቄሶች ቡድን

የቄሶች ቡድን እስከ 96 የተኛውም ብዛት ያህል የቄሶች አባል ሊኖረው ይችላል እናም በአንድ ዋርድ ውስጥ የሚኖሩትን ቄሶች ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ቄሶቹ (ቀሳውስቱ) ከ96 በላይ ከሆኑ ሌላ የቄሶች (ቀሳውስት) ቡድን ይደራጃል፡፡ የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ያላገኙ ሰዎች ክህነቶች ጋር ለትምህርት፣ ለማህበራዊ ተሳትፎ፣ እና ለሥራ ምድቦች ሊገናኙ ይችላሉ።

አንድ ፕሬዚዳንት እና ሁለት አማካሪዎች የቀሳውስትን ቡድን ይመራሉ፡፡

የሊቀ ካህናት ቡድን

አንድ የሊቀ ካህናት ቡድን በስቴክ ውስጥ ያሉትን ሊቀካህናትን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ የስቴክ ፕሬዚዳንትና ሁለት አማካሪዎቹ የሊቀካህናቱን ቡድን ይመራሉ፡፡

የአሮናዊ የክህነት ሥልጣን ቡድን

የዲያቆናት ቡድን

የዲያቆን ቡድን እስከ 12 ዲያቆናች ሊኖሩት ይችላል፡፡ በዋርዱ ውስጥ ከ12 በላይ ዲያቆናች ካሉ፣ ሌላ የዲያቆናት ቡድን ይመሰረታል። የዲያቆናች ቡድን ፕሬዚዳንትና ሁለት አማካሪዎች ይኖሩታል፡፡

የአስተማሪዎች ቡድን

የአስተማሪዎች ቡድን እስከ 24 አስተማሪዎች ሊኖሩት ይችላል፡፡ በአንድ ዋርድ ውስጥ ከ24 አስተማሪዎች በላይ ካሉ ሌላ የአስተማሪዎች ቡድን ይመሰረታል። የአስተማሪዎች ቡድን አንድ ፕሬዚዳንትና ሁለት አማካሪዎች ይኖሩታል፡፡

የካህናት ቡድን

የቄሶች ቡድን እስከ 48 ቀሳውስት ይይዛል። በአንድ ዋርድ ውስጥ ከ48 ቀሳውስት በላይ ካሉ፣ ሌላ የቄሶች (የካህናት) ቡድን ይደራጃል። የቄሶች (የካህናት) ቡድን ፕሬዚዳትንት፣ ኤጲስ ቆጶስ ወይም የቀርንጫፍ ፕሬዚዳንት ነው። የሱ ረዳቶች እንዲሆኑ ከቡድን ውስጥ ሁለት ቄሶችን ይሾማል።

## ***ውይይት***

- ቡድን ምንድን ነው?
- ምን ያህል የቄሶች፣ የሊቀካህኖች፣ የዲያቆናት፣ የአስተማሪዎች፣ የካህናቶች ቡድን አባላትን ይመሰርታሉ?
- የቡድን አባላት እንዴት እርስበርሳቸው ሊረዳዱ ይችላሉ?

## ***ማጣቀሻ***

- ወደ እብራውያን ሰዎች፤ 7፤ ትምህርትና ቃልኪዳን 84፥6–30 (የመልከዒዴቀ የክህነት ሥልጣንና የአሮናዊ የክህነት ሥልጣን ተብራርተዋል፡)
- ትምህርትና ቃል ኪዳን 20፡38–60 ትምህርትና ቃል ኪዳን 107 (የክህነት ሥልጣን ኃላፊነትና ተግባር ተገልጿል።)

# ስርዓቶች

*ምዕራፍ 21*

*ለዋቂ ወንዶች እና ወንዶች ልጆች በክህነት ሥልጣን ምን ማድረግ ይችላሉ?*

## በክህነት ሥልጣን፣ ለዋቂ ወንዶች ስርዓቶችን ለማከናወን ኢየሱስ የነበረውን ዓይነት ስልጣን አላቸው

ሥርዓቶች የክህነት ስልጣን በተሰጣቸው የሚከናወኑ የተቀደሱ ክንውኖች ናቸው። ጥምቀት፣ ለአባልነት ማጽደቅ፣ እጅን እራሳቸው ላይ በመጫን በሽተኛን መፈወስና መባረክ እናም ቅዱስ ቁርባንን ማሳለፍ ጥቂቶቹ ሥርዓቶች ናቸው፡፡

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፣ ሰዎችን ለመርዳት ስርዓቶችን አከናውኗል። ሕሙማንን ፈውሷል እናም እውሮች እንዲያዩ አድርጓል። ደንቆሮዎች መስማት እንዲችሉ አድርጓል፣ ሙታንንም እንኳን ወደ ህይወት መልሷል። ቅዱስ ቁርባንን ለተከታዮቹ ሰጥቷል፡፡

ኢየሱስ የክህነት ስልጣን ላላቸው ሰዎች ስርዓቶችን እንዲያከናውኑ ሃይልና ስልጣን ሰጥቷቸዋል። ብቃት ያላቸው ለዋቂ ወንዶች እና ወንዶች ልጆች የክህነት ስልጣን ያላቸው ስርዓቶችን ማከናወን ይችላሉ። እነርሱም ስርዓቶችን የሚፈፅሙት እኛን ለመባረክ እና የሰማይ አባታችንን እንድንመስል ለመርዳት ነው፡፡ ሥርዓቶቹ ወደ እርሱ ተመልሰን ለመኖር እንድንዘጋጅ ይረዱናል፡፡

ኢየሱስ ምድር ላይ ዛሬ ለሚገኙ ወንዶች የክህነት ሥልጣንን ስለሰጣቸው፣ በሕይወታችን ብዙ በረከትን መቀበል እንችላለን፡፡ መጠመቅ፣ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ መቀበል እና ለዘለዓለም ከቤተሰባችን ጋር መተሳሰር እንችላለን፡፡

የቡድን ፕሬዚዳንት ሥርዓቶች እንዴት መፈፀም እንዳለባቸው ለቡድኑ አባላት ያስተምራሉ። አንድ የክህነት ሥልጣን ያለው ሰው ሥርዓቶችን ለመፈፀም ቢፈልግና እንዴት እንደሚፈፀም ባያውቀ የቡድኑን ፕሬዚዳንት እንዲያስተምረው መጠየቀ አለበት፡፡

### ውይይት

• ሥርዓቶችን ለምን ያከናውናሉ?



*ኢየሱስ በመጨረሻው እራት ለሐዋሪያቶቹ ቅዱስ ቁርባንን ሰጥቷል፡፡*

*በካርል ብሎች። ዋናው የፀሎት ቤት በፍሬደሪክቦርጅ ግንብ፣ ዴንማርክ ነው፡፡*
*በፍሬደሪክቦርጅ ቤተ መዘክር ፍቃድ ጥቀም ላይ ዋለ።*

## ሥርዓቶች የሚከናወኑት እኛን ለመርዳት ነው

ጥምቀት

*ጥምቀት የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የመጀመሪያው ሥርዓት ነው፡፡ አንድ ሰው* ከመጠመቁ በፊት በኢየሱስ ማመን፣ ስለፈፀመው ኃጢያት ንስሐ መግባት፣ እና ኢየሱስ ያስተማረውን ነገሮች መስራት አለበት።

ከኤጲስ ቆጶሱ ወይም ቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ፈቃድ ማግኘት አለበት። አጥማቂው ሰው ከተጠማቂው ሰው ጋር በመራመድ በውሃ ውስጥ ይገባል። አጥማቂው ሰው ተጠማቂውን በስም በመጥራት አጭር ፀሎት ያደርጋል። ከዚያም በኋላ የተጠማቂው ሰው አካል ሙሉ በሙሉ በማጥመቀ ከውሃው በታች በማስገባት እና እንደገና ከውሃው ውስጥ ያወጣዋል።

ግለሰቡ የሚለው ፀሎት "በኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጠኝ ስልጣን መሰረት፣ በአብ፣ በወልድ፣ እናም በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቀሃለሁ። አሜን።" ነው።

### *ውይይት*

• የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የመጀመሪያው ሥርዓት ምንድን ነው?

*የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን መስጠት*


አንድ ሰው ከተጠመቀ በኋላ፣ የመልከ ጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ያላቸው ወንዶች እጃቸውን በሰውየው አራስ ላይ ይጭናሉ፣ ከእነሱ አንዱ ልዩ ፀሎት ይፀልያል። በዚያ ፀሎት፣ ውስጥ ሰውየው የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆኑን አረጋግጠው እናም እንዲህ ይሉታል፣ "መንፈስ ቅዱስን ተቀበል።" ይህ ማለተ ያ ሰው ሁልጊዜ የኢየሱስን ትዕዛዛት በታማኝነት ለመታዘዝ ሙከራ ሲያደርግ የመንፈስ ቅዱስ መመሪያ መብትን ያገኛል። ይህን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መስጠት ሁለተኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሥርዓት ነው፡፡ ከዚያም ሥርዓቱን የሚፈጽመው በመንፈስ ቅዱስ ተነሳስቶ ለሰውየው ቡራኬ ይሰጠዋል። ወንዶች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለሰውየው ለመስጠት ከኤጲስ ቆጶስ ወይም ከቀርንጫፍ ፕሬዚዳንት ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

### *ውይይት*

*• የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን መስጠት የሚችለው ማነው?*

*የክህነት ስልጣን ሹመት*

ለአንድ ሰው የክህነት ሥልጣንን መስጠት ሥርዓት ነው። የክህነት ሥልጣን ባላቸው ሌሎች ወንዶች መከናወን አለበት። ከኤጲስ ቆጶሱ ወይም ከቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን ለመስጠት ፈቃድ ማግኘት፣ እናም የመልከ ፄዴቀ የክህነት ሥልጣንን ለመስጠት ከስቴክ ፕሬዚዳንቱ ፈቃድ ማግኘት ይገባቸዋል። የክህነት ሥልጣንን መቀበል ለአንድ ሰው ወይም ወንድ ልጅ ታላቀ ክብር ነው፡፡ የክህነት ስልጣንን ሲቀበሉ የገቡትን ቃል ኪዳን የሚጠብቁ ለዘለዓለም የክህነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡



*ኢየሱስ ክርስቶስን እና የሐጢያት ክፍያውን ለማስታወስ እንዲረዳን ቀዱስ ቁርባንን እንቀበላለን፡፡*

## ውይይት

• ለሌሎች የክህነት ሥልጣንን ሊሰጥ የሚችለው ማነው?

ቅዱስ ቁርባን

የክህነት ሥልጣን ያለው ሰው ጥቂት ዳቦና ውሃን ለመባረክ ፀሎት ይፀልያል፡፡ ከዚያም እርሱ ወይም ሌላ የክህነት ሥልጣን ያለው ሰው ለቤተክርስቲያን አባላት ቁራሽ ዳቦውን እንዲበሉ እና ጥቂት ውሃ እንዲጠጡ ይሰጣቸዋል። ይህ ቅዱስ ቁርባን ይባላል። ቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ነው፡፡

ዳቦው እና ውሃው የኢየሱስ ስጋና ደም ምሳሌዎች ናቸው፡፡ እርሱ ህይወቱን ለእኛ ሲል *እንደሰዋ ለማስታወስ ይረዱናል፡፡ እርሱ ለእኛ ያለውን ፍቀር ማስታወስ አለብን። ለኃጢአታችን ይቀርታን እንድናገኝ ስላመቻቸልን እና እንደገና ተመልሰን ከሰማያዊ አባታችን ጋር እንድንኖር ስላደረገልን ማመስገን አለብን።

በየጊዜው የቀዱስ ቁርባንን ስንወስድ፣ ስንጠመቀ ለሰማያዊ አባታችን የገባነውን ቃል ኪዳን ደግመን እንገባለን። ሁልጊዜ ኢየሱስን ለማስታወስ በእርሱ ስም በፈቃደኝነት ለመጠራት እናም ሁልጊዜ ትዕዛዛቱን ለማክበር እንደገና ቃል ኪዳን እንገባለን። እናም ቀዱስ ቁርባኑን ከመቀበላችን አስቀድሞ፣ ለፈፀምነው ስህተተ ነገሮች ንስሃ መግባት እና ስለገባነውም ቃል ኪዳን ማሰብ አለብን፡፡

የሰማዩ አባታችን ለመስራት ቃል የገባነውን ነገሮች ከሰራን፣ ሁልጊዜ መንፈስ ቀዱስ ከእኛ ጋር እንዲሆን እንደሚልክልን ቃል ይገባል።

ዳቦን መባረክ

ኢየሱስ ቀዱስ ቁርባንን የመባረኪያ ልዩ ፀሎቶች ሰጥቶናል። ይህ ለዳቦ የሚፀለይ ፀሎት ነው።

“አቤቱ ዘለዓለማዊ አባት እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህንን ዳቦ ለሚለሚበሉተ ነፍሳተ ሁሉ የልጅህን ስጋ ለማሰብ ይበሉተ ዘንድ፤ መንፈሱንም ሁል ጊዜ ከእነርሱ ጋር ይሆን ዘንድ፤ የልጅህንም ስም በላያቸው ለመውሰድ ፈቃደኞች ይሆኑ ዘንድ፤ እናም ሁልጊዜም እርሱን ሊያስታውሱና የተሰጣቸውንም ትዕዛዛቱን እንዲጠብቁ አቤቱ ለአንተ ለአምላክ፣ ዘለዓለማዊ አባትም ይመሰክሩ ዘንድ በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተባርከው እና ተቀድሰው ዘንድ እንጠይቀሃለን። አሜን።”

ውሃውን መባረክ፥

ይህ ለውሃው የሚፀለይ ፀሎተ ነው፥

“አቤቱ ዘለዓለማዊ አባተ እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህንን ውኃ ለሚጠጡተ ነፍሳተ ሁሉ ለእነርሱ ለፈሰሰው ለልጅህ ደም መታሰቢያነተ ያደርጉተ ዘንድ፤ አቤቱ ዘለዓለማዊ አባተ እግዚአብሔር፣ መንፈሱም ከእነርሱ ጋር ይሆን ዘንድ፤ ሁልጊዜም እርሱን በማሰብ ለአንተ ይመሰክሩ ዘንድ እንድተባርከው በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶ ስም እንጠይቀሃለን። አሜን።”

### ውይይት

• ቀዱስ ቁርባን ምንድን ነው?
• የክህነት ሥልጣን ያላቸው የቀዱስ ቁርባን ሲባርኩና ሲያድሉ እኛ ስለ ምን ማሰብ ይኖርብናል?
• ቀዱስ ቁርባንን ስንቀበል ምን ቃል ኪዳን ማድረግ ይገባናል?

*ህፃናትን መባረክ*

አብዛኛውን ጊዜ ሕፃናቶች በተወለዱ በጥቂት ሳምንታት ጊዜ የክህነት ስልጣን ያላቸው ሰዎች ህፃናትን ይባርካሉ። ይህን ለመፈፀም ከሌጂስ ቆጶሱ ወይም ቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። የህፃኑ አባት የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ካለው ሕፃኑን መባረክ ይችላል፣ የመልከ ጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ከሌለው፣ ሕፃኑን መባረክ አይችልም ወይም ህፃኑን ከበው ከሚባርኩት ጋር አይገኝም። የመልከጼዴቀ ክህነት ሥልጣን ካላቸው አንዳቸውን ሕፃኑን እንዲባርኩት መጠየቀ ይችላል፡፡ የህፃኑ አባት፣ የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ካለውና ብቁ ከሆነ፣ ወይም የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ያለው ሌላ ሰው ህፃኑን በክንዱ ውስጥ በመያዝ፣ በሌሎች የመልከ ጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ባላቸው በመረዳት፣ አባተየው ይፀልይለታል። በፀሎቱ ውስጥ የሰማይ አባታችንን በመጥራት ሥርዓቱን የሚፈፅመው ባለው የመልከጼዴቀ የቀስና ሥልጣን መሆኑን ይናገራል። እናም ለህፃኑም በወላጆቹ የተመረጠለትን ሥም ይሰጠዋል፡፡ ከዚያም ህጻኑን በመንፈስ ቀዱስ እንደተገለፀለተ ይባርከዋል።

### ውይይት

• የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ያለው ሰው ህፃንን በሚባርክበት ጊዜ ምን ማድረግ አለበት?

*ሕሙማንን መባረክ*

አንድ ሰው ሲታመም፣ የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ያላቸውን እንዲባርኩት መጠየቀ ይችላል፡፡ በመጀመሪያ ከእነሱ አንዱ ይቀባዋል፡፡ ይህን የሚያደርገው አነስተኛ መጠን ቀባቀዱስ ጠብታ በራሳቱ ላይ በማድረግ ነው፣ ከዚያም እጁን በሰውየው እራስ ላይ በመጫን ልዩ ፀሎት ይፀልይለታል። ከዚህ በኋላ፣ በአንድላይ ሆነው እጃቸውን በሰውየው እራስ ላይ በመጫን ከእነሱ አንዱም ቀብአቱን ማተም እና በመንፈስ ቀዱስ በመመራት ሰውየውን ይባርከዋል። ብዙ ሰዎች ይህንን የክህነት መባረክ ሲያገኙ ተሽሎአቸዋል፣ ወይም የካህናት ቡራኬ ሲያገኙ ከህመማቸው ተፈውሰዋል። የህሙማን ሰዎች ቡራኬ ሥርዓት ነው፡፡

ሕሙማን ሰዎችን ለመቀባት የሚጠቀመው ዘይት ለዚህ ተግባር ተብሎ በሌላ ሥርዓት ተቀድሶ የተዘጋጀ ነው፡፡ ዘይቱን ለመቀደስ፣ የመልከጼዴቀ ክህነት ስልጣን ያለው ሰው አነስተኛ የሆነ ዘይት በክፍት መያዣያ ይዞ ልዩ ፀሎት ይፀልይበታል፡፡

ይህንን ሥርዓት ለመፈፀም የመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ያለው አንድ ሰው ከሌጂስ ቆጶሱ፣ ከቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ወይም ስቴክ ፕሬዚዳንቱ ፈቃድ አያስፈልገውም፡፡

### ውይይት

• ሰዎች ሲታመሙ መባረክ የሚችለው ማን ነው?

*አንድ አባት የቤተሰቡን አባላት መባረክ ይችላል*

የመልከጼዴቅ የክህነት ሥልጣን ያለው አንድ አባት የቤተሰቡን አባላት መባረክ ይችላል፡፡ ሰው ሲታመም ወይም ልዩ እርዳታ ሲያስፈልገው ይህን ማድረግ ይችላል፡፡ ከኤጲስ ቆጶሱ፣ ከቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ወይም ስቴክ ፕሬዚዳንቱ ይህንን ለመፈፀም ፈቃድ አያስፈልገውም። አባትየው በታመመው ሰው እራስ ላይ እጁን በመጫን ይፀልይለታል፡፡ በፀሎቱ ውስጥ፣ ለሰውየው መንፈስ ቅዱስ በአዕምሮው ውስጥ የሚነግረውን በመከተል ቡራኬ ይሰጠዋል። የቤተሰብ አባላትን መባረክ ሥርዓት ነው፡፡

### ውይይት

• አንድ አባት የቤተሰቡን አባላት መባረክ የሚችለው መቼ ነው?

**አንዳንድ ስርዓቶች በጣም አስፈላጊ ስለሆኑ እያንዳንዱ ሰው መቀበል አለበት**

አንዳንድ የክህነት ሥልጣን ስርዓቶች ሰው ከሰማዩ አባታችን ጋር ተመልሶ እንዲኖር የሚያስፈልጉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሥርዓቶች ሁለቱ ጥምቀትና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን መቀበል ናቸው፡፡ አዋቂ ወንዶች እና ወንዶች ልጆችም የክህነት ሥልጣንን መቀበል አለባቸው። ሌሎች ሥርዓቶች አንድ አባት የቤተሰቡን አባላት እንደሚባርከው ዓይነት፣ ዕርዳታና መፅናናትን ስንፈልግ የሚከናወኑ ናቸው፡፡

### ውይይት

• አንዳንዱ ሥርዓቶች ምን ምን ናቸው?
• እያንዳንዱ ምን ዓይነት በረከት ያመጣል?

### ማጣቀሻ

*በክህነት ሥልጣን፣ አዋቂ ወንዶች ሥርዓቶችን ለማከናወን ኢየሱስ የነበረውን ዓይነት ሥልጣን አላቸው*

• የማቴዎስ ወንጌል 16፥19 የማርቆስ ወንጌል 3፥14፣ (ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የክህነት ሥልጣን ሰጥቷቸዋል፡፡)
• የማርቆስ ወንጌል 1፥34 (ኢየሱስ ሕሙማንን ፈውሷል እናም እርኩስ መንፈስን አውጥቷል።)
• የሐዋሪያት ሥራ 9፥1–6 (የኢየሱስ ሐዋሪያቶች ሥርዓቶችን አከናውነዋል።)

*ሥርዓቶች የሚከናወኑት እኛን ለመርዳት ነው*

• የማቴዎስ ወንጌል 19፥14–15 (ኢየሱስ ህፃናትን ባርኳል።)
• የማቴዎስ ወንጌል 26፥26–28 (ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቶቹ ቅዱስ ቁርባንን ባረከላቸው።)
• የሐዋሪያት ሥራ 8፥17 (የኢየሱስ ሐዋሪያቶች መንፈስ ቅዱስን ሰጥተዋል፡፡)

- የያዕቆብ መልዕክት 5፥14 (ቀሳውስት በበሽተኛ አናት ላይ አነስተኛ መጠን ጠብታ ዘይት ማድረግና መባረክ አለባቸው።)
- 3 ኔፊ 11፥23–28 (ጥምቀት የሚከናወንበት ስነስርዓት ተሰጥቶአል።)
- ሞሮናይ 4፥5 (ኢየሱስ ከብዙ ጊዜ በፊት ለነበሩ ሕዝቦች ቀዱስ ቁርባንን ለመባረክ ፀሎት ሰጥቷቸዋል፡፡)
- ሞሮናይ 6፥1–3 (ጥምቀተን ለሚቀበሉ አስፈላጊውን መሥፈርቶች ተሠጥቶአቸዋል፡፡)

# ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል

ክፍል ሰባት





ሊየሱስ ለአባቱ ታዛዥ መሆኑን በመጠመቅ አሳይቷል፡፡

# መታዘዝ

*ምዕራፍ 22*

*የሰማዩ አባታችን ደስተኛ በመሆንና ከእሱ ጋር ተመልሰን ለመኖር ማድረግ የሚገባንን ነገሮች ነግሮናል። እነዚህን ነገሮች ለማድረግ እንዴት መማር እንችላለን?*

**የሰማዩ አባታችን ስለሚወደን ሕጎችን ሰጠን**

የሰማዩ አባታችን ስለሚወደን በዚህ ምድር ላይ ደስተኞች እንድንሆን ይሻል። ወደ እርሱ እንድንመለስ እና እርሱ ያለውን ደስታም እንድናገኝ ይፈልጋል፡፡ ይህን ማድረግ የምንችለው እንደርሱ እንድንሆን የሰጠንን ችሎታ ስንጠቀም ብቻ ነው።

የሰማዩ አባታችን እንደርሱ ለመሆን ምን ማድረግ እንደሚገባን ያውቃል፡፡ እኛ ለስራችን መልካም የሆኑትን እንድናደርግ የሚነግሩንን ትዕዛዛቶችን ሰጥቶናል። ለእኛ መልካም ያልሆኑትን ደግሞ ነግሮናል።

የሰማይ አባታችን የሰጠን እያንዳንዱ ትዕዛዛት ለእኛ መልካም እና የሚረዳን ነው። እነዚህም ትዕዛዛት ለእኛ ህይወት መመሪያ ሊሆኑ ይችላሉ፣ እናም ከታዘዝናቸው ደስተኞች እንሆናለን፡፡

ሁላችንም የሰማይ አባታችንን ትዕዛዛት አላከበርንም። የሰማዩ አባታችንን ትዕዛዛቶች ባለመታዘዛችን ምክንያት፣ ኃጢአተኞች ነን። ኃጢአተኞች በመሆናችን የተነሳ ከሰማዩ አባታችን ዘንድ ተለይተናል። ለኃጢአታችን ትክክለኛው ቀጣት ለዘለዓለም ከሰማያዊ አባታችን ጋር መለያየት ነው፡፡

ነገር ግን የሰማዩ አባታችን ይወደናል። የኃጢአታችንን የቀጣት ዋጋ የሚከፍልበትን መንገድ አበጅቶልናል። የኃጢአታችን የቀጣት ዋጋ ለመክፈል ልጁን፣ ኢየሱስን ላከልን። ኢየሱስ ያንን ዋጋ ከፍሎልናል፤ እናም በኢየሱስ በማመን ወደ ሰማይ አባታችን መመለስ እንችላለን፡፡ በኢየሱስ እምነት መኖር ማለት እሱን ማመንና የእርሱ ታዛዥ ተከታይ መሆን ማለት ነው። በኢየሱስ እምነት ያላቸው የእርሱን ትዕዛዛት ያከብራሉ። ወደ ሰማይ አባታችን ለመመለስ የመጀመሪያው ደረጃ በኢየሱስ ላይ እምነት መኖር፣ እርሱን ከልብ ለመታዛዝ መሞከር ነው፡፡ ከዚያም፣ በኢየሱስ ማመንን ከቀጠልን፣ እርሱ ለሰማዩ አባታችን ጠቀላላ ትዕዛዛት ታዛዦች እንድንሆን ይረዳናል፣ እናም የሰማይ አባታችን ሐጢአታችንን ይቀር ይለናል፡፡

አንዳንዶቹ የኢየሱስ ትዕዛዛት ለሁሉም የቤተክርስቲያን አባሎች ናቸው። እነዚህንም በቀዱሳን መጽሃፍትና በነቢያቶች አማካኝነት ሰጥቷል፡፡ አንዳንድ ትዕዛዛትን ለየግላችን፣ በመንፈስ ቀዱስ አማካኝነት ሰጥቶናል፡፡ ለምሳሌ፣ ሁሉም የቤተክርስቲያን አባላት ሌሎችን ወንጌልን ለማስተማር መርዳት እንዳለባቸው ቀዱሳን መፃህፍትና ነቢያቶች ይነግሩናል። ነገር ግን ወንጌልን ለቤተሰቦቻችን አባላት፣ ለጓደኞቻችን፣ እና ለጎረቤቶቻችን በየግላችን ለማስተማር ምን ማድረግ እንደምንችል ለየአንዳንዳችን መንፈስ ቀዱስ ይነግረናል። ቀዱሳን መጻህፍትን ካጠናን፣ የነቢያትን ቃሎች ካዳመጥን፣ የመንፈስ ቀዱስን ሹክሹክታ መልዕክት ከተከተልን፣ ዘወትር ማድረግ ያለብንን ነገሮች እናውቃለን።

### *ውይይት*

- የሰማይ አባታችን እና የኢየሱስ ትዕዛዛት ለእኛ ያላቸውን ፍቅር የሚያሳዩት እንዴት ነው?
- የሰማዩ አባታችንና ኢየሱስ እንድንፈፅም የነገሩንን እንዴት ማወቅ እንችላለን?

## እያንዳንዱ የሰማይ አባታችን ትዕዛዝ አስፈላጊ ነው

ኢየሱስ እንድናደርግ ያዘዘንን ሁሉን ነገር ለማድረግ ፈቃደኞች መሆን አለብን፡፡ ሁሉም ትዕዛዛት አስፈላጊና ከሰማይ አባታችን ጋር ለመኖር እንድንዘጋጅ ይረዱናል። መጽሐፍ ቀዱስ ነእማን፣ ስለሚባለው ሰው ታሪክ ይነግረናል። እሱም በጣም ህመምተኛ ስለነበሩ ኤልሳዕ የተባለው ነቢይ እንዲፈውሰው ፈለገው። ቤቱንም ትቶ ኤልሳዕ ወደ ሚኖርበት አገር ሄደ። ኤልሣዕም ንእማንን ዮርዳኖስ ተብሎ በሚጠራው ወንዝ ውስጥ ሰባት ጊዜ ከታጠበ እንደሚፈወስ እንዲነግረው መልዕክተኛ ላከበት (ታሪኩን ነገሥት ካልዕ 5፣1–27 ይመልከቱ)

ንእማንም ይህን እንዲያደርግ በተነገረው ጊዜ ተቆጣ። እሱ ከሚኖርበት አካባቢ ብዙ ታላላቅ ወንዞች እያሉ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ለምን መሄድ እንዳለበት አስገረመው። ነገር ግን ቢቆጣም፣ በመጨረሻ የተነገረውን ለመታዘዝ ወሰነ። ትዕዛዙን በማክበሩም ተፈወሰ። ባይታዘዝ ኖሮ አይፈወስም ነበር።

አንዳንድ ሰዎች የኢየሱስን ትዕዛዛት ለመታዘዝ በጣም ከባድ አድርገው ያስባሉ። በአንድ ወቀት፣ ከወንድሞቹ፣ ጋር፣ አንድ በጣም አስቸጋሪ ነገርን እንዲሰራ የተጠየቀ ኔፊ የሚባል አንድ ወጣት ነበር፡፡ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ተመልሰው አንዳንድ አስፈላጊ ቀዱሳን መፅሐፍቶችን እንዲያመጡ ነገራቸው፡፡ ወንድሞቹ በጣም አስቸጋሪ ስለሆነ ልናደርገው አንችልም አሉ። ነገር ግን ኔፊ ኢየሱስ እንደነገረው አደርጋለሁ አለ፡፡ ኢየሱስ አንድን ነገር እንድናደርግ ሲነግረን፣ ምን ያህል ከባድ መስሎ ቢታየንም እንኳ፣ እርሱ እንድናደርግ ይረዳናል አለ።

ኢየሱስ እንደ እርሱና እንደ ሰማይ አባታችን ለመሆን በርትተን መስራት እንዳለብን ነግሮናል፣ ይህንን ማድረግ እንደማንችል ቢያውቀ ይህን እንድንሰራ አይነግረንም ነበር።

ኢየሱስ ምንም ሐጢያት ባለመፈፀሙ እንደ ሰማይ አባታችን ነው። እኛ ሁላችንም ሀጢያት ሰርተናል፣ ነገር ግን በኢየሱስ ላይ ባለን እምነታችንና ንስሐ በመግባት እንደ ሰማይ አባታችን መሆን እንችላለን፡፡

አንዳንድ ጊዜ ከኢየሱስ ትዕዛዛት የአንዱን ምክንያት አንረዳም ይሆናል። ነገር ግን ኢየሱስን ከወደድንና ካመንነው እንድናደርግ የነገረንን እናደርጋለን። ምንም እንኳ አንድን ነገር ለምን እንደምንሰራ ባናውቅም እንኳ እንታዘዛለን። አዳምና ሄዋንም ይህንን አድርገዋል። ኢየሱስ አዳምና
ሔዋን ለሰማዩ አባታችን *መስዋዕት እንዲያቀርቡ ነግሮአቸዋል፡፡ አንድ ቀን መልአክ ወደ አዳም መጥቶ ለምን መስዋዕት አንደሚያቀርብ ጠየቀው። አዳምም ለምን እንደሚያቀርብ እንደማያውቅና፣ ኢየሱስ እንዲያደርግ ስለነገርው ብቻ መሆኑን መለሰለት፡፡ መልአኩም ለአዳም እንዲህ የሚያደርግበትን ህግ ነገረውና ስለወንጌልም አዳምን አስተማረው፡፡ አስቀድሞ ስለህግ ምክንያት ሳይረዳ እሱን በመታዘዙ ኢየሱስ በአዳም ተደሰተ፡፡

ኢየሱስን ስለምናፈቅረው እና እሱን መታዘዝ በመፈለጋችን ትዕዛዛቱን ማክበር አለብን። የሰ-ማዩ አባታችን ኢየሱስን መታዘዝ በሚፈልጉት ሁሉ እደሰተባቸኋለሁ ብሏል። ልጆቹ ኢየሱስን እንዲታዘዙ የሚያስገድዳቸው ነገር እስኪያጋጥማቸው ድረስ ባለመታዘዛቸው ያዝናል። የሰማዩ አባታችን ልጆች በሙሉ ኢየሱስን ማፍቀርና መታዘዝ እንዲማሩ ይፈልጋል፣ ምክንያቱም ይህ ወደ ሰማይ አባታችን ለመመለስ የሚያስችል ብቸኛው መንገድ ነው፡፡

## *ውይይት*

- ለመታዘዝ አስቸጋሪ መስሎ ቢታየንም እንኳ የኢየሱስን ትዕዛዛት ማክበር አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?
- ምንም እንኳ መረዳት ባንችልም ትዕዛዛቶችን መታዘዝ ለምን ይኖርብናል?
- መታዘዝ በመፈለጋችን ምክንያት መታዘዝ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?

## የሰማይ አባታችንን ስንወድ፣ ኢየሱስን ለመታዘዝ እንፈልጋለን

የሰማይ አባታችን ያዘዘውን ሁሉ ኢየሱስ ፈጽሟል። ኢየሱስ የሰማይ አባታችንን በመውደዱ ምክንያት የሰማዩን አባታችን ታዟል። ሰይጣን ኢየሱስን የሰማዩ አባታችንን እንዳይታዘዝ ፈትኖታል፡፡ ኢየሱስ ሰይጣን እንዲያደርግ የፈተነውን ነገር ሁሉ አላደረገም፡፡

*የመጀመሪያውና በጣም አስፈላጊው ትዕዛዝ የሰማይ አባታችንን መውደድ ነው*

የሰማይ አባታችንን ስንወድ፣ ኢየሱስ እንዳደረገው እሱን ለመታዘዝ ፍላጎት ይኖረናል። የሰማዩ አባታችንን መውደድ የምንችለው ስለእርሱ የበለጠ ስንማር ነው። ምን እንዳደረገልን ስለ እርሱ መማር አለብን። ይህንን ቅዱሳን መጻሕፍትን በማንበብ እና የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን መሪዎችን በማዳመጥ መማር እንችላለን። የሰማይ አባታችንን ስንወድ፣ ኢየሱስ እኛ ተመልሰን ከሰማያዊው አባታችን ጋር እንድንኖር ስለአደረገልን ዕርዳታ የተነሳ ኢየሱስንም እንወዳለን። ኢየሱስን ማፍቀር የምንማረው እርሱ እንድናደርግ ያዘዘንን ነገሮች በማድረግ ነው። ለሰማዩ አባታችንና ለኢየሱስ ያለን ፍቅር ታላቅ ሲሆን የእነሱን ትዕዛዛቶች መታዘዝ ቀላል ይሆንልናል፡፡

*ሁለተኛይቷ እና ታላቂቷ ትዕዛዝ ሁሉንም ሰው መውደድ ነው*

ኢየሱስ ሌሎች ሰዎችን እንድንወድና እንድንረዳ ነግሮናል። እነርሱ እንዲንከባከቡን በምንፈልገው መንገድ እንድንከባከባቸው ነግሮናል፡፡ ስለሌሎች መጥፎ ነገር እንዳንናገር ነግሮናል፡፡ ለፈፀሙት ስህተቶችም ይቅር ማለት አለብን። በምንችለው መንገድ ሁሉ ሌሎችን መርዳት አለብን።

የሰማዩ አባታችንንና ኢየሱስን ስንወድ፣ ሌሎችንም እንወዳለን እናም እንረዳቸዋለን። ኢየሱስንና ሌሎች ሰዎችን ስንወድና ስናገለግል የሰማዩ አባታችንና የኢየሱስን ሁሉንም ትዕዛዛት ለመታዘዝ ይቀለናል፡፡

## ውይይት

- ሁለቱ አበይት ትዕዛዛት ምን ምንድን ናቸው?
- የኢየሱስ አርአያነት የሰማይ አባታችንን ትዕዛዛቶች ለመታዘዝ እንዴት ሊረዳን ይችላል?
- የሰማይ አባታችንና ኢየሱስን መውደድና ትዕዛዛታቸውን ለመታዘዝ መፈለግን እንዴት መማር እንችላለን?

## ማንኛውም የምንቀበለው በረከት የሚመጣው በመታዘዝ ምክንያት ነው

የሰማይ አባታችን ትዕዛዛቱን ስንታዘዝ ይባርከናል። እኛ ለምንታዘዛቸው እያንዳንዱ ትዕዛዛት በረከትን እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል። ትዕዛዛትን በታዘዝን ጊዜ ሁሉ በመታዘዛችን በረከትን እናገኛለን። ትዕዛዛቱን ካልታዘዝን ቃል የተገባልንን በረከት ለመቀበል መጠበቅ የለብንም፡፡

የሰማያዊ አባታችንን ትዕዛዛት በመታዘዝ የምናገኛቸው አንዳንድ መባረኮች ደስታ፣ ከፍርሃት ነፃ መሆን፣ ጥሩ ጤንነት እና ተጨማሪ እውቀትና ችሎታ ናቸው፡፡ የሰማያዊ አባታችን የገባልን ታላቅ በረከት እንደ እርሱ መሆን እንድንችልና ዘለዓለም ከእርሱ ጋር እንድንኖር ነው፡፡ ይህን በረከት ትዕዛዛቱን ሁሉ በመታዘዝ ለመቀበል እንችላለን፡፡

በተጋት የሰማዩ አባታችንን ትዕዛዛት ለመታዘዝ ስንሞክር፣ በኢየሱስ ዕርዳታ ብቻ ልናደርግ እንደምንችል ማስታወስ አስፈላጊ ነው። የምንታዘዝ ከሆነ፣ እምነታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ካደረግንና ንሥሐ ከገባን የሰማዩ አባታችን ይቅር እንደሚለንም ማስታወስ ይገባናል። ሁላችንም ኃጢአተኞች ስለሆንን ለኢየሱስ ክርስቶስ የሀጢያት ክፍያ በጣም እናመሰግነዋል፣ በእርሱ የኃጢአት ክፍያ ምክንያት፣ የሰማዩ አባታችን ይቅር ሊለን፣ ሊባርከን እና ታዛዦች እንድንሆን ሊረዳን ይችላል። በራሳችን ለሰማይ አባታችን በረከት በፍጹም ብቁ መሆን አንችልም፡፡

## ውይይት

- ለሰማይ አባታችን በመታዘዝ ምክንያት ለአንተ ሊመጣ የሚችለው በረከት ምንድነው?
- እነዚህን በረከቶች ለማግኘት ኢየሱስ እንዴት አድርጎ ረዳን?
- የሰማይ አባታችንን ታላቅ ስጦታ ለመቀበል እንዴት እንችላለን?

## *ማጣቀሻ*

*የሰማይ አባታችን ስለሚወደን ሕጎችን ሰጠን*

- የዮሐንስ ወንጌል 15፥10–14 (የሰማይ አባታችንን ትዕዛዛት ከታዘዝን፣ እርሱ እንደሚወደን ማወቃችንን እንቀጥላለን።)

*እያንዳንዱ የሰማይ አባታችን ትዕዛዝ አስፈላጊ ነው*

- መጽሐፈ ነገስት ካልዕ 5፥1–14 (ነቢዩ ኤልሳዕ ነአማንን ለመፈወስ ምን ማድረግ እንዳለበት ነገረው።)
- 1 ኔፊ 3፥1–7 (ኢየሱስ የእርሱን ትዕዛዛት የምንታዘዝበትን መንገድ ሰጥቶናል።)
- 3ኔፊ 12፥48 (ኢየሱስ ፍፁም እንድንሆን ነግሮናል፡፡)

*የሰማዩ አባታችንን ስንወድ፣ ኢየሱስን ለመታዘዝ እንፈልጋለን*

- የማቴዎስ ወንጌል 22፥37–40 (ኢየሱስ ሁለቱን አበይት ትዕዛዛት ሰጠ።)
- የዮሐንስ ወንጌል 8፥29 (ኢየሱስ ሁልጊዜ አባቱን የሚያስደስቱትን ነገሮች ይሰራ ነበር።)
- የዮሐንስ ወንጌል 14፥15, 21–24 (የሰማዩ አባታችንን እና ኢየሱስን የምንወድ ከሆነ የእነርሱን ትዕዛዛት እንጠብቃለን።)
- 1ቆሮንቶስ 2፥9 (የሰማዩ አባታችን ለሚወዱት ታላቅ በረከትን አዘጋጅቶላቸዋል፡፡)

*ማንኛውም የምንቀበለው በረከት የሚመጣው በመታዘዝ ምክንያት ነው*

- መጽሐፈ ምሳሌ 3፥1–4፣ ትንቢተ ኤርምያስ 7፥23 (የሰማይ አባታችን ሰዎች የሚታዘዙት ከሆነ እንደሚባርካቸው ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል፡፡)
- 2 ኔፊ 2፥3–9 አልማ 22፥19፣ ሞሮናይ 6፥4 (ኢየሱስ ካልረዳን በስተቀር በራሳችን ለሰማይ አባታችን በረከት ብቁ መሆን አንችልም፡፡)
- ሞዛያ 2፥24 (የሰማይ አባታችንን ስንታዘዝ ይባርከናል)
- ሞዛያ 2፥41 (ትዕዛዛትን የሚታዘዙ ብዙ በረከቶችን ይቀበላሉ እናም ደስተኞች ናቸው፡፡)



ወጣቱ ሀብታም ገዥ ንብረቱን ለመሰዋትና ኢየሱስን ለመከተል አምነት ነሎት ነበር።

# መስዋዕት

*ምዕራፍ 23*

*ሌላውን ሰው ለመርዳት አንድን ነገር አሳልፈን በመስጠት እንደ እርሱ እንድንሆን እኛን ለመርዳት የሰማይ አባታችን የዕቀዱ ክፍል ነው፡፡ አንድን ሰው ለመርዳት አንድን ነገር አሳልፈህ በመስጠት የሚያስደስት ስሜት ተሰምቶህ ያውቃልን?*

**ኢየሱስ ህይወቱን ለእኛ ሲል ሰውቷል**

የሰማይ አባታችንን ለመታዘዝ፣ ሁልጊዜ መስዋዕት ማድረግ አለብን፡፡ መስዋዕት መክፈል ማለት አንድን ሰው ለመርዳት አንድን ነገር አሳልፎ መስጠት ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ታላቅ መስዋዕትነትን አድርጓል፡፡ ስለእኛ ሀጢያት ተሰቃይቷል። ከዚያም ሕይወቱን ሰጥቶናል፡፡

ኢየሱስ ሕይወቱን ለእኛ ሲል በመስጠቱ ምክንያት፣ ማንኛውም ሰው ከሞት በኋላ እንደገና ይኖራል፡፡ ሁላችን ዳግም የማይሞት ፍጹም አካል ይኖረናል፡፡ ይህም ትንሳኤ ይባላል፡፡ ደግሞም፣ በኢየሱስ እምነት ያላቸው፣ ስለፈፀሙት ኃጢአት ሁሉ ንሥሐ የገቡ፣ ኢየሱስ ባደረገው የኃጢአት ሥርየት ምክንያት ለኃጢአታቸው ይቅርታን ያገኛሉ እናም ወደ ሰማይ አባታችን ለመመለስ ይችላሉ።

አዳም ከኖረበት ጊዜ አንስቶ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከኖረበት ጊዜ ድረስ፣ ሰዎች ለሰማይ አባታችን እንስሳትን ይሰዉ ነበር። መልካሙን እንስሳ ከመንጋዎቻቸው ወይም ከእረያዎቻቸው መንጋ መርጠው ይሰዋሉ። እነዚህም ሁልጊዜ በመጀመሪያ ከተወለዱት ከወንዶቹ ነበር። ትክክለኛውን እንስሳ ከመረጡ በኋላ፣ ያርዷቸውና፣ ግማሹን በእሳት በማቃጠል ለሰማይ አባታችን መስዋዕት ያቀርባሉ፡፡

ሰዎቹ እነዚህን እንስሳትን ይሰዉ የነበረው የሰማዩ አባታችንን ሕግ ለመታዘዝ ነው። በዚህ ዓይነት ምንም እንኳ ለእነሱ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ማቀም ቢሆንም የሰማዩ አባታችንን ለመታዘዝ ፍቃደኘነታቸውን አሳይተዋል። የሰማያዊ አባታችን እንስሶችን እንዲሰዉ ያዘዛቸው እርሱ አንድ ልጁን እንደሚሰዋላቸው ለማስገንዘብ ነበር። ኢየሱስ የሰማዩ አባታችን የበኩር ልጅ፣ በማናቸውም መንገድ ፍጹም ሆኖ ወደዚህ ዓለም ይመጣል እናም ስለእኛ ኃጢአት እራሱን ለመሰዋት ፈቃደኛ ይሆናል፡፡



*ሉብርሃም ባለው ታላቅ እምነት ልጁን ይስሃቅን በጌታ ትእዛዝ ለመሰዋት ተዘጋጅቶ ነበር፡፡*

ኢየሱስ ህይወቱን ከሰጠ በኋላ፣ ህዝቡ እንስሳትን በጭራሽ እንዳይሰዉ አዟል። እርሱ ያደረገልንን ታላቀ መስዋዕተ እንድናስታውስ ቀዱስ ቁርባንን ሰጥቶናል። የቀዱስ ቁርባን ዳቦና ውሃ ሲሞተ የሰጠንን የኢየሱስን ስጋና ደም ይወክላል።

### ውይይት

• በጥንቱ ጊዜ የእንስሳተ መስዋዕተነተ ምንን ይወክላል?

### መስዋዕትነት የሰማይ አባታችን ለእኛ ካለው ዕቀድ አንዱ ክፍል ነው

የሰማዩ አባታችን አሁንም በተለያየ መንገድ መስዋዕተ እንድናደርግ ይጠይቀናል። በተሰበረ ልብና የዋህነተ በተሞላበተ መንፈስ መስዋዕተ እንድንሰዋለተ ያዘናል። ይህ ማለተ ዛጢያታችንን እና ተዕቢታችንን ማቆም ማለተ ነው። ይህም ማለተ ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆንም ሁልጊዜ ኢየሱስን ለማስታወስና ተዕዛዛቱን ለመጠበቀ ፈቃደኛ መሆን ማለተ ነው። ይህም ማለተ፣

1. በኢየሱስ እምነተ ይኖረናል፣ ለኃጢአታችን ንስሐ እንገባለን፣ እንጠመቃለን፣ እናም የኢየሱስን ተዕዛዛተ እንጠብቃለን።
2. ለሌሎች ሰዎች በኢየሱስ ስለአለን እምነተ እንናገራለን ስለዚህም የእርሱ ተከታዮች እና የቤተክርስቲያኑ አባል መሆን ይችላሉ።
3. በኢየሱስ ቤተክርስቲያን እርሱ እንድናደርግ የሚፈልገውን ማንኛውንም ስራ ለመስራተ ፈቃደኞች እንሆናለን።
4. ወንዶች ቤተሰቦቻቸውን እና ሌሎችንም በሚቀጥለው ሕይወተ ወደ ሰማይ አባታችን ለመመለስ እንዲዘጋጁ ለመርዳተ የክህነተ ስልጣንን ለመቀበል ፈቃደኞች ናቸው።

ወደ ሰማይ አባታችን ለመመለስ፣ ኢየሱስ እንድንሰጥ የጠየቀንን ማንኛውንም ነገር ለመስጠተ ፈቃደኞች መሆን አለብን። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ዓለም ላይ የኢየሱስን ሥራ ለመርዳተ የተቻለንን ሁሉ በማድረግ ሰዓታችንን መጠቀም ይኖርብናል ብሏል፡፡

### ውይይት

• የኢየሱስን መስዋዕተነተ ዛሬ እንደምታስታውስ እንዴተ ለማሳየተ ተችላለህ?

አንድ ሃብታም ሰው ኢየሱስን ለዘለዓለም ከሰማዩ አባታችን ጋር ለመኖር ምን ማድረግ እንዳለበተ ጠየቀው። ኢየሱስም የሰማዩ አባታችንን ተዕዛዛተ ሁሉ እንዲጠብቀ ነገረው፡፡ ሀብታሙም ሰው ከልጅነተ ጊዜው አንስቶ ተዕዛዛቶችን ማክበሩን መለሰለተ። ኢየሱስም አንድ ተጨማሪ ነገር ማድረግ የሚገባው መኖሩን ነገረው። ያለውን ማንኛውንም ነገር መሸጥ አለበተ። ከዚያም ገንዘቡን ለድሆች ሰጥቶ ኢየሱስን መከተል አለበተ። ሃብታሙ ሰው ይህን ሲሰማ፣ አዘነ። ያለውን ሁሉ ተቶ ኢየሱስን ለመከተል አልፈለገም ነበር፡፡

ሀብታሙ ሰው ጥሩ ሰው ነበር። ከልቡ በመጣር ተዕዛዛቶችን መታዘዝ ሞክሮ ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ያለውን ማንኛውንም ነገር እንዲሰጥና እሱን እንዲከተለው ሲጠይቀው፣ ሊያደርገው አልቻለም።

ሁለቱ የኢየሱስ ሐዋሪያት፣ ጴጥሮስና እንድሪያስ የሚባሉት፣ እርሱን ለመከተል ያላቸውን ማንኛውንም ነገር ለመተው ፈቃደኞች ነበሩ። ኢየሱስ እሱን እንዲከተሉት ሲጠይቃቸው፣ ሥራቸውን ተተው እናም ተከተሉት።

አብርሃምም ያለውን ማንኛውንም ነገር ለሰማዩ አባታችን ለመስጠት ፈቃደኛ ነበር። አብርሃም በምድር ላይ የኖረው ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት ነበር፡፡ በዚያን ወቀት፣ የሰማዩ አባታችን ሰዎች እንስሳቶችን መስዋዕት እንዲያቀርቡ ይፈልግ ነበር። የአብርሃምን ታዛዥነት ለማየት ፈተነው ልጁን ለመስዋዕትነት እንዲያቀርብ አዘዘው። አብርሃም ለመታዘዝ ፍቃደኛ ነበር። መሰዊያ ገንብቶ ልጁን በላዩ ላይ አኖረ፣ መልአክ እርሱን ሲያስቆመው አብርሃም ልጁን ለመባረክ ዝግጁ ነበር። መልአኩም ለአብርሃም ልጁን መሰዋት እንደሌለበት ነገረው። አብርሃም የታዘዘውን ሁሉ ለመስጠት ፍቃደኛ መሆኑን የሰማዩ አባታችን ያውቀ ነበር፣ የራሱንም ልጅ እንኳ ቢሆን። አብርሃም የሰማዩ አባታችንን በጣም ስለሚወደው እርሱ ያዘዘውን ማናቸውንም ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ ነበር፣ አብርሃም ማንኛውንም ነገር ለሱ ለመሰዋት ፈቃደኛ በመሆኑ ምክንያት የሰማይ አባታችን አብርሃምን ባረከው።

### ውይይት

- ኢየሱስ ያዘዘውን ማናቸውንም ነገር ለመስጠት ፍቃደኛ ያልነበርው ሰው ምሳሌ ማን ነው?
- የሰማይ አባታችን እንዲስጥ ያዘዘውን ማናቸውንም ነገር ሁሉ በፈቃደኝነት የሚሰጥ ሰው ምሳሌ ማን ነው?
- እነዚህ ሁኔታዎች ቢያጋጥሙህ ምን ታደርግ ነበር?

## ለኢየሱስ ሥራ አንዳንድ ነገሮችን መስዋዕት ልናደርግ ይገባናል

ኢየሱስን ከተከተልን ቤተሰቦቻችን ሊቃወሙን ይችላሉ። የእርሱን ትዕዛዛቶች ስንታዘዝ ሌሎች ሰዎች ሊስቁብን ወይም ጉዳት ሊያደርሱብን ይሞክራሉ። የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን በመቀላቀላችን ሥራችንን ልናጣ እንችላለን።

ሌሎችን ስለ ኢየሱስ ሄደን ለማስተማር ጊዜያችንና ገንዘባችንን መስዋዕት በማድረግ መተባበር አለብን። የቤተክርስቲያን መሪዎች የእሱን ተግባር ማከናወን እንዲችሉ ጊዜአችንን እነርሱን በመርዳት መጠቀም ይገባናል፡፡ ሌሎች ከእኛ ቤተሰቦች የኢየሱስን ሥራ ሲያከናውኑ ጊዘያችንንና ገንዘባችንን ለመርዳት መጠቀም አለብን። የሰማይ አባታችን የኢየሱሱን ምስክርነት ከምንከድ ህይወታችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይፈልጋል።

### ውይይት

- የምትወደውን ንብረት እንድትተው ብትጠየቀ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማሃል?
- ለኢየሱስ ሥራ ለመሰዋት ምን ያህል ፍቃደኛ ነህ?

## መስዋዕትነት በሌላ መንገድ የማይመጣ በረከትን ያስገኛል

መስዋዕትነት እራስ ወዳድ እንዳንሆን ይረዳናል። የሰማዩ አባታችንን ማገልገልና ሌሎች ሰዎችን መርዳት እንማራለን። ለሌሎች የምናደርገው ነገር ደስተኞች እንደሚያደርገን

እንማራለን። ኢየሱስ እንድንሰራ ያዘዘንን መስራት በዚህ ምድር ላይ ሊኖረን ከሚችለው ማንኛውም ነገሮች የበለጠ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ እንማራለን። ሌሎችን ማገልገል ለእራሳችን ብቻ ከማሰብ የተሻለ እንደሆነ እንማራለን፡፡ በፍቃደኝነት መስዋዕትነት ስንከፍል የሰማያዊ አባታችንም ከተውነው ነገሮች ሁሉ የተሻለ በረከትን ሲሰጠን እናገኘዋለን።

ለሌሎች መስዋዕት መክፈል ኢየሱስ ለእኛ ያደረገልንን በተሻለ ለመረዳት ያስችለናል። ህይወቱን አሳልፎ እስከ መስጠት ይወደናል። አንድ ነገርን፣ ለሰማያዊ አባታችን ወይም ለሌሎች ሰዎች ስንሰዋ፣ እኛ የበለጠ እንወዳቸዋለን፡፡ ተወዳጅ፣ እንደ ኢየሱስና እንደ ሰማይ አባታችን መሆን እንጀምራለን።

ብዙ ንብረት ማግኘት መጥፎ አይደለም። ሰማያዊው አባታችን አንዳንድ ጊዜ ሌሎችን መርዳት እንድንችል እነዚህን ነገሮች ይሰጠናል። ነገሮን ንብረታችንና ገንዘባችን ያለመውደድ ከባድ ነው፡፡ እነርሱን ለማግኘት ጠንክረን እንሰራለን። ከነዚህ ጥቂቶቹ ነገሮች ለመኖር አስፈላጊያችን ናቸው። ቢሆንም፣ ለእነዚህ ነገሮች የሰማዩ አባታችን ሌሎች ልጆቹን ለመርዳት የሚፈልጋቸውን ማናቸውንም ነገሮች ስለማንተው በጣም መጨነቀ የለብንም።

ሁሉም የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላቶች በህይወታቸው ውስጥ የሰማያዊ አባታችንንና ኢየሱስን ማገልገል ይገባቸዋል። የሰማዩ አባታችንን እና ኢየሱስን ንብረታችንን ከምንወደው በላይ እንደምንወዳቸው ማሳየት፣ የምንችለው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን መሪዎች እንድናደርግ የሚጠይቁንን ነገር ስናደርግ ነው። ጊዜያችንን በመሰዋት ሌሎችን ማስተማርና ማገልገል ይኖርብናል፣ ብቁ ሆነን ከሰማያዊ አባታችን ጋር ለመኖር፣ የኢየሱስን ስራ ለማገዝ እርሱ ከእኛ የሚጠብቀው ያለንን ነገር በሙሉ በፈቃደኝነት መስጠት ነው።

ኢየሱስ ለሚታዘዙት እና ለሚያገለግሉት ታላቀ በረከተን ቃል ገብቶላቸዋል። አሁን ለርሱ ስራ መስዋዕት ብንከፍል በኋላ የምንቀበለውን አስደናቂ ነገሮች መገመት አንችልም ብሏል።

## *ማጣቀሻ*

*ኢየሱስ ህይወቱን ለእኛ ሲል ሰውቷል*

- የሉቃስ ወንገል 9፡57–62 (ኢየሱስን መታዘዝ በህይወታችን ዘመን ከማናቸውም ነገር የበለጠ አስፈላጊ ነው።)
- የዮሐንስ ወንጌል 15፡12–13 (ኢየሱስ ለእኛ ያለውን ታላቀ ፍቀር ሕይወቱን ለእኛ በመስጠት አሳይቶናል፡፡)

*መስዋዕትነት የስማዩ አባታችን ለእኛ ካለው ዕቀድ አንዱ ክፍል ነው*

- ኦሪት ዘፍጥረት 22፡1–14 (አብርሃም ልጁን ይስሃቀን ለመስዋዕት እንዲያቀርብ ተነገረው።)
- የማቴዎስ ወንጌል 4፡18–20 (ኢየሱስ ጴጥሮስንና እንድሪያስን የእሱ ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ጠራቸው፡፡)
- ወደሮሚ ሰዎች 12፡1 (የሰማዩ አባታችንን ለማገልገል ጊዜያችንን መጠቀም አለብን።)

*ለኢየሱስ ሥራ አንዳንድ ነገሮችን መሰዋት ልናደርግ ይገባናል*

- ት እና ቃ ክፍል 64፥23 (ይህ የመስዋዕት ጊዜ ነው፡፡)
- ት እና ቃ 97፥8 (የሰማዩ አባታችን በፍቃደኝነት ለእሱ መስዋዕት የሚካፈሉትን ይቀበላቸዋል።)

*መስዋዕትነት በሌላ መንገድ የማይመጣ በረከትን ያስገኛል*

- የማቴዎስ ወንጌል 19፥29 (ለወንጌሉ ሲሉ ለሚሰዉ ኢየሱስ ታላቅ በረከትን ቃል ገብቶላቸዋል።)
- የሉቃስ ወንጌል 12፥16–34 (ከዚህ ዓለም ነገሮች በፊት የሰማዩ አባታችንን መንግስት መሻት ይኖርብናል፡፡)

# የአምልኮ ቀን

*ምዕራፍ 24*

*የሰማይ አባታችን በየሳምንቱ አንድ ቀን እርሱን ለማምለክ እንድንጠቀምበት ነግሮናል። ያን ቀን የተቀደስ ቀን ስናደርገው ብዙ በረከቶችን እናገኛለን፡፡*

## የሰማይ አባታችን እኛን ለመርዳት የአምልኮን ቀን ሰጥቶናል

የሰማይ አባታችን ብዙ ችግሮች እንዳሉን ያውቃል። በየቀኑ ብዙ ነገሮችን ማድረግ ይገባናል። ምግብና ልብሶቻችንን ለማግኘት መስራት ይኖርብናል። ምግባችንን ማዘጋጀት እና ሌሎች የዕለት ስራዎችን ማከናወን ይገባናል፡፡

እነዚህን ሁሉ ነገሮች ስንሰራ፣ የሰማይ አባታችንን በቀላሉ እንዘነጋለን። እንዲሁም የሰማይ አባታችን እንድናደርግ የሚፈልገውን ነገሮች በቀላሉ እንዘነጋለን። ስለእርሱ ሰማያዊ አባታችን ከምናደርገው በላይ አብዛኛውን ስለ ዕለታዊ ፍላጎቶቻችን የበለጠ እናስባለን።


የሰማይ አባታችን ስለሱ ለማስብ ጊዜ እንደሚያስፈልገን ያውቃል። እሱ እንድናደርግ የሚፈልግውን ለመማር ጊዜ ያስፈልገናል፡፡ በዚህ ምክንያት፣ ከሰባት ቀናቶች ውስጥ አንድ ቀን ከስራችን እንድናርፍና ስለ እሱ እንድንማር ነግሮናል፡፡

በስድስተ ቀናት ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት የሰማይ አባታችን ምድርን ፈጠረ። እነዚህን ጊዜያቶች ቀን ብሎ ጠራቸው። ምድርን በመፍጠር በሰባተኛው ቀን ከስራው አረፈ። በሳምንተ አንድ ቀን ከእለታዊ ሥራችን ማረፍ እንዳለብን ነግሮናል፡፡

## የአምልኮ ቀን የትኛው እንደሆነ የሰማይ አባታችን ነግሮናል

የሰማይ አባታችን በጥንት ዘመን ለነበሩተ ሰዎች ከሳምንቱ ቀናቶች ሰባተኛውን ቀን ለአምልኮ እንዲጠቀሙበተ ነግሮአቸዋል። ይህም ቀን እርሱ ምድርን ከፈጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን ያረፈበተን ሕዝቦች ለማስታወስ እንዲረዳቸው ነበር፡፡

ኢየሱስ ከሞተ በኋላ፣ በሳምንቱ መጀመሪያው ቀን ከሞት ተነሳ። የኢየሱስ ተከታዮች የሳምንቱን የመጀመሪያ ቀን የኢየሱስን የትንሳኤ ቀን እንዲያስታውሱና እንዲያከብሩ ለመርዳት እንደ አምልኮ ቀን ይጠቀሙበታል። ይህንንም የጌታ ቀን ብለን እንጠራዋለን። (ኢየሱስ አንዳንድ



*እሁድ የአምልኮ ቀን ነው፡፡*

ጊዜ ጌታ ተብሎ ይጠራል።) እኛም ይህንን *የሰንበት ቀን ብለን እንጠራዋለን። በጥንት ጊዜ ለአምልኮት ከሚጠቀሙበት የተለየ ቢሆንም፣ እስከአሁንም ከሰባቱ ቀናት አንዱ ነው። አሁንም በሳምንት ስድስቱን ቀናት መደበኛ ሥራችንን እናከናውናለን። ከዚያም በሰባተኛው ቀን የሰማዩ አባታችንን እናመልከበታለን፡፡

በጊዜያችን፣ አብዛኛው ህዝብ የሳምንቱን የመጀመሪያውን ቀን፣ እሁድን፣ እንደ አምልኮት ቀን ይጠቀሙበታል። በአንዳንድ ምክንያቶች የሰማዩ አባታችን ለነቢያቶቹ እንደነገራቸው በጥቂት አገሮች ውስጥ ሕዝቦች ሌላ ቀንን እንደ አምልኮት ቀን ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ነው።

## የጌታን ቀን በቅድስና መጠበቅ እንችላለን

የክህነት ሥልጣን ያለው ሰው ብቻ ሌሎችን ማጥመቅ ይችላል። ማንኛውንም ሰው ለማጥመቅ ከሌጲስ ቆጶሱ ወይም ከቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ፍቃድ ማግኘት ይኖርበታል፣ የሚያጠምቀ ሰው ከተጠማቂው ሰው ጋር አብሮ ወደ ውሃው ውስጥ ይገባል። አጥማቂው ሰው ተጠማቂውን በስሙ በመጥራት አጭር ፀሎት ያደርጋል። ከዚያም እሱ ሙሉ በሙሉ የሚጠመቀውን ሰው ከውሃ ውስጥ በማስገባት እንደገና ከውሃው ውስጥ ያወጣዋል።

4. የሰማዩ አባታችንና እየሱስ ክርስቶስ ያደረጉልንን እርስ በርሳችን በመነጋገር ስለ ክርስቶስና ስለወንጌል ተምህርቶች ታሪክን መማር እንችላለን።
5. ከሌሎች የሳምንቱ ቀናቶች ከምንሰራው ሥራ ማረፍ
6. ፀሎት
7. የታመሙትን ሰዎች መጎብኘትና እንዲሻላቸው መርዳት።
8. በኋላ ማስታወስ እንድንችል በቤተሰቦቻችን ላይ ሊከሰቱ የሚችሉትን ነገሮች ይፃፉ፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላቶች በአምልኮት ቀን ቅዱስ ቁርባንን መካፈል አለባቸው፡፡ ለእኛ ያደረገውን ነገሮች እና ስለ ኢየሱስ በማሰብ ለመካፈል መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ኢየሱስን ለማስታወስ እንዲረዳቸው የሰማያዊ አባታችንን መጠየቀ ይኖርባቸዋል፡፡ ቅዱስ ቁርባንን ሲቀበሉ፣ የገቡትን የተቀደሰ ቃል ኪዳናቸውን ማስታወስ ይኖርባቸዋል፡፡ የሰማዩ አባታችን ኢየሱስን ከታዘዙ ስለገባላቸው ቃል ኪዳን ማሰብ ይኖርባቸዋል፡፡

በአምልኮት ቀን ማድረግ የሌለብን ብዙ ነገሮች አሉ። መሥራት የለብንም። ቤተሰቦቻችንን፣ አገልጋዮቻችን፣ ወይም እንስሳትን እንዲሰሩ ማድረግ የለብንም፡፡ ማናቸውንም ነግሮች ማንበብ፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ማየተ፣ ወይም ሙዚቃ መስማት በአጠቃላይ ስለ ሰማያዊ አባታችንና ኢየሱስ ከማስብ የሚያግዱንን መከታተል የለብንም። ወደ ስፖርት ጨዋታ መሄድ አያስፈልገንም። እቃዎችን መግዛት ወይም መሸጥ አይገባንም፡፡ እነዚህ ነገሮች አስፈላጊ ይመስሉን ይሆናል፣ ነገር ግን ስለ ሰማዩ አባታችንና ኢየሱስ በዚህ በተቀደሰ ቀን እንድናስብ ሊረዱን አይችሉም፡፡

ምናልባት በሰንበት ቀን መሥራት የሚኖርብን ቀን ይኖራል፣ ነገር ግን ላለመሥራት ሙከራ ማድረግ ይኖርብናል። መስራታችን በፍጹም አስፈላጊ ሲሆን፣ በምንሰራበት ወቀት የሰማዩ አባታችንንና ኢየሱስን ለማስታወስ መሞከር ይኖርብናል፡፡

### ውይይት

- በጌታ ቀን ምን ማድረግ አለብን?
- በሰንበት ቀን መስራት የማይገባን ምንድነው?

## የጌታን ቀን በቅድስና በመጠበቅ የሰማዩ አባታችን ይባርከናል

የሰንበት ቀን ዓላማ ዘወተር አንድ ዓይነት ነው፡፡ በየቀኑ ከምንሰራው ሥራ የምናርፍበት ቀን ነው፡፡ ይህ ቀን ስለሰማዩ አባታችን የምንማርበትና ከሱ ጋር ለዘለዓለም ለመኖር መዘጋጀት ነው፡፡ የሰማዩ አባታችን እንድንሰራ የሚፈልገውን ይበልጥ በመማር ህይወታችንን የምናሻሽልበት ቀን ነው።

ይህ ለእኛ ጥሩ ቀን ነው፡፡ የሰማዩ አባታችንን እና በዚህ ምድር ያለንበትን ምክንያት እንድናስታውስ ይረዳናል፡፡ የሰማዩ አባታችን በጌታ ቀን እንድናደርግ የሚፈልገውን ብናደርግ፣ በረከትን እናገኛለን። ቤተሰቦቻችን የበለጠ ደስተኞች ይሆናሉ፡፡ ሰውነታችን ይነቃቃል። ወደ ሰማዩ አባታችን እና ወደ ትምህርቶቹ የበለጠ እንጠጋለን፡፡ በሳምንቱ ጊዜ ይበልጥ የመንፈስ ቅዱስ ጠንካራ ተጽዕኖ ይሰማናል፡፡ ለሰማዩ አባታችን ታዛዦች በመሆናችን ምክንያት ምግባችንን፣ ልብሳችንን፣ እና የምንፈልገውን ሌሎች ነገሮች እንድናገኝ ይረዳናል፡፡ ደስተኞች እንድንሆንና የበለጠ ስለእሱ እንድንማር ይረዳናል፡፡

### ውይይት

- የሰንበት ቀንን እንደ ተቀደሰ ቀን የምንጠብቀበት አንዳንድ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

### ማጣቀሻ

*የሰማይ አባታችን እኛን ለመርዳት የሰንበት ቀን ሰጥቶናል*

- ኦሪት ዘፍጥረት 2፥2–3 (የሰማዩ አባታችን በሰባተኛው ቀን ከሚሰራው ስራ አርፎአል፡፡
- ኦሪት ዘፀዓት 20፥8 (የሰማዩ አባታችን የሰንበትን ቀን በቅድስና እንድንጠብቀ አዞናል።)
- ኦሪት ዘፀዓት 35፥1–3 (በሰንበት ቀን ማረፍ ይኖርብናል።)
- የማርቆስ ወንጌል 2፥27 (የሰማዩ አባታችን የሰንበት ቀንን የሰጠን እኛን ለመርዳት ነው፡፡)
- ሞዛያ 18፥23 (የዕረፍት ቀንን በቅድስና መጠበቅ አለብን።)

*የትኛው ቀን የሰንበት ቀን እንደሆነ የሰማይ አባታችን ነግሮናል*

- የሐዋሪያት ሥራ 20፥7 (ሐዋሪያቶችም በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ቅዱስ ቁርባንን ተካፍለዋል፡፡)
- 1ኛ ቆሮንቶስ 16፥2 (ሰዎች በመጀመሪያው ቀን ለሰንበት ተዘጋጅተዋል።)

የጌታን ቀን በቅድስና መጠበቅ እንችላለን

- ኦሪት ዘፀዓት 20፥9–10 (በሰባተኛው ቀን መሥራት እንደማያስፈልገን የሰማያዊ አባታችን ይነግረናል፡፡)

*የጌታን ቀን በቅድስና በመጠበቅ የሰማይ አባታችን ይባርከናል*

- ትንቢተ ኢሳያስ 58፥13–14 (የአምልኮን ቀን በቅድስና በመጠበቃችን የሰማዩ አባታችን ይባርከናል።)

# የንጽህና ሕግ

*ምዕራፍ 25*

*የሰማዩ አባታችን ልጆች እንዲኖረን የተቀደሰ ሃይል ሰጥቶናል። ይህንን ሃይል እንዴት እንደምንጠቀምበተ ነግሮናል፡፡ በተክክል ከተጠቀምንበት፣ በጣም ደስተኞች መሆን እንችላለን፡፡*

**የሰማዩ አባታችን ልጆች እንዲኖረንና የንጽህናን ህግ እንድንታዘዝ ነግሮናል**

አዳምና ሄዋን ከተጋቡ በኋላ፣ የሰማዩ አባታችን ልጆች እንዲኖራቸው ነግሯቸዋል፡፡ ለአዳምና ለሚስቱ፣ ለሄዋን፣ ልጆች እንዲኖራቸው የነገራቸው፣ በሰማይ የሚኖሩት መንፈሶች ወደ ምድር መጥተው ስጋና አጥንት ያለው አካል ሊቀበሉ እንዲችሉ ነው። የስጋና አጥንት አካል የሰማይ አባታችን ከሰጠን ታላላቀ ስጦታዎች አንዱ ነው። የሰማያዊ አባታችን የስጋና የአጥንት አካል ስላለው ልጆቹም እንደርሱ እንዲሆኑ ይፈልጋል፡፡

ልጆች እንዲኖሩን የሚያደርገው ሃይል በጣም የተቀደሰ ነው፡፡ የሰማዩ አባታችን ይህን ሃይል እንዴት እንደምንጠቀም የሚነግረን ሕግ ሰጥቶናል። ይህም ህግ የንጽህና ህግ ተብሎ ይጠራል፡፡ ህጉም እንደዚህ ይላል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሊኖረን የሚገባው በህግ ከተጋባነው ሰው ጋር ብቻ መሆን አለበት። ይህም ማለተ ከጋብቻ በፊተ በፍጹም የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸም አይገባንም፣ ከጋብቻ በኋላም የግብረስጋ ግንኙነት የሚኖረን ባል ከሚስት ወይም ሚስት ከባሏ ጋር ብቻ መሆን አለባተ፡፡

ማስወረድ ወይም ያልተወለደን ሕጻን በእናቱ ማህፀን ውስጥ እያለ ማስወገድ እና እንዲሞተ መፍቀድ ወይም በእናቱ ውስጥ እያለ ህጻኑን መግደል፣ ከፀሎተ እና ከጳጳሱ ወይም ከቀርንጫፍ ፕሬዚዳንተ አርዳታ ከሚያስፈልገው በስተቀር ስህተተ ነው። ማንኛውም ሰው እንዲያስወርድ መርዳተ የለብንም፡፡

የንጽህናን ህግ ለልጆቻቸው ማስተማር ያለባቸው ወላጆች ናቸው፡፡ አካላቸው የተቀደሰ እንደሆነና ማንም የአካላቸውን የተወሰኑ ክፍሎች እንዲነካ መፍቀድ እንደማይገባቸው ቤተሰቦች ማስተማር አለባቸው። ልጆቻቸው ከሌሎች የሚማሩተን የተሳሳተ ሃሳቦችንና ቃላቶችን ማረም አለባቸው።

ልጆች እያደጉ ሲሄዱ፣ የሰማዩ አባታችን ልጆች እንዲኖረን ሃይል የሰጠን መሆኑን እና ያንንም ሃይል መጠቀም ጥሩ የሚሆነው ከጋብቻ በኋላ መሆኑን መማር አለባቸው። የልጆቻችን ዕድሜ 12 ወይም 13 ዓመት በሚሆናቸው ጊዜ፣ ልጆች እንዴት እንደሚፈጠሩ አስቀድመን እንዲረዱት መርዳት አለብን። ከመጥፎ አደጋ ወይም ከሃሰተ ትምህርቶች እነርሱን ለመጠበቅ አስቀድመን በጣም ብልሃት በተሞላበተ መንገድ ማስተማር ያስፈልገናል።

## *ውይይት*

- የሰማያዊ አባታችን ልጆች እንዲኖረን ሃይል የሰጠን ለምን ነበር?
- የንጽህና ህግ ምንድን ነው?
- ለልጆቻችን ስለ አካላቸው ምንድነው ማስተማር የሚገባን?

## ሰይጣን የንጽህናን ህግ እንድንተላለፍ ይፈልጋል

ሰይጣን ወደ ሰማያዊ አባታችን እንዳንመለስ ሊያግደን ይፈልጋል፡፡ ሰይጣን የንጽህናን ህግ እንድንተላለፍ ይፈልጋል። ልጆችን የማግኘት ሃይል ቅድስና እንደሌለው እንድናስብ ይፈልጋል። የንጽህናን ህግ መተላለፍ ሀጢያት እንዳልሆነ እንድናስብ ፍላጎቱ ነው፡፡

ሰይጣን ይህንን ህግ እንድንተላለፍ ለማግባባት የብልሃተ መንገዶችን ይጠቀማል፡፡ ሌሎች ሰውነታችንን እንዲያዩና እንዲነኩ መፍቀድ ተቀባይነተ እንዳለው አድርገን እንድናስብ ያደርጋል። ሰይጣን መጥፎ ሃሳቦችን እንድናስብ ይፈልጋል፡፡ ንፁህ እንዳንሆን የሚፈተኑን ስዕሎችን፣ ፊልሞች እና ዳንሶችን እንድንመለከተ ይገፋፋናል። ንጽህና እንዲጎድለን የሚፈታተኑን ዳንስና ታሪኮችን፣ ቀልዶችንና ሙዚቃ እንድናደምጥም ይገፋፋናል። ሰይጣን እነዚህን ነገሮች እንድናደርግ የሚፈልገው፣ አካላችን ቅድስና የሌለው መስሎ እንዲታይ እናም ልጆች የማግኘተ ሃይላችንን በተሳሳተ መንገድ እንድንጠቀም ነው።

አንዳንድ ጊዜ ሠይጣን በስሜቶቻችን አማካኝነተ ይፈታተነናል። ሰይጣን ብቸኛ ስንሆን፣ ስንደናገር ወይም ደስታ ሲርቀን ያውቃል፡፡ የንጽሑናን ሕግ ለመተላለፍ ፍላጎተ እንዲኖረን ለማድረግ እነዚህን የድክመተ ጊዜያቶችን ይመርጣቸዋል። በፈለግነው በማናቸውም መንገድ ልጆች እንዲኖሩን የሚያደርገውን ሃይልን ለመጠቀም መብተ እንዳለን አድርገን እንድናስብ ይፈልጋል፡፡ የንጽህናን ህግ በመተላለፋችን ምንም መጥፎ ነገር እንደማይፈጸምብን አድርገን እንድናስብ ይሞክራል፡፡

የሰማዩ አባታችን የሰይጣንን ፈተናዎች ለመቋቋም ጥንካሬ ሊሰጠን ይችላል፡፡ እርሱ ክፉ ነገሮችን እንድናይ ወይም የክፋተ ሃሳቦችን እንድናስብ አይፈልግም፡፡ እኛ መቋቋም ከምንችለው በላይ ሰይጣን እንዲፈታተነን እንደማይፈቅድለተ ቃል ገብቶልናል። ፈተናን መቋቋም እንድንችል መፍተሔን አዘጋጅቶልናል፡፡

ሰይጣንን ለመቋቋም እንዲረዳን ለሰማያዊ አባታችን መፀለይ እንችላለን። ስንፀልይ፣ የሰማዩ አባታችን መንፈስ ቅዱስን እንዲረዳን ይልክልናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ አካላችን የተቀደሰ እንደሆነ እና ልጆች እንዲኖሩን የሚያደርገውም ሃይል የተቀደሰ መሆኑን እንድናስታውስ ይረዳናል፡፡

ይህንን ሃይል በስህተት መንገድ እንዳንገለገልበት መንፈስ ቅዱስ ይረዳናል፡፡ መልካም ነገርን መርጠን እንድናይና እንድናነብ ስለ እሱም እንድናስብ ይረዳናል፡፡ የንጽህናን ህግ መተላለፍ እንደሚያሳዝነን እና ይህን ህግ ማክበር ደስተኞች እንደሚያደርገን እንድናስታውስ ይረዳናል፡፡

### *ውይይት*

- ሰይጣን የንጽህናን ህግ እንድንተላለፍ የሚፈልገው ለምንድነው?
- የሰይጣንን ፈተናዎች ለመቋቋም ምን ማድረግ እንችላለን?
- የሰማይ አባታችን የንጽህናን ህግ እንድንጠብቅ እንዴት ይረዳናል?

### የንጽህናን ህግ መተላለፍ በጣም ከፍ ያለ ኃጢአት ነው

አርስ በርሳቸው የሚፈቃቀሩና የሚከባበሩ ባልና ሚስት መሃከል ያለው የወሲባዊ ግንኙነቶች ጥሩና ንፁህ ነው። ልጆች እንዲኖረን የሰማዩ አባታችን የሰጠን መንገዶች ናቸው፡፡ ለባልና ሚስትም አርስ በርሳቸው ፍቀራቸውን እንዲገላለፁ በስሜቶቻቸው እንዲቀራርቡ መንገዶች ናቸው። ነገር ግን ከጋብቻ ውጪ የወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም በጣም ከፍ ያለ ሃጢያት ነው፡፡

የንጽህናን ሕግ መተላለፍ ደስተኞች አያደርገንም፡፡ የሰማዩ አባታችንን አለመታዘዛችን ስናገናዝብ፣ ጥፋተኝነትና ሐፍረት ይሰማናል፡፡ የሰጠንን የተቀደሰ ሃይል በተሳሳተ መንገድ እንደተጠቀምንበትና ሌሎችን እንዳስከፋን እንገነዘባለን። የንጽህናን ሕግ መተላለፍ ሐጻናቶች ከትክክለኛ ቤተሰቦች ውጭ እንዲወለዱ ምክንያት ያደርጋል።

ሁለት ኃጢአቶች ብቻ የንጽህናን ሕግ ከመተላለፍ የበለጡ በጣም ከፍ ያሉ ናቸው፡፡ እነዚህም መንፈስ ቅዱስን መካድና መግደል ናቸው፡፡ የንጽህናን ሕግ የተላለፉ ይቀርታን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ የሰማዩ አባታችን በኢየሱስ ካመኑና ስለፈጸሙት ሃጢአት ንስሐ ከገቡ፣ ይቀር እንደሚላቸው ተናግሯል። የንጽህናን ሕግ የተላለፉና ንስሐ ያልገቡ ከሰማዩ አባታችን ጋር ለመኖር አይችሉም።

ያለ አግባብ የተደፈሩ ወይም በመጥፎ ሁኔታ ግብረስጋ የተፈፀመባቸው የንጽህናን ሕግ በመተላለፍ አይጠየቁም።

ይቀርታ በኢየሱስ በማመንና በንስሃ ብቻ ሊገኝ ይችላል፡፡ ስለሃጢአታችን እውነተኛ የመፀፀት ስሜትና ሃጢአት መስራታችንን መገንዘብ ይገባናል። ስህተት ነገሮችን ማድረግ ማቆም እና ስለሃጢአታችን ለሰማያዊ አባታችን፣ ጉዳት ላደረስንበት ሰውና፣ ለትክክለኛ የክህነት ስልጣን ላለው (ኤጲስ ቆጶስ፣ የቅርንጫፍ ፕሬዚዳንት፣ ለስቴክ ፕሬዚዳንት ወይም ለሚሽን ፕሬዚዳንት) መናዘዝ አለብን፡፡ የሰማያዊ አባታችን በኢየሱስ አምነት ላላቸው፣ ኃጢአታቸውን ለሰማዩ አባታችን እና ለትክክለኛ የቤተክርስቲያን መሪዎች በትህትና ለሚናዘዙና ከልባቸው ንስሃ ለሚገቡ ይቀር እላችኋለሁ ብሏል። ይህንን ሁሉ ነገሮች ያላደረገ ማንኛውም ሰው እውነተኛ ንስሃ ስላልገባ ይቀርታን ሊያገኝ አይችልም፡፡

### ውይይት

- የንጽህናን ሕግ መተላለፍ ከባድ ኃጢአት የሆነው ለምንድን ነው?
- የንጽህናን ሕግ ስንተላለፍ ምን ልንሆን እንችላለን?
- የንጽህናን ሕግ ማክበር የሚገባን ለምንድነው?
- የንጽህና ሕግ በመተላለፍ ንስሃ ለመግባት ምን ማድረግ አለብን?

## የንጽህናን ህግ መታዘዝ ደስተኛ ያደርገናል

የንጽህናን ሕግ ስንጠብቀ፣ ልጆቻችን ሊከተሉት የሚገባ መልካም ምሳሌ እናሳያቸዋለን። እርሱን በመታዘዛችን የሰማዩ አባታችን እንደሚደሰተብን እናውቃለን። ስንታዘዝ፣ በቤተሰባችን ውስጥ ያሉ እንደምንወዳቸው ያውቃሉ፣ እና ጥፋተኝነት ወይም እፍረት ሊሰማን የሚችልበተ ምክንያተ አይኖረንም፡፡ በይበልጥ እንደ ሰማዩ አባታችን እንሆናለን። የሰማዩ አባታችን እኛንና ልጆቻችንን ወይም የምናገኛቸውን ልጆች፣ የንጽህናን ሕግ ስንጠብቀ ይባርከናል፡፡

የሰማዩ አባታችንን በሰውነታችን ውስጥ ያደረገውን ሃይል በጋብቻ መጠቀም ደስታንም ያስገኛል፡፡ በጥንዶች ጋብቻ መሃከል የሚደርግ ወሲባዊ ግንኙነተ ደስታን ሊያስገኝ ይችላል፡፡ በጠነከረ የፍቀር ስሜተ በአንድ ላይ ሊያቀራኛቸው ይችላል፡፡ የሚወለዱ ልጆች ከሰማዩ አባታችን በረከተ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ልጆች ጭንቀተንና ተካዜን በወላጆቻቸው ላይ ቢፈጥሩም ደግሞ፣ ታላቀ ደስታን ያስገኛሉ፡፡ በሕይወታችን ውስጥ የምናውቃቸው አንዳንድ ታላላቀ ደስታዎች ልጆቻችን በሚያድጉበተ፣ በሚማሩበተ፣ በሚያገቡበተ እና የራሳቸው ልጆች በሚኖራቸው ጊዜ ይመጣሉ።

### ውይይት

- የንጽህናን ሕግ ስንታዘዝ ምን ዓይነተ በረከቶችን እናገኛለን?
- የንጽህናን ሕግ ካለመጠበቃችን ይልቀ ስንጠበቀ ደስተኛ የምንሆነው ለምንድን ነው?

### ማጣቀሻ

*የሰማዩ አባታችን ልጆች እንዲኖሩንና የንጽህናን ሕግ እንድንታዘዝ ነግሮናል*

- ኦሪተ ዘፍጥረተ 1፣28 (የሰማዩ አባታችን አዳምንና ሔዋንን ልጅ እንዲኖራቸው አዟቸዋል።)
- ኦሪተ ዘፀዓተ 20፣14 (የሰማዩ አባታችን ዝሙተን እንዳንፈፅም አዞናል።)
- ኦሪተ ዘሌዋውያን 20፣10–23 (የሰማዩ አባታችን የንፅህናን ህግ የጣሱተን ይቀጣል እንዲሁም
 የታዘዙተን ደግሞ ይባርካቸዋል።)
- 1ኛ ቆሮንቶስ 6፣19 (አካላችን የተቀደሰ ነው።)
- ሞሮናይ 9፣9 (ንጽህና ከሌላ ነገሮች የበለጠ የከበረ ነው፡፡)

*ሰይጣን የንጽህናን ሕግ እንድንተላለፍ ይፈልጋል*

- የማቴዎስ ወንጌል 5፣27–28 (ስህተተ ነገሮችን ለመስራተ ማሰብ እንኳን የለብንም።)
- 1ኛ ቆሮንቶስ 10፣13 (የሰማዩ አባታችን ፈተናን ለመቋቋም ሃይል ይሰጠናል።)
- አልማ 12፣14 (ጥሩ ነገርን መናገር እና ማሰብ አለብን።)

*የንፅህናን ህግ መተላለፍ በጣም ከፍ ያለ ሃጢያት ነው*

- መጽሐፈ ምሳሌ 6፥25–32 (የንጽህናን ህግ መተላለፍ ሃዘንተኛ ያደርገናል።)
- ትንቢተ ኢሳይያስ 1፥16–18 (የሰማዩ አባታችን ንስሃ የሚገቡትን ይቀር ይላቸዋል።)
- 1 ቆሮንቶስ 6፥9 (ዝሙትን የሚፈጽሙ ወደ ሰማዩ አባታችን መንግስት ሊገቡ አይችሉም)
- አልማ 39፥5 (የንጽህናን ሕግ ካለመታዘዝ የሚበልጡ ሁለት ኃጢአቶች ብቻ ናቸው።)

*የንጽህናን ሕግ መታዘዝ ደስተኛ ያደርገናል*

- ወደ ገላቲያ ሰዎች 5፥16–24 (የሰማዩ አባታችን የንጽህናን ህግ የሚታዘዙትን ይባርካቸዋል።)
- ወደ ቲቶ 2 (በጽድቀ መኖር ደስተኛ ያደርጋል።)

# ታማኝነት

*ምዕራፍ 26*

*የሰማዩ አባታችን በሚያደርገው ሁሉ ታማኝ ነው፡፡ እኛ እንደእርሱ ታማኝ እንድንሆን ይፈልጋልን?*

**የሰማዩ አባታችን በምናደርገው ሁሉ ታማኝ እንድንሆን ይነግረናል**

ታማኝ መሆን ማለት እውነትን መናገር ማለት ነው፡፡ ታማኝ መሆን ማለት አለመዋሸት ወይንም አለመስረቅ ነው፡፡ እውነት ያልሆነውን ነገር ከተናገርን፣ እየዋሸን ነው። የእውነትን ከፊል ብቻ ከተናገርን፣ እየዋሸን ነው። ሰዎችን እውነት ያልሆነውን ነገር እንዲያምኑ ከመራን፣ ታማኞች እየሆንን አይደለም፡፡

መስረቅ የሌላ ሰው የሆነን ነገር ያለ ፈቃድ መውሰድ ነው፡፡ አንድን ነገር ከመደብር ያለክፍያ መውሰድ ስርቆት ነው፡፡ የሰማዩ አባታችን መስረቅ እንደሌለብን ነግሮናል፡፡

ታማኝ ሰው ለሚከፈልባቸው ሰዓታት ሁሉ ጠንክሮ ይሰራል። ታማኝ አሰሪ ለሰራተኞቹ በስራቸው መጠን የሚገባቸውን ይከፍላል። ታማኝ ሰው ለአገልግሎቱና ለሚሸጣቸው ነገሮች ተገቢውን ክፍያ ይጠይቃል፡፡ ከሰማዩ አባታችን ጋር ለመኖር የምንፈልግ ከሆነ ታማኞች መሆን ይኖርብናል፡፡

ሰይጣን ታማኝ እንዳንሆን ሊያግባባ ይሞክራል። በማንኛውም መንገድ ታማኝ ካልሆንን፣ ሰይጣንን መከተላችን ነው። ሰይጣን ውሸትን ይወዳል፡፡ ሰይጣን ታማኝ አለመሆን ብልህነት እንደሆነ እንድናስብ ይፈልጋል። ታማኞች በማንሆንበት ጊዜ ደስተኞች እንደምንሆን አድርገን እንድናስብ ለማድረግ ይሞክራል፡፡ ታማኝ ያለመሆን ሃጢያት እንዳልሆነ እንድናስብ ይፈልጋል፡፡ ሰይጣን ታማኝ እንዳንሆን ይፈልጋል ስለዚህ ደስተኞች አንሆንም፡፡

የሰማዩ አባታችን በማንኛቸውም ጊዜያቶች ሁሉ ታማኞች እንድንሆን አስተምሮናል፡፡ በምንዋሽበት ጊዜ ያዝናል፡፡ መዋሸት በማንኛቸውም ጊዜ ስህተት እንደሆነ እንድናውቅ ይፈልጋል፡፡ ታማኝ ያለመሆን ሁሌም ስህተት ነው እናም ደስተኞች እንዳንሆን ያደርገናል፡፡

አንዳንድ ሰዎች ዕቃዎችን የሚሰርቁበት ምክንያት የራሳቸው የማድረግ መብት እንዳላቸው በማሰብ ነው፡፡ አንዳንድ ወጣት ሰዎች በትምህርት ቤት የሚያታልሉበት ምክንያት የተሻለ

ደረጃን ለመቀበል ወይም ሌሎች ተማሪዎች እንደሚያደርጉት ለማድርግ ነው። አንዳንድ ሰዎች የሚዋሹት ሌሎች ስለነሱ መልካም እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። ከነዚህ አንዳቸውም ምክንያት ሌብነትን ወይም ውሸትን ትክክል አያደርጓቸውም፡፡ ለመዋሸት ምክንያት ስናደርግ፣ ታማኞች አይደለንም፡፡

## *ውይይት*

- ታማኝነት ምንድን ነው?
- ታማኝ ስንሆን የምንከተለው ማንን ነው?

## በምናደርገው ሁሉ ታማኞች መሆን እንችላለን

ምንም እንኳ አስቸጋሪ ቢሆን እውነትን ለመናገር ድፍረት ሲኖረን ታማኞች መሆን እንችላለን። የሰማዩ አባታችን እርሱን ከጠየቅን ታማኞች እንድንሆን ይረዳናል፡፡ ታማኝ መሆንን እንድንመርጥ መንፈስ ቅዱስን እንዲረዳን ይልክልናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ታማኝነት ትክክለኛ ነገር እንደሆነ እንድናውቅ ይረዳናል፡፡

የኢየሱስን ተምሕርቶች ስንረዳ፣ በምናደርገው ሁሉ ታማኝ ለመሆን እንሻለን፡፡ እኛ የሰማዩ አባታችን ልጆች እንደሆንን እና ሁላችንም ወንድሞችና እህቶች እንደሆንን ኢየሱስ አስተምሮናል፡፡ ታማኞች በመሆን ብቻ እውነተኛ ደስተኞች መሆን እንደምንችል አስተምሮናል። የእኛ ያልሆነ አንድ ነገር በቤታችን ውስጥ ቢኖር ሰላምን ለራሳችን ልናገኝ አንችልም፡፡ በእርሱ እምነት ካለን፣ ንስሃ ከገባንና፣ እውነተኛ ታማኞች ከሆንን ተመልሰን ከሰማዩ አባታችን ጋር ለዘለዓለም ደስተኞች ሆነን ለመኖር እንደምንችልም አስተምሮናል።

እነዚህን ነገሮች ሁሉ ስንረዳ፣ ታማኝ ለመሆን መፈለግን እንሻለን፡፡ ሌሎች ሰዎችን ለመዋሸት አንፈልግም። ከእርሱ ጋር ተመልሰን ለመኖር እንድንችል የሰማዩ አባታችንን ማስደሰት እንፈልጋለን። የሰማይ አባታችን ይቀር እንዲለን ስህተቶቻችንን ለመቀበልና ለማረም እንፈልጋለን።

## *ውይይት*

- ትንሽ ውሸት ብንዋሽ እንኳ፣ ለምን ንሰሃ እንገባለን?
- በምናደርገው ሁሉ እንዴት ታማኞች መሆን እንችላለን?
- የሰማዩ አባታችን ታማኝ እንድንሆን እንዴት ይረዳናል?

## ታማኝ መሆን ደስተኛ ያደርገናል

ታማኝ ስንሆን፣ ጥሩ ስሜት ይሰማናል። የሰማዩ አባታችንም በእኛ ደስ ይለዋል። የጥፋተኝነት ስሜት አይኖረንም፡፡ ከሌሎች የምንደብቀው ነገር ስለሌለ ጥሩ ስሜት ይሰማናል። አንድ ሰው መዋሸታችንን ያውቅብናል ብለን አንጨነቅም።

ታማኝ ስንሆን በይበልጥ እንደ ሰማዩ አባታችን እንሆናለን፡፡ ከእርሱ ጋር ተመልሰን ለመኖር ዝግጅት እያደረግን እንደሆነ እናውቃለን። ታማኞች ስንሆን ሌሎች ሰዎች ያምኑናል፡፡ ታማኝ

ከሆንን፣ የሰማዩ አባታችን ማድረግ የምንፈልገውን ትክክለኛውን ነገር እንድናደርግ እንድንችል ይረዳናል፡፡

## *ውይይት*

- ታማኝ ስንሆን እንዴት ያለ ስሜት ይኖረናል?
- ማንኛውም ሰው ታማኝ ቢሆን ኖሮ ዓለም ምን ተመስል ነበር?

## *ማጣቀሻ*

- ኦሪት ዘፀዓት 20፥15–26 የማቴዎስ ወንጌል 19፥18 (የሰማዩ አባታችን እንዳንሰርቀ ወይም እንዳንዋሽ ነግሮናል።)
- መጽሃፈ ምሳሌ 19፥5 (ውሸታሞች ከቀጣት ማምለጥ አይችሉም፡፡)
- የዮሐንስ ወንጌል 10፥44፣ 2ኛ ኔፊ 2፥18 (ሰይጣን የውሸት ሁሉ አባት ነው፡፡ ዛዘንተኞች እንድንሆን ይፈልጋል፡፡)
- የሐዋሪያት ሥራ 5፥1–10 (የሰማዩ አባታችን የሚዋሹትን ይቀጣል፡፡)
- ወደ ፊልጵስዮስ ሰዎች 4፥8 (ማናቸውም እውነት ወይም ታማኝ ነገር፣ ለማድረግ መሞከር ይኖርብናል፡፡)
- ወደ ዕብራውያን ሰዎች 6፥18 (የሰማዩ አባታችን አይዋሽም።)

# የጥበብ ቃል

*ምዕራፍ 27*

*የሰማዩ አባታችን ከሰጠን ታላቅ በረከቶች አንዱ የአካላችን ስጋና አጥንቶች ናቸው፡፡ ለሰውነታችን ጥንቃቄ እንድናደርግ የሚረዳንን የጤንነት ሕግን ሰጥቶናል። ስለዚህ የጤንነት ህግ ምን ታውቃለህ?*

**አካሎቻችን የተቀደሱ ናቸው**

ወደ እዚህ ምድር የመጣንበት አንዱ አስፈላጊ ምክንያት የስጋና አጥንት አካልን ለማግኘት ነው፡፡ የሰማዩ አባታችንን ለመምሰል እንድንችል አካል ያስፈልገናል፡፡ እንደ እርሱ ለመሆን ማወቅ የሚገቡንን ነገሮች መማር የምንችለው በሥጋና አጥንት አካላቶች ብቻ ነው። ልጆች ሊኖሩን ይችላሉ፡፡ ከሰማያዊ አባታችን ጋር ተመልሰን ለመኖር የሚያስፈልገንን ሥርዓቶች ማግኘት እንችላለን፡፡ ከአካል ውጪ እነዚህን ነገሮች ማድረግ አንችልም፡፡

መንፈሳችን በአካላችን ውስጥ በመኖሩ ምክንያት፣ አካላችን የተቀደሰ ነው፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ሲኖረንና እርሱን ለመታዘዝ ስንሞክር፣ የሰማዩ አባታችን መንፈስ ቅዱስን ከእኛ ጋር እንዲሆን ይልክልናል፡፡ ለአካላችን ጥንቃቄ ካላደረግን እና የማንታዘዝ ከሆንን መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር መቆየት አይችልም፡፡

ስንሞት መንፈሳችን ከአካላችን ይለያል። ኢየሱስ ሲሞት፣ መንፈሱ ከአካሉ ተለየ። ከሶስት ቀናት በኋላ፣ መንፈሱ ወደ አካሉ እንደገና ተመለሰ እናም ተነሳ፡፡ ኢየሱስ ወደ ህይወት ለመመለስ ሃይል ነበረው፣ ለእኛ ሲል በመሰዋቱ ምክንያት፣ እኛም ከሞትን በኋላ እንነሳለን፡፡ መንፈሳችንና አካላችን እንደገና አንድ ይሆናል። ለዘለዓለም ከሰማያዊ አባታችን ጋር ለመኖርና እንደ እርሱ ለመምሰል የማይሞት የስጋና አጥንት አካል እንዲኖረን የሚያስፈልግ መሆኑን ኢየሱስ ያውቃል፡፡

የሰማዩ አባታችን ለአካሎቻችን ጥሩ ጥንቃቄ እንድንወስድ ይፈልጋል፡፡ ለአካሎቻችን ጥሩ ጥንቃቄ ከወሰድን፣ ጤነኞችና ጠንካሮች በመሆን እናም እርሱ እንድናደርግ የሚፈልግብንን ሌሎች ነገሮች ማድረግ እንችላለን። ሁላችንም ለሰውነታችን ጥሩ ጥንቃቄ ለማድረግ ወይም ጉዳት የሚያስከትልባቸውን ነገሮች ለማድረግ መወሰን አለብን፡፡ ሰውነቶቻችን በዚህ ህይወት

እና በኋለኛው ህይወት አስፈላጊ እንደሆኑ እናውቃለን፡፡ ጥሩ ጥንቃቄ ልንወስድላቸው ያስፈልገናል። ለአካሎቻችን ጥንቃቄ የማናደርግ ሲሆን የሰማዩ አባታችን ደስተኛ አይሆንም፡፡

ወላጆች ለልጆቻቸው አካሎቻቸው የተቀደሱ ከሰማይ አባታችን የተሰጡ ስጦታዎች እንደሆኑ ለማስተማር እና አካሎቻቸውም ለምን አስፈላጊ እንደሆኑ ለመግለፅ ዋነኞቹ መሆን አለባቸው። ለሰውነታቸው ጥሩ ጥንቃቄ ማደረግ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ልጆች ሲረዱ፣ የሰይጣንን ፈተና ሊከተሉ አይፈልጉም፡፡

## *ውይይት*

- የስጋና አጥንት አካል ያለን ለምንድነው?
- አካላችን ቅዱስ የሆነው ለምንድነው?
- ለልጆቻችን ለአካሎቻቸው ጥንቃቄ አስፈላጊነቱን ማስተማር አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?

## የሰማይ አባታችን የጤንነትን ሕግ ሰጥቶናል

የሰማዩ አባታችን ለሰውነታችን መልካም የሆኑትንና መልካም ያልሆኑትን ነገሮች ነግሮናል፡፡ ይህም በቅዱስ መጽሃፍት የተጻፈና የጥበብ ቃል ተብሎ የሚጠራው ነው፡፡

የሰማዩ አባታችን የጥበብ ቃልን ለነብዩ ዮሴፍ ስሚዝ ገልፆለታል። ይህም ህግ ነው፡፡ ጠንካራ አዕምሮና አካሎች እንዲኖረን ይህን ሕግ መጠበቅ አለብን።

የጥበብ ቃል ለሰውነታችን መልካም የሆነውን ያስተምረናል፡፡ ለሰውነታችን መልካም የሆነውን ነገር ብቻ መብላትና መጠጣት ይገባናል። ፍራፍሬ፣ አተክልቶች፣ እና ጥራጥሬዎችን መብላት አለብን፡፡ እነዚህን ምግቦች ከመጠን በላይ መብላት ሳይሆን (አመጣጥነን) መመገብ አለብን። ብዙ ስጋ መመገብ የለብንም፡፡

## *ውይይት*

- ለሰውነታችን መልካም የሆኑ ምግቦች ምንድን ናቸው?
- ዕረፍት እና የአካል እንቅስቃሴ ማድረግ ከሰማያዊ አባታችን የጤና ሕጎች ጋር የሚያገናኘው ምንድነው?
- ሰውነታችንን በንጽህና መጠበቅ የሚገባን እንዴት ነው?

## የሰማዩ አባታችን ለሰውነታችን መልካም ያልሆነውን ነግሮናል

ሰይጣን ሰውነታችንን ያለ አግባብ እንድንጠቀምበት ሊያሳምነን ሙከራ እንደሚያደርግ የሰማይ አባታችን ያውቃል፡፡ አንዳንድ ለሰውነታችን መልካም ያልሆኑትን ነገሮች የሰማዩ አባታችን ነግሮናል፡፡ አልኮልን መጠጣት ለሰውነታችን ጥሩ አይደለም። የሰማዩ አባታችን ቢራ፣ አልኮሆል፣ እና የአልኮልነት ይዘት ያላቸው ሌሎች መጠጦችን እንዳንጠጣ አዞናል፡፡ እነዚህ ነገሮች በሽታን እና በቤት ውስጥ ደስታን ሊያሳጡን ይችላሉ፡፡ አንድ ሰው እነዚህን ነገሮች ሲጠጣ፣ በትክክል ማሰብ አይችልም፡፡ እነዚህ መጠጦች ብዙውን ጊዜ ሰዎች መጥፎ ነገሮችን እንዲመርጡ፣ እንዲዋሹ፣ ያላቸውን ገንዘብ እንዲያባክኑ እናም የንጽህናን ሕግ እንዲተላለፉ

ይመሯቸዋል። ነፍሰጡር ሴት የአልኮል መጠጥ ስትጠጣ፣ በማሕጸኗ ያለውን ሕጻን ልትጎዳ ትችላለች፡፡ የአልኮልን መጠጥ የሚጠጡ ሰዎች ብዙ የከፉ ችግሮችን ያስከትላሉ።

የሰማዩ አባታችን ደግሞ ትንባሆ ለሰውነታችን ጎጂ እንደሆነ ነግሮናል። ትንባሆን ማጤስ ወይም ማኘክ የለብንም፡፡ የሳይንስ ሊቆች እንዳረጋገጡት ትንባሆ በሽታን እንደሚያስከትል እናም በማህጸን ያለ ጽንስን ሊጎዳ እንድሚችል ነው፡፡

የሰማዩ አባታችን ቡናና ሻይም ደግሞ እንዳንጠጣ ነግሮናል፡፡ ቡናና ሻይን ጎጂ ዕጽ ስላላቸው መጠጣት የለብንም። ንጥረ ነገሮችን ዶክተር በመድሃኒትነት ከሚሰጠን በስተቀር መውሰድ የለብንም፡፡

የሰማዩ አባታችን አልኮል፣ ትንባሆ፣ እና ንጥረ ነገሮች እንዴት በአግባቡ እንደምንጠቀምባቸው ካወቀን ሊረዱን እንደሚችሉ ነግሮናል፡፡ አልኮልን ሰውነታችንን ለማጠብ አገልግሎት እንድናውል ነግሮናል። ትንባሆ ቆስለው የታመሙ ከብቶችን ለማዳን ልንገለገልበት እንችላለን፡፡ ንጥረ ነገሮችም አንዳንድ ጊዜ ስንታመም ለፈውስ ሊረዱን ይችላሉ። ነገር ግን እነዚህን ነገሮች ለመጠቀም ከመሞከራችን በፊት፣ ከአዋቂ ሰዎች ለምን እንደሚያገለግሉና እንዴት ልንገለገልበት እንደምንችል ተምህርት ማግኘት አለብን፡፡ በተሳሳተ መንገድ ከተገለገልንባቸው፣ ጉዳት ሊያስከትሉብን ይችላሉ፡፡

ማንኛቸውንም መልካም የማይሆኑንን ነገሮች ወደ ሰውነታችን መውሰድ የለብንም፡፡ የጥበብ ቃል በጣም ጎጂ ስለሆኑት ነገሮች ይነግረናል፡፡ ይህ በጣም አስፈላጊ ህግ ነው፡፡

የጥበብ ቃል ልንጠቀምበተ የማይገባንን ማናቸውንም ነገሮች አይነግረንም። ሰውነታችን ወይም አዕምሮአችን ጎጂ የሆኑትን ማናቸውንም ነገሮች ምንም እንኳ በጥበብ ቃል ያልተዘረዘሩ ቢሆንም መጠቀም እንደሌለብን ማስተዋል አለብን፣ በሌሎች መንገዶች ለሰውነታችን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል፡፡ ለሰውነታችን ጥንቃቄ መውሰድ አለብን፣ በሌላ አነጋገር ንጽህናቸውን ለመጠበቀ በየጊዜው በማጠብና በቂ የአካል ማጎልመሻ ማድረግና እረፍት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ውይይት

- አንዳንድ ነገሮች ለሰውነታችን መልካም እንዳልሆኑ እንዴት እናውቃለን?
- ወደ ሰውነታችን መውሰድ የሌለብን አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

## የጥበብ ቃልን በመታዘዝ ታላቀ በረከት ይመጣል

የጥበብ ቃልን ከጠበቅን፣ የሰማዩ አባታችን ሰውነታችን እነዚህን ትዕዛዛቶች ባለመታዘዛችን ከሚጠነከረው በላይ እንዲጠነክር ይባርከዋል። ይህንን ትዕዛዝ ካከበርን በዚህ ምድር የሱን ስራ በተሻለ ሁኔታ ለመስራት እንችላለን። ይህን ሕግ ከጠበቅን ያለድካም መሬመድ እና ያለ መዝለፍለፍ ለመሮጥ እንደምንችል ነግሮናል፡፡ ይህም ታላቀ በረከት ነው፡፡

የሰማዩ አባታችን ደግሞ የጥበብ ቃልን ከታዘዝን በታላቀ ጥበብና እውቀት እንደሚባርከንም ቃል ገብቶልናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ያለእርሱ ማወቀ የማንችለውን ብዙ አስፈላጊ የሆኑትን

ነገሮች ይገለፅልናል። ሰይጣንም በእኛ ላይ ሃይል አይኖረውም፡፡ የጥበብን ቃል ከጠበቅን፣ በይበልጥ ጤነኞች እንሆናለን እናም ከሰማያዊ አባታችን ጋር *ለዘለዓለማዊ ህይወት እንዘጋጃለን።

## *ውይይት*

- የጥበብ ቃልን በመታዘዝ የምናገኘው በረከት ምንድን ነው?

## *ማጣቀሻ*

*አካሎቻችን የተቀደሱ ናቸው*

- 1 ቆሮንቶስ 3፡16–17 (መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር ሊሆን ይችላል፡፡)

የሰማዩ አባታችን የጤንነትን ሕግ ሰጥቶናል

- መጽሐፈ መሳፍንት 13፡13–14 (የሳምሶን እናት ሳምሶን ጤነኛ ልጅ እንዲሆን አንዳንድ ነገሮችን እንዳትጠጣና እንዳትበላ ታዛ ነበር።)
- ትንቢተ ኢሳይያስ 5፡11–12 እና መጽሐፈ ምሳሌ 20፡1 (የወይን ጠጅና ሌሎች የአልኮል መጠጦች ለእኛ ጥሩ አይደሉም።)
- ት እና ቃ 89፡5–17 (አንዳንድ ምግቦችና መጠጦች ለእኛ መልካም ሲሆኑ፣ ሌሎች ግን አይደሉም)

*የጥበብ ቃልን በመታዘዝ ታላቀ በረከት ይመጣል*

- ትንቢተ ዳንኤል 1፡8–17 ዳንኤልና ጓደኞቹ ለእነሱ መልካም የሆነውን ምግብ ስለተመገቡ እናም ለእነሱ ተስማሚ ያልሆነውን ከተመገቡት ይበልጥ ጤነኛና ብልህ ለመሆን ችለዋል፡፡
- ት እና ቃ 89፡1–4፣ 18–21 (የጥበብ ቃልን በመታዘዝ የሚገኙት በረከቶች ተመዝግበዋል።)



# አስራት እና በኲራት

*ምዕራፍ 28*

*አስራትና በኲራት ምንድን ናቸው፣ እናም በፍቃደኝነት ስንከፍል የሰማዩ አባታችን እንዴት አድርጎ ይባርከናል?*

**የሰማዩ አባታችን አስራት እንድንከፍል ነግሮናል**

አስራት ከምናገኘው ገንዘብ እና ማናቸውም ነገሮች ከአስር አንዱ ነው፡፡ የሰማዩ አባታችን ለሰዎች አስራት እንዲከፍሉ ከብዙ ብዙ ዓመታት በፊት ነግሯቸዋል፡፡ አብርሃም፣ ያዕቆብ ብዙ ሌሎችም ይሄን ትዕዛዝ ታዘዋል።

ገንዘብን ብናገኝ ወይም ብንቀበል፣ ለአስራት አንድ አስረኛውን መስጠት አለብን፡፡ እንስሳት ወይም አዝርዕት ካለንም ደግሞ አስራትን መክፈል እንችላለን፡፡ ከአዝርዕቱ ወይም በአመት ውስጥ ካሳደግነው አዲስ እንስሳት ከአስር አንድ እንሰጣለን፡፡ አዝርዕትና እንስሳትን ከመስጠት ፋንታ ከተቻለ ሸጠ ገንዘቡን ለቤተክርስቲያን መስጠት አለብን፡፡ አስራታችንን ለኤጲስ ቆጶሱ ወይም ለቅርንጫፍ ፕሬዚዳንት እንከፍላለን። የምንሰጠው ምን ያህል እንደሆን ካላወቅን፣ ኤጲስ ቆጶሱን ወይም የቅርንጫፍ ፕሬዚዳንቱን ስለ አስራት ህግ ለመገንዘብ እንዲረዳን መጠየቅ አለብን፡፡

አስራትን ስንከፍል፣ በመላው ዓለም ወንጌል እንዲሰራጭ እንረዳለን። አስራት የሚጠቀመው የቤተክርስቲያንን ህንጻ ለመገንባት፣ መጽሃፍቶችን ለማሳተም፣ እና በኢየሱስ እውነተኛ ቤተክርስቲያን ውስጥ አስፈላጊ ለሆኑ ሌሎች ነገሮች ለመክፈል ይውላል፡፡

ልጆችም ቢሆኑ አስራት መክፈል አለባቸው። ቤተሰቦቻቸው አስራት ሲከፍሉ ሲመለከቱ እነሱም ይህንን ማድረግ ይማራሉ፡፡ በወጣትነታቸው ጊዜ አስራት መክፈል ከጀመሩ፣ ለአካለ መጠን ሲደርሱና የራሳቸውን ቤተሰብ ሲመሰርቱም አስራታቸውን ለመክፈል ፍላጎት ይኖራቸዋል።

***ውይይት***

- አስራትን ለመክፈል የተነገረን ምን ያህል ነው?
- ልጆቻችን አስራታቸውን እንዲከፍሉ እንዴት ማስተማር እንችላለን?

## አስራትን በመክፈል ለሰማዩ አባታችን ፍቅራችንን እናሳየዋለን

አስራታችንን በፈቃደኝነት መክፈል አለብን ስለስዚህም የሰማይ አባታችን ይቀበልና ስለክፍያውም ይባርከናል። አስራታችንን መክፈል በመፈለጋችን ምክንያት መክፈል ይገባናል።

አስራትን ለመክፈል ፍላጎት ከሌለን፣ የሰማዩ አባታችን ስለሰጠን በረከት ሁሉ ማሰብ አለብን፡፡ አስራትን በፈቃድኝነት በመክፈል የሰማዩ አባታችንና ሌሎች ሰዎችን እንደምንወድ እናሳያለን።

### *ውይይት*

- 2ኛ ቆሮንቶስ 9፥6–7 ያንብቡ
- በፈቃደኝነት መስጠት ለምን አስፈላጊ ይሆናል?

## አስራትን ከከፈልን የሰማዩ አባታችን ሊባርከን ቃል ገብቶልናል

አስራታችንን ስንከፍል የሰማዩ አበታችን ደስተኛ ይሆናል። ከከፈልን እንደሚባርከን ቃል ገብቶልናል፡፡ በሚሰጠን ሁሉ ምን መስራት እንዳለብን ማወቀ እስኪያቀተን ብዙ በረከቶችን እንደሚሰጠን ነግሮናል። ደግሞም አስራታችንን በፈቃደኝነት ከከፈልን ከዛጢአተኞች ጋር እንደማንጠፋም ነግሮናል፡፡

የሰማዩ አባታችንን በይበልጥ ብናውቀው ይባርከናል። በይበልጥ ስለ ወንጌል እንድናውቀም ይባርከናል፡፡ በየዕለቱ የወንጌል ትምህርትን በመጠበቅና ቤተሰቦቻችንም እንደወንጌሉ እንዲኖሩ ለመርዳት የበለጠ ጥንካሬ ይሰጠናል። ሌሎች ስለ ወንጌል እንዲማሩ ስንረዳቸውም እሱን ደስተኛ ያደርገዋል፡፡

አስራታችንን ስንከፍል፣ ገንዘባችንን በተሻለ ሁኔታ ለመቆጣጠርና ራስ ወዳድነታችንም ለመቀነስ እንማራለን። መጀመሪያ ከገቢያችን ላይ አስራታችንን ስናነሳ፣ እና ከዚያ በኋላ የሰማዩ አባታችን የተረፈንን ገንዘብ ለመቆጣጠር እንድንችል ለሚያስፈልገን በቂ እንዲኖረን ይባርከናል።

### *ውይይት*

- አስራትን በመክፈል የምንቀበላቸው ሶስቱ በረከቶች ምንድን ናቸው?

## የፆም በኩራት ስንከፍል ሌሎች ሰዎችን እንረዳለን

እንደ ቤተክርስቲያን አባልነታችን በየወሩ አንድ ቀን እንጾማለን፡፡ ይህ ማለት ያለመብል ሁለት የምግብ ጊዜያትን እንቆያለን። ለ24 ሰዓታት ምንም አንበላም ወይም አንጠጣም። ጾም ጠንካራ መንፈስ እንዲኖረን እንደሚረዳን እናምናለን።

የሰማዩ አባታችን በኩራት የሚባለውን የፆም በኩራት የሚባለውን ስጦታ እንድንሰጥ ነግሮናል። ይህም በኩራት ስንጾም በቀን ውስጥ ላልበላናቸው ምግቦች የምናውለውን መሆን አለበት። ከቻልን ከዚህ የበለጠ መስጠት ይገባናል። ይህን ካደረግን የሰማዩ አባታችን ይባርከናል፡፡

እነዚህ በኩራቶች ችግረኞች ለሆኑት ምግብ፣ መጠለያ፣ ልብስ፣ እና ሌሎች ለሚያስፈልጋቸው ነገሮች ይውላል። የፆም በኩራት ስንከፍል ሌሎች ሰዎችን መውደዳችንን እናሳያለን።

የፆም በኩራትን ለኤጲስ ቆጶስ ወይም ቀርንጫፍ ፕሬዚዳንት እንሰጣለን፣ እና እሱም ገንዘቡን ለድሆችና ልዩ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ለመርዳት ይጠቀምበታል፡፡ ድሆችን ብንረዳ የሰማዩ አባታችን እንደሚባርከን ነግሮናል፡፡ ለጸሎታችን ምላሽ ይሰጠናል እናም እርዳታ በምንሻ ጊዜ ይረዳናል። ዘወትርም ይመራናል እናም ወንጌልን በተሻለ እንድንረዳ ይረዳናል፡፡

ቤተክርስቲያኑ አስራትና በኩራትን የምትጠቀመው

1. ወንጌልን ለሌሎች ለማስተማር፡፡
2. ቤተመቀደስን፣ የፀሎት መሰብሰቢያ አዳራሾችንና ሌሎች የቤተክርስቲያን ህንጻዎችን ለመገንባትና ለመንከባከብ ይውላል።
3. የትምህርት መጽሃፍቶችን ለማተም እና የቤተክርስቲያኑ ሰዎች ሊያውቁ የሚፈልጉትን ሌሎች ነገሮችን ስለወንጌል እንዲማሩና እናም እንዲያውቁ የሰማዩ አባታችንን ስራ ለመስራት።
4. እራሳቸውን ለመጠበቅ የማይችሉትን ለመርዳት፡፡

## ውይይት

- የሰማዩ አባታችን ለሰጠን በረከቶች ሁሉ ምስጋናችንን እንዴት ልናሳየው እንችላለን?
- የጾም በኩራትን መክፈል ለምን ደስተኛ ያደርገናል?

## ማጣቀሻ

*የሰማዩ አባታችን አስራትን እንድንከፍል ነግሮናል*

- ኦሪት ዘፍጥረት 14፥20፣ ወደ ዕብራዊያን ሰዎች 7፥1–10 (አብርሃም ለመልከ ጼዴቀ አስራትን ከፍሏል።)
- ኦሪት ዘፍጥረት 28፥20–22 (ያዕቆብ የሰማዩ አባታችን የሰጠውን አንድ አስርኛውን ለመመለስ ቃል ገብቷል፡፡)
- መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ፡ 31፥5–6, 12, ነህሚያ 10፥37–39 (የእስራኤል ልጆች አስራትና ብኩራትን ከፍለዋል።)

*አስራትን በመክፈል ለሰማዩ አባታችን ፍቀራችንን እናሳየዋለን*

- ትንቢተ ሚልኪያስ 3፥8–10 (አስራትና በኩራትን ካልከፈልን የሰማዩ አባታችንን ሰርቀናል ማለት ነው።)
- 2ኛ ቆሮንቶስ 9፥6–7 (የሰማዩ አባታችንን ለማስደሰት ሥጦታን በፈቃደኝነት መስጠት ይኖርብናል፡፡)

*አስራትን ከከፈልን የሰማዩ አባታችን ሊባርከን ቃል ገብቶልናል*


- ኦሪት ዘፍጥረት 14፥19–20 (አብርሃም አስራት በመክፈሉ በሰማያዊ አባታችን ተባርኳል።)
- ሚልኪያስ 3፥10 (የሰማይ አባታችን ከምንፈልገው በላይ በብዙ በረከቶች ይባርከናል።)


*የጾም በኩራት ስንከፍል ሌሎች ሰዎችን እንረዳለን*

- ትንቢተ ኢሳይያስ 58፥6–11 (የሰማዩ አባታችን ሌሎች የሚፈልጉትን ነገሮች ለእነሱ በመስጠት መልካም እንድናደርግ ጠይቆናል፡፡)

# ቤተሰቦቻችንን ማዳን

*ክፍል ስምንት*





ቤተሰብ ለዘለዓለም አንድ ላይ መሆን ይችላል።

# ቤተሰብ አስፈላጊ ነው

*ምዕራፍ 29*

---

*የሰማዩ አባታችን በዚህ ምድር ላይ እንደ ቤተሰብ እንድንኖር ያቀደው ለምንድነው?*

**የሰማዩ አባታችን እንደ ቤተሰብ አንድንኖር አቀዶልናል**

በዚህ ምድር ላይ ያለው ቤተሰባችን እንደ ሰማያዊ ቤተሰባችን ነው፡፡ ወደዚህ ምድር ከመምጣታችን በፊት የሰማያዊው ቤተሰብ አካል ነበርን፡፡ እኛ የሰማዩ አባታችን የእግዚአብሔር የመንፈስ ልጆች ነበርን፡፡ እርሱም ይወደናል ስለእኛም ይጠነቃቀልናል፡፡ እርሱ መልካም ነገሮችን ለእኛ ይሻል እናም አንድ ቀን ተመልሰን ከእርሱ ጋር መኖር እንድንችል ይፈልጋል፡፡

የሰማዩ አባታችን አዳምና ሔዋንን ሲያጋባ የመጀመሪያውን ቤተሰብ በአንድ ላይ አደረጋቸው። ልጆች እንዲኖራቸው ነግሯቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት የሰማያዊ አባታችን የመንፈስ ልጆች ስጋና አጥንት ያለው አካል ለማግኘት ቻሉ፡፡ ለልጆቻቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች እንዲሰጡ ነግሯቸዋል፡፡ እንዲሁም ደግሞ ልጆቻቸውን ወንጌልን እንዲያስተምሩና የወንጌልን ሥርዓቶች መቀበል እንዲችሉ መርዳት እንዳለባቸውም ነግሮአቸዋል፡፡

የሰማዩ አባታችን በቤተሰብ ያዋቀረን ለብዙ ምክንያቶች ነው።

መጀመሪያ፣ ከወላጆቻችን ስጋና አጥንት ያለው አካል እንቀበላለን፡፡ ማድረግ የምንፈልገውን ነገሮች በመማር ስለዚህም ከሰማይ አባታችን ጋር ለዘለዓለም መኖር እንድንችል ስጋና አጥንት ያለው አካል ያስፈልገናል፡፡

ሁለተኛ፣ በዚህ ምድር ላይ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ቤተሰብ ሊሰጠን ይችላል። ወላጆች ምግብ፣ ልብሶች፣ መጠለያ፣ ፍቅርና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ለልጆቻቸው (ማሟላት) ይችላሉ፡፡ በኋላ ወላጆች በዕርጅና እራሳቸውን መርዳት ሲሳናቸው ልጆች ወላጆቻቸውን መርዳት ይችላሉ።

ሶስተኛ፣ ወላጆች የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለልጆቻቸው ማስተማር ይችላሉ። የሰማዩ አባታችንን ትዕዛዛቶች መጠበቅን እንዲችሉ ማስተማር ይችላሉ። እና ኢየሱስን መቀበል አለባችሁ ያለውን ስርዓት ልጆች መቀበላቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ።

---

### ውይይት

• የሰማዩ አባታችን እንደ ቤተሰብ ወደ ምድር እንድንመጣ ያደራጀን ለምንድነው?
• ወደዚህ ምድር ለመምጣት የመጀመሪያው ቤተሰብ የቱ ነው?
• የሰማዩ አባታችን ቤተሰቦቻችን ለእኛ ምን እንዲያደርጉልን ነበር ያቀደው?

## የቤተሰብ አባላት እርስ በርሳቸው እንዲፋቀሩ የሰማዩ አባታችን ይፈልጋል

በዚህ ምድር ላይ ያለው ቤተሰባችን በሰማይ እንደነበረው እንደ ሰማያዊ ቤተሰባችን መሆን ይችላል፡፡ ቤተሰብ እርስ በርሳቸው መረዳዳት እንዲሹ እርስበርሳቸው ደግ ነገርን እንዲባባሉና እንዲያደርጉ የሚያደርጋቸውን የፍቀር ስሜት ሊሰማቸው ይችላል።

በቤተሰብ ውስጥ ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው መፋቀር አለባቸው። እርስበርሳቸው ደግ መሆንና መረዳዳት አለባቸው። የሌላውን ስሜት የሚያስከፋ ነገር መናገር ወይም ማድረግ የለባቸውም፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን ማፍቀር ይኖርባቸዋል፡፡ እርስበርሳቸው እንዲፋቀሩ ልጆቻቸውን ማስተማር አለባቸው፡፡ እንዲረዳዱና እርስበርሳቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ማስተማር አለባቸው፡፡

ልጆች ወላጆቻቸውን ማፍቀር አለባቸው። እነሱም ወላጆቻቸውን ማክበር፣ መታዘዝ፣ እና መርዳት ይኖርባቸዋል፡፡

### ውይይት

• ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4፥29–32 ያንብቡ፡፡
• የቤተሰብ አባላት እርስበርሳቸው እንዲፋቀሩ እንዴት መርዳት እንችላለን?
• የቤተሰብ አባላት እርስበርሳቸው እንዲፋቀሩ የሰማዩ አባታችን ለምን ይፈልጋል?

## ማድረግ የምንችለው በጣም አስፈላጊ ነገር ደስተኛ እና ጻድቃን ቤተሰብ እንዲኖረን መስራት ነው

ጻድቀ ቤተሰብን ለማግኘት፣ ልንሰራው የምንችለው በጣም አስፈላጊ ሥራ ነው፡፡ ሌሎች ነገሮችን በማድረግ ምንም ያህል ስኬታማ ብንሆንም፣ ቤተሰቦቻችን የሰማዩ አባታችንን እንዲያፈቅሩና እንዲታዘዙ ካላስተማርን፣ በጣም አስፈላጊ በሆነው ተግባራችን ወድቀናል። አንዳንድ ጊዜ፣ ልጆቻችን የሰማዩ አባታችንን ለማፍቀርና ለመታዘዝ ላይመርጡ ይችላሉ፣ ነገር ግን የእርሱን መንገዶች እንዲያውቁ ለማስተማር የምንችለውን ሁሉ ማድረግ አለብን። ወላጆች በአግባቡ ልጆቻቸውን የሚችሉትን ያህል ለማስተማር ካጠሩ፣ የሰማዩ አባታችን ልጆቻቸው ለፈጸሙት ስህተተኛ አድራጎቶች በሃላፊነት ተጠያቂ አያደርጋቸውም፡፡ ወላጆች የሚጠየቁት ጥሩ ቤተሰብ ለመሆን ሙከራ ማድረግን ካቆሙ ብቻ ነው።

ቤተሰቦቻችን በሕይወታችን ውስጥ ታላቅ ደስታን ሊሰጡን ይችላሉ፡፡ በትጋት መልካም በማድረግ ልጆች የቤተክርስቲያን አባል እንዲሆኑ እና በሚኖሩበት አገር ጥሩ ዜጎች እንደሆነ አድርገን ስናሳድጋቸው በጣም ጥሩ እናደርጋለን።

ቤተሰብ የቤተክርስቲያኑ በጣም አስፈላጊ ክፍል ነው፡፡ የሰማዩ አባታችን ቤተሰቦች ወደ እርሱ ለመመለስ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ለማድረግ እንዲረዳቸው ቤተክርስቲያኑን አደራጅቷል። ቤተክርስቲያኗ እያንዳንዱ ቤተሰብ ለዘለዓለም በአንድ ላይ እንዲኖር ለመርዳት ተፈልጋለች።

በሰማያዊ አባታችን ዕቀድ ቤተሰብ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ሰይጣን ያውቃል፡፡ ቤተሰባችን እንዲለያዩ የሚያደርጉትን ነገሮች እንድናደርግ ለማድረግ ሙከራ ያደርጋል።

### *ውይይት*

• የአንተ ቤተሰብ ለአንተ ምን ያህል አስፈላጊ ነው?

## የሰማዩ አባታችን እንዴት መልካም ቤተሰብ ሊኖረን እንደሚችል ነግሮናል

ሁላችንም መልካምና ደስተኛ ቤተሰብ እንዲኖረን እንፈልጋለን፡፡ እነዚህ ቤተሰብን ለመርዳት የሚችሉ ጥቂቶቹ ነገሮች ናቸው፥

1. ቤተሰብ በአንድነት ጥዋትና ማታ መፀለይ ይገባዋል፡፡
2. ወላጆች በየዕለቱ በአንድ ላይ መፀለይ ይገባቸዋል።
3. ወላጆች ለልጆች ወንጌልን ማስተማር ይገባቸዋል፡፡
4. ቤተሰብ በየዕለቱ በአንድ ላይ ቅዱሳን መጽሃፍትን ማንበብ ይገባዋል፡፡
5. ቤተሰብ በየሰንበቱ በአንድ ላይ የቤተክርስቲያንን ስብሰባ መካፈል ይገባዋል፡፡
6. በወር አንድ ቀን ቤተሰብ በአንድነት ልጆች ዕድሚያቸው ሲፈቅድና የፆምን ዓላማ ከተረዱ መፆም ይገባዋል።
7. ቤተሰብ በየሳምንቱ አንድቀን በአንድነት በቤተሰብ ስብሰባ፣ *የቤተሰብ ምሽት ተብሎ በሚታወቀው ቤተሰቡ ስላከናወነው መልካም ነገር መነጋገር አለበት። ማንም አንድ ሰው ያለውን ማንኛውንም ችግር እንዴት መፍታት እንደሚገባቸው ይነጋገሩበታል። በዚሁ ስብሰባ ላይ ደግሞ መዘመር፣ ትምህርት መውሰድ፣ ከቅዱሳን መጽሐፍት ውስጥ አንዳንድ ጥቅሶችን መማር፣ ጨዋታ መጫወትና፣ የሚበሉ ወይም የሚጠጡ ነገሮችን መውሰድ ይቻላል።
8. ቤተሰብ በአንድነት መስራትና ማንበብ አለባቸው።
9. የቤተሰብ አባላት እርስበርሳቸው ተዕግስተኛና ደግ መሆን አለባቸው።
10. ቤተሰብ ስላደረጉተ ነገሮች ታሪካቸውን መመዝገብ አለባቸው።

በቤተሰብ እና በእራሳችን ለመፀለይ ካስታወስን፣ የሰማዩ አባታችን ይቀርበናል። ፀሎታችንንም ይሰማናል እናም ለእኛ በተሻለ መንገድ ምላሽ ይሰጠናል፡፡

### *ውይይት*

• ጥሩ ቤተሰብ እንዲኖረን ማድረግ የሚኖርብን ጥቂት ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

## ማጣቀሻ

*የሰማዩ አባታችን እንደ ቤተሰብ እንድንኖር አቀዶልናል*

- የማቴዎስ ወንጌል 19፥3–8 (ባልና ሚስት ሁልጊዜ እንደተጋቡ እንዲቆዩ የሰማዩ አባታችን አቀዷል።)

*የቤተሰብ አባላት እርስበርሳቸው እንዲፋቀሩ የሰማዩ አባታችን ይፈልጋል*

- ኦሪት ዘፍጥረት 2፥21–24 (የሰማዩ አባታችን አዳምንና ሔዋንን ፈጠረና ባልና ሚስት እንዲሆኑ አደረገ፡፡)

*ማድረግ የምንችለው በጣም አስፈላጊ ነገር ደስተኛ እና ጻድቃን ቤተሰብ እንዲኖረን መስራት ነው*

- ወደ ኤፌሶን ሰዎች 5፥25 (ባል ሚስቱን እንዲያፈቅራት ተነግሮታል፡፡)
- ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6፥1 (ልጆች ቤተሰቦቻቸውን እንዲታዘዙ ተነግሮአቸዋል።)
- ወደቲቶ ሰዎች 2፥4 (ሚስት ባሏን እንድትወደው ተነግሯታል።)
- ሞዛያ 4፥14–15 (ወላጆች ለልጆቻቸው ፍላጎት መጠንቀቅና እንዴት ጻድቃን ለመሆን እንደሚችሉ ማስተማር አለባቸው።)

*የሰማዩ አባታችን እንዴት መልካም ቤተሰብ ሊኖረን እንደሚችል ነግሮናል*

- 1ኛ ቆሮንቶስ 13፥1–7 (ስለ ፍቅር አስፈላጊነት ተነግሮናል።)
- ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6፥4 (አባቶች ለልጆቻቸው እንዲከፉ እንዳያደርጓቸው ታዘዋል።)

# ተግባራችን የቤተሰብ አባላትን ለመርዳት ነው

*ምዕራፍ 30*

*የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል እርዳታ ቤተሰብን እንዴት ደስተኛ ሊያደርግ ይችላል?*

**እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል አስፈላጊ ነው**

የሚዋደዱ እና ደስተኛ የቤተሰብ አባላት እንዲኖር ከፍተኛ የስራ ጥረት ከሁሉም የቤተሰብ አባላት ይጠበቃል፡፡ የሰማዩ አባታችን በቤተሰብ ውስጥ ላለ ለእያንዳንዱ ሰው ሃላፊነት ሰጥቷል። እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚረዳ፣ ደስተኛ እናም ለሌሎች ደግ መሆን አለበት፡፡ ስንጸልይ፣ ስንሰራ፣ ስንዘምር፣ እናም በአንድነት ስንጫወት፣ ቤተስቦቻችን ደስተኛ መሆን ይችላሉ፡፡

ለሌሎች የቤተሰቦቻችን አባላት ፍቀር ካለን የሰማይ አባታችን እንድናደርግ የሚፈለግብንን ነገሮች ለመስራት ቀላል እንዲሆኑልን ያደርግልናል፡፡ ቤተሰቦቻችንን በምንወድበት ጊዜ፣ እነሱን ለመርዳት የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ እንፈልጋለን፡፡ በፍቀር የምናደርግ ከሆነ ከባድ የሆኑ ነገሮች እንኳን ቀላል ይሆናሉ፡፡ ጥሩ የቤተሰብ አባል ለመሆን ሥራና ጊዜ ይጠይቃል።

***ውይይት***

- እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ቤትን ደስተኛ ቦታ ለማድረግ እንዴት መርዳት ይችላል?
- እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ለምን አስፈላጊ ሆነ?

*የሰማዩ አባታችን ለወላጆች ልዩ የሆኑ ሃላፊነቶችን ሰጥቷቸዋል*

አባትና እናት ለልጆቻቸው ጥንቃቄ ለመውሰድና የሚፈልጉትን ነገሮች ለማሟላት በአንድነት መስራት አለባቸው፡፡ ልጆቻቸውን ደግሞ ወንጌል ማስተማር አለባቸው፡፡ እንዲፀልዩና የሰማዩ አባታችንን ትዕዛዛት እንዲታዘዙም ማስተማር አለባቸው፡፡

አባትና እናት አንዳንድ ጊዜ ልጆች ተክክለኛ የሆነውን ካስተማሩአቸውም በኋላ እንኳ የስህተተ ምርጫን እንደሚያደርጉ መረዳት አለባቸው፡፡



ቤተሰቦች አብሮ በመስራት ጠንካሮች ይሆናሉ።

ልጆች ስህተት የሆነ ነገር ሲሰሩ፣ ወላጆች እነርሱን ለመርዳት መሞከራቸውን ማቆም የለባቸውም። ወላጆች ልጆቻቸውን መውደድና ማስተማር መቀጠል አለባቸው። እነርሱም ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑላቸው እናም ሊጸሙላቸውና ሊፀልዩላቸው ይገባል።

ወላጆች አንዳንድ ነገሮችን ለቤተሰቦቻቸው መስጠት አለባቸው፥

1. ልጆቻቸውን መውደድና ልጆቻቸው ሌሎችን እንዲወዱ ማስተማር አለባቸው።
2. ልጆቻቸውን ወንጌል ማስተማር አለባቸው።
3. የቤተሰብ አባላትን እንዴት መጸለይ እንደሚችሉ ማስተማር አለባቸው።
4. ልጆቻቸውን አስራትና በኩራትን እንዲከፍሉ የራሳቸውን አስራትና በኩራትን በመክፈል ማስተማር አለባቸው።
5. ልጆቻቸውን ሥራ እንዴት እንደሚሰራ ማስተማር አለባቸው።
6. ንጹህ ቤት፣ ልብስና ምግብ ማቀረብ አለባቸው።
7. ልጆቻቸው ማንበብ፣ መጻፍና መሰረታዊ የሂሳብ ስሌቶችን መስራት የሚችሉ መሆኑን ወደ ትምህርት ቤት በመላክ ወይንም በቤት ውስጥ በማስተማር እርግጠኛ መሆን አለባቸው።
8. ልጆቻቸው ሙያን እንዲማሩ ስለዚህም ለሚፈልጉት ጉዳዮች በቂ ገንዘብ ለማግኘት እንዲዘጋጁ የሚቻላቸውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው።
9. ልጆቻቸው ገንዘብን እንዴት በብልሃት እንደሚጠቀሙበትና ለወደፊት ፍላጎታቸው ገንዘብ እንዴት እንደሚቆጥቡ ማሳየት አለባቸው።
10. ልጆቻቸው ሙያቸውን እና ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ መርዳት አለባቸው። እነዚህ የማስተማር ችሎታ፣ ሙዚቃን የመጫወት፣ የመዘመር፣ አንዳንድ ነገሮችን የመጠገን ችሎታን፣ ወይንም ሌሎች የሚፈልጉትን መረዳት ሊሆኑ ይችላሉ።

ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ለመርዳት በርትተው ለመስራት ፈቃደኛ መሆን አለባቸው። የሰማዩ አባታችን ወለጆች ልጆቻቸው በሚገባ እርስበርስ እንደሚረዳዱ እና ምግብና ልብስ እንዳላቸው እርግጠኛ መሆን አለባቸው ብሏል።

ወላጆች ቢታመሙ፣ ሥራቸውን ቢያቆሙ፣ ወይንም ሌሎች ችግሮች ቢያጋጥማቸው እንኳን እነዚህን ነገሮች ለመስጠት ለመቻል አስቀድመው ማቀድ አለባቸው። ይህን ለማድረግ የሚችሉት ገንዘባቸውን በመቆጠብና ተጨማሪ ምግብን፣ ልብስንና ነዳጅን ይህ በተፈቀደበት ክልል በማከማቸት ነው።

## *ውይይት*

• የቤተሰቦቻቸውን ፍላጎት ለማሟላት ወላጆች ምን ማድረግ ይችላሉ?
• ችግሮች ሊያጋጥሙአቸው በሚችልበት ጊዜ ለመዘጋጀት ወላጆች ምን ማድረግ ይችላሉ?

*አባት ልዩ የሆኑ ሃላፊነቶች አሉት*

አባት የክህነት ሥልጣን ያለው የቤተሰቡ መሪ ነው። አባት ቤተሰቡን በፍቅርና በደግነት መምራት አለበት። ለቤተሰቡ እንዴት የሰማዩ አባታችንን ትዕዛዛት እንደሚጠብቁ ራሱ

በመጠበቅ ማሳየት አለበት፡፡ ቤተሰቡን ደግሞ ወንጌልን ማስተማር አለበት፡፡ ቤተሰቡን ጠዋትና ማታ ለቤተሰብ ፀሎት በአንድነት መጥራት አለበት፡፡ ሚስቱም እነዚህን ነገሮች እንዲያከናውን መርዳት አለባት፡፡

አባት የቤተሰቡን አባላት ለመባረክ የክህነት ሥልጣኑን መጠቀም አለበት፡፡ ለትንንሽ ልጆቹ በረከትና ስም መስጠት ይችላል፡፡ ዕድሚያቸው ስምንት ዓመት ሲሞላም ሊያጠምቃቸው ይችላል፡፡ ወንዶች ልጆቹን በክህነት ሥልጣን ሊሾማቸውና ልጆቹን ልዩ በረከት በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ በታመሙ ጊዜ ሊባርካቸው ይችላል።

አባት ከእያንዳንዱ ልጆቹ ጋር በተናጠል ጊዜን ማሳለፍ አለበት፡፡ ከእነርሱ ጋር በመነጋገርና ፍላጎታቸውንና ሃሳባቸውን ለመርዳት መማር አለበት፡፡ እነርሱን ማበረታታትና እንደሚወዳቸውም መንገር አለበት፡፡ በሚያጋጥማቸው ማናቸውም ችግር ሁልጊዜ ወደ እርሱ መጥተው ዕርዳታ መጠየቅ እንደሚችሉም መንገር አለበት፡፡

### *ውይይት*

- የአባት ሃላፊነቶች ምን ምንድናቸው?
- ቤተሰቡን ለመርዳት የያዘውን የክህነት ሥልጣን እንዴት መጠቀም ይችላል?

*እናት ልዩ የሆኑ ሃላፊነቶች አሏት*

የእናት ይበልጡን አስፈላጊ ሃላፊነት ልጆችን መውለድና ለእነርሱ ጥንቃቄ ማድረግ እና ማስተማር ነው፡፡ ለሰማዩ አባታችን የመንፈስ ልጆች የስጋና አጥንት አካልን መስጠት የተቀደሰ ተግባር ነው፡፡ እናት ይህን ስታደርግ፣ የሰማዩ አባታችንን ሥራ ተካፈለች ማለት ነው፡፡ ልጆችን መውለድ ከሁሉም ታላላቅ በረከቶች አንዱ ነው።

እናት አፍቃሪ መሆን አለባት፡፡ ባለቤቷ እያንዳንዱን ልጅ ወንጌልን እንዲያስተምር መርዳት አለባት፡፡ እያንዳንዱን ህፃን በፍላጎቷ መርዳትና ብዙ ነገሮችን ማስተማር አለባት፡፡ እናት ልጆቿን በቤተሰብ ውስጥ ተፈላጊ ሰዎች እንደሆኑ እንዲሰማቸው የሚያደርጉ ነገሮችን ማለት አለባት እና በዙሪያቸው ያሉትን ነገሮች እንዲገነዘቡ መርዳት አለባት፡፡ እነዚህን ነገሮች ከባለቤቷ ጋር በመረዳዳት መፈጸም አለባት፡፡

መጽሐፈ ሞርሞን የእናቶቻቸውን ትምህርት ስለታዘዙ ጻድቃን ወጣት ወንድ ልጆች ቡድን ይናገራል። የእነዚህ ወጣት ልጆች እናቶች ታማኞች፣ ነበዞችና ጻድቃን እንዲሆኑ አስተምሯቸዋል፡፡ እናቶቻቸው በተጨማሪ በኢየሱስ እምነት ካላቸው የሰማዩ አባታችን እንደሚጠብቃቸው አስተምረዋቸዋል፡፡ እነዚህ ወጣት ወንዶች አገራቸውን ለመከላከል ወታደሮች መሆን ነበረባቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ወጣት ወንዶች የእናቶቻቸውን ትምህርት ስላከበሩ እና እምነትም ስለነበራቸው፣ ተግባራቸውን ለመፈጸም በከፍተኛ አደጋ ውስጥ በነበሩ ጊዜ እንኳ ብርታት ነበራቸው። እያንዳንዷ እናት በልጇ ሕይወት ላይ ታላቅ ተጽዕኖ ሊኖራት ይችላል፡፡

### ውይይት

• የእናት ሃላፊነቶች ምንድን ናቸው?
• እናት መሆን የሰማዩ አባታችን አጋር መሆን ነው ተብሎ የሚጠራው ለምንድነው?

*አንድ ወላጅ ብቻ በሚኖርበት ጊዜ*

አንዳንድ ጊዜ አባት ወይንም እናት ብቻቸውን ሆነው ቤተሰብን ለማሳደግና የሁለቱንም የአባትና እናትን ተግባር የሚያከናውኑበት አጋጣሚ አለ፡፡ የሰማዩ አባታችን ይህን መፈጸም አስቸጋሪ እንደሆነ ያውቃል፡፡ እንደዚህ ያለ ብቸኛ ወላጅ የምንለውን ሰው፣ የሰማዩን አባታችንን ከለመኑ፣ የሰማዩ አባታችን ያንን ግለሰብ ቤተሰቡን እንዲጠብቀ ይረዳዋል፡፡

ብቸኛ ወላጅ ደግሞ የቤት አስተማሪዎችን ዕርዳታ ማግኘት ይችላል፡፡ *የቤት አስተማሪዎች የክህነት ሥልጣን ያላቸው የቤተክርስቲያኑ አባሎች ሲሆኑ በክህነት ሥልጣን መሪዎች ለሌሎች የቤተክርስቲያኑ አባላት እንዲረዱ የተመደቡ (የተጠየቁ) ናቸው፡፡

### ውይይት

• ብቸኛ ወላጆችን መርዳት የሚችለው ማን ነው?

*ልጆችም ልዩ ሃላፊነቶች አሏቸው*

ልጆች ቤታቸው የደስታ ሥፍራ እንዲሆን ወላጆቻቸውን መርዳት አለባቸው፡፡ ልጆች ወላጆቻቸውን ቤት በማፅዳትና በዙሪያው ያለውን ቦታ በማጽዳት መርዳት አለባቸው፡፡ ለቤተሰብ ምግብን በማዘጋጀት፣ ድስቶችን (ሳህኖችን) እና ልብሶችን በማጠብ መርዳት ይችላሉ፡፡ እናም ደግሞ ታናናሽ ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን በመጠበቀ መርዳት ይችላሉ፡፡

ልጆች ወላጆቻቸው የሚያስተምሩአቸውን ነገሮች በርትተው ለመማር መሞከር አለባቸው፡፡ በርትተው ሥራ መስራትንና ሥራን በሚገባ ማከናወን አለባቸው፡፡ የተሰጣቸውን ተግባር ማከናወንን መማር አለባቸው፡፡

ልጆች የኢየሱስን ትዕዛዛት መታዘዝ አለባቸው፡፡ ሌሎችን የቤተሰብ አባላትን መርዳት አለባቸው፡፡ ልጆች በሚጣሉበት ጊዜ የሰማዩ አባታችን አይደሰተባቸውም፡፡ የሰማዩ አባታችን ልጆች ወላጆቻቸውን እንዲታዘዙና እንዲያከብሩ ነግሯቸዋል።

ልጆች ወላጆቻቸውን መውደድ አለባቸው፡፡ ሊታዘዙአቸው፣ ሊያከብሩአቸው ይገባል፡፡ እንዲሁም ደግሞ በታመሙ ጊዜ፣ ወይንም ባረጁ ጊዜ እናም ራሳቸውን መርዳት ባቃታቸው ጊዜ ሊረዱአቸው ይገባቸዋል፡፡

### ውይይት

• የሰማዩ አባታችን ልጆች እንዲፈጽሙ የሚጠብቀባቸው ምንድነው?
• ወላጆቻቸው ባረጁ ጊዜ ልጆች ለወላጆቻቸው ምን ማድረግ አለባቸው?
• ልጆች ለወላጆቻቸው ለመታዘዝና ክብርን ለማሳየት ምን ማድረግ አለባቸው፡፡

## ቤተሰብን የማጠናከር አስፈላጊነት

ዛሬ በዓለም ላይ፣ በርካታ ክፉ ሰዎች በቤተሰብ ላይ ያለንን ዛሳባችንን ለመለወጥ እየጣሩ ናቸው፡፡ ቴሌቪዥኖች፣ ፊልሞች፣ እና መጽሔቶች ስለወንዶችና ሴቶች ብዙ አንግዳና የተሳሳቱ ጉዳዮችን አንዱ ለአንዱ የሚያሳየውን ምግባር ያሳያሉ፡፡ መጥፎ ዓላማዎችን በአስቂኝና በሚያስደስት መልክ በሚቀርቡ ፕሮግራሞች አማካኝነት እንዲማሩ ይደረጋል፡፡ ዝሙት (ህሊናችንን በሚያቆሽሽ መልኩ) እንደቀልድና እንደ አስፈላጊያችን ሆኖ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ በነዚህም የመገናኛ ብዙሃን ላይ ልጆች ወላጆቻቸውን (እንደማያከብሩ) ያላቸውን ታላቀ ውርደት እንመለከታለን፡፡ ሰዎች መልካም ቤተሰቦች ላይ በመቀለድ ሲያፌዙባቸውና ሲሳለቁባቸው እናያለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ ልጆቻችን በፊተም ወይም ቴሌቪዥን ጥሩ የቤት ህይወት ምን እንደሚመስል በፍፁም አያዩም።

ወላጆች ልጆቻቸውን እንደዚህ ያሉተን ፊልሞች፣ ቴሌቪዥን ከማየተ ለመከላከል ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡ ለምን ክፉ የሆኑ ፕሮግራሞችን ወይንም ፊልሞች መከታተል እንደሌለባቸው ማስተማር አለባቸው፡፡ ከሁሉም በላይ፣ አስፈላጊው ወላጆች በቤታቸው ምንጊዜም ጥሩ ዓርአያ መሆን አለባቸው፡፡ ልጆች በየዕለቱ ጥሩ ምሳሌን በቤት ውስጥ ካዩ፣ መልካም ልጆች ይሆናሉ። እናም፣ በኋላ፣ ባደጉ ጊዜ መልካም ወላጆች ይሆናሉ፡፡ ወላጆቻቸው እርስበርስ ፍቀርን ሲያሳዩ ከተመለከቱም፣ እነሱም በአንድ ወቀተ የዚህን ዓይነቱን ወላጅ ባህርይን መውሰድ ይሻሉ፡፡

### *ውይይት*

- በቴሌቪዥን ወይንም በፊልሞች ልጆቻችን እንዲከታተሉ የምንፈቀደውን ነገሮች በጥንቃቄ መምረጥ የሚገባን ለምንድነው?

## የሰማዩ አባታችን እርስበርስ እንድንረዳዳ ይፈልጋል

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል መፋቀርና እርስበርስ መረዳዳተ አለበተ፡፡ እኛ አስቀድመን ወላጆቻችንና ወንድም እህቶቻችንን በመርዳት ሌሎችን መርዳትን እንማራለን፡፡ ዘመዶቻችንም ዕርዳታ ሲያስፈልጋቸው መርዳት አለብን፡፡ እኛ ራሳችን የራሳችንን ፍላጎተ ማሟላተ እስከቻልን ሌሎች እንዲረዱን መጠየቀ የለብንም፡፡ ይህን ካደረግን፣ የሰማዩ አባታችን አይደሰተብንም፡፡

ኢየሱስ ሁላችንንም ይወደናል፣ እናም ወደዚህ ዓለም ሊረዳን መጣ፡፡ እያንዳንዱን ሰው እንድንወድና እንድንረዳ አስተምሮናል። ኢየሱስ እንዳደረገው ሌሎችን ስንወድ እነርሱን ለመርዳተ የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን።

አንዳንዶቻችን የሰማዩ አባታችንን እርዳታ የሚፈልጉተን እንዲረዳ እንጠይቃለን፣ እናም እኛ ግን እነርሱን ለመርዳተ ምንም አናደርግም፡፡ ይህ ተክክል አይደለም፡፡ የሰማዩ አባታችን ሌሎችን የሚረዳው በእኛ አማካይነተ እንደሆነ ማስታወስ አለብን፡፡ አስቀድመን እርዳታ ለሚፈልጉ መፀለይ አለብን፣ እናም ከዚያ በኋላ በሚቻለን ሁሉ መርዳተ አለብን፡፡

ሁላችንም ከሌሎች ሰዎች እርዳታ እንፈልጋለን፡፡ ልጆች በነበርን ጊዜ፣ ወላጆቻችን መግበውናል፣ አልብሰውናል፣ እና ጥንቃቄ አድርገውልናል። ባደግን ጊዜም፣ ሌሎች ሰዎች ማወቅና ማድረግ የምንፈልገውን ያስተምሩናል። ብዙዎቻችን በታምምን ጊዜ የሌሎችን እርዳታ እንፈልጋለን፡፡

ሌሎች ሰዎችን ስንረዳ፣ በረከተን እናገኛለን፡፡ የመውደድ ችሎታችንም ይጨምራል፣ ራስ ወዳድነታችን ደግሞ ይቀንሳል፣ የራሳችን ችግርም አሳሳቢነት ይቀነስልናል፡፡ የሰማዩ አባታችን ከእርሱ ጋር መኖር የሚፈልጉት የእርሱን ልጆች ሁሉ ማፍቀርና መርዳት እንዳለባቸው ተናግሯል፡፡

## ***ውይይት***

- የሰማዩ አባታችን ሌሎችን እንድንረዳ የሚፈልገው ለምንድነው?
- ከእርዳታችን የሚጠቀመው ማነው?

## ***ማጣቀሻ***

*እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል አስፈላጊ ነው*


- ዘፀአት 20፥12፤ ወደ ኤፈሶን ሰዎች 6፥1 (ቤተሰቦቻችንን እንድናከብር ተናግሮናል።)
- 2ኛ ኔፊ 1፥14–32፣ አልማ 36–42 (የመጽሃፈ ሞርሞን ነቢያት ልጆቻቸው ተክክለኛውን እንዲያደርጉ ይመክራሉ)
- ሞዛያ 4፥14፣ ተ እና ቃ 68፥25–28 (ወላጆች ለልጆቻቸው ህይወተ አስፈላጊ የሆኑተን ማቀረብና ጻድቃኖች እንዲሆኑ ማስተማር አለባቸው፡፡)

*ቤተሰብን የማጠንከር አስፈላጊነተ*

- 2ኛ ጢሞቲዎስ 3፥1–4 (በመጨረሻው ዘመን ታላቀ ክፋተ ይሆናል፣ እናም ይህን ለመቋቋም መዘጋጀተ አለብን።)

*የሰማዩ አባታችን እርስበርስ እንድንረዳዳ ይፈልጋል*

- ሉቃስ 22፥27፤ ማቴዎስ 20፥26–27፤ የዮሐንስ ወንጌል 13፥15–16 (ኢየሱስ የእውነተኛ አገልግሎተ ምሳሌ ሰጥቷል።)
- ቆላስያስ 3፥18–20 (የቤተሰብ አባላተ ለርስበርሳቸው ሃላፊነተ አለባቸው)
- ሞዛያ 2፤ ቆላስያስ 3፥23–24፤ ማቴዎስ 25፡32–46 (ሌሎችን የሚያገለግሉ የሰማይ አባታችንንም ያገለግላሉ፡፡)



ኢየሱስ ሐዋሪያቶቹ ወንጌልን በዓለም ሁሉ እንዲያስተምሩ ለዟቸዋል፡፡

# ተግባራችን ወንጌልን መስበክ ነው

*ምዕራፍ 31*

---

*ሁሉም የሰማይ አባታችን ልጆች ወንጌልን እንዲሰሙ እንዴት መርዳት እንችላለን?*

**የሰማይ አባታችን ልጆቹ ሁሉ ወንጌልን እንዲያውቁ ይፈልጋል**

የሰማዩ አባታችን ልጆቹን ሁሉ ይወዳቸዋል፡፡ እያንዳንዳችን ለእርሱ አስፈላጊዎች ነን፣ እናም እያንዳንዳችንም እንደእርሱ መሆን እንችላለን፡፡ ተመልሰን ከእርሱ ጋር እንድንኖርና እርሱ ያለውን ተመሳሳይ ደስታና ክብር እንዲኖረን ይፈልጋል፡፡

የሰማዩ አባታችን እያንዳንዳችን ተመልሰን ከእርሱ ጋር እንድንኖር ለመርዳት እቀድ አለው፡፡ እቀዱም የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ይባላል፡፡ ወንጌልን ስናጠና፣ ምን ያህል አስፈላጊዎች እንደሆንን እንማራለን፡፡ እዚህ በዚህ ምድር ላይ ለምን እንዳለን እንማራለን። ደግሞ ስንሞት ወዴት እንድምንሄድ እንማራለን፡፡ ወደ ሰማይ አባታችን ለመመለስ ምን ማድረግ እንዳለብንም እንማራለን፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ የመንፈስ ወንድማችን ነው፡፡ እርሱ በቀድመ ሕይወት የሰማዩ አባታችን የመንፈስ ልጅ ሆኖ ተወለደ፡፡ እርሱ በምድር ላይ እንደ የሰማዩ አባታችን አንዲያ ልጅ ሆኖ በሥጋ ተወለደ እውነተኛ አባቱም የሰማዩ አባት ነበር። በጣም ስለወደደን ተሰቃይቶ ሞተልን፡፡ የሰማዩ አባታችን እንድናውቀውና እንድናደርግ የሚፈልገውን አስተማረን፡፡ እኛን ለመርዳት ቤተክርስቲያኑን አደራጀ፡፡ በምድር ላይ ላሉ ወንዶች ሥራውን እንዲሰሩ የክህነት ሥልጣኑን ሰጠ፡፡

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ብቸኛ የሰማዩ አባታችን የክህነት ሥልጣንና የሱ እውነተኛ ዕቀድ ያለው ቤተክርስቲያን ነው። የሰማዩ አባታችን ሁሉም ሰዎች ዕቀዱን እንዲማሩት እና እንዲቀበሉት ይፈልጋል፡፡ የእውነተኛ ቤተክርስቲያን ሥርዓቶች ተመልሰን ከሰማዩ አባታችን ጋር ለመኖር አስፈላጊዎች ናቸው።

የሰማዩ አባታችን እያንዳንዱን ቤተክርስቲያን አባል ስለወንጌል ለሌሎች እንዲነገሩ ነግሯቸዋል። ሁሉም ነቢያቶች ከአዳም ጀምሮ ለሌሎች ወንጌልን ለማስተማር አብዛኛው ጊዜያቸውን ተጠቀመውበታል። እያንዳንዱ የቤተክርስቲያኑ አባል ወንጌላዊ መሆን እንዳለበተ ነግረውናል፡፡ ይህ በተጠመቀን ጊዜ ከገባነው ቃል ኪዳን አንዱ ነው፡፡ በሚቻለን ጊዜ ሁሉ ለሰዎች ስለ ኢየሱስ ለመናገር ቃል ገብተናል፡፡

## *ውይይት*

- ሁሉም ሰዎች ወንጌልን መስማት ያለባቸው ለምንድነው?
- ወንጌልን ለሁሉም ሰዎች ለማስተማር ዛላፊነት ያለበት ማን ነው?

በቤተክርስቲያኑ ውስጥ እያንዳንዱ ቤተሰብ ወንጌልን የማስተማር አስፈላጊነት መገንዘብ አለባቸው፡፡ የወንጌል ዕቀድ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እናውቃለን፡፡ ማንኛውንም በማድረግ የሰማዩን አባታችን ዕቀድ ያውቁ ዘንድ ሌሎች ሰዎችን ለመርዳት በሚገባ መውደድ አለብን፡፡

የቤተሰብ አባላት ስለወንጌል እንዲማሩ ሌሎችን ለመርዳት ብዙ ነገሮችን ማድረግ ይችላሉ፡፡ ከነዚህም ነገሮች ውስጥ አንዳንዶቹ፥

1. ለሌሎች ጥሩ ነገሮችን አድርጉላቸው፡፡
2. ደስተኛ የሆናችሁት የወንጌልን ትምህርት በመታዘዛችሁ ምክንያተ መሆኑን ለሌሎች ንገሩዋቸው፡፡
3. ለጓደኞች (ወዳጆች) እና ለጎረቤቶች ወንጌልን አስረዷቸው ከእናንተ ጋር ወደ ቤተክርስቲያን ስብስባዎች እንዲሄዱ ጋብዙአቸው፡፡
4. ሰዎች ወደ እናንተ ቤት ለቤተሰብ ምሽት እንዲመጡ ወይንም ወንጌላውያን ሊያስተምሩአቸው በሚችሉተ ሁኔታ ጋብዙአቸው፡፡
5. ስለወንጌል ለመማር የሚፈልጉተን የጓደኞቻችሁን ወይንም የዘመዶቻችሁን ስምና አድራሻ ለወንጌላውያን ስጡአቸው፡፡
6. ልጆችን በወንጌላዊነተ የማገልገልን አስፈላጊነት አስተምሩአቸው። በወንጌላዊነተ ለማገልገል ይዘጋጁ ዘንድ ገንዘብ እንዲቀጥቡ እርዱአቸው፡፡
7. አስራታችሁን ክፈሉ፡፡
8. ለወንጌላውያን የገንዘብ እርዳታ አድርጉ፡፡

## *ውይይት*

- የቤተክርስቲያኑ አባል ላልሆኑ ሰዎች በምን ሁኔታ ስለወንጌል እንደምትነግሩአቸው አስቡ፡፡
- ሌሎች ሰዎች ስለወንጌል እንዲማሩ ለመርዳት ቤተሰቦችህ ምን ማድረግ ይችላሉ?

## **ቤተሰቦችህ የቤተክርስቲያን የወንጌላዊ ሥራ አስፈላጊ ክፍል መሆን ይችላሉ**

ቤተክርስቲያናችን በርካታ ወንጌላዊያንን ወንጌል እንዲያስተምሩ ወደ ብዙ አገሮች ልኳል፡፡ አብዛኞቻቸው ዕድሚያቸው በ19 እና 25 መካከል የሆኑ ወጣቶች ናቸው፡፡ አረጋዊ የሆኑ

ሰዎችም በወንጌላዊነት ያገለግላሉ። እነርሱ የሰማዩ አባታችንን ለማገልገል ፍላጎት ያላቸው ታማኝና ታዛዥ የቤተክርስቲያኑ አባላት ናቸው።

ብዙ በርካታ ወንጌላውያን ይፈለጋሉ። ቤተሰቦችህ የቤተሰብ አባላት ለወንጌላዊነት በማዘጋጀት በዚህ አስፈላጊ ሥራ ላይ መሳተፍ ይችላሉ። ወላጆች ልጆቻቸው የወንጌል ምስክርነት እንዲያገኙና ወንጌልን ለሌሎች እንዴት እንደሚያስረዱ መርዳት ይችላሉ። ልጆቻቸውን የሁሉንም ሰዎች ባህሎች እንዲወዱ ማስተማር ይችላሉ። ወላጆችም ደግሞ ልጆቻቸው ካደጉ በኋላ ራሳቸውን ለወንጌላዊነት ማዘጋጀት አለባቸው።

ብዙ ሰዎች ስለወንጌል ገና አልሰሙም። አንዳንዶቻቸው የሚኖሩት ወንጌላዊያን ሔደው የወንጌላዊ ሥራን እንዲያከናውኑ በማይፈቀድባቸው (በመንግሥት) አገሮች ነው። እነዚህ ሰዎች ወንጌልን የመስማትና የመቀበል ዕድሉ ሊኖራቸው ይገባል። የሰማዩ አባታችን ለነዚህ ሰዎች (ወንጌልን ለመስማትና ለመቀበል ዕድል ያልነበራቸው) ይህን አጋጣሚ ያገኙ ዘንድ ያመቻችላቸዋል። የነዚህም አገሮች መሪዎቹ ወንጌላውያን ሕዝቦቻቸውን እንዲገቡ እና እንዲያስተምሩ እንዲፈቀዱ ወደ እርሱ መፀለይ አለብን፣

### *ውይይት*

- በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች ለሁሉም ሕዝቦች ወንጌልን ለማስተማር ሃላፊነታቸውን እንዴት ይወጡ ነበር?
- ዛሬም እንኳ በርካታ ወንጌላዊያን የሚፈለጉበተ ለምንድን ነው?

## ለሌሎች ሰዎች ስለወንጌል የሚናገሩ ታላቅ በረከትን ያገኛሉ

የሰማዩ አባታችን ለሌሎች በሚገባ በመጠንቀቀ ስለወንጌል የምንነግራቸው ከሆነ ይባርከናል። ትዕዛዛቱን በመጠበቃችን እና ወንጌልን ለተቀበሉት ስላመጣንላቸው ደስታ ይባርከናል። ከልጆቹ አንዱን እንኳን ወንጌልን እንዲማሩ ወደ እርሱ እንዲመለስ ብንረዳ እንደምንደሰተ ነግሮናል። ብዙ ልጆቹን ወደ እርሱ እንዲመለሱ ብንረዳ ደግሞ ደስታችን (እጥፍ) የላቀ ይሆናል።

### *ውይይት*

- ወንጌልን ወደ ሌሎች በመውሰድ ምን ዓይነት በረከተ ይገኛል?
- የእነዚህን ዓይነት በረከቶች ተቀብለሃልን?

### *ማጣቀሻ*

*የሰማይ አባታችን ልጆቹ ሁሉ ወንጌልን እንዲያውቁ ይፈልጋል*

- የማቴዎስ ወንጌል 24፥14 (ወንጌል ለሁሉም ህዝቦች መሰበክ አለበት።)
- የማርቆስ ወንጌል 16፥15–17 (ኢየሱስ ለሐዋሪያቶች ወንጌልን ለእያንዳንዱ ሰው እንዲያስተምሩ ነግሯቸዋል።)
- የሐዋሪያት ሥራ 5፥42 (ቀደምት ሐዋሪያቶች ወንጌልን ለቻሉት ለእያንዳንዱ ሰው ሁሉ አስተምረዋል።)

*ቤተሰቦችህ የቤተክርስቲያን የወንጌላዊ ሥራ አስፈላጊ ክፍል መሆን ይችላሉ*

- 1ኛ ጢሞቲዎስ 4፥12 (ወጣቶች ለሌሎች አርዓያ መሆን ይችላሉ።)
- ሞዛያ 4፥15 (ልጆቻችሁ እርስበርስ እንዲዋደዱ አስተምሩአቸው።)

ለሌሎች ሰዎች ስለወንጌል የሚናገሩ ታላቀ በረከተን ያገኛሉ

- ት እና ቃ 18፥15–16 (ወንጌልን እንዲቀበሉ ከረዳናቸው ጋር ታላቀ ደስታ ይኖረናል።)

# በቤተሰብ ለዘለዓለም መኖር

*ምዕራፍ 32*

*ቤተሰብ ከምድራዊ ሕይወት በኋላ እንኳን፣ ለዘለዓለም እንዴት አብሮ መሆን ይችላል?*

**እግዚአብሔር ቤተሰብ ለዘለዓለም አብረው እንዲሆኑ አቀዷል**


ቤተሰብ በምድር ላይ በጣም አስፈላጊ የሆኑ የሰዎች ቡድን ነው፡፡ ምድራዊ ቤተሰቦቻችን በሰማይ በነበርን ጊዜ ከነበሩን ቤተሰቦች ጋር በጣም ይመሳሰላሉ፡፡ በሰማይ ሁላችንም ወንድምና እህት ነበርን፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች ነበርን፡፡ እግዚአብሔር የሰማይ ቤታችን መሪ ነበር፡፡ ከሰማዩ ወላጆቻችን የፍቀርን፣ እንክብካቤ መመሪያን አግኝተናል፡፡

እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን በዚህ ምድር ወደ ቤተሰብ ልኮናል፡፡ በዚህ ምድር ሳሉ ለእያንዳንዱ ልጆች እንዲጠነቀቁ ለወላጆች ኃላፊነት ሰጥቶአቸዋል፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን መውደድና፣ ምግብ፣ ልብስ እናም ቤት መስጠት አለባቸው፡፡ ልጆቻቸውን ስለ እግዚአብሔርና እንደርሱ እንዴት እንደሚሆኑ ማስተማር አለባቸው፡፡

እግዚአብሔር ቤተሰቦች ለዘለዓለም አብሮ እንዲሆኑ አመቻችቶላቸዋል፡፡ ለቤተክርስቲያኑም መሪዎች ሥልጣን በመስጠት ቤተሰቦች በአንድነት ለዘላለም እንዲጣመሩ (እንዲተሳሰሩ) አድርጓል፡፡ ይህ አብሮ መጣመር (መተሳሰር) ይባላል። ይህ መተሳሰር የሚከናወነው በቤተመቀደስ ብቻ ነው። ቤተመቀደሶች የቤተክርስቲያኑ ታማኝ አባላት ብቻ የሚሔዱበት የተቀደሱ ህንፃዎች ናቸው፡፡ ወንድና ሴት በቤተመቀደስ ውስጥ የክህነት ሥልጣን ባለውና የማሰር ልዩ ኃይል ባለው ሰው ከተሳሰሩ ጋብቻቸው በሚሞቱበት ጊዜም አያበቃም፡፡ በቤተመቀደስ የገቡትን ቃልኪዳን ከጠበቁ ጋብቻቸው እስከመጨረሻው ለዘለዓለም ይፀናል፡፡ ይህ ዘለዓለማዊ ጋብቻ ተብሎ ይጠራል፡፡

አንድ ወንድና ሴት በቤተመቀደስ ካልተሳሰሩ፣ ጋብቻቸው አንዳቸው ሲሞቱ ያበቃል፡፡ በቤተመቀደስ ከተሳሰርን፣ እናም በታማኝነት ክርስቶስን እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ ብንከተል፣ ቤተሰቦቻችን ለዘለዓለም አብረው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ባልና ሚስትም ደግሞ የኢየሱስ ታማኝ ተከታዮች ከሆኑ፣ ወደ ቤተመቀደስ ሄደው መተሳሰር ይችላሉ፡፡ እዚያም፣ የክህነት ሥልጣን የያዘ ልዩ ሥልጣን ያለው በአንድነት ሊያስተሳስራቸው



*በፖርትላንድ፣ ኦሪገን፣ USA ያለው ቤተመቅደስ።*

ይችላል፡፡ ልጆቻቸውንም ከነሱ ጋር ሊያስተሳስራቸው ይችላል። በአንድነት ከተሳሰሩ በኋላ፣ ልክ ቀድሞውኑ በቤተመቅደስ እንደተጋቡ ያህል ለዘለአለም አብረው መሆን ይችላሉ፡፡

እግዚአብሔር ልጆቹ ሁሉ በቤተመቅደስ ውስጥ ለመተሳሰር እንዲያቅዱና ታዛዥ ቤተሰብ እንዲያሳድጉ ይፈልጋል፡፡ ወላጆች በሚጋቡ ጊዜ ወደ ቤተመቅደስ ሄደው ለመተሳሰር ልጆቻቸውን መምራት አለባቸው፡፡ ወላጆች ልጆቻቸው በሚያገቡበት ጊዜ ወደ ቤተመቅደስ ሔደው ለመተሳሰር ዝግጁ እንዲሆኑ መምራት አለባቸው። አንድ ወንድና ሴት በቤተ መቅደስ ከተሳሰሩ፣ ከተስሰራቸው በኋላ የሚወልዷቸው ልጆች ሁሉ ወዲያውኑ ከነርሱ ጋር ይተሳሰራሉ።

### *ውይይት*

- እግዚአብሔር ከቤተሰቦቻችን ጋር ለዘለዓለም እንድንሆን እንዴት አድርጎ አመቻቸልን?
- በቤተመቅደስ ውስጥ መተሳሰራችን ለምን አስፈለገ?

## የቤተክርስቲያን ታማኝ አባላት ብቻ ቤተመቅደስ ውስጥ ይገባሉ

ቤተመቅደሶች ቅዱስ ሥፍራዎች ናቸው፡፡ በኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት በክርስቶስ እምነታቸውን ያደረጉና ትዕዛዛቱን የታዘዙ ብቻ እንዲገቡ ይፈቀድላቸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ወደ ቤተመቅደስ ለመሄድ ብቁ የሆኑ ናቸው፡፡ አንድ ሰው ቤተመቅደስ ከመግባቱ በፊት፣ ቢያንስ ለአንድ ዓመት የቤተክርስቲያን አባልነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ወንዶች የመልከ ፄዴቀ የክህነት ሥልጣን ማግኘት አለባቸው፡፡

ወደ ቤተመቅደስ ለመሄድ ብቃታቸውን ለማየት፣ ሁለቱም ማለት ወንድ እና ሴቷ ከጳጳሱ ወይም ከቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ጋር መነጋገር አለባቸው። ጳጳሱ ወይም ቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ግለሰቡን ብቁ ሆኖ ካገኘው፣ የተፈረመ ወረቀት የቤተመቅደስ መግቢያ ድጋፍ የሚባለውን ይሰጠዋል፡፡ ከዚያም በኋላ የስቴክ አመራር አባል ወይንም የሚስዮኑ ፕሬዚዳንት ደግሞ ለግለሰቡ ቃለመጠይቅ ማድረግ አለበት። እርሱም ደግሞ ግለሰቡን ብቁ ሆኖ ካገኘው በቤተመቅደስ መግቢያ ድጋፍ ላይ ይፈርምበታል፡፡ ግለሰቡም የቤተመቅደስ መግቢያ ፈቃዱን ወደ ቤተመቅደስ ለመግባት መውሰድ አለበት።

የሚከተሉት ጥያቄዎች ጳጳሱ ወይንም የቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ የቤተክርስቲያኑ አባል ወደ ቤተመቅደስ ለመሄድ ብቁ እንደሆነ ለመወሰን ከሚጠይቁት ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፣

1. በእግዚአብሔር፣ በልጁ ኢየሱስ ክርስቶስና፣ በመንፈስ ቅዱስ ታምናለህ?
2. ከፍ ያለ ኃጢአት ፈፅመህ እናም አግባብ ላለው የክህነት ሥልጣን መሪዎች ሳትናዘዝ የቀረ አለን?
3. የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፕሬዚዳንት እንደነብይ፣ እንደ ባለራዕይ እና እንደትንቢተ ገላጭ ተቀበላለህን? እርሳቸው ሁሉንም የክህነት ሥልጣን ቁልፎች ለመጠቀም ሥልጣን ያላቸው በምድር ላይ ብቸኛ ሰው እንደሆኑ ትቀበላለህን?
4. ከገቢህ ላይ አንድ አስረኛውን ለቤተክርስቲያን ትሰጣለህን?
5. የጥበብ ቃልን ትጠብቃለህን?

6. ከሌሎች ሰዎች ጋር ታማኝ ለመሆን ጥረት ታደርጋለህን?
7. በቤተክርስቲያን ውስጥ ተግባርህን ለመስራት ወደ ስብሰባዎች በመሄድ እና ትዕዛዛትን በመጠበቅ ብርቱ ጥረት ታደርጋለህን?
8. የንጽህናን ሕግ ትጠብቃለህን?

ቤተመቅደስ መግባት የተቀደሰ ክብር ነው፡፡ እያንዳንዱን በቤተመቀደስ ከእግዚአብሔር ጋር የገባነውን የተቀደስ ቃል ኪዳን ለመጠበቅ ብቁና ፈቃደኞች መሆን አለብን፡፡ በቤተመቀደስ የተከናወነው መተሳሰር የተቀደሰ እንደሆነ ማስታወስ አለብን። ለዘለዓለም እንደቤተሰብ አብረን የምንሆንበተ ብቸኛው መንገድ ይህ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሄር ለእኛ ያለውን ሁሉንም በረከቶች የምንቀበልበተ ብቸኛ መንገድ ይህ ብቻ ነው፡፡ ለዘለዓለማዊ ደስታችን ለመተሳሰር ወደ ቤተመቀደስ ለመሄድ መጣራችን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

### *ውይይት*

- ቤተመቀደስ መግባተ የሚችል ማን ነው?
- አንድ ሰው ቤተመቀደስ ለመግባተ ብቁ ለመሆን ምን ነገሮች ማድረግ አለበተ?
- ወደ ቤተመቀደስ መሄዳችንና መተሳሰራችን ለምን አስፈለገ?

### ቤተሰብዎ ለዘለዓለም አብረዎ እንዲኖሩ ማዘጋጀት

በቤተመቀደስ መተሳሰር እንድቤተሰብ አብሮ ለዘለዓለም ለመኖር ያመቻቻል፣ ነገር ግን ይህን ታላቀ በረከተ ለማግኘተ ስንፈልግ ማድረግ ያለብን ሌሎች ጉዳዮች አሉ፡፡ ኢየሱስን መከተል በታማኝነተ መቀጠል አለብን፡፡ በቤተመቀደስ ውስጥ ያደረግነውን ቃልኪዳኖች መጠበቀ አለብን፡፡ መልካም የቤተሰብ አባላተ ሌሎችን የምንወድና የምናገለግል መሆንን መማር አለብን፡፡ በምናደርገው ማናቸውም ነገር መንፈስ ቀዱስ አግባብ ያለው ምርጫዎችን እንድናደርግ ይረዳን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር መፀለይ አለብን፡፡ ሁልጊዜ ቤተሰቦቻችን ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ብቁ እንዲሆኑ ለመርዳተ መጣር አለብን፡፡

### *ውይይት*

- በቤተመቀደስ ከመተሳሰር ባሻገር፣ ቤተሰብ ለዘለዓለም አብሮ ለመኖር ምን ማድረግ አለበተ?

### እግዚአብሔር ቀደመ አያቶቻችንን ለማዳን አመቺ ሁኔታን ፈጥሮልናል

በሚሊዮን የሚቆጠሩ የእግዚአብሄር ልጆች ወንጌሉን ሳይሰሙ ሞተዋል፡፡ ለኃጢአታቸው ይቀርታን ለማግኘተና ተመልሰው ከእርሱ ጋር እንደገና ለመኖር ለመቻል አስፈላጊውን ሥርዓተ አላገኙም፡፡ እግዚአብሄር ሁሉንም ልጆቹን ይወዳል እናም ሁሉም ወደ እርሱ እንዲመለሱ ይፈልጋል፣ ስለዚህ የወንጌል ሥርዓቶች እንዲደርጉላቸው የመፍትሄ መንገድ ሰጥቶአቸዋል፡፡ የሥርዓቶቹ ክንዋኔ በቤተመቀደስ ውስጥ መደረግ አለበተ፡፡

ለሙታኖች በቤተመቀደስ ውስጥ የሚፈጽሙላቸው ሥርዓቶች አንዳንዶቹ ጥምቀተ፣ የመንፈስ ቀዱስ ስጦታ፣ መስጠተ እና ቤተሰቦችን ለዘለዓለም ማስተሳሰር ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሥርዓቶች ተመልሰው ከእግዚአብሄር ጋር ለመኖር ለሚፈልጉተ ሁሉ አስፈላጊ ስለሆኑ ይህን ሥርዓተ ለቀድመ አያቶቻችን ማከናወን እንችላለን፡፡

### ውይይት

- ወንጌልን ሳይሰሙ የሞቱት ሰዎች አስፈላጊ ሥርዓትን በመቀበል ወደ እግዚአብሔር መመለስ እንዴት ይችላሉ?
- አስፈላጊ ሥርዓቶች ለሙታኖች መደረጋቸውን የማየት ኃላፊነት ያለው ማን ነው?

## በሕይወት ያሉ ለሙታኖች ሥርዓቶችን ያከናውኑላቸዋል

ለሞቱት ወገኖቻችን ሥርዓቶችን ለመፈጸም አንዳንድ የምናከናውንላቸው ነገሮች አሉ፡፡ ይህም በስማቸው መለየት እና የተወለዱበትን ቀን፣ ቦታ የሞቱበትን ጊዜ ለይተን ማወቅ አለብን፡፡ ይህን መረጃ ማግኘት ካልቻልን፣ በተቻለን መጠን ከቤተሰብ ክፍል (አባትን፣ እናትን፣ እና ልጆችን) በመመዝገብ የመለየት ጥረታችንን ማድረግ እንችላለን፡፡

የሞቱትን የቀድመ አያቶቻችንን ስሞችና ስለነርሱ ሌሎች መረጃዎችን የመፈለግ ሥራ ሁሉ የዘር አወራረድ፣ ወይንም የቤተሰብ ታሪክ ይባላል፡፡

ይህን መረጃ የምትጽፉባቸው ሁለት ቀጾች የዘር ሐረግ ሠንጠርዥ እና የቤተሰብ ቡድን መመዝገቢያ የሚባሉ አሉ፡፡ የእነዚህን ቀጾች ቀጂ ከራሳችሁ የክህነት መሪ ማግኘት ትችላላችሁ፡፡ እርሱም ይህን መረጃ ስትጽፉ የሚረዳችሁን ሰው ይሰጣችኋል፡፡ ከዚያም በኋላ መረጃውን ሥርዓቶቹ ወደሚከናውኑበት ወደ ቤተመቀደስ መውሰድ ወይንም መላክ ትችላላችሁ፡፡

ማናቸውም በሕይወት ያሉ ዘመዶቻችን እኛ የምንፈልገው መረጃ ከሌላቸው፣ ከመንግስት መዝገቦች፣ የቀድመ አያቶቻችን ከሆኑት ቤተክርስቲያኖች መዝገቦች (ዜጎች በመንግሥት ዘንድ ወይንም በቤተክርስቲያኖቻቸው ተመዝግበው እንደሆን፣) ከመካነ መቃብሮች፣ ወይንም መረጃዎች ከሚገኙበት ከማንኛውም ሥፍራዎች ልናገኝ እንችላለን፡፡

ብቁዎች ከሆንን፣ ወደ ቤተመቀደስ በመሔድ ለዘመዶቻችን ሥርዓቶችን ልናከናውንላቸው እንችላለን፡፡ ወደ ቤተመቀደስ መሄድ የማንችል ከሆነ፣ ሌሎች ሰዎች ሥርዓቶቹን ያከናውኑላቸዋል፡፡ ሁልጊዜ ወደ ቤተመቀደስ ሄደን ለሙታን ሥርዓቶችን ማድረግ አለብን፡፡

### ውይይት

- ለሞቱት ቀድመ አያቶቻችን በቤተመቀደስ ሥርዓቶችን ከማከናውናችን በፊት ምን መደረግ አለበት?
- እነዚህ ሥርዓቶች እንዲከናውኑ ምን ዓይነት መረጃዎች ይፈለጋሉ?
- ለሞቱት ቀድመ አያቶቻችን ሥርዓቶችን መፈጸም የሚችል ማን ነው?

## ግላዊ ታሪኮች አስፈላጊዎች ናቸው

የቤተሰባችን አባል ስለራሱ የፃፈውን ስናነብ፣ ያንን ሰው እናውቀዋለን እናም የበለጠ እንወደዋለን፡፡ ስለሙታን ዘመዶቻችን በማወቅና ሥርዓቶችን ለእነርሱ ከማከናወናችን ጎን፣ ስለራሳችንም ሕይወት መዝገብ መጠበቅ አለብን፡፡ ስለወላጆቻችን፣ ስለልደታችን፣ በሕይወት ዘመን በራሳችን ላይ ስለተፈጸሙት ነገሮች መጻፍ አለብን፡፡ ስለ ሃሳቦቻችንም ደግሞ

ልጆቻችን እና የልጅ ልጆቻችን ይበልጥ ስለ እኛ አውቀው እናም በዚህ ዓይነት እኛ የሰራነውን ጥሩ ነገሮችን ለመስራት ብርታት እንዲያገኙ መጻፍ አለብን።

እግዚአብሄር ለአዳም የራሱን ህይወት ታሪክ እና የልጆቹን እንዲመዘግብ ነግሮታል። ነቢያትም ደግሞ የዚህን ዓይነት ታሪክ ጽፈዋል፣ እና እኛም ደግሞ መጻፍ አለብን። አዳምና ሌሎች ነቢያት የጻፉትን መዝገቦች በማንበብ፣ ከእግዚአብሄር የተቀበሉትን በረከቶችና ተዕዛዛትን እንረዳለን። ይህ ትክክለኛውን እንድናደርግ ይረዳናል። የራሳችንን መዝገብ በመጠበቀ ልጆቻችንን መርዳት አለብን።

## ውይይት

- እግዚአብሄር ለራሱ ሰዎች የራሳቸውን የህይወተ መዝገብ እንዲኖራቸው የነገራቸው ለምንድነው?
- የግል ታሪክዎን በማንበብ ለልጆችዎና ልጅ ልጆችዎ ምን ዓይነት በረከት ሊመጣላቸው ይችላል?

## ማጣቀሻ

*እግዚአብሔር ቤተሰብ ለዘለዓለም አብረው እንዲሆኑ አቀዷል*

- የማቴዎስ ወንጌል 18፥18 (አግባብ ባለው ባለሥልጣን በምድር የታሰረ በሰማይም የታሰር ይሆናል)
- የማቴዎስ ወንጌል 19፥46 (እግዚአብሐር አንድ ያደረገው አይለያይም።)

*የቤተክርስቲያን ታማኝ አባላት ብቻ ቤተመቀደስ ይገባሉ*

- ት እና ቃ 88፥119–21 (ቤተመቀደስ ለመግባተ ለኃጢያታችን ንስሐ መግባት አለብን።)

*ቤተሰብዎ ለዘለዓለም አብረው እንዲኖሩ ማዘጋጀት*

- 1ኛ ጴጥሮስ 3፥1–9 (ባልና ሚስት በአንድነት በሰላም እንዲኖሩ ተነግሮአቸዋል።)

*እግዚአብሔር ቀድመ አያቶቻችንን ለማዳን አመቺ ሁኔታን ፈጥሮልናል*

- ትንቢተ ሚልኪያስ 4፥6 (ሰዎች ለቀድመ አያቶቻቸው እንዲሁም ከእነርሱ በኋላ ለሚኖሩ ቤተሰቦች ማሰብ ይገባቸዋል።)
- ወደ ዕብራዊያን 11፥40 (ከእኛ ቀድመው ከሞቱት ውጭ ፍጹም መሆን አንችልም።)

*በሕይወተ ያሉ ለሙታኖች ሥርዓቶችን ያከናውኑላቸዋል*


- 1ኛ ቆሮንቶስ 15፥29 (በጥንት ሐዋሪያት ዘመን የኖሩት ሰዎች ለሙታኖች ተጠምቀዋል።)

*ግላዊ ታሪኮች አስፈላጊዎች ናቸው*

- ሚልኪያስ 3፥16 (የእግዚአብሔር ወዳጆች የነበሩት ሰዎች ስም በመዝገብ ውስጥ ተመዝግቧል።)

# የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት

*ክፍል ዘጠኝ*





የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምፅዓት መቃረብ የሚገልጹ ብዙ ምልክቶች አሉ፡፡

# የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓት

*ምዕራፍ 33*

*ኢየሱስ ክርስቶስ እንደገና ወደ ምድር ይመጣል፡፡ የእርሱ መምጫ ምልክቶች ምንድናቸው፣ እናም በሚመጣ ጊዜ እርሱን ለመገናኘት እንዴት እንዘጋጃለን?*

## ኢየሱስ ዳግም ወደ ምድር ለመምጣት ቃል ገብቷል

ኢየሱስ ከተነሳ ከአርባ ቀናት በኋላ፣ እርሱና ሐዋሪያቶቹ በአንድነት ደብረዘይት ተራራ በሚባለው ላይ ተገናኙ፡፡ ኢየሱስ ወደ ሰማይ የሚመለስበት ጊዜ ደርሶ ነበር፡፡ የሰማዩ አባታችን እንዲያደርግ የላከውን ሁሉ አድርጓል፡፡ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ ሐዋሪያት ተመልክተዋል፡፡ ሐዋሪያቶች እያዩት ሳለ ሁለት መላዕክቶች መጥተው ኢየሱስ እንደገና ወደ ምድር ይመለሳል አሉአቸው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከአሁን፣ በክርስቶስ የሚያምኑ የእርሱን መመለስ በመጠባበቅ ላይ ናቸው፡፡ የእርሱም መመለስ የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ይባላል፡፡

በዳግም ምፅዓቱ፣ ኢየሱስ በታላቅ ኃይል ከሰማይ ይመጣል፡፡ ክፉዎችን፣ ኃጢያተኛ ሰዎችን እናም መጥፎ የሆነ ማንኛውንም ነገር በማጥፋት ምድርን ያነፃል። እናም ሰይጣን በሰዎች ላይ ኃይል አይኖረውም፡፡ ኢየሱስ ለእርሱ ታማኝ የሆኑትን ሰዎች ሁሉ ለሺህ ዓመታት ይገዛል፡፡

### *ውይይት*

• ኢየሱስ እርሱ እንደገና ወደ ምድር እንደሚመለስ እንዴት ማወቅ እንችላለን?

## ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት ምን እንደሚሆን ነግሮናል

ኢየሱስ እንደገና ከመምጣቱ በፊት የሚሆነውን ብዙ ነገሮችን ነግሮናል፡፡ እነዚህ ነገሮች የዳግም ምፅዓቱ ምልክቶች ይባላሉ፡፡ እነዚህን ምልክቶች በማየት ለእርሱ መምጣት እንድንዘጋጅ ነግሮናል፡፡ እነዚህ ነገሮች ሲከሰቱ በምናይበት ጊዜ፣ የእርሱ መምጣት (በቀርቡ) እንደሚሆን እናውቃለን፡፡ ነገር ግን በትክክል የሚመጣበትን ጊዜ ማወቅ አንችልም፡፡

ቅዱሳን መጻህፍትን በማጥናትና ለኢየሱስ ታማኝ ብንሆን፣ የኢየሱስን የመምጫ ምልክቶች ምን እንደሚሆኑ ማወቀ እንችላለን፡፡ ብዙ ነገሮች ኢየሱስ እንደገና ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ይፈጸማሉ፡፡ ለንዳንዶቹ ቀደም ብለው ተፈጽመዋል፣ አንዳንዶቹም ለሁን እየተፈጸሙ ናቸው እናም የተቀሩት ወደፊት ይፈጸማሉ፡፡

ከኢየሱስ ዳግም መምጣት በፊት፣ ወንጌል ለሁሉም ሕዝቦች ይሰበካል፡፡ ይህ ብዙ ሰዎችን ያስደስታል እናም በረከትንም ያመጣላቸዋል፡፡ ሌሎቹ የሚፈፅሙት ነገሮች እምነታችንን ይፈትናሉ፡፡ ታላቀ ኃጢአት፣ የመሬት መናወጦች እናም ሌሎች ዓይነት ጥፋቶች ይሆናሉ፡፡

*በምድር ላይ ታላቀ መከራ ይሆናል*

ኢየሱስ ብዙ ክፋት፣ ጦርነት እናም የምድር ላይ ሥቃይን በምናይበት ጊዜ የእርሱ መምጫ መቃረቡን ታውቃላችሁ ብሏል። ይህ የታላቀ መከራ ጊዜ ይሆናል፡፡ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ታላቀ ዓውሎ ንፋስ፣ በሽታ እና ረሃብ ይሆናል፡፡ የበርዶ ቋጥኝ የምድርን ሰብል ያጠፋል፡፡

ብዙ ሰዎች የሰማይ አባታችንን መውደድ አቁመው ወደ ሰይጣን ይመለሳሉ፡፡ ሌሎች ሰዎችን መውደድና ማገልገልን አቁመው መጉዳተን (ማጥቃተን) ይጀምራሉ፡፡ በርካታ ጦርነቶች በምድር ላይ ይሆናሉ፡፡ መንግሥታተ እርስበርስ ይዋጋሉ፡፡ እነዚህ ጦርነቶች ታላቁና የመጨረሻው ጦርነት እስከሚመጣ ድረስ ይቀጥላሉ፣ ይህም በምድር ላይ ከተደረጉት ጦርነቶች ሁሉ አፍራሽ ይሆናል፡፡ ከዚያም ኢየሱስ ይመጣል፡፡

*ወንጌል ተመልሷል*

ኢየሱስ እንደገና ሳይመጣ ወንጌል ወደ ምድር እንደሚመለስ ነቢያቶች ተናግረዋል፡፡ ወንጌል በነብዩ ዮሴፍ ስሚዝ ለማካይነት ተመልሷል፡፡ ማንኛውም ነገር ማወቀና ማድረግ ያለብን ወደ ሰማዩ ለባታችን መመለስ የምንችልበትም የወንጌል ትምህርተ ወደ ምድራዊ ሰዎች ተመልሷል፡፡

ኢየሱስ መጽሐፈ ሞርሞን ታተሞ ለዓለም ሲሰጥ ምፅዓቱ እየተፋጠነ መሆኑን ታውቃላችሁ ብሏል። ከብዙ ዓመታተ በፊት፣ ነብዩ ኢሳያስ እና ሕዝቀኤል ስለ መጽሐፈ ሞርሞን ተናግረዋል፡፡ መጽሐፈ ሞርሞን በነብዩ ዮሴፍ ስሚዝ ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉሟል፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በብዙ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት ለሁሉም የዓለም ህዝቦች ይሰጣል፡፡

*ቤተ እስራኤል እንደገና መሰብሰብ ለለበተ*

የሰማዩ ለባታችን የቤተ እስራኤል ተውልዶች ወንጌልን በመስማትና በመቀበል ኢየሱስ እንደገና ሲመጣ ለመገናኘተ ራሳቸውን ማዘጋጀተ እንዳለባቸው ተነግሯል፡፡ ወንጌልን የተቀበሉተ ሰዎች ለሁሉም ሰዎች ማስተማር ቤተመቀደሶችን መገንባተ፣ እና ለሙታን ሰዎች ሥርዓቶችን ማከናወን ለለባቸው፡፡

በደም ወይንም በማደጎ ከእስራኤል ቤት የሆኑ ብዙ ሰዎች፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል እንደተቀበሉ ወደ ቤተክርስቲያኑ ተለውጠዋል፡፡ ቀዲስቲቱ ምድር (የዛሬዋ እስራኤል) ለብዙዎቹ የአብረሃም ዘሮች መሰባሰብ ተባርካለች። የአብርሃም ወገኖች የሚባሉት እንደ ዓረቦችና አይሁዶች ተብሎ የሚታወቁትንና ሌሎችን ያጠቃልላል፡፡ በአሜሪካ የሚኖሩ፣ የመጽሐፈ ሞርሞን ሕዝቦች፣ ደግሞ የአብርሃም ወገኖች ሲሆኑ፣ ወንጌልን በመቀበል ጠንካሮችና ጻድቃኖች ሕዝቦች በመሆን ላይ ናቸው፡፡

*ወንጌል ለሁሉም ዓለም ይሰበካል*

ኢየሱስ ተከታዮቹ ወንጌልን ለሁሉም ዓለም ሲሰብኩ እርሱ በፍጥነት እንድሚመጣ እንደምናውቀ ተናግሯል፡፡ ቤተክርስቲያኑ ከተመለሰበተ ጊዜ ጀምሮ ወንጌላውያን በተለያዩ አገሮች (ሕዝቦች) ወንጌል እንዲሰብኩ ይላካሉ፡፡ ብዙ ወንጌላውያን በአሁኑ ወቀተ ወንጌልን ከሞላ ጎደል በየትኛውም ዓለም በመስበክ ላይ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ የቤተክርስቲያኑ አባል ለእርሱ ወይንም ለእርሷ ዘመዶች፣ እና ጓደኞች ስለወንጌል እንዲናገሩ ይጠይቃሉ፣ እናም ብዙዎች ወንጌልን ለመስበክ ወደ ሌሎች አገሮች እየሄዱ ናቸው፣ ስለሆነም ሁሉም ሕዝቦች ለመስማተ ዕድል ያገኛሉ ማለተ ነው፡፡

*ኤልያስ መጥቷል*

ነቢዩ ሚልኪያስ በመጽሐፍ ቀዱስ ኢየሱስ ለሁለተኛ ጊዜ ከመምጣቱ በፊተ፣ ነብዩ ኤልያስ ምድርን ይጎበኛል ብሏል፡፡ ቤተሰቦችን ለዘለዓለም አብሮ የማስተሳሰር ሥልጣንን መልሶ ያመጣል፡፡ ሰዎች ስለ ቀድመ አያቶቻቸውና ወገኖቻቸው እንዲድኑ ለመርዳተ እንዲማሩ እንዲፈልጉ ያደርጋቸዋል፡፡ በሚያዝያ 1836፣ ኤልያስ መጥቶ ይህን ሥልጣን ለነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ ሰጠው፡፡ ኤልያስ በመምጣቱ ምክንያተም በአሁኑ ወቀተ ቤተሰቦች በምድር ላይ በአንድነተ በቤተመቀደስ ይተሳሰራሉ፡፡

*አዲሲቷ ከተማ ኢየሩሳሌም ተገነባለች*

ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑ አዲሷ ኢየሩሳሌም በምትባል ከተማ ስትገነባ መምጫው መፋጠኑን እንደምናውቀ ተናግሯል፡፡ ኢየሱስ ያችን ከተማ እርሱ እንደሚገዛተ፣ እናም ጻድቃን የሆኑ ሰዎች እዚያ እንደሚኖሩም ተናግሯል፡፡ ይህችም ከተማ የተ እንደምትገነባ ነግሮናል፡፡ ይህ የሚሆነውም በተባበሩት የአሜሪካ መንግሥታተ ማዕከል በሚዙሪ ግዛተ ነው፡፡

እነዚህ የኢየሱስን መምጣተ መፋጠኑን ከሚያሳዩን ምልክቶች ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው፡፡ ቀዱሳን መጻሕፍተ ሌሎች ምልክቶችን ይነግሩናል፡፡ ብዙ ምልክቶች ቀደም ብሎ የታዩ ቢሆንም፣ ኢየሱስ ዳግም የሚመጣበተን ተክክለኛ ጊዜን አናውቀም፡፡

## ውይይት

- የኢየሱስ ዳግም ምፅዓት መቃረቡን እንዴት እናውቃለን?
- የኢየሱስ ዳግም መምጫው ምልክቶች ምን ምንድን ናቸው?

## ክፉትና መከራ የከበበን ቢሆንም ሰላምና ተስፋ ማግኘት እንችላለን

ለኢየሱስ ዳግም ምፅዓት መዘጋጀት አለብን። ለእርሱ መምጣት ለመዘጋጀት የተሻለው መንገድ የእርሱን ትምህርቶች በየቀኑ መጠበቅ ነው። ለዛሬው የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት የሚሰጠውን መመሪያዎችና ትዕዛዛት ደግሞ መጠበቅ አለብን። መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር በማንኛውም ጊዜ ሆኖ ሃሳባችንና ስራዎቻችንን በመቆጣጠር እንዲመራን ብቁ መሆን አለብን። ኢየሱስ በሚመጣበት ጊዜ ዝግጁ ከሆንን፣ መፍራት እንደሌለብን ተናግሯል። ደስተኞች እና ከእርሱ ጋር ለመሆን የምንፈልግ እንሆናለን። መልካም ሰዎች እርሱ በመጣ ጊዜ አይጠፉም። በምድር ላይ ይኖራሉ፣ እናም ልጆቻቸው ያለኃጢአት ያድጋሉ። ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ይሆናል፣ እናም ይባርካቸዋል፣ ይመራቸዋልም።

ኢየሱስ እንደገና ከሰማይ ሲመጣ፣ ክፉ ሰዎች ይጠፋሉ። የሞቱት መልካም ሰዎች ከመቃብር ተነስተው እርሱ ከሰማይ እንደመጣ ያገኙታል። አንድ ሺው ዓመት እስኪያልቅ ድረስ ክፉዎች ከመቃብሮቻቸው አይነሱም። ይህ የአንድ ሺህ ዓመታት ጊዜ "ሚሊኒየም" (አንድ ሺኛው) ተብሎ ይታወቃል።

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፣ እርሱ የዓለም አዳኝ ሆኖ መምጣቱን በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ያውቁ ነበር። ኢየሱስ እንደገና ሲመጣ፣ እያንዳንዱ ሰው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ የዓለም አዳኝ መሆኑን ያውቃሉ።

### *ውይይት*

- የዳግም ምፅዓትን ምልክቶች ማወቅ እንዴት ሊረዳን ይችላል?
- ኢየሱስ ሲመለስ በምድር ላይ ያሉ መልካም ሰዎች ላይ ምን ይሆናል?
- በዚያን ጊዜ በምድር ላይ በሚኖሩት ክፉ ሰዎች ላይ ምን ይፈጸማል?

### *ማጣቀሻ*

*ኢየሱስ ዳግም ወደ ምድር ለመምጣት ቃል ገብቷል*

- ማቴዎስ 24፡36፤ 42–44 (የኢየሱስን መመለሻ ቀንና ሰዓት አናውቅም።)
- ማቴዎስ 26፡64 (ኢየሱስ በሰማይ በደመና ውስጥ ይመጣል።)
- ዮሐንስ 14፡2–3 (ኢየሱስ ለመመለስ ቃል ገብቷል።)
- የሐዋሪያት ሥራ 1፡11 (መላዕክቶች ለሐዋርያት ኢየሱስ እንደገና እንደሚመጣ ነግረዋቸዋል።)

*ኢየሱስ እርሱ ከመምጣቱ በፊት ምን እንደሚሆን ነግሮናል*

- ማቴዎስ 24 (ከኢየሱስ ዳግም ምፅዓት አስቀድሞ የሚመጡት ምልክቶች ተገልፀዋል።)

*ክፉትና መከራ የከበበን ቢሆንም ሰላምና ተስፋ ማግኘት እንችላለን*

- ማቴዎስ 13፡40–43 (ክፉዎች ይቃጠላሉ፣ ነገር ግን ጻድቃኖች ይድናሉ።)
- ዘካሪያስ 14፡9 (ኢየሱስ በተመለሰ ጊዜ ምድርን ይገዛታል።)

# አንድ ሺህ ዓመት

*ምዕራፍ 34*

---

*አንድ ሺው ዓመት ማለት ምን ማለት ነው? በአንድ ሺው ዓመት የምድር ሕይወት ምን ይመስላል?*

**በአንድ ሺህ ዓመት ዘመን ጻድቃኖች በምድር ላይ ይኖራሉ**

ኢየሱስ እንደገና ሲመጣ፣ ለአንድ ሺህ ዓመታት ዓለምን ይገዛል። ይህ ክፍለ ጊዜ አንድ ሺው ዓመት ይባላል።

የአንድ ሺህ ዓመት የሰላምና የጽድቀ ጊዜ ይሆናል። ኢየሱስ የአንድ ሺህውን ዓመታት ከመጀመሩ በፊት ምድርን ያጸዳል። ክፉ ሰዎች በሙሉ ይደመሰሳሉ። በዚህን ጊዜ ጻድቃኖች ብቻ በምድር ላይ ለመኖር ይድናሉ። ሰይጣን በሰዎች ላይ ዳግም እስከ ሺህኛው ዘመን መጨረሻ ድረስ ኃይል አይኖረውም።

ነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ እንዳለው በሺህኛው ዘመን ሰዎች ከሰማይ ሁልጊዜ ምድርን ይጎበኛሉ። እነርሱም በቤተመቀደስ ሥራዎችና በወንጌላውያን ሥራ ይረዳሉ ብሏል።

***ውይይት***

- አንድ ሺህ ዓመት ምንድነው?
- በሺህ ዓመት ዘመን በምድር ላይ ማን ይኖራል?
- ክፋት በሌለበት ሥፍራ መኖር ምን እንደሚመስል ለመገመት ይሞክሩ።

**በአንድ ሺህ ዓመት ዘመን ሁለት ታላላቀ ሥራዎች ይከናወናሉ**

የመጀመሪያው ታላቀ ሥራ በሕይወት ላሉትና ለሙታን ሰዎች በቤተመቀደስ ውስጥ መከናወን ያለበትን ሥርዓት ማከናወን ነው። በትንሳዔ የሚነሱት ሰዎች በምድር ላይ የሚኖሩትን ሙታን ዘመዶቻቸውን ስም ለማግኘት ማንኛውንም በመዝገቦች ላይ ያሉ ስህተቶችን ለማረም ይረዱአቸዋል።

ቤተሰቦችን በአንድነት ለማስተሳሰር የሚያስፈልጉ ሥርዓቶች ሁሉም በቤተመቀደስ ውስጥ ይደረጋሉ። ቤተሰቦች ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ እስከ አዳም ድረስ በመተሳሰር አንድ ይሆናሉ።

---

ሌላው ታላቅ ሥራ ወንጌልን መስበክ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ወንጌልን መስማትና መቀበል ይችላል፡፡ አንዳንድ መልካም የሆኑ ሰዎች የኢየሱስ ቤተክርስቲያን አባል ባይሆኑም ሺህኛው ዘመን ሲጀምር በምድር ላይ መኖር ይችላሉ፡፡ በመጨረሻም ሰዎች ሁሉ እየሱስ የአለም አዳኝ እንደሆነ ያውቃሉ እናም የአለም አዳኝ ነው ይላሉ።

### *ውይይት*

• በሺህ ዓመታት ምን ሁለት ታላላቅ ስራዎች ይሰራሉ?

## በሺህ ዓመታት ህይወት ምን ይመስላል?

በሺህ ዓመታት ወቀት ምድር አዳምና ሔዋን እንደኖሩባተ ኤደን ገነተ ተሆናለች፡፡ ምንም ጦርነተ አይኖርም፡፡ መንግስታትንና ቤተክርስቲያንን የሚገዛው ኢየሱስ ነው፡፡ ሕጎች ሁሉ በእውነተና በጽድቀ መሰረተ ዓላማ ላይ የተመሰረቱ ይሆናሉ፡፡ በዚያም ሁለተ ዋና ከተሞች ይኖራሉ፡፡ አንደኛዋ በኢየሩሳሌም ተሆናለች፡፡ ሌላኛዋ ዋና ከተማ በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም በተባበሩተ የአሚሪካ መንግሥታተ ተሆናለች፡፡

ሰዎች በሰላምና በፍቀር በአንድነተ ይኖራሉ፡፡ ሁሉም እንስሳተ በአሁኑ ጊዜ በጠላተነተ (በአውሬነተ) የሚፈረጁተ እንኳን ሳይቀሩ፣ በሰላም አብረው ይኖራሉ፡፡ ከእንግዲህም እርስ በርስ አይጣሉም፡፡

በሽታም አይኖርም፣ እናም ሞተም አይኖርም፡፡ ሰዎች ባረጁ ጊዜ፣ በአሁኑ ጊዜ እኛ እንደምንሞተው አይሞቱም፡፡ አሁን ካለንበተ ሁኔታ በፍጥነተ ወደ ሕያውነተ ሁኔታ ይለወጣሉ፣ ማለተም ደግሞ በፍጹም አይሞቱም፡፡

በሺህኛው ዓመተ መኖር ታላቅ ዕድል ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የማናውቃቸው ነገሮች ግልጽ ይሆኑልናል፡፡ ህይወተ ሁሉም ነገር በፍቀርና በሰላም ከሚፈጸም በስተቀር እንዳሁኑ ይሆናል። ሰዎች ልጅ መውለድና ማሳደግን፣ እህል መዝራተን፣ ማምረተንና መብላተን እናም ቤቶች መገንባተ ይቀጥላሉ፡፡

### *ውይይት*

• በሺህ ዘመን ምድር ምን ተመስላለች?

## በሺህ ዓመተ ማለቂያ አቀራቢያ ላይ አንድ የመጨረሻ ተግል ይኖራል

በሺህኛው ዘመን ማለቂያ አቀራቢያ፣ ሰይጣን በድጋሚ በምድር ላይ ኃይል ማግኘተ ይጀምራል፡፡ የተወሰኑ ሰዎች ያምኑታል፡፡ ሰይጣንና እርሱን የሚከተሉተ ኢየሱስን የተከተሉተን ይወጋሉ፡፡ በዚህ ውጊያ፣ ሰይጣንና እርሱን የተከተሉተ ለዘለዓለም ይሸነፋሉ፡፡ ከዚህ ጦርነተ በኋላ፣ ሰዎች ፍርድ ያገኛሉ፣ እናም እያንዳንዱ ሰው ለተዘጋጀበተ መንግሥተ ይደላደላል፡፡

### *ውይይት*

• በሺህ ዘመን መጨረሻ ላይ ምን ይሆናል?

## *ማጣቀሻ*

*በአንድ ሺህ ዓመት ዘመን ጻድቃኖች በምድር ላይ ይኖራሉ*

- 2ኛ ኔፊ 30፥10 (ክፉዎች ይደመሰሳሉ)፡፡
- ሙሴ 7፥64 (ምድር ከኃጢአተኞች ነፃ ትሆናለች)፡፡

*በአንድ ሺህ ዓመት ዘመን ሁለት ታላላቅ ሥራዎች ይከናወናሉ*

- ትንቢተ ኤርሚያስ 31፥34 (ሰዎች ስለ ኢየሱስ እርስበርስ አይማማሩም፣ ምክንያቱም ሁላቸውም ያውቁታልና)።

*በሺህ ዓመታት ህይወት ምን ይመስላል?*

- ትንቢተ ኢሳይያስ 2፥3–4 (የአለም ሁለት ዋና ከተሞች ይኖራሉ፣ እናም ሁሉም ዓለም ሰላም ይሆናል)፡፡
- ትንቢተ ኢሳይያስ 11፥6–9 (እንስሳት እርስበርሳቸው በሰላም ይኖራሉ)፡፡
- የዮሐንስ ራዕይ 20፥1–3 (ሰይጣን ይታሰራል)፡፡

*በሺህ ዓመት ማለቂያ አቅራቢያ ላይ አንድ የመጨረሻ ትግል ይኖራል*

- የዮሐንስ ራዕይ 20፡7–10 (ሰይጣንና ተከታዮቹ በመጨረሻው ጦርነት ይሸነፋሉ)፡፡

# ከሞት በኋላ ሕይወት

## ክፍል አስር





*ከሞትን በኋላ ከቤተሰቦቻችን እና ከምንወዳቸው ጋር በመንፈስ ዓለም እንገናኛለን።*

# ከሞት በኋላ ሕይወት

*ምዕራፍ 35*

*ለቀጣዩ ሕይወት እንዴት መዘጋጀት እንችላለን?*

**ከሞትን በኋላ መንፈሳችን ይኖራል**

እኛ የሰማዩ አባታችን የመንፈስ ልጆች ነን። ከእርሱ ጋር በሰማይ እንደመንፈስ ሆነን በምንኖርበት ጊዜ፣ አካላዊ ስጋ አልነበረንም። በዚህ ምድር ላይ እንድንወለድና መንፈሳችንም የሥጋና የአጥንትን አካል እንዲያገኝ ማድረጉ ከዕቅዱ ክፍል አንዱ ነበር። በምድራዊ ኑሮአችን ወቀት መንፈሳችን ለአካላዊ ገላችን ህይወትን የሰጠ ነው።

መወለድ ልክ የሰማዩ አባታችን ለእኛ ካለው ዕቀድ አንዱ እንደነበር፣ ሌላው ለኛ ያለው የዕቀዱ ክፍል የሆነው መሞት ነው። አንድ ሰው ሲሞት፣ መንፈሱ ከአካሉ ይለያል፣ ከመንፈስ ውጭ፣ አካል ሕይወት አይኖረውም። እናም በመቃብር ውስጥ ይቀመጣል።

ነገር ግን መንፈሳችን ከመወለዳችን በፊት ኖሯል፣ እናም ከሞት በኋላም መኖሩን ይቀጥላል። በምንሞትበት ጊዜ፣ አካላችን በመቃብር ውስጥ ሲቀር፣ መንፈሳችን ትንሳኤን ለመጠበቀ ወደ መንፈስ ዓለም ይሔዳል።

በመንፈስ ዓለም መንፈሳችን በምድር ላይ ሥጋና አጥንት እንደነበረን ቀርጽ ይኖረዋል። እዚህ እንደነበረን እንመስላለን። እንደ አሁኑ እናስባለን፣ እናም እዚህ የምናምንባቸው የነበሩትን ሁሉ እዚያም እናምንባቸዋለን፣ በዚህ ሕይወት ጻድቃን የሆኑ እዚያም ዳድቃን ይሆናሉ። ጻድቃን ያልሆኑት እዚያም ጻድቃን አይሆኑም። ከሞትን በኋላ እዚህ ምድር ላይ በነበርን ጊዜ እንደነበርን ዓይነት ፍላጎት ይኖረናል።

***ውይይት***

- የመንፈስ አካላችን የመጣው ከየት ነው?
- ስንሞት ምን ይሆናሉ?
- የመንፈስ አካል ምን ይመስላል?

## የመንፈስ ዓለም የሥራ፣ የመማሪያ እና የመቆያ ሥፍራ ነው

የሰማዩ አባታችን ነቢያት ስለመንፈስ ዓለም ብዙ ነገሮችን ነግረውናል። አንዱ ሥፍራ ገነት ይባላል። አንድ ወንጌልን የተቀበለና የኢየሱስ ተከታይ የነበረ ሰው ሲሞት መንፈሱ ወደ ገነት ትሔዳለች። ይህ ሰዎች የሚደሠቱበትና ሰላም የሚያገኙበት ሥፍራ ነው። እነዚህ ሠዎች ከመከራ፣ ከሃዘን፣ እናም ከበሽታ ነፃ የሚሆኑበት ነው። ብዙ ዋጋ ያለው ጠቃሚ ሥራን መስራት ይችላሉ፣ ሌሎችን ወንጌል ማስተማር ወይንም ለራሳቸው በበለጠ ለመማር ይችላሉ።

ሌላኛው ስፍራ የመንፈስ እስር ቤት ይባላል። ሶስት ዓይነት ሰዎች በዚያ ይሆናሉ። በዚህ ምድራዊ ሕይወታቸው ዘመን ክፉ የነበሩ፣ መልካም ሕይወት የኖሩ ነገር ግን ወንጌልን ያልተቀበሉ፣ እናም ወንጌልን የመስማት ዕድል በፍጹም ያላገኙ ናቸው።

የሰማዩ አባታችን ነቢያት በመንፈስ ዓለም ውስጥ ለሁሉም ሙታን ሰዎች ለመንፈስ ወንጌልን እንዲያስተምሩ ከጻድቃን መካከል ወንጌላዊያን ይላካሉ ሲሉ ነግረውናል። ብዙዎች ወንጌልን ተቀብለው ንስሐ ይገባሉ። ተገቢ የደህንነት ሥርዓቶች በህይወት ባሉ ሰዎች አማካይነት በሰማዩ አባታችን ቤተመቅደስ ውስጥ ይደረግላቸዋል። ወላጆች ወይም ሌሎች የቤተክርስቲያኑ አባላት እነዚህን ሥርዓቶች ያከናውኑላቸዋል። ከዚያም በኋላ ከመንፈስ እስር ቤት መውጣት ይችላሉ። የሰማዩ አባታችን ለልጆቹ ሁሉ በምድር ላይ በማንኛውም ጊዜ ቢኖሩ የወንጌልን በረከት እንዲያገኙ በዚህ መንገድ ዕድሉን ሰጥቶአቸዋል።

በመጨረሻም በመንፈስ ዓለም ውስጥ ያሉ ሁሉ ይነሳሉ። በትንሳኤው መንፈስና አካል እንደገና ይገናኛሉ። በመቃብር ውስጥ በነበረ ጊዜ አካል በስብሶ ወደ አፈርነት ቢለወጥም፣ ሕያውና ፍጹም አካል ይሆናል። ነብዩ አልማ "እያንዳንዱ የእጅና እግር መጋጠሚያ እንደነበረው ወደ አካላቸው ይመለሳሉ፤ አዎን፣ አንዲት የጸጉር ዘለላ እንኳን አትጠፋም፣ ነገር ግን ሁሉም ነገሮች ወደ ነበሩበትና ፍጹም ቀርጻቸው ይመለሳሉ"።

በትንሳኤው አካልና መንፈስ ይወሃዳሉ፣ በፍጹምም አይለያዩም። ኢየሱስ በእርሱ ፍቅርና ታላቅ የመስዋዕትነት ክፍያው ለዘለዓለም በዚህ ምድር ለሚኖሩ ለእያንዳንዱ ሰው ይህን ግሩም ትንሳኤን ሰጥቶናል።

### *ውይይት*

- በመንፈስ ዓለም ውስጥ ያሉ ሁለቱ ክፍሎች ምንድን ናቸው?
- በገነት የሚሆነው ማን ነው? በገነት ውስጥ መንፈስ ምን ያደርጋል?
- በመንፈስ እስር ቤት ውስጥ የሚሆን ማን ነው? እዚያስ ምን ይሆናል?

## በመጨረሻው ፍርድ ሁላችንም ይፈረድብናል

በዘለዓለማዊው ሕይወታችን ወቀት ብዙ ጊዜያት ተፈርዶብናል። ከሰማዩ አባታችን ጋር ስንኖር ወደዚህ ምድር መጥተን አካል እንድናገኝና ብቃት ያለን መሆናችንን ለማየት ተልከናል። እዚህም ባለን ጊዜ ለመጠመቅ ብቁ መሆን እንዳለብን ተነግሮናል። ሰዎች የክህነት ሥልጣን ሲሰጣቸው ብቁ እንዲሆኑ ታዘዋል። ቤተመቅደስ በመግባት ልዩ በረከትን ለማግኘት ብቁ

መሆናችንን ለማየት ተፈርዶብናል። ከሞትን በኋላም ይፈረድብናል፣ እናም ዋጋችንን የምናገኘው በምድር ላይ በኖርነው አኗኗር ይሆናል።

ከሞት ከተነሳን በኋላ፣ ለፍርድ በሰማዩ አባታችን ፊት ለመጨረሻ ጊዜ እንቀርባለን። ይህ የመጨርሻ ፍርድ ይባላል። ይህም የመጨርሻ ፍርድ ለዘለዓለም ለመኖር የት እንደምንሔድ ይወስንልናል። እዚህ በተናገርነው፣ ባደረግነው እናም በዚህ ሕይወታችን ባሰብነው ይፈረድብናል። ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ የኢየሱስን ትምህርቶች እንደተከተልን ይታያል። በዚህ ምድርና በሰማይ በተያዘው መዝገባችን መሰረት ይፈረድብናል። የሰማዩ አባታችን ኢየሱስ እንዲዳኘን ያደርጋል።

ኢየሱስ በጣም ይወደናል፣ ነገር ግን እርሱ ተክክለኛ ዳኛ ነው በኖርነው ዓይነት ሕይወታችን መሰረት ሊፈርድብን ይገባል። እና ያሰብነው፣ ወይም ያልነው፣ ወይንም ያደረግነው ሁሉ ተመዝግቧል፣ በአዕምሮአችንና በተያዘውም መዝገብ ተመዝግቧል። ኢየሱስ ሁሉንም ድርጊታችንን ያውቃል፣ እናም በእርሱ ፊት ስንቆም እንደዚሁ እናስታውሳቸዋለን።

## *ውይይት*

- አንዳንድ ጊዜ መቼ እንደሚፈረድብን ጥቀስ?
- የሚያስፈርዱብን አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?

## ከሞትን በኋላ የሚፈጸምብንን ሁኔታ በዕለታዊ ተግባራችን እንወስናለን

በዚህ ሕይወታችን ዘመን ትክክለኛውን ብናደርግ፣ ለዘለዓለም ከሰማዩ አባታችን ጋር ለመኖርና መልካም የምድር ሰዎች ለመሆን ራሳችንን እናዘጋጃለን። የሰማዩ አባታችን ትዕዛዛት የማንከተል ከሆነ፣ ለፍርድ ኢየሱስ ፊት ስንቆም በጣም መጥፎ ስሜት ይሰማናል።

ነቢያት እንዳሉት፣ “ቃላችን ይኮንነናል፣ አዎን፣ ሥራችን ሁሉ ይኮንነናል፣ ንጽህና የጎደለን ሆነን መገኘት የለብንም፣ እናም ሃሳባችን ደግሞ ይኮንነናል”። ክፉዎች “በእፍረትና በአሰቃቂ ጥፋት” እናም አለቶችና ተራሮች በላያቸው ወድቀው ከእርሱ ፊት ቢደብቋቸው ይመኛሉ ብለዋል።

ለእያንዳንዱ በዚህ ምድር ላይ ለኖረ ሰው፣ በኋላ የመጨረሻው ፍርድ ቀን ግሩም ወይንም የተካዜ ቀን ሊሆን ይችላል። እኛም የደስታ ቀን እንዲሆንልን ለዚህ ለሚመጣው ጊዜ መዘጋጀት አለብን። በሰማዩ አባታችን ፊት ያለ እፍረትና በሕይወታችን ዘመን ስላደረግነው የሚወስነውን መስማት እንድንችል እንፈልጋለን።

ስለዚህም የመጨረሻ ፍርድ ማሰብ አለብን። ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኞች እናም እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ ዝግጁዎች ሆነን ለኃጢአታችን ንስሐ መግባት አለብን። ያ ጊዜ ሲደርስ ከሁሉም ኃጢያት ነጻ መሆን የምንችለው በዚያ መንገድ ብቻ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ አምነት ካለንና ለኃጢአታችን ሁሉ ንስሐ ከገባን፣ የሰማዩ አባታችን ኃጢአታችንን ይቀር ይለናል፣ እናም ሙሉ በሙሉ ኃጢአተ አልባ እንድንሆን ይረዳናል። ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኞች ብንሆን፣ ጥሩ ሥራዎችን በመስራት፣ ጥሩ ሃሳቦችን በማስብ፣ እና ጥሩ ቃሎችን በመናገር ጊዜያችንን እናሳልፋለን። በማንኛውም መንገድ መጥፎ ሃሳብ የሚያሳስቡንን ሰዎች፣ መፃህፍትና ስፍራዎች ወይም ፅድቀ እንዳንሰራ የሚያደርጉንን እናስወግዳለን።

የሰማዩ አባታችን እያንዳንዳችንን ይወደናል እናም እርሱ ወዳለበት ለመመለስ ብቁዎች ሆነን እንድንኖር ይፈልገናል። ከእርሱ ጋር ለመኖር ፍላጎት ካለን እና ጥሩ ሰዎችን ብንሆን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ሊኖረን እና እርሱ እንድናደርግ ያዘዘንን ማድረግ ይገባናል። ቤተሰቦቻችን ደግሞ ጥሩ ኑሮ እንዲኖሩ መርዳት አለብን። የሰማዩ አባታችን ይረዳናል። መንገዱን ሊያሳየን እና ለዕርዳታው ሁልጊዜ ወደ እርሱ እንድንጸልይ ወንጌልን ሰጥቶናል እና እንዲረዳን ዘወትር ወደ እርሱ እንድንፀልይ ነግሮናል።

## ውይይት

- የዕለት ሃሳባችንና ድርጊታችን ለምን በጣም አስፈላጊ ሆኑ?
- ሃሳብዎን፣ ቃላትዎን፣ እና ተግባርዎን ለማሻሻል ምን ማድረግ ይችላሉ?
- ፍጹም ለመሆን የሰማዩ አባታችንን እርዳታ ለምን እንፈልጋለን?
- ከሰማዩ አባታችን ጋር ለመኖር ብቁ በመሆን ፍርድ ለማግኘት እንድንችል በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እምነት በመኖር ብቻ ለምን ሆነ?

## ማጣቀሻ

*ከሞትን በኋላ መንፈሳችን ይኖራል*

- ሉቃስ 23፥43 (ኢየሱስ በመስቀል ላይ አብሮት ለነበረውን ሌባ በቀርቡ በገነት እንደሚገናኙ ቃል ገብቶለታል።)
- አልማ 40፥11 (ከሞትን በኋላ መንፈሳችን ወደሰማዩ አባታችን ይመለሳል)።

*የመንፈስ ዓለም የሥራ፣ የመማሪያ፣ እና የመቆያ ሥፍራ ነው*

- 1ኛ ጴጥሮስ 3፥18–20 (ኢየሱስ መንፈሶችን በእስር ቤት ሰብኳል)።
- አልማ 40፥12–14 (ክፉዎች በእስር ቤት ክፉኛ ሲያዝኑ፣ ጻድቃን በገነት ይደሰታሉ።)

*በመጨረሻው ፍርድ ሁላችንም ይፈረድብናል*

- የሐዋሪያት ሥራ 17፥31፤ ወደሮሜ ሰዎች 14፥10 (አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ሰው ይዳኛል።)
- የዮሐንስ ራዕይ 20፥12 (በምድርና በሰማይ በተያዘው መዝገብ መሰረት ይፈረድብናል።)

*ከሞትን በኋላ የሚፈጸምብንን ሁኔታ በዕለት ተግባራችን እንወስናለን*

- ማቴዎስ 25፥31–46 (ኢየሱስ ክርስቶስ በሥራችን ይፈርድብናል)
- 2ኛ ኔፊ 29፥11 (በቅዱስ መጻሕፍት መሰረት ይፈረድብናል)።
- ያዕቆብ 6፥9 (ንስሐ ካልገባን በእፍረትና በአሰቃቂ ጥፋት እንቆማለን)።
- አልማ 12–14 (ቃላችን፣ ሃሳባችን እና ተግባራችን መጥፎ ከሆኑ ይኮንኑናል)።
- 2ኛ ኔፊ 31፥19–20 (የዘለዓለም ህይወት ለማግኘት እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ ድረስ ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኞች ሆነን መዝለቅ ለኃጢአታችንም ንስሐ መግባት አለብን)።

# ዘለዓለማዊ ሕይወት

*ምዕራፍ 36*

---

*ከመጨረሻ ፍርድ በኋላ ለመኖር የምንሄደው የት ነው?*

**እያንዳንዳችን ስንዘጋጅበት ወደ ነበረው ስፍራ እንሔዳለን**

ኢየሱስ የሰማዩ አባታችን ብዙ የምንኖርበትን ሥፍራዎች እንዳዘጋጀልን አስተምሮናል፡፡ እያንዳንዳችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኞች በነበርነው መሰረተ ከአራቱ ሥፍራዎች በአንዱ እንመደባለን፡፡ ባደረግነው ምርጫችን ወደተዘጋጀንበተ መንግስት እንሄዳለን፡፡ እነዚህ አራቱ ሥፍራዎች የሰለስቲያል መንግስተ፣ የተረስቲያል መንግሥተ፣ የተለስቲያል መንግስትና ውጫዊ ጨለማ ናቸው፡፡

*የሰሌስቲያል መንግሥት*

ይህ ሥፍራ የሰማዩ አባታችንና ኢየሱስ የሚኖሩበት ቦታ ነው፡፡ ይህ ቦታ ሰዎች የሚደሰቱበት፣ እና ከምናስበው በላይ የበለጠ ውብ ሥፍራ ነው፡፡ በዚህ መንግሥት የሚኖሩ ሰዎች የሰማዩ አባታችንንና ኢየሱስን የሚወዱ እናም እነርሱን ለመታዘዝ የሚመርጡ ናቸው፡፡ ኃጢአታቸውን ሁሉ ንስሃ የገቡና ኢየሱስን እንደ አዳኛቸው የተቀበሉ መሆን አለባቸው፡፡ የተጠመቁና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን የተቀበሉ መሆን አለባቸው፡፡ ኢየሱስ አዳኝ መሆኑን የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

በከፍተኛው የሰሌስቲያል መንግስተ ክፍል መኖር *ከፍ ማለተ ወይንም ዘለዓለማዊ ሕይወተ ማግኘተ ይባላል፡፡ በዚህ በሲለስቲያል መንግስተ ክፍል ለመኖር ለመቻል፣ ሰዎች በቤተመቀደስ ውስጥ መጋባተ እና በቤተመቀደስ የገቡተን የተቀደሰ ቃልኪዳን መጠበቀ አለባቸው፡፡ የሰማዩ አባታችን ያለውን ሁሉንም ነገር ይቀበላሉ እናም እንደርሱም ይሆናሉ፡፡ የመንፈስ ልጆችም ሊኖራቸው ይችላል፣ እና የሚኖሩበተን አዲስ አለማተ ያበጁላቸዋል፣ እናም የሰማዩ አባታችን ያደረገውን ሁሉንም ነገር ያደርጋሉ፡፡ በቤተመቀደስ ያላገቡ ሰዎች በሌላ የሲሌስቲያል መንግስተ ክፍል ውስጥ ይኖራሉ፣ ነገር ግን ከፍ አይሉም።

---



አስከ መጨረሻው ታማኞች የሆኑት ከሰማዩ አባታችንና ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ከፍ ይላሉ።

*የተረስቲሪያል መንግሥት*

ይህ መንግሥት እንደ ሴሌስቲያል መንግሥት አስደናቂ አይደለም፡፡ ምንም እንኳ ኢየሱስ የቴለስቲያል መንግሥትን የሚጎበኝ ቢሆንም፣ እዚያ የሚኖሩት ከሰማዩ አባታችን ጋር አይኖሩም፣ እናም እርሱ ያለው ሁሉ አይኖራቸውም፡፡ ወደ ተሬስቲሪያል መንግሥት የሚገቡ የተከበሩ ሰዎች ይሆናሉ፡፡ አንዳንዶቹ የቤተክርስቲያኑ አባላት ሲሆኑ፣ ሌሎቹ አባል ያልሆኑ ናቸው፡፡ እነርሱም በምድር ኢየሱስን ያልተቀበሉ ነገር ግን በኋላ በመንፈስ ዓለም የተቀበሉ ናቸው፡፡ እዚያ የሚኖሩት ሰዎች ከዘላለማዊ ሕይወት ከሚኖሩ ቤተሰቦች ወገን አይሆኑም፣ ነገር ግን ተለይተው ያለ ቤተሰብ ይኖራሉ፡፡ የሰማዩ አባታችን ለነዚህ ሰዎች እነርሱ የተዘጋጁለትን ደስታ ይሰጣቸዋል፡፡

*የቴለስቲያል መንግሥት*

ይህ መንግሥት እንደ ሰሌስቲያል ወይንም ተረስቲያል መንግሥቶች (ታላቀ) አስደናቂ አይደለም፡፡ የሰማዩ አባታችንም ሆነ እየሱስ እዚህ የሚኖሩትን አይጎበኙም፡፡ መላዕክት እነዚህን ሰዎች ይጎበኛሉ፣ የመንፈስ ቅዱስ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል፡፡ በቴሌስቲያል መንግሥት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ወንጌልን፣ ወይንም የኢየሱስን ምስክርነት በምድርም ሆነ በመንፈስ ዓለም ያልተቀበሉ ናቸው፡፡ ስለ ኃጢአታቸው በመንፈስ እስር ቤት እስከ ሺህኛው ዘመን በኋላ ድረስ ይሰቃያሉ፡፡ ከዚያም በኋላ በመጨረሻ በትንሳዔ ይነሳሉ፡፡

እዚህ ምድር ላይ በነበሩ ጊዜ ዋሾ፣ ሌቦች፣ ነፍሰ ገዳዮች፣ የውሸት ነቢያት፣ ዝሙት አድራጊዎች እና በቀዱስ ነገሮች የተሳለቁ ነበሩ፡፡ እነርሱ ከኢየሱስ ትምህርቶች ይልቀ የዓለምን እምነት የተቀበሉ ሰዎች ነበሩ፡፡ በዚህ መንግሥት ብዙ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ የሰማዩ አባታችን እነዚህ ሰዎች ለመቀበል የተዘጋጁለትን ደስታ ይሰጣቸዋል፡፡

ውጫዊ ጨለማ

ውጫዊ ጨለማ ሰይጣንና እርሱን የተከተሉ የሚኖሩበት ስፍራ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ከሰይጣን ጋር ለመኖር የመረጡ ናቸው፡፡ ይቀርታን አያገኙም፡፡ እነዚህ ሰዎች ለዘለዓለም በጨለማ፣ በሃዘንና በስቃይ ከሰይጣንና እርሱን ከተከተሉት መንፈሶች ጋር ይኖራሉ፡፡

## *ውይይት*

- እንደ ሰማዩ አባታችን ለመምሰል ለየትኛው መንግሥት መዘጋጀት ይገባናል?
- ከዚህ በምድር ላይ ብቁ ሆነን እንደ ሰማዩ አባታችን ለመኖር አንዳንድ ማድረግ የሚገቡን ነገሮች ምንድናቸው?

## የሰማዩ አባታችን በሰለስቲያል መንግሥት ውስጥ ለዘለዓለማዊ ሕይወት የሚያዘጋጀንን ወንጌል ሰጥቶናል

የሰማዩ አባታችን እያንዳንዳችን ከእርሱ ጋር ዘለዓለማዊ ሕይወት እንዲኖረን ዕድል ሰጥቶናል፡፡ ዘለዓለማዊ ሕይወት የሰማዩ አባታችንና ኢየሱስ የሚኖሩት ዓይነት ሕይወት ነው፡፡ የሰማዩ

ለባታችን ፍጹም ነው፡፡ እርሱ ሁሉንም ነገር ያውቃል፡፡ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ኃይል አለው፡፡ እርሱ ሁሉንም ነገር ይገዛል፡፡ እርሱ እንደ ዘለዓለማዊ እውነትና ሕግ መሰረት ይኖራል፡፡

ኢየሱስ የሰማዩ ለባታችንን ታዝዟል፣ እና ስለዚህ ከሰማዩ ለባታችን ጋር ይኖራል፡፡ ኢየሱስ እንድናደርግ ያስተማረንን ነገሮች ብናደርግ፣ እርሱና የሰማዩ ለባታችን እንደኖሩት መኖር እንችላለን፡፡ ከሰማዩ ለባታችን ጋር በሰማይ ዘለዓለማዊ ሕይወት ለማግኘት እርሱ የሚሰጠን ታላቀ ስጦታ ነው፡፡ ይህ ከማንኛውም ነገር በላይ የበለጠ ደስታን ይሰጠናል፡፡

ወንጌል ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት ማወቀ ያለብንን ሁሉ እናም ማድረግ ያለብንን ሁሉ ይነግረናል፡፡ የሰማዩ ለባታችንና ኢየሱስን እንድናውቀ ይረዳናል፡፡ እነርሱ እንደኖሩት እንድንኖር ያስተምረናል፡፡ በመጸለይና ቀዱሳን መጽሐፍትን በማጥናት እነርሱን በተሻለ ማወቀ እንችላለን፡፡ እነርሱን ስናውቃቸውና ስንወዳቸው፣ ቃላቸውን ለመታዘዝ እንፈልጋለን። ስንታዘዛቸው እንደእነርሱ እንችላለን እናም ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም ለመኖር ብቁ እንሆናለን፡፡

### *ውይይት*

- ዘለዓለማዊ ሕይወት ምንድነው? ማንስ ያገኛታል?
- ወንጌል ለዘለዓለማዊ ሕይወት እንዴት ሊያዘጋጀን ይችላል?

### የሰማዩ አባታችን ወንጌልን ለመታዘዝ ስንመርጥ ይረዳናል

የሰማዩ ለባታችን ሁላችንም ወንጌልን ለመታዘዝ የዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት እንደምንችል ያውቃል፡፡ የእርሱ ልጆች እንደመሆናችን፣ እንደእርሱ ለመሆን ኃይል አለን፡፡ እያንዳንዳችን ያለንን ድክመት እናም ምን ነገሮች እንደሚፈታተኑንም ያውቃል፡፡ በአንድ ወቀት ወደ ምድር እንድንመጣ እናም ጥሩ ነገሮችን የምናደርግበትና የምንማርበት ዕድል በሚሰጠን ቦታ ፈቀዶልናል።

አሁን ወቀቱ ዘለዓለማዊ ህይወትን ለማግኘት ማድረግ ያለብንን የምናደርግበት ነው፡፡ የሰማዩ ለባታችን ይወደናል እናም እንዲሳካልንም ይፈልጋል፡፡ የሚችለውን ሁሉ ለድርጎልናል፡፡ የምናድግበትንና የምንማርበትን ምድር ሰጥቶናል፡፡ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን ለዳኛችንና ወንጌልን እንዲያስተምረን ልኮልናል፡፡ ወደ እርሱ እንድንፀልይ ጋብዞናል። መንፈስ ቀዱስ መሪያችን እንዲሆን ለመቻቸቶልናል፡፡ አሁን ተክክለኛውን ነገር ማድረግ ይጠበቀብናል፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ቢኖረንና እርሱን ብንታዘዝ፣ ይረዳናል፣ በሕይወታችን የሚመጡብንን ፈተናዎችና ሌሎች ችግሮችን ማሸነፍ ኃይል ይሰጠናል፡፡

የሰማዩ ለባታችን ወንጌልን እንድንቀበል ጠይቆናል፡፡ ይህን ለማድረግ በመጀመሪያ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ሊኖረን ይገባናል፡፡ ከዚያም ለመጠመቀና የኋለኛው ቀን ቀዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባልነትን ለማረጋገጥ ለኃጢአታችን ንስሐ መግባት አለብን፡፡ በሚረጋገጥልን ጊዜ፣ የመንፈስ ቀዱስ ስጦታን የክህነት ሥልጣን ካለው ሰው እንቀበላለን፡፡ መንፈስ ቀዱስ ለእያንዳንዳችን ኢየሱስ እንድናደርግ የሚፈልግብን እና ዘለዓለማዊ ህይወትን ለማግኘት ቀሪውን ሕይወታችንን እርሱን መታዘዝና ማገልገል እንዳለብን ይነግረናል፡፡

ኢየሱስ ሁላችንን ወደ ሰማዩ አባታችን እንድንመለስ ከእርሱ ጋር እንድንኖር ለመዘጋጀት ትዕዛዛትን እንድንታዘዝ ጠይቆናል፡፡ እነዚህም የንጽህና ህግን፣ የአስራት መክፈልን፣ በኩራትን መስጠት፣ የጥበብ ቃልን ማክበር፣ በሁሉም ወቀት ታማኝ ሆኖ መገኘትን እና የሰንበትን ቀን ቀድሶ መጠበቅን ያካትታል፡፡

እንደ ሰማዩ አባታችን ለመሆን በቤተመቀደስ የሚሰጠውን *የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሚባለውን ሥርዓት ደግሞ መቀበል አለብን፡፡ እዚያ መታተም አለብን፣ ለዘለዓለም ከቤተሰቦቻችን ጋር በአንድነት እንድንሆን እዚያ መተሳሰር አለብን፡፡ ስለዚህ የሙታን ዘመዶቻችንን በተመለከተ ስምና መረጃን በመፈለግ እና አስፈላጊው ሥርዓቶች በቤተመቀደስ ውስጥ ይከናወንላቸው ዘንድ ለቤተክርስቲያም መስጠት አለብን፡፡

ኢየሱስ ብዙ ነገሮችን እንድናደርግ አዞናል፡፡ እነዚህም ስለወንጌል ለሌሎች መንገርን፣ እነርሱን መርዳትና መውደድን፣ እናም ለእነርሱ መልካም ዓርአያ መሆንን ያጠቃልላል፡፡

ለሰማዩ አባታችን የገባነውን ቃል ኪዳን ሁሉ ደግሞ መጠበቀ፣ በቋሚነት የቤተክርስቲያናችንን ስብሰባን በመደበኛነት መሳተፍ፣ በየዕለቱ መጽሃፍ ቅዱስን በማጥናት ለቤተሰቦቻችን ወንጌልን ማስተማር፣ እናም በግልና ከቤተሰብ ጋር በየቀኑ መጸለይ አለብን፡፡

በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ካለንና ትዕዛዛቱን ሁሉ ለመታዘዝ ከሞከርን ዘለዓለማዊ ሕይወትን እናገኛለን እናም እንደ ሰማዩ አባታችን እንሆናለን፡፡

እንደ ሰማዩ አባታችን መሆን መሰላል እንደመውጣት ነው፡፡ ከመነሻው ላይ ጀምረን እያንዳንዱን እርምጃ አላይ እስከምንደርስ ድረስ መውጣት አለብን። ነብዩ ዮሴፍ ስሚዝ እንደ ሰማዩ አባታችን መሆን ከፈለግን እንደርሱ እንዴት እንደሚሰማው ሊሰማን፣ እንደርሱ ልናስብ፣ እና እንደርሱ መሥራትን መማር አለብን ብሏል፡፡ ስለ እርሱ እነዚህን ነገሮች ስንረዳ፣ ከዚያ በኋላ እንዴት እንደርሱ እንደምንሆን እስከምናውቀ ድረስ ስለ እርሱ ሌሎች ነገሮችን መማር እንችላለን፡፡

የሰማዩ አባታችን በአንድ ወቀት እኛ እንደምንኖረው ሰው ሆኖ በምድር ላይ እንደኖረ ለማስታወስ ይረዳናል፡፡ እርሱ የሰማዩ አባታችን መሆን የቻለው እኛ በዚህ ምድር ላይ ማድረግ እንዳለብን ችግሮችን በማሸነፍ ነው፡፡ ይሁን አንጂ፣ ነብዩ ዮሴፍ ስሚዝ በዚህ ዓለም ላይ ሳለን ማንኛውንም መማር ያለብንን አንማርም ብሏል፡፡ እንደ ሰማዩ አባታችን ለመሆን ይህን ሕይወታችንን ከፈጸምን በኋላ ሁሉንም ማወቀ ያለብንን ነገሮች ለማወቀ ረጅም ጊዜ ይወስድብናል ብሏል፡፡

የሰማይ አባታችንን ትዕዛዛት መጠበቅን ከተማርን፣ ወደ እርሱ ከተመለስን እንዴት ደስተኞች እንደምሆን አስቡ፣ እርሱ በኖርነው ሕይወት እንደሚደሰትና እርሱንም በመምሰል ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም እንደምንኖር ይነግረናል።

## ውይይት

- ለእያንዳንዳችን እንደሰማዩ አባታችን ለመሆን እንዴት ይቻለናል?
- የሰማዩ አባታችን ያለውን ዓይነት ህይወት እንዲኖረን ምን ነገሮች ማድረግ አለብን?

- እንደርሱ እንድንሆን የሰማዩ አባታችን የረዳን እንዴት ነው?
- የሰማዩ አባታችን መልካም መሥራትህንና እንደሚወድህ በነገረህ ጊዜ ስትሰማ እንዴት እንደሚሰማህ ግለጽ፡፡

***ማጣቀሻ***

*እያንዳንዳችን ስንዘጋጅበት ወደነበረው ስፍራ እንሄዳለን*

- የዮሐንስ ወንጌል 14፥2 (ኢየሱስ በአባቱ ቤት ቦታ አዘጋጅቶልናል)፡፡

*የሰማዩ አባታችን በሰለስቲያል መንግሥት ውስጥ ለዘለዓለማዊ ሕይወት የሚያዘጋጀንን ወንጌልን ሰጥቶናል*

- ሞዛያ 4፥26–27 (ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለመውረስ ማድረግ ያለብንን ነገሮች ተናግሮናል)።
- አልማ 34፥32–34 (ከሰማዩ አባታችን ጋር ለመኖር የምንዘጋጅበት ወቀቱ አሁን ነው)።

*የሰማዩ አባታችን ወንጌልን ለመታዘዝ ስንመርጥ ይረዳናል*

- ማቴዎስ 25፥23 (የሰማዩ አባታችን ታማኞች የሆኑትን በብዙ ነገሮች ላይ ይሾማቸዋል።)

# የእምነት አንቀፆች

በ1842 ፀደይ ወራት፣ ነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ የቺካጎ ዲሞክራት ጋዜጣ አዘጋጅ ለሆኑት፣ ለጆን ዌንትወርዝ ደብዳቤ ላከ። ይህ ደብዳቤ በብዛት የጥንቱን ቤተክርስቲያን አመሰራረት ይዘትን የያዘ ነበር። ሰነዱ በተጨማሪም አስራ ሶስቱን የኋለኛው ቀን ቅዱሳን እምነት ደንቦችን ይዟል። እንዚህም ከዚህ በታች እንደተዘረዘሩት የእምነት አንቀጾች ተብሎ ይታወቃሉ።

የእምነት አንቀጾቹ የቤተክርስቲያኗ ሕጋዊ ትምህርት እና የኋለኛው ቀን መንፈሳዊ መመርያ ናቸው እነዚህንም የቤተክርስቲያኑ አባላት መሰረታዊ እምነቱን እንዲረዱና፣ እነዚህንም እምነቶች ለሌሎች እንዲገልጹ የሚረዱ የእምነት ዓረፍተ ነገሮች ናቸው። ቢሆንም፣ እነዚህ ብቸኛ የተሟሉ የቤተክርስቲያኑ ማጠቃለያ ትምህርቶች አይደሉም። በሕያው ነቢያት አማካይነት፣ ቤተክርስቲያኗ በተከታታይ ራዕይና በመንፈስ መገለጥ ተመራለች።

1 በዘለዓለማዊ አባት፣ በእግዚአብሔር፣ በልጁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን።

2 ሰዎች በአዳም መተላለፍ ሳይሆን፣ በኃጢአታቸው እንደሚጠየቁ እናምናለን።

3 ሰዎች ሁሉ፣ በወንጌል ህግጋት እና ሥርዓቶች በመታዘዝ፣ በክርስቶስ የኃጢአተ ክፍያ አማካኝነት እንደሚድኑ እናምናለን።

4 የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መርሆች እና ሥርዓቶች፥ አንደኛ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን፤ ሁለተኛ፣ ንስኃ፤ ሶስተኛ፣ ለኃጢአተ ሥርየተ ውሃ ውስጥ በመጥለቀ መጠመቀ፤ አራተኛ፣ እጅን በራስ ላይ በመጫን መንፈስ ቅዱስን መቀበል መሆናቸውን እናምናለን።

5 አንድ ሰው ወንጌልን ለመስበክ፣ ሥርዓቶችን ለማከናወን ሥልጣን ባላቸው ሰዎች፣ በትንቢት እና እጅን በራስ ላይ በመጫን በእግዚአብሔር መጠራት እንዳለበት እናምናለን።

6 በጥንቷ ቤተክርስቲያን እንደነበረው አመሰራረት፥ በሐዋሪያት፣ በነቢያት፣ በፓስተሮች፣ በአስተማሪዎች፣ በወንጌላዊያን እና በመሳሰሉት እናምናለን።

7 በልሳን፣ በትንቢት፣ በራዕይ፣ በመገለጥ፣ በመፈወስ፣ ልሳንን በመተርጎም እና በመሳሰሉት እናምናለን።

8 መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል እስከተተረጎመ ድረስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እናምናለን፤ እንዲሁም መጽሐፈ ሞርሞን የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እናምናለን።

9 እግዚአብሔር የገለጠውን ሁሉ፣ አሁንም የሚገልጠውን ሁሉ እናምናለን፣ እናም የእግዚአብሔርን መንግሥት በተመለከተ እርሱ ወደ ፊትም ብዙ ታላቅ እና ጠቃሚ ነገሮችን እንደሚገልጥ እናምናለን።

10 በእስራኤሎች ዳግም መሰባሰብ እና በአሥሩ ነገዶች መመለስ፤ ጽዮን (አዲስቷ ኢየሩሳሌም)። በአሜሪካን አህጉር እንደምትገነባ፤ ክርስቶስ እራሱ በምድር ላይ እንደሚነግስ፤ እናም መሬት እንደምትታደስ እና ገነታዊ ክብርን እንደምትጎናጸፍ እናምናለን።

11 ህሊናችን በመራን መሠረት ሁሉን ቻይ የሆነውን እግዚአብሔርን የማምለክን መብት እንደግፋለን፣ እናም ለሰዎች ሁሉ፣ በፈለጉበት ቦታ ወይም እንደፈለጉት እንደቻሉት ያመልኩት ዘንድ ይህንኑ መብት አንቃወምም።

12 ለነገስታት፣ ለፕሬዚዳንቶች፣ ለገዢዎች፣ እና ለህዝብ ባለሥልጣናት በመታዘዝ፣ ህግን በማክበር፣ በመደገፍ እናምናለን።

13 ታማኝ፣ እውነተኛ፣ ንጹህ፣ በጎ አድራጊ፣ ለጋስ እና ለሰዎች ሁሉ መልካምን በማድረግ እናምናለን፤ በእርግጥም የጳውሎስን ተግሳጽ እንከተላለን እንላለን . . . ሁሉንም ነገሮች እናምናለን፣ ሁሉንም ነገሮች ተስፋ እናደርጋለን፣ ብዙ ነገሮችን ተቋቁመናል፣ እናም ሁሉንም ነገሮች ለመቋቋም ተስፋ እናደርጋለን። ልግስና፣ ተወዳጅ ወይም ስመጥሩ፣ ወይም መልካም ነው የሚባልለት ካለ እነዚህን ነገሮች እንከተላለን።

ዮሴፍ ስሚዝ

# መዝሙር



# ባርኮትህን ቁጠር

*በድምቀት* ♩ = 80–96




r. m: f. s | t. l: s. f | m: r | d:—
tₗ. d: r. m | s. f: m. r | d: tₗ | d:—
እና ም፡ ትደ ነቃ ለ ህ፡ በአ ምላ ክ፡ ሥ ራ።
እና ም፡ በ ዘ መ ንህ፡ ት ዘ ም ሬ ለህ።
ዋጋ ህ ን ም፡ በሰ ማይ፡ በ መ ኖ ሪ ያህ።
ለት ዘህም፡ ፍፃ ሚ፡ ይሰ ጡህ፡ መ ጽ ና ና ት።
s. s: s. s | s. s:—. | s. s: f. f | m:—
sₗ. sₗ: sₗ. sₗ | sₗ. sₗ:—. | sₗ. sₗ: sₗ. sₗ | d:—
s:— .s | d'. s: s. m | f: f | f:—
m:— .m | m. m: m. d | r. d: tₗ. lₗ | sₗ:—
ባር ኮ ት ህን፡ ዘር ዝር፡ በ ተ ሬ።
ባር ኮት ህን ቁ ጠር፡ ዘር ዝር፡ በ ተ ሬ።
d'. d': d'. d' | s. s:—. | s. s: s. s | s:—
d. d: d. d | d. d:—. | sₗ. sₗ: sₗ. sₗ | sₗ:—
f:— .s | t. l: s. f | m: f | s:—
r:— .m | s. f: m. r | d: r | m:—
አይ ተህ፡ ተ ገን ዘብ፡ የር ሱን፡ ሥ ራ፡
አይተህ፡ ተ ገን ዘብ፡ የር ሱን ታምር፡ ሥራ፡
s. s: s. s | s. s:—. | s. s: s. s | d':—
sₗ. sₗ: sₗ. sₗ | sₗ. sₗ:—. | d. d: d. d | d:—




ጽሑፍ፡-ጆሀንሠን ኦአትማን፤ ጀአር፡ 1856–1922
ዜማ፡-ኤድዊን ኦ. ኤክሴል፤1851–1921

ትምህርት እና ቃልኪዳን 78፡17–19
አልማ፡- 34፡38

# ኑ፤ ኑ፤ እናንተ ቀዱሳን

*በእምነት* ♩ = 66–84







*ፅሁፍ፡-* ዊልያም ክሌይቶን፤ 1814–1879
*ዚማ፡-* የእንግሊዝ ህዝብ መዝሙር

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 61፡36–39
ትምህርት እና ቃል ኪዳን 59፡1–4

# ኑ፤ እናንተ የጌታ ልጆች

*በፍንደቃ* ♩ = 96–112






*ጽሁፍ፦* ጀምስ ኤች ዋሊስ፤ 1861–1940
*ዜማ፦* የስፔይን ዜማ፤ በቤንጃሚን ካር፤ 1768–1831 ተዘጋጀ

ትምህርት እና ቃልኪዳን 133፥25፥33፥56
የዮሐንስ ራዕይ 7፥9–17

# የእስራኤል አዳኝ


በእርግጠኝነት ♩ = 84–100
Key of D
1. የእ ስራ ኤል፡ አ ዳ ኝ፤ የእኛ፡ ብ ቻ፡ ደ ስታ፤ የም
2. ይ መ ጣ ል፡ ሊሰበ ስብ፡ በ ጎ ቹ ን ም፡ ሊ
3. ምን፡ ያህል፡ ተ ን ከራ ተትን፡ በ ኃ ጢ አ ት፤ በ
4. እን ደ፥ፅ ዮ ን፡ ል ጆች፤ የም ስ ራች፡ ለ እኛ፡፡ ም
ንጠ ራ ህ፡ ለበ ረ ከ ት፤ በ ቀ ን፡ ጥላ ችን፡ በ ለ
መሬ ቸው፡ ወ ደ፥ፅ ዮ ን፤ ለ ም ን ስ፡ በሞ ት፡ ሸ
በረሃ፡ ወደ፡ አንተ፡ አለ ቀስ ን! ጠ ላት ም፡ ተ ደሰተ፡ ሲ ያይ
ል ክትም፡ ቀ ድ ሞ፡ ታ የ፡፡ አት ፍሩ፤ ቀ ን፡ ሁኑ፤ መ ን




5. የፊትህን፡ ብርሃን፤
   መልስ፡ አዳኜ፤
   ለነፍሴ፡ መፅናናትን፡ ስጥ፤
   ጣፋጭ፡ ናፍቆቴ፡
   ለቅዱስ፡ ቦታህ፡ ይሁን፡
   ላዘነውም፡ ልቤ፡ አምጣ፡ ተስፋን፡፡

6. ሲመለከት! አዕላፍ
   መላዕክት፡ ተደሰቱ፤
   ብዙዎችም፡ ቃሉን፡ ጠበቁ፤
   ሲናገር! ሕያውነት፤
   በድምጹ፡ ተሞላ፤
   ተስተጋባ፡ የጌታ፡ ውዳሴ።

*ጽሁፍ፡-* ዊሊያም ደብሊው ፊሊፕስ፤ 1792–1872፤ ከዮሴፍ ስወይን ተወሰደ
እና ተለወጠ፤ 1761–1796 በመጀመሪያው © IRI የመዝሙር
መጽሐፍ፤ በ1835 ተጠቃለለ
*ዜማ፡-* ፍሪማን ሊዊስ፤ 1780–1859

ኦሪት ዘፀአት 13፡21–22
አንደኛ ኔፊ 22፡12

# እንዴት ጽኑ መሰረት ነው

*በክብር* ♩ = 100–112









4. በጥልቁም ውኃ ላይ እንድትሔድ ጠርቼሃለሁ፣
 አስጨናቂ ወንዞች አያሰጥሙህም
 ከአንተ ጋር ስለሆንኩ፣ በመከራህ ልባርክህ፣
 እቀድስሃለሁ፣ እቀድስሃለሁ፣
 እቀድስሃለሁ፣ በጥልቁ፡ ጭንቀህ፡

5. በመከራ እሳትም መንገድ እከፍትልሃለሁ፣
 ፀጋዬም፣ አስፈላጊው ሁሉም፣ ይሞላልሃል።
 ነበልባልም አይጎዳህም፣ እኔ ብቻ አቀድልሃለሁ
 ዝገትህን ላቃጥል፣ ዝገትህን ላቃጥል፣
 ዝገትህን ላቃጥል ወርቅህን ላጠራ።

6. በእርጅናቸውም ቢሆን፣ ሕዝቦቼ ያውቃሉ፣
 ክብሬ ዘለዓለማዊ፣ እንደማይለወጥ፣
 በሽምግልናቸው አድሳቸዋለሁ፣
 ገና እንደ ጠቦት፣ ገና እንደ ጠቦት፣
 ገና እንደ ጠቦት በእቅፌ ይሆናሉ።

7. በኢየሱስ ታምኖ የተጠጋን ነፍስ
 በምንም አይነት፣ ለጠላቱ አልተወውም
 ያንን ነፍስ ሲኦል ቢያንቀጠቅጠውም።
 በፍጹም፣ በፍጹም፣ በፍጹም፣ በፍጹም
 በፍጹም፣ በፍጹም እኔ አልረሳውም።

ተጻፈ ተብሎ የሚታሰበው በሮበርት ኪን፣ በ1787 ገደማ በመጀመሪያው
© IRI መዝሙር መጽሐፍ ተጠቃለለ
የዜማ ደራሲ ተብሎ የሚታሰበው ጄ.ኤሊስ፣ በ1889 ገደማ

ትንቢተ ኢሳይያስ፡- 41፥10፣ 43፥2–5
ሔለማን፡- 5፥12

# ሁልጊዜ እሻካለሁ

*በሞቀታ* ♩ = 60–72






ፅሑፍ፡- አን፡ኤስ፡ ሐውክስ፤ 1835–1918
ዜማ፡-ሮበርት፡ ሎውሪ፡ 1826–1899

2 ኔሬ 4፥16–35
መዝሙረ ዳዊት 143፥1

# ጣፋጭ ስራ ነው

*በጋለ* መንፈስ ♩ = 84–96






5. ኀጢአት፣ ክፉ ጠላቴ የነበረ፣
አይኖቼን ዳግም አያስለቅስም
ውስጣዊ ጠላቶቼ ይሞታሉ፣
ሰይጣንም ሰላሜን አይሰብርም፡፡

6. አያለሁም እሰማለሁም
የተመኘሁትንና የፈለግኩትንም
እያንዳንዱ ያገኛ ጣፋጭ ስራ
በዘለዓለማዊው ደስታ፡፡

ጽሁፍ፡-ይስሐቅ ዋትስ፣ 1674–1748
ዜማ፡-ዮሐንስ ጄ ማክ ክሊላን፣ 1874–1925

መዝሙረ ዳዊት 92፡1–5
መፅሐፈ ሂኖክ 1፡27

# የዮሴፍ ስሚዝ የመጀመሪያ ፀሎት







ጽሁፍ፡- ጆርጅ ማንዋሪንግ፤ 1854–1889
ዜማ፡- ሲልቫነስ ቢሊንግስ ፖንድ፤ 1792–1871፤ የተሰማማው
በኤሲ ስሚዝ፤ 1840–1909

የዮሴፍ ስሚዝ ታሪክ 1፡14–20፡25
የያዕቆብ ወንጌል 1፡5

# ሁላችንም እንቀጥል

*በብርታት* ♩ = 92–108




:t: .t | d': m: .f: m: f. r | d:—: d: :
:f: .f | m: d: .d: d: tı | d:—: d: :
ታ ላቁ ን፡ የእው ነት፡ ሰይፍ።
ለ ብ ሩ ህ፡ እውነት፡ ዓ ላማ፡፡
የእ ውነ ትን፡ ዓላማ፡ ያበ ለፀጋል።
s: .s | s: d': .d': d'. s: s. f | m:—: m: :
r: .r | d: l: .l: s: sı | d:—: d: :
r':—: t: t: .l | s: .fe: s: .l: s: :
f: f: f: .f: f: .f | m: .re: m: .f: m: s: .s
አት ፍሩ፤ ጠ ላ ት ም፡ ቢ.ያ ፌዝ፤
አን ፍሬ፤ እንበ ርታ፤ ጠ ላ ት ም፡ ቢ.ያ ፌዝ፤ ባለ ድ
t: t: r': .r': s: .t | d': d': .d': d': s: .s
s: s: s: .s: s: .s | d: d: .d: d: s: .s
m':—: d': t: .d' | r': .d': t: .l: s: s: .s
m: s: m: .s: f: .m | f: .f: f: .f: f: r: .f
እንበ ርታ፤ ጌታ፡ ከእ ኛ፡ ጎ ን፡ ስላ ለ። ከ ፋ
ል፡ እን ሆ ናለን፤ ጌታ፡ ከእ ኛ፡ ጎ ን፡ ስላ ለ። ከፋ ዋ
d': d': s: .s: s: .s | t: .l: s: .l: t: t: .t
d: d: d: .m: r: .d | s: .s: s: .s: s: s: .s




ጽሑፍ እና ዜማ፡-ኢቫን ስቲፈንስ፤ 1854–1930

ትምህርት እና ቃልኪዳን 6፥33–37
አንደኛ ኔፊ 22፥15–17

# እግዚአብሔር፤ አባታችን፤ ፀሎታችንን ስማን




ጽሁፍ፡-አኒ፡ ፒኖክ፡ ማሊን፤1863–1935
ዜማ፡-ሉዊስ፡ ኤም ጉትስላክ፤1829–1869፤
በኤድዊን ፒ ፓርከር 1836–1925 ተስማማ

ትምህርት እና ቃልኪዳን 59፡9–12
2 ኔፊ 10፡24–25

# እነሆ ታላቅ አዳኝ ሞተ






5. ሞተ፤ በአሰቃቂ ትርዒት
ፀሐይም አነሳች ብርሃኗን!
ፍጥረታትም ሁሉ አሉ፤
ፍጥረታትም ሁሉ አሉ፤
በስጋት መልስ፤ "እግዚአብሔር ሞተ!"

6. ሕያው ነው ሕያው ነው። በትሕትና
ሰገድን፡ በተቀደሱት ምልክት፡ ዙሪያ፤
ፈለግን፤ እንደኋለኛው ቀን ቀዱሳን፤
ፈለግን፤ እንደኋለኛው ቀን ቀዱሳን፤
በማወደስ፡ ለመኖር፡ ፈቃዱንም፡ ለማድረግ።

ጽሑፍ፡- ኤሊዛ፡ አር፡ ስኖው፤ 1804–1887
ዜማ፡- ጆርጅ፡ ከርለስ፤ 1839–1932

ትምህርት እና ቃልኪዳን 18፥11
የሉቃስ ወንጌል 22፥42፤ 23፥46

# ዘላለማዊ፡ አባት፤ እግዚአብሔር፤ ሆይ

*በአምልኮ* ♩ = 69–84







ጽሑፍ፡- ዊሊያም ድብሊው ፊሊፕስ፤ 1792–1872
1835 በመጀመሪያው © IRI የመዝሙር መጽሐፍ ተጠቃለለ
ዜማ፡-ፊሊክስ ሜንድልስሆን፤ 1809–1847


ትምህርት እና ቃልኪዳን 20፥77፤ 79
ትንቢተ ኢሳይያስ 53፥2–5

# እንዴት ታላቅ ጥበብና ፍቅር ነው

*በእርጋታ* ♩ = 66–76






5. ስጋውን፡ እንዲያስታውሰን
ህብስቱን፡ እንበላለን፤
በክርስቶስ፡ ያለንን እምነት
ከፅዋውጋ፡ እንመስክር

6. እንዴት፡ ታላቅ፡ ፍጻሜ፡ ነው
የቤዛችን፡ አላማ፤
ቀንነት፡ እና፡ ምህረት
በፀጋ፡ የታዩበት፡፡

ፅሁፍ፡- ኤሊዛ፡ አር፡ ስኖው፣ 1804–1887
ዜማ፡- ቶማስ ማክኢንታየር፣ 1833–1914
ምዕራፍ 1፣ 2፣ 5 እና 6፣ በተለይ፡ ለቅዱስ ቁርባን የሚስማሙ፡ ናቸው፡፡

መጽሐፈ ሙሴ 4፥1–2
አልማ 42፥14–15

# በመደነቅ ቆሚያለሁ

*በትኩረት* ♩ = 66–84






ጽሑፍ፡ እና፡ ዜማ፡-ቻርለስ ኤች ገብርኤል፤ 1856–1932

ሞዛያ፡-3፥5–8
የዮሐንስ፡ ወንጌል 15፥13

# በትህትና፤ አዳኛችን



በየዋህነት ♩ = 72–84
Key of F
1. በ ት ህ ት ና፤ አዳ ኛች ን፤ መን ፈ
2. በም ህ ረ ት፡ ሙላው፡ ልባ ች ንን፤ አስተ ምረን፡
ስህ ን፤ ስጠ ን፤ ስን ፀልይ ስን ባር ክ፡ ሕብ
ት ዕ ግስ ትን፡ እና፡ ፍቀርን። ፀሎ ታች ን፡ ይቀ
ስቱ ን፡ እና፡ ውሃ ው ን፡ በቀ ዱስ፡ ቀ ን፡ በስ ም ህ፡፡
ረ ብ፡ ወደ፡ አን ተ፡ በ ቀ ዱ ሱ፡ መን ግ ስትህ፡፡




ፅሑፍ፡- ሚብል ጆንስ ጋብት፤ 1910፤ ተወለደ © 1948 IRI
ዜማ፡- ሮውላንድ ኤች፡ ፕሪቻርድ፤ 1811–1887

ሁለተኛ ኔፊ 2፡7
ትምህርት እና ቃልኪዳን 59፡9

# ኢየሱስ፤ ትሑቱ፡ ያኔ፡ የተወለደው




ጽሁፍ፡- ፓርሊይ፡ ፒ.ፕራት፤ 1807–1857
ዜማ፡- ጊያኮም ማይርቢር፤ 1791–1864፤ ተስማማ

የሉቃስ ወንጌል፡- 2፡7
የማቴዎስ ወንጌል፡- 25፡31

# በርቀት ለምለም ኮረብታ አለ

*በአክብሮት* ♩ = 72–84




ፅሁፍ፡- ሲስል፡ ፍራንስስ፡ አሌክሳንደር፤ 1818–1895
ዜማ፡- ዮሐንስ፡ ኤች ጋወር፤ 1855–1922

የዮሐንስ ወንጌል፡- 19፡16–20
ወደ ዕብራውያን፡- 13፡12

# እንዘምር ለኢየሱስ ምስጋና





ጽሑፍ፡- ሪቻርድ ኦልድሪጅ፤ 1815–1896 — ኔሬ 9፡5፤10–12
ዜማ፡- ዮሴፍ ኮስሌት፤ 1850–1910 — መጽሐፈ ሙሴ 4፡20–21

# የእግዚአብሔር መንፈስ

*በፍንደቃ* ♩ = 96–112




መ ላ እ ክ ት ም፡ ም ድ ር ን፡ ይጎ በኛ ሉ።
የ ም ድ ር ም፡ ሽ ፋ ን፡ ይ ሰ ነ ጣጠ ቃል።
በ እ ም ነ ታ ች ን ም፡ እ ን ወ ርሳ ለን።
ኢ የ ሱ ስ ም፡ ሲ ወ ር ድ፡ በእ ሳት፡ ሰረ ገላ።
እን ዘ ምር፡ ሆ፡ እን በል፡ ክሰ ማይ፡ ሰራ ዊ ት፡ ጋ ር፤
ሆ ሳዕ ና፤ ሆ ሳ ዕና፡ ለ አብ፡ እና፡ ወ ልድ!







ጽሑፍ፡- ዊሊያም ደብሊው ፍሊፕስ፤ 1792–1872 በመጀመሪያው
© IRI የመዝሙሩ መጽሀፍ፤ 1835 ተጠቃለለ። በ1836 በኪርትላንድ
ቤተመቀደስ የምረቃ ስነ ስርዓት ተዘምሯል።

ትምህርት እና ቃልኪዳን፤ 109፥79–80
ትምህርት እና ቃልኪዳን፤ 110

# ከፍ ካለው ተራራ አፋፍ

*በቆራጥነት* ♩ = 56–72











ፅሁፍ፡- ኢዮኤል ኤች ጆንሰን፤ 1802–1882
ዜማ፡- አቤኔዘር ቢሳሊይ፤ 1840–1906

ትንቢተ ኢሳይያስ 2፡2–3
ትንቢተ ኢሳይያስ 5፡26

# ኦ፤ በል እውነት ምንድን ነው?







ጽሑፍ፡- ዮሐንስ ጃኩስ፣ 1827–1900
ዜማ፡ ኤለን ኖውልስ ሚሊንግ፣ 1820–1905

ትምህርት እና ቃልኪዳን 93፡23–28
የዮሐንስ ወንጌል 18፡37–38

# እግዚአብሔር ሆይ፤ ስለ ነቢይ እናመሰግንህ






ፅሁፍ፡- ዊልያም ፎውለር፣ 1830–1865
ዜማ፡- ካሮላይን፡ ሺሪዳን፡ ኖርተን፤ 1808–1877 ገደማ

ትምህርት እና ቃልኪዳን 21፡1–5
ሞዛይ 2፡41

# አዳኜ እንዳለ አውቃለሁ

*ሰላም በሞላበት* ♩ = 72–84






ጽሁፍ፡- ሳሙኤል መድሊይ፣ 1738–1799
በመጀመሪያው © IRI መዝሙር መጽሐፍ በ1835፣ ተጠቃለለ
ዜማ፡- ሊዊስ፡ ዲ፡ ኤድዋርድስ፡ 1858–1921

መጽሐፈ ኢዮብ፡ 19፡25
መዝሙረ ዳዊት 104፡33–34

# አምላክ ከእናንተ ዘንድ ይሁን እስክንገናኝ እንደገና

*በአክብሮት* ♩ = 66–80






ጽሑፍ፦ ኤርሚያስ ኢራንኪን፤ 1828–1904
ዜማ፦ ዊሊያም ጂ. ቶመር፤ 1833–1896

ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች፡ 2። 3፡16
ዘኁልቁ 6፡24–26

# አባቴ ሆይ

*በጋለ ስሜት* ♩ = 42–56






ጽሁፍ፡- ኤሊዛ አር. ስኖው፤ 1804–1887
ዜማ፡ ጀምስ ማክግራንሀን፤ 1840–1907

ወደ ሮሜ ሰዎች 8፡16–17
የሐዋሪያት ስራ 17፡28–29 (22–31)

# መልካምን አድርጉ


በቆራጥነት ♩ = 96–116
Key of G
1. መል ካ ምን፡ ሥሩ፤ ቀኑ፡ እየ ሮ ጠ፡ ነ ው።
2. መል ካ ምን፡ ሥሩ፤ እስ ራታ ችን፡ ይ ፈታ ል።
3. መል ካ ምን፡ ሥሩ፤ በእም ነት፡ ተሞ ሉ፡ አት ፍሩ።
የወደ ፊቱ ን፡ ብር ሀን፡ ነፃ ነትን፡ እያ ያ ችሁ።
የባ ርነ ት፡ ቀን በር፡ ከእ ንግ ዲህ፡ አይ ታይም፤
ግቡ፡ እየ ታየ፡ ነው፡ ወደ፡ ፊ ት፡ ቀ ጥ ሉ።
መ ላ እ ክት፡ ከ ላይ በፀ ጥታ፡ ያዩ ና ል።
በ ተስ ፋ፡ ተሞሉ፤ የሚ ያስ ጨን ቁን፡ ያቀ ማ ሉ።
የረ ጠበ ው፡ ዓይን፡ ከእ ንግ ዲህ፡ አያ ነ ባ ም።


d:— .tₗ: lₗ | sₗ: d: m | r:— .d: r | d:—:—
lₗ:— .sₗ: fₗ | mₗ: mₗ: sₗ | fₗ:— .mₗ: fₗ | mₗ:—:—
የምና ደርገውን፡ ስለ ዚህ፡ መ ል ካ ም፡ ሥ ሩ!
አው ነት፡ ይቀ ጥላል፡ ስለ ዚህ፡ መል ካምን፡ ሥ ሩ!
መል ካምን፡ ስ ሩ፡ ትባ ረ ካ ላ ች ሁ!
dˡ:— dˡ: dˡ | dˡ: dˡ: dˡ | t:— .dˡ: t | dˡ:—:—
f:— .f: f | d: d: d | s:— .s: s | d:—:—
sₗ: sₗ: sₗ | lₗ: sₗ: sₗ | sₗ: sₗ: sₗ | lₗ: sₗ:—
mₗ: mₗ: mₗ | fₗ: mₗ: mₗ | mₗ: mₗ: mₗ | fₗ: mₗ:—
መል ካ ምን፡ ስሩ፤ ው ጤቱ፡ ይ ከ ተ ላ ችሁ።
dˡ: dˡ: dˡ | dˡ: dˡ: dˡ | dˡ: dˡ: dˡ | dˡ: dˡ:—
d: d: d | d: d: d | d: d: d | d: d:—
sₗ: d: m | s: m: d | tₗ. r:—. feₗ | sₗ:—:—
mₗ: mₗ: sₗ | sₗ: sₗ: sₗ | sₗ. feₗ:—. rₗ | rₗ:—:—
ለነ ፃነ ት፡ ተዋ ጉ፡ በመን ፈስና፡ በ ዛ ይል፤
dˡ: dˡ: dˡ | mˡ: dˡ: mˡ | rˡ. dˡ:—. dˡ | t:—:—
dˡ: dˡ: dˡ | dˡ: dˡ: d | r. r:—. r | s:—:—




ጽሁፍ፡- አኖን፣ የዳዊት መዝሙሮች ሕይወት፣ ቦስትን፣ 1857
ዜማ፡- ጆርጅ ኪልማርክ፣ 1781–1835

ኦሪት ዘዳግም፡- 6፥17–18
ሖለማን፡- 10፥4–5

# አሁን እንደሰት


በደስታ ♩ = 100–120
Key of D
1. አ ሁን፡ እ ን ደ ሰ ት፡ በደ ህ ንነ ት፡ ዘመ ን።
2. እር ስ፡ በእ ርሳ ችን፡ እን ፋቀ ር፡ ሐሰ ትም፡ አይ ኑ ር፤
3. በያ ህዌ፡ ክ ን ድ፡ ላይ፡ በእ ም ነት፡ እን ኖሬ ለ ን፡
ከእ ንግ ዲ ህ፡ በም ድር፡ ላይ፡ አን ከ ራተ ትም።
ክፋ ት ን፡ አ ቁመ ን፡ ሁሌም፡ አን ድ፡ እን ሁን።
በእ ነዚ ህ፡ በመ ጨረ ሻ፡ መከራ፡ ዘመ ን፡ እንዲ መራን፤
ለእኛም፡ ለ ሁሉም፡ ሐ ዝ ብ፡ የ ምሥ ራች፡ ይ ሰማ ል፤
ክፉ ዎች፡ ሲ ፈ ሩ፡ እ ና፡ ሲ ር በ ተ በ
መከሩ፡ እና፡ መ ቀ ሰ ፍ ቱ፡ ካ ለ ፈ፡ በኋ ላ፤


:s | d':— .t: l: .s | l:—: s: .s | s: l: t | d':—
:d | m:—: f: .m | f:—: m: .m | m: f: f | m:—
በ ቀር ቡ፡ የመ ዳን፡ ጊ ዜ፡ ይ መ ጣ ል፤
ቱ፤ እኛ፡ አ ዳ ኛች ን ን፡ እን ጠብ ቃ ለን፤
አዳ ኛችን፡ ሲመ ጣ፡ ከቀ ኖች፡ ጋር፡ እን ነሳ ለ ን።
:m | s:—: d': .d' | d':—: d': .d' | d': s: s | s:—
:d | d:—: d: .d | f:—: s: .s | s: s: s, | d:—
:s | s:—: fe: .s | l: s:— .s | s:—: fe: .s | l: s
:d | d:—: d: .d | d: d:— .d | d:—: d: .d | d: d
የተ ገባ ው ን፡ ቃል፡ ኪዳ ን፡ ቀዱ ሳን፡ ሲቀ በ ሉ፤
የተ ገባ ው ን፡ ቃል፡ ኪዳ ን፡ ቀዱ ሳን፡ ሲቀ በ ሉ፤
የተ ገባ ው ን፡ ቃል፡ ኪዳ ን፡ ቀዱ ሳን፡ ሲቀ በ ሉ፤
:m | m:—: re: .m | f: m:— .m | m:—: re: .m | f: m
:d | d:—: d: .d | d: d:— .d | d:—: d: .d | d: d
:s | s: f: f | f: m: m | m: r: r | r:—: m: .r
:d | r: r: r | r: d: d | d: t,: t, | t,:—: t,
ከ ጠዋት፡ እ ስከ፡ ማታ፡ ሳ ይታ ወኩ፡ ይ ው ላሉ፤ ምድር፡
ከ ጠዋት፡ እ ስከ፡ ማታ፡ ሳ ይታ ወኩ፡ ይ ው ላሉ፤ ምድር፡
ከ ጠዋት፡ እ ስከ፡ ማታ፡ ሳ ይታ ወኩ፡ ይ ው ላሉ፤ ምድር፡
:m | s: s: s | s: s: s | s: s: s | s:—: s: .f
:d | t,: t,: t, | d: d: d | s: s: s | s:—: s,




ጽሑፍ፡- ዊሊያም ድብሊው ፊሊፕስ፣ 1792–1872
በ1835፣ በመጀመሪያው © IRI የመዝሙር መጽሐፍ ተጠቃለለ፡፡
ዜማ፡- ሔነሪ ተከር፣ በ1863 ገደማ


መጽሐፈ ሙሴ፡- 7፥61–67
አስረኛው የእምነት አንቀጽ

# እሔዳለሁ እንድሔድ የምትፈልግበት

*በቀራጥነት* ♩. = 48–58




ግ ን፤ በ ት ንሹ፤ ድም ፅ፡ ቢጠ ራኝ፡ ወደ
አዳ ኜ፡ሆ ይ፤ መ ሪ ዬ፡ ብ ት ሆ ን፤ ብ
ሁለ ንተ ናዬ፡ ባ ንተ፡ እ ንዲ ታ መ ን፤ በማ
ማላ ውቀ ው፡ መን ገ ድ፤ አመ ለ ሣለሁ፤ ጌ ታ፤ አጆ ን፡
ርቱ፡ መን ገ ድ፡ ቢሆ ንም፤ ጣፋ ጩን፡ መልዕ ክ ት፡
ወ ቀ፡ እንደ ምት ወደ ኝ፤ ፍቃ ድህን፡ ላድ ርግ፡ በ
በአንተ፡ አድ ርጌ፤ እሄ ዳለ ሁ፡ ል ሄ ድ፡ የም ትፈ ልግበት።
ድም ጼ፡ ያስተጋባ፤ እላ ለ ሁ፡ እን ድ ል፡የ ምት ፈል ገውን።
ቅን፡ ል ቤ፤ እሆ ናለ ሁ፡ እን ድ ሆን፡ የም ትፈ ልገውን።




ጽሑፍ፡- ሜሪ ብራውን፤ 1856–1918
ዜማ፡- ካሪ ኢ. ሮውንስፌል፤ 1861–1930

አንደኛ ኔፊ 3፡7
ትምህርት እና ቃል ኪዳን 4፡2

# ውዳሴ ለሰው



በብርታት ♩ = 76–96
Key of C
1. ውዳሴ፡ ከ ያ ህዌ፡ ለ ተ ነጋ ገ ረው፡ ሰ ው!
2. ውዳሴ፡ ለ ት ዝታ ው፤ ሞ ተ፡ እን ደ፡ ሰማዕ ታት፤
3. ክብ ሩ፡ ታ ላ ቅ፡ ክህ ነ ቱ፡ ወሰ ን፡ የ ለሽ።
4. መስ ዋዕ ትነት፡ ያመ ጣ ል፡ የሰማ ይን፡ በ ረከ ት፤
ኢየ ሱስ፡ ባ ለ፡ ራ ዕ ዩ ን፡ ቀባ ው።
ይባ ረክ፡ ይ ከበ ርም፡ የም ን ጊ ዜም፡ ስሙ!
ዘለ አለም፡ ለ ዘለ አለም፡ ለሚ ይዘው፡ ቁ ል ፍ።
ምድ ርም፡ ት ዋዥ፡ ለ እዛ፡ ሰ ው፡ ደ ም።
ተባ ረክ፡ የ ኋለ ኛውን፡ ዘመ ን፡ ለ መ ክ ፈት፤
በከ ዛ ዲ ዎች፤ የፈ ሰ ሰ ው፡ ደ ሙ ም፡
በታ ማ ኝ ነቱ፤ ገ ባ፡ ወ ደ፡ መ ንግ ስቱ፤
ዓለ ም፡ ተ ነፃ፡ ለ ፍ ት ህ ም፡ ትግ ል።


ነገ ስ ታ ት ም፤ ሕዝ ቦ ችም፡ ያሞ ግሱት፡
ይማፀን፡ ወ ደ፡ ላይ፡ ምድ ር፡ ስ ትመ ሰክ ር።
ዘውዱ ን፡ ደ ፋ፡ በ ነ ቢያ ት፡ መዛ ከል፡፡
ዳ ግም፡ ያው ቁታል፡ ወ ን ድም፡ የ ሴ ፍን፡፡
አልልታ፡ ለ ነ ቢ ዩ፤ ወ ደ፡ ላ ይ፡ አ ረ ገ!
ከሐ ዲዎች ና፡ ዛይ ለኞች፡ በከ ንቱ፡ ተ ዋ ጉት።




ፅሁፍ፡- ዊልያም.ደብሊው ፊሊፕስ፤ 1792–1872
ዜማ፡-የስኮቲሽ ህዝብ መዝሙር

ትምህርት እና ቃልኪዳን 135

# መፀለይ አስበሃል ወይ?

በተመስጦ ♩ = 72–88






ፀሁፍ፡-ሚሪ፡ ኤ. ፒፐር፡ኪደር.፤ 1820–1905
ዜማ፡- ዊልያም፡ ኦ. ፐርኪንስ፤ 1831–1902

መዝሙረ፡ ዳዊት፡5፡3፤12
የማርቆስ፡ ወንጌል፡ 11፡24–25

# ፍቅር በቤት (ቤተሰብ፤ ቤት)






ጽሁፍ እና ዜማ፤ ዮሐንስ ማክናውተን፤ 1829–1891

መጽሐፈ ሞዛይ 4፡14–15
መጽሐፈ መክብብ 9፡9

# ሩቅ፤ ሩቅ ወዲያ በይሁዳ ሜዳ






ፅሑፍ፡-እና፡ ዜማ ዮሐንስ ሚንዚስ ማክፉርላን፤ 1833–1892


የሉቃስ ወንጌል 2፥8–20
ትምህርት እና ቃልኪዳን 45፥71

# ብፁዕ ሌሊት

*ሰላም በተሞላበት* ♩ = 80–100









ጽሁፍ፡- ዮሴፍ ሞሀር፤ 1792–1848 ትርጉም፡- በዮሐንስ ኤፍ ያንግ፤ 1820–1885 — የሉቃስ ወንጌል 2፣7–14

ዚማ፡- ፍራንዝ ግሩበር፤ 1787–1863 — አልማ 7፣10–12


# ክርስቶስ ጌታ ተነስቷል ዛሬ

*በፍንደቃ* ♩ = 96–108











ጽሁፍ፡-ቻርለስ ዌስሊ፤ 1707–1788
ዜማ አኖን፤ ሊራ ዴቪድካ፤ 1708

የማቴዎስ ወንጌል 28፥5–6
ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1፡፡ 15፥20፤ 53–57

# ተነስቷል!

*በክብር* ♩ = 92–104






ጽሁፍ፡- ሲሲል ፍራንሲስ አሌክሣንደር፤ 1818–1895
ዜማ፡ ጃቺሞ ኒአንደር፤ 1650–1680

የማርቆስ ወንጌል 16፥6–7
ሞዛያ 16፥7–9

# የልጆች መዝሙር

# የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ

*በጋለ ስሜት* ♩ = 80–96










ፅሁፍ፡- ናኦሚ ደብሊው ራንደል፤ ተወለደ በ1908፤ © 1957 IRI
ዜማ፡- ሚልድረድ ቲ ፐቲት፤ 1895–1977 © 1957 IRI

መዝሙረ ዳዊት 82፥6
መጽሐፈ ሞዛያ 4፥15
ትምህርት እና ቃልኪዳን 14፥7

# ያንን ጣፋጭ ታሪክ ሳነብ አስባለሁ

*በፍቀር* ♩ = 42–46 *(በሁለት ምቶች ልክ የሚመራ)*






ቃላት፡- ጀሚማ፡ ሉቃስ፤ 1813–1906
ዜማ፡ ሊህ አሽተን ላዩድ፤ 1894–1965

3 ኔፊ 17፡21–23
የሉቃስ ወንጌል 18፡16

# አባቴ እንዳለ አውቃለሁ

*በዕርጋታ* ♩ = 76–96




ፅሁፍ እና ዜማ፡- ሪድ ኤን። ኔብሊ. (የተወለደው) 1923
©(ቀጂው) 1969 IRI
በኦርጋን ሲጫወቱ መምሪያውን ብቻ ይጠቀሙ መርገጫ አይጠቀሙ

መጽሐፈ ሞሮናይ 10፡5
መጽሐፈ አብርሃም 3፡22–28

# አመሰግንሃለሁ፤ ውድ አባት






ጽሑፍ፡- አኖን
ዜማ፡- ጆርጅ ከርለስ፤ 1839–1932

ወደ ኤፌሶን ሰዎች 5፡20
መጽሐፈ አልማ 37፡36–37

# ደግነት በእኔ ይጀምራል

*በቀላሉ* ♩. = 60–69 *(በሁለት ምቶች ልክ የሚመራ)*





ጽሑፍ፡- እና ዜማ፡- ክላራ ደብሊው. ማክማስተር፤
1904–1997 ተወለደ ግልባጭ © 1969 IRI

የሉቃስ ወንጌል፡- 6፡31፤ 10፡30–37
ወደ ኤፌሶን ሰዎች፡ 4፡32

# መልካምን ለማድረግ ድፈር

*በልበ ሙሉነት* ♩. = 44–54 *(በሁለት ምቶች ልክ የሚመራ)*






ቃላት፡- አሮን
ዜማ፡- በኤ.ሲ. ስሚዝ፤ 1840–1909 ተዘጋጀ

የማቴዎስ ወንጌል፡- 4፥1–11
ወደ ኤፌሶን ሰዎች፡- 6፥1

# ጌታ ቤተ መቅደስ ስጠኝ

*በጣፋጭ* ♩ = 96–116






ጽሁፍ፡- ዳንኤል ሀንተር፤ ቢ፡ 1930 ቀጂው 1969 IRI
ዜማ፡- ዳርዊን ውልፎርድ፤ በ፡ 1936 ተወለደ ቀጂው 1969 IRI

ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች፡ 1። 3፤16–17
ትምህርት እና ቃልኪዳን 88፤27–29

# ወርቃማው ሰሌዳ




ጽሁፍ፡- ሮስ ቶማስ ግረሃም፤ 1875–1967
ዜማ፡-ጀ፡ ስፔንሰር ኮርንዎል፤1888–1983 © 1989 IRI

የዮሴፍ፡ ስሚዝ፡ ታሪክ 1፤51–53፤59

# በብርሃን መኀዝን አስተምረኝ




ጽሁፍና ሙዚቃ፡- ክላራ ድብሊው ማክ ማስተር የተወለደው፤ 1904–1997

© 1958 IRI የቀጂው መብት ታድሷል በ 1986።

ትንቢተ ኢሳይያስ 2፡5
ወደ ኤፈሶን 5፡8

# የቤተሰብ ጸሎት




ጽሁፍና ዜማ፡- ዲቪታ ሚፍሊን ፒተርሰን፤ የተወለደው በ1910–1996 © (ቀጂው)1969 IRI

ትምህርት እና ቃልኪዳን 59፥7
ሶስተኛ ኔፊ 18፥21

# መወቅ የሚገቡ ቃላቶች

**ኃላፊነት፥** በክህነት ሥልጣን ውስጥ ያለ የሥልጣን ደረጃ ነው። (ዲያቆን፣ አስተማሪ፣ ካህን፣ የመሳሰሉትን ይመልከቱ።)

**ሐዋሪያ፥** 1. በመልከጼዴቀ የክህነት ሥልጣን ውስጥ ያለ ሹመት ነው። 2. ከአስራ ሁለቱ የኢየሱስ ምስክሮች አንዱ ነው።

**ሊቀካህን፥** በመልከጼዴቀ ክህነት ውስጥ ያለ ሹመት ሲሆን ለመንፈሳዊ ነገሮች አስተዳደር ኃላፊ ነው።

**መስዋዕት፥** 1. በጥንት ዘመን፣ የሰማዩ አባታችንን ሕግ ለመጠበቅ ሲባል የእንስሳት እርድ ነበር። 2. በአሁኑ ወቀት ግን፣ ለእኛ ውድ የሆኑትን እንደ ግዜያችን፣ እና ሃብታችን ያሉትን ነገሮች አሳልፈን መስጠት ነው።

**መተሳሰር፥** ለዘለዓለም ባልና ሚስትን፣ ወይም ልጆችን ከወላጆቻቸው ጋር የሚያስተሳስር በቤተመቀደስ ውስጥ የሚከናወን ሥርዓት ነው።

**የሰለስቲያል መንግሥት፥** ከሰማዩ አባታችን ጋር ፃድቃን የሚኖሩበት እና እርሱ ያለውን ሁሉ የሚወርሱበት መንግስት ነው፡፡

**መንፈስ፥** ለአካል ሕይወትን የሚሰጥ ነው። የአካላችን ክፍል ሆኖ ከዚህ ህይወት በፊት የነበረና በኋላም በመኖር የሚዘልቀ ነው። በትንሳኤ መንፈስና አካል ዳግም ፍጹም ላለመለያየት ይገጣጠማሉ።

**መንፈስ ቀዱስ፥** የመንፈስ አካል ሆኖ አካላዊ ሰውነተ የሌለው እና ዓላማው የሰማዩ አባታችንና ኢየሱስ የሚሉትንና የሚያደርጉትን ለመመስከር ነው። የሰማዩ አባታችን መንፈስ ከእኛ ጋር ነው ስንል፣ የመንፈስ ቀዱስን ማለታችን ነው።

**መንፈሳዊ ሞት፥** ከሰማዩ አባታችን የመለየት ሁናቴ ነው።

**መንፈሳዊ ስጦታ በቤተመቀደስ፥** ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት የሚያስችል በቤተመቀደስ ውስጥ በሰማያዊ አባታችን የሚሰጥ በረከተ ነው።

**መፅሐፈ ሞርሞን፥** በአሜሪካን አህጉር ይኖሩ ለነበሩ ሕዝቦች የተሰጠ የሰማዩ አባታችንን ትምህርት የያዘ ቅዱስ መፅሐፍ ነው።

**ሚሲዮን፥** 1. በዓለም ውስጥ ቤተክርስቲያኑ የወንጌላዊ ሥራ የሚከናወንበት ወይም ይህን ለማድረግ ጥረት የሚደረግበት ክልል ነው። አብዛኛውን ጊዜ ዲስትሪክቶች በሚባሉ በትናንሽ ክፍሎች ይከፈላሉ። 2. ወንጌልን ለመስበክ ወይም አገልግሎትን ለማበርከት በቤተክርስቲያኑ መሪ የሚሰጥ ለተወሰነ ክፍለ ጊዜ ጥሪ ነው።

**ማጥመቅ፥** አንድን ሰው ውኃ ውስጥ መቀበርና ከዚያም ከውኃ ውስጥ በአዲስ ሕይወት እንዲኖር ማውጣት ነው። (ጥምቀትን ይመልከቱ።)

**ቴሬስቲያል መንግሥት፥** የክብር መንግስት አካል ሆኖ ደረጃው ከሰሌስቲያል መንግስት በታች የሆነ፣ ነገር ግን ከሳልሳዊ መንግስት በላይ የሆነ ነው። የሰማዩ አባታችን የሚፈልግባቸውን ሁሉንም ሥራ ላልሰሩ ለምድራዊ መልካም ሰዎች የተዘጋጀ ነው።

**ሰማይ፥** የሰማዩ አባታችን የሚኖርበት ሥፍራ ነው። አንዳንዴ ወደ ምድር ከመምጣታችን በፊት መንፈሳችን የኖረበት ቦታ፣ እና ከሞትም በኋላ የሚሄዱበትን የመንፈስ ዓለም ለማመልከት ይውላል። ደግሞም ጻድቃኖች ከትንሳኤ በኋላ ለዘለዓለም የሚኖሩበት ቦታ ስም የሰለስቲያል መንግስት ነው።

**ሰባዎች፥** በመልከጼዴቀ ክህነት ውስጥ ያለ ኃላፊነት ሆኖ ወንጌልን ለመስበክና ቤተክርስቲያኑን ለማስተዳደር ኃላፊነት የያዘ ነው።

**ቴሌስቲያል መንግሥት፥** ከሶስቱ የክብር መንግሥታት ዝቀተኛውና ሰዎች ከሞት ከተነሱ በኋላ የሚመደቡበት ነው። ይህ መንግሥት ለዋሾች፣ ለነፍሰገዳዮች፣ ለሌቦች እናም ለሌሎች ክፉ ሰዎች የተዘጋጀ ነው።

**ሥርዓት፥** ሥነሥርዓት ወይም በክህነት ሥልጣን ኃይል አማካይነት የሚከናወን ቅዱስ አከባበር ነው።

**ስቴክ፥** ቤተክርስቲያኑ ሙሉ በሙሉ በተደራጀበተ መልከአ ምድራዊ ክልል ውስጥ ያለ የአባላት ድርጅት ሆኖ፣ በተሾሙት የካህናት መሪዎች የሚተዳደር ነው። ዋርዶችና ቅርንጫፎች በሚባሉ በትናንሽ ክፍሎች ተከፋፍሏል።

**ራዕይ፥** አብዛኛውን ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት፣ ስለአለፉት፣ ስለወቀቱ፣ ወይም ስለወደፊቱ ሁናቴዎች ለመረዳት፣ ለሰው በሰማዩ አባታችን የሚሰጥ ጥበብ ነው።

**ሹመት፥** ብቃት ላለው ሰው በክህነት ሥልጣን ሹመት ውስጥ እጅን በራስ ላይ በመጫን ኃላፊነትን መስጠት ነው።

**ቃል ኪዳን፥** በሰማዩ አባታችንና በሰው መካከል የሚደረጉ ቅዱስ ቃል ኪዳኖች ናቸው።

**(ቄስ)፥** በመልከጼዴቅ ክህነት ውስጥ የመጀመሪያ ሹመት፣ የሆነ እና፣ ዕድሜያቸው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ብቃት ላላቸው ወንዶች የሚሰጥ ነው። አንዳንድ ሥርዓቶችን፣ ማለትም በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ በረከትን እንዲያደርጉ ሥልጣንን ይሰጣቸዋል፥

**ቅርንጫፍ፥** አነስተኛ ክፍልን ወይም የቤተክርስቲያኑን ትልቀ ቤተሰብ ለመወከል የአንድ ዛፍ ግንዶችን የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፡፡ ክፍሉ የሰማዊ አባታችን አገልጋዮች ባሉበት አስተዳደር ስር አባላት በሚኖሩበትና በሚሰባሰቡበት መልከአ ምድራዊ ወሰን ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

**ቅዱሳን፥** እውነተኛውን የኢየሱስን ቤተክርስቲያን አባል ለመለየት የምንገለገልበት ቃል ነው።

**ቅዱስ ቁርባን፥** የቤተክርስቲያኑ አባላት የኢየሱስን የኃጢአት ክፍያን ለማስታወስ የአካሉንና የደሙን ምሳሌ ዳቦውንና ውኃን የሚካፈሉበት ሥርዓት ነው።

**የሰማዩ አባት፥** ምድራዊ ሰውን የሚመስል ፍጹም ፍጡር ሲሆን፣ ነገር ግን ሕያው የሆነ አካላዊ ሥጋና አጥንት ያለው ነው። የምንፀልይበት የመንፈሳችን አባት ነው። ኃያል እና ሕያው ነው። ልጆቹ ከመሆናችን የተነሳ ይወደናል። እኛም ደግሞ የሰማዩ አባት ብለን እንጠራዋለን።

**ቤተመቅደስ፥** ቀዱስ ህንፃ ሲሆን በተለምዶ እንደ ጌታ ቤት (የሰማዩ አባታችን)፣ ዘለዓለማዊ ጋብቻን ጨምሮ የተቀደሱ ሥርዓቶች የሚከናወኑበት ነው።

**ቤተ እስራኤል፥** በማንኛውም ተፈጥሮአዊ ወይም በማደጐ ስሙ ወደ እስራኤል የተለወጠው ከአስራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች ወገን የሆነ ነው። (ዘፍጥረተ 32፥28 ይመልከቱ)።

**ትምህርት እና ቃልኪዳን፥** ለዘመኑ ሕዝቦች የሰማዩ አባታችንን መልዕክት የያዘ ቀዱስ መጻሕፍት ነው።

**ትንቢት፥** አብዛኛውን ጊዜ ወደፊት ስለሚሆነው ሁናቴ የሚገልጽ በመንፈስ የተሞላ የነቢያት ቃላት ነው።

**ትንሳኤ፥** ከሞት በኋላ ሕያው አካልን ለመመሥረት፣ የአካልና የመንፈስ ተመልሶ መዋሃድ ነው።

**ትንቢት ገላጭ፥** በሰማዩ አባታችን ስለተገለፀለት የወደፊቱን መተንበይ የሚችል ሰው ነው። ትንቢት ገላጭ ከነቢይ ጋር ተመሳሳይ ነው።

**ንስሐ፥** ኃጢአትን የሰራ ሰው ይቀር እንዲባል የሚፈጽመው ክንዋኔ ነው። (ምዕራፍ 14 ይመልከቱ)

**ነቢይ፥** በሰማዩ አባታችን የተጠራው ሰው ሲሆን፣ እርሱም ከእርሱ ጋር የተገናኘና ለእርሱ የሚናገር ነው።

**ነፍስ፥** እንደ አንድ ሰው (አካልና ነፍስ በአንድ ላይ መሆን) ነው። ቢሆንም፣ አንዳንድ ጊዜ ይህ ቃል መንፈሳችን ለማለት ያገለግላል።

**አሥሩ ነገዶች፥** የአሥራ ሁለት የእስራኤል (የያዕቆብ) ልጆች ወገን የሆኑ በምርኮ የተወሰዱና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክልላቸው ከሰው ዘር ዕውቀት የጠፋ ነው።

**አሥራት፥** ከሁሉም ገቢያችን ለቤተክርስቲያኑ የሚሰጠው አንድ አስረኛው ነው።

**አስተማሪ፥** በአሮናዊ ክህነት ውስጥ የሆነ ኃላፊነት ሆኖ ዕድሚያቸው ቢያንስ 14 ለሆነው ወጣት ወንዶች የሚሰጥ ነው። ስሙም የተገኘው የዚህ ኃላፊነት ከሆነው፣ ማለትም የቤተክርስቲያኑን አባላት ማስተማር ከሚለው ነው።

**አሮናዊ የክህነት ስልጣን፥** የሰማዩ አባታችን በምድር ላይ ለሰው ልጆች በእርሱም ስም ለልጆቹ መዳኛ እንዲሰሩበት የሰጣቸው ከሁለቱ የቀስና ሥልጣናት አነስተኛው ነው። ይህ አነስተኛው ክህነት ስሙን ያገኘው ከሙሴ ወንድም ከአሮን ሲሆን፣ እናም ከትልቁ የመልከዒዴቅ ክህነት የተለየ ነው። የአሮናዊ የክህነት ሥልጣን የዲያቆን፣ የአስተማሪ፣ የቄስና የጳጳስን ሹመቶች ያጠቃልላል።

**አንድ ሺህ ዓመት፥** ክርስቶስ ዳግም ወደ ምድር ሲመጣ ለእኛ እንደ ዳግም ምፅዓት የሆነው አንድ ሺህ የሰላም ዘመን ነው።

**አካላዊ ሞት፥** አካላችን ከመንፈሳችን የሚለይበት ሞት ነው።

**አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥** ከአንድ ሺህ ዓመት ቀደም ብሎ በተባበሩት የአሜሪካን መንግሥት ማዕከል የምትገነባ ከተማ ናት። ኢየሱስ በአንድ ሺህኛው ዓመት፣ ከዚህ ቦታ ሆኖ የሰማዩ አባታችንን መንግሥት በምድር ላይ፣ አስተዳደሩን ይመራል።

**አዳኝ፥** ሌላውን ከጎጂ ነገር የሚያድን ነው። ኢየሱስ አዳኛችን ነው ምክንያቱም ከአካላዊ ሞትና ከመንፈሳዊ ሞት አድኖናል።

**ዲስትሪክት፥** በቤተክርስቲያኑ ሚሲዮን በቀርንጫፎች የተከፋፈለ ክልል ወይም ክፍል ነው እርሱም በፕሬዚዳንትና ሁለት አማካሪዎቹ ይተዳደራል።

**ኢየሱስ ክርስቶስ፥** በሰማይ ያለ ታላቅ ወንድማችንና አዳኛችን ነው። የሁላችንንም ኃጢአት ለመክፈል ወደ ምድር መጥቷል። (በተለይ ምዕራፍ 3፣ 11፣ እና 12 ይመልከቱ)

**እግዚአብሔር፥** ኃያል አምላክ እና የዓለማት ገዥ ነው። እግዚአብሔር የሚለው ስም አብዛኛውን ጊዜ የሰማዩ አባታችንን ያመለክታል፣ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በቅዱሳን መፃሕፍት ውስጥ ኢየሱስንን ያመለከታል።

**ካህን፥** በአሮናዊ ክህነት ውስጥ ያለ ኃላፊነት ሲሆን ዕድሚያቸው ቢያንስ 16 ለሆናቸው ብቃት ላላቸው ወንዶች የሚሰጥ ነው። ይህ ኃላፊነት ጥምቀትን የማከናወንና አሮናዊ የክህነት ሥልጣን ሹመቶችን፣ ቅዱስ ቁርባንን ለመባረክ፣ እናም ሌሎች ተግባሮችን ለማከናወን ሥልጣን ይሰጣቸዋል።

**ክህነት፤** የሰማዩ አባታችን የእርሱን ሥራ እንዲያከናውኑና ለእርሱ እንዲናገሩ ለሰዎች የሚሰጠው ሥልጣን ነው፣ ይህም ሁለት ክፍሎች አሉት፤ ትልቁ ወይም የመልከጼዴቀ የክህነት ውልጣንና አነስተኛው ወይም አሮናዊ የክህነት ሥልጣን ናቸው።

**ኮረም ወይም ቡድን፤** በክህነት ሥልጣን ውስጥ በተመሳሳይ ኃላፊነት ላይ የሆኑ፣ የተደራጁ የሰዎች ወይም የወንድ ልጆች ቡድን ነው፣ እያንዳንዱ ኮረም በፕሬዚዳንትና ሁለት አማካሪዎቹ ይመራል።

**ዋርድ፤** በስቴክ ውስጥ የተደራጁ በጳጳስና ሁለት አማካሪዎች የሚመሩ የቤተክርስቲያኑ አባላት ቡድን ናቸው።

**ወንጌል፤** የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ነው፣ በመሆኑም ቢከተሉት፣ ሰውን የሰማዩ አባታችን ወደሚኖርበት ተመልሶ እንዲኖር የሚያስችል ነው።

**ውጫዊ ጨለማ፤** ሰይጣን እና እርሱን ለመከተል የመረጡት የሚኖሩበት ሥፍራ ነው። እዚያ የሚኖሩት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል አያገኙም እናም ከብርሃንና እውነት ውጭ ይሆናሉ።

**ዘለዓለማዊ ሕይወት፤** ይህ የሚያመለክተው ለዘለዓለም መኖርን ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን የሰማዩ አባታችን የሚኖረውን ሕይወት ዓይነትና እንደርሱ መሆንን ነው። ማለትም እንደ ዘለዓለማዊ መዳኛ ማለት ነው።

**ዘለዓለማዊ አባት፤** ለሰማዩ አባታችን የምንሰጠው ሌላ ስም ነው።

**ዘለዓለማዊ መዳኛ ወይም ሕይወት፤** በመንግስተ ሰማያት ውስጥ ከፍተኛው ደረጃ ነው። እዚያ የሚኖሩት እንደ ሰማዩ አባታችን ይሆናሉ።

**ዘለዓለማዊ ጋብቻ፤** ከሰማዩ አባታችን ጋር ብቁ ሆነን ለመኖር በቤተመቅደስ ውስጥ የተደረገ መተሳሰር እናም ከሞትንም በኋላ ለዘለዓለም የሚቀጥል ነው።

**የኋላኛውን ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፤** ሕጋዊ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ስም ሲሆን በነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ አማካይነት በዘመናችን እራሱ የመለሰው ነው። ይህ ቤተክርስቲያን አንዳንድ ጊዜ በሞርሞን ቤተክርስቲያን ቅጽል ስም ይጠራል።

**የኃጢአት ክፍያ፤** በአዳም መተላለፍ በሰው ልጆች ኃጢአት የተነሳ አካላዊና መንፈሳዊ ሞትን ላስከተለው እናም ሰው ከሰማዩ አባታችን እንዲለይ ውጤት ለሆነው ኢየሱስ በሥቃይና ሞት የከፈለው ነው።

**የመልከጼዴቀ ክህነት፤** ከሁለቱ ክህነቶች ትልቁ ነው፣ የካህናት፣ የሊቀካህናት፣ የፓትሪያርክ፣ የሰባዎች እና የሐዋሪያት ሹመቶች አሉት።

**የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ፤** ቋሚ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የማግኘት መብት ነው። ይህ ስጦታ የሚሰጠው ከጥምቀት በኋላ ነው።

**የመንፈስ ዓለም፡** እስከ ዕለተ ትንሳኤ ድረስ የሁሉም የሰው ዘር መንፈስ ከሞት በኋላ የሚሄዱበት ሥፍራ ነው።

**የመንፈስ እስር ቤት፡** የመንፈስ ዓለም አካል የሆነና ከሞቱ በኋላ የሶስት ዓይነት ሰዎች መንፈሶች የሚሄዱበት ሥፍራ ነው፣ እነርሱም በዚህ ምድራዊ ሕይወት ዘመን ክፉዎች የነበሩ፣ ጥሩ ሕይወት የኖሩ፣ ነገር ግን ወንጌልን ያልተቀበሉ፣ ወይም ያልጠበቁ፣ እናም ወንጌልን ለመስማት ፍፁም ዕድል ያላገኙ ናቸው። በመጨረሻም እነዚያ ሰዎች ሁሉ በትንሳኤ ይነሳሉ።

**የሙታን ጥምቀት፡** በሰማዩ አባታችን ቤተመቀደስ ውስጥ ሕያው የሆነ ግለሰብ በሞተ ሰው ፈንታ የሚያከናውነው የጥምቀት ሥርዓት ነው።

**የሰማዩ አባት፡** በሰማይ የሚኖር አባትን ይመልከቱ።

**የጥበብ ቃል፡** መብላት እና መጠጣት ያለብንና ያሌለብንን ከሰማዩ አባታችን የሚነግረን ትዕዛዝ ነው። በተለይም የአልኮል መጠጦችን፣ ትምባሆን፣ ሻይንና ቡናን መጠቀም እንደሌለብን ይነግረናል። (ምዕራፍ 27 ይመልከቱ።)

**የሰንበት ቀን፡** የዕረፍት ቀን፣ በኢየሱስ እንደ ሰማዩ አባታችን የማምለኪያና ልሎችን የማገልገያ ቀን የተወሰነ ነው። በዓለም ውስጥ በአብዛኛው ቦታዎች እሁድ ዕለት ይከበራል።

**የቤተመቀደስ ድጋፍ፡** በማንኛውም የቤተክርስቲያኑ ቤተመቀደሶች ሰውን የሚያስገባ የተፈረመ ወረቀት ነው። ወረቀቱን ለማግኘት፣ ግለሰቡ የቤተክርስቲያኑ ብቁ አባል መሆን ይገባዋል። የድጋፍ ወረቀቱ አግባብ ባላቸው የካህናት መሪዎች፣ ማለተ ለግለሰቡ ብቃት በሚመሰክሩ ይፈረማል።

**የቤተሰብ የቤት ምሽት፡** ቤተሰቦች አብዛኛውን ጊዜ በየሰኞ ማታ፣ በሚዘምሩበት ጊዜ፣ ወንጌልን በሚያጠኑበት ጊዜ፣ ያለባቸውን ማንኛውንም ችግሮች በሚወያዩበት ጊዜ፣ በአንድ ላይ ጨዋታ በሚጫወቱበት ጊዜ፣ እናም እንደቤተሰብ ሌሎች ጉዳዮችን በሚያከናወኑበት ጊዜ የሚያደርጉት ስብሰባ ነው።

**የቤት ለቤት አስተማሪዎች፡** የክህነት ስልጣን ያላቸው ሁለት ሰዎች ሆነው በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የተለያዩ ቤተሰቦችን እንዲጎበኙ የተመደቡትን ነው። ቤተሰቦችን በመንፈሳዊና በማህበራዊ (ወቀታዊ) ፍላጎቶች ይረዳሉ።

**የታላቁ ዕንቁ ዋጋ፡** የሙሴን የአብርሃምን፣ መጽሐፍት እና የዮሴፍ ስሚዝን ጽሁፎች የያዘ ቅዱስ መፅሐፍ ነው። ስሙ በእውነቱ በጣም የከበረ ድንጋይ ማለት ነው፣ ማለትም መፅሃፉ በቤተክርስቲያኑ አባላት የተከበረ መሆኑን ነው።

**የአዳም መውደቅ፡** የተከለከለውን በለስ በመብላታቸው የተነሳ በአዳምና በሄዋን ላይ የመጣ ለውጥ ነው። የሰማዩ አባታችን እርሱ ካለበተ አስወጣቸው፣ እናም ሟቾች ሆኑ። ይህ ለሁሉም የሰው ልጅ እንዲወለዱና እንዲሞቱ ምክንያት አስከተለ።

**የንጽህና ሕግ፡** የሰማዩ አባታችን ትዕዛዝ የሆነ ማለትም አንድ ሰው ከራሱ ወይም ከራሷ ባለቤት ጋር ብቻ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚፈቀድ ነው።

**የክህነት ቁልፎች፡** የክህነት ሥልጣን ሥርዓቶችን ለማከናወን መብት የመስጠት ሥልጣን ነው።

**የጾም በኩራት፡** በጾም ምክንያት የተቆጠበ ለሁለት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ምግቦች የሚወጣ የገንዘብ አስተዋጽኦ ነው። ይህም ድሆች እንዲረዱበት ለቤተክርስቲያኑ የሚሰጥ ነው።

**የክህደት ዘመን፡** 1. በመንፈስ ከሰማዩ አባታችን የመለየት ሁናቴ ነው 2. የሰማዩ አባታችን ትምህርቶችና የክህነት ሥልጣኑ በምድር ላይ ያልነበሩበት ወቀት ነው።

**ዳግም ምፅዓት፡** ሺህኛውን ዓመት ወይም የአንድ ሺህ የሰላም ክፍለ ዘመንን ለመጀመር፣ የአዳኛችን፣ የኢየሱስ ክርስቶስ መመለስ ነው።

**ዲያቆን፡** በአሮናዊ ክህነት ውስጥ የመጀመሪያ ሹመት ሲሆን፣ ብቁ ለሆኑ ወጣት ወንዶች በ12 ዓመት ዕድሜያቸው የሚሰጥ ነው። አንዳንድ ወቀታዊ ተግባሮችን ለማከናወን የሚያስችላቸውን ሥልጣን ይሰጣቸዋል።

**ገነት፡** የመንፈስ ዓለም ክፍል ሆኖ የጻድቃን መንፈሶች የሚኖሩበት ሥፍራ ነው።

**ጌታ፡** የእግዚአብሔር ስም ነው። አንዳንዴ የሰማዩ አባታችን እናም አንዳንዴ ኢየሱስ ክርስቶስን ያመለክታል።

**ጥምቀት፡** አንድ ግለሰብ የሰማይ አባታችንን ለመታዘዝና የሰማዩ አባታችንም ይቀርታ ሊያደርግለት እና ከኃጢአቱ ሊያነጻው እናም የቤተክርስቲያኑ አባልነቱን ሊፈቀድለት ቃል የሚገባለት ተገቢ የሆነ የወንጌል ሥርዓት ነው።


**ጳጳስ፡** በአሮናዊ ክህነት ውስጥ የሆነ ለአንድ ሰው ለመንፈሳዊና ዓለማዊ ደህንነት የቤተክርስቲያኑን አባላት ቡድን ኃላፊነት የሚሰጥ ነው።

**ጽዮን፡** የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ሌላው ስም ነው፤ ኢየሱስ በሺህኛው ዓመት ወቀት ተቀምጦበት ምድርን የሚገዛበት ከተማ ናት።

**ፓትሪያርክ፡** በመልከጼዴቀ ክህነት ውስጥ ያለ ሹመት ሲሆን ሊቀካህን ለሆነ ሰው የሚሰጥ ነው፣ ለፓትሪያርክ ኃላፊነት ከተሾመ በኋላ ልዩ ቡራኬን የሚሰጥ፣ ይህም ፓትሪያርካዊ ቡራኬዎችን ለቤተክርስቲያኑ ብቁ አባላት የሚሰጥ ማለት ነው።

# ሥዕላዊ መግለጫዎች

ድጋፍ ሰጪ ቁሳቁሶች



# የማብራሪያ ቁልፍ 1–16

1. ኢሳይያስ፣ የተባለው የብሉይ ኪዳን ነቢይ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት አስቀድሞ ተናግሯል፡፡
2. መጥምቁ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ኢየሱስን አጥምቋል፡፡
3. ጴጥሮስና ሌሎች እንዲከተሉት ኢየሱስ ጠርቷቸዋል።
4. ኢየሱስ 12ቱን ሐዋሪያት ሾሟቸዋል።
5. ኢየሱስ ሕፃናትን ወዷቸዋል እናም ባርኳቸዋል፡፡
6. ኢየሱስ ወንጌልን ለህዝቦች አስተምሯል፡፡ (የተራራው ስብከት፣ በካርልብሎች ቀናው ፀሎት ቤት በፍሬደሪክቦርጅ ግንብ፣ ዴንማርክ። በፍሬደሪክ ቦርጅ ቤተመዘክር ፍቃድ ጥቀም ላይ ውሏል።)
7. ክርስቶስስ ለሰው ልጆች ሁሉ ሃጢያት በጌተሰማኔ የአተክልት ሥፍራ ውስጥ መከራን ተቀበለ፡፡
8. ለሰው ልጆች ሁሉ ሃጢአት ሲል ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞተ።
9. በሶስተኛው ቀን፣ ክርስቶስ ከመቃብር ተነስቷል።
10. ከሙታን ተለይቶ የተነሳው ክርስቶስ ቁስሉን ለሐዋሪያቶቹ አሳይቷቸዋል፡፡
11. ከሙታን የተነሳው ክርስቶስ በአሜሪካ ያሉትን ህዝቦቹን ጎብኝቷል፡፡
12. ዮሴፍ ስሚዝ በያዕቀብ መልዕክተ 1፥5–6 የትኛው እውነተኛ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ እግዚአብሔርን ለመጠየቀ በመንፈስ ተነሳስቷል፡፡
13. ለፀሎቱ ምላሽ፣ ዮሴፍ ስሚዝ በሰማይ አባታችንና በኢየሱስ ክርስቶስ ተጎብኝቷል፡፡
14. መልአኩ ሞሮናይ ምጽሐፈ ሞርሞንን የያዘውን የወርቀ ሰሌዳ ለዮሴፍ ስሚዝ ሰጥቶታል፡፡
15. መጥምቁ ዮሐንስ ዮሴፍ ስሚዝንና ኦሊቨር ካውድሪን ጎብኝቶ አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን ሰጥቷቸዋል።
16. ጴጥሮስ፣ ያዕቀብና፣ ዮሐንስ የመልክጼዴቀን የክህነት ስልጣን ለዮሴፍ ስሚዝና ኦሊቨር ካውድሬ ሰጥቷቸዋል፡፡

































የኋለኛው ቀን ቅዱሳን

# የኢየሱስ ክርስቶስ

ቤተክርስቲያን

AMHARIC

4 02311 29506 7

31129 506